# መጽሐፈ ዜና መዋዕል - አንደኛ

## መግቢያ

### አሰያየሙ

"ዲብሪ ሐይያሚም" የሚለው የዕብራይስጡ ርእስ "የየቀኑ ወይም የየዓመቱ ሁነቶች" በሚል ሊተ ረጐም ይችላል:: የመጽሐፈ ነገሥት ጸሓፊ ወይም አርታኢ ይህን ሐረግ የተጠቀመበት የጽሑፉን ምንጭ ለመግለጽ ሲሆን ሐረጉ በመጽሐፈ ነገሥት ውስጥ "የታሪክ መጽሐፍ" ተብሎ ተተርጒሞአል:: (ለምሳሌ 1ነገ 14፥19:29፤ 15፥7:23:31፤ 16፥5:14:20:27፤ 22፥46 ይመ):: የሰብዓ ሊቃናት ተርጓሚዎች (ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የመለሱት) ይህን መጽሐፍ፣ "የተገደፉ ታሪኮች" በማለት ሰይመውታል፤ እንዲህ ለማለት የበቁት ለሳሙኤልና ለነገሥት መጻሕፍት ተጨማሪ ነው የሚል አመ ለካከት ስለ ነበራቸው ነው:: የላቲኑ ቩልጌት ተርጓሚ ጄሮም (ጄሮም፤347-420 ዓ.ም) ይህ መጽሐፍ መጠራት ያለበት "የቅዱሳን ታሪኮች ሁሉ ዜና መዋዕል" ተብሎ ነው ብሎአል:: ማርቲን ሉተር ይህን ሐሳብ በመቀበል በጀርመኑ ትርጒም ይህንኑ ርእስ ተጠቅሞበታል፤ ሌሎች ሰዎችም የእርሱን ፈለግ ተከትለዋል:: መጻሕፍተ ዜና መዋዕልን ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለት መጻሕፍት አድርገው የከፈሉት የሰብዓ ሊቃናት ተርጓሚዎች ናቸው::

### ጸሓፊው፣ የተጻፈበት ጊዜና ምንጩ

እንደ ጥንቱ የአይሁድ ትውፊት አባባል ከሆነ፣ ዜና መዋዕልን፣ መጽሐፈ ዕዝራንና መጽሐፈ ነህምያን የጻፈው ዕዝራ ነው (የመጽሐፈ ዕዝራን መግቢያ ይመ)፤ ነገር ግን የዚህን ትውፊት እውነተ ኛነት ለማረጋገጥ አይቻልም:: በርካታ ሰዎች መጻሕፍተ ዜና መዋዕል የተጻፉት በ5ኛው ምእተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ አጋማሽ ላይ ነው ይላሉ፤ ይህ ደግሞ ዕዝራ የኖረበት ዘመን ነው:: ጸሓፊው ዕዝራ አይደለም ቢባል እንኳ ይብዛም ይነስም በመጽሐፉ ዝግጅት ላይ ጸሓፊው፣ የተሐድሶ ሰው ከሆነው ካህን ጋር የሚጋራቸው ነገሮች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል::

ጸሓፊው ይህን ታሪክ በሚጽፍበት ጊዜ፣ እንደ ምንጭ አድርጎ የተጠቀመባቸው በርካታ ጽሑ ፎች አሉ:: ከጽሑፉ ግማሽ የሚያህለው ክፍል የተወሰደው ከመጽሐፈ ሳሙኤልና ከመጽሐፈ ነገሥት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ከአምስቱ ብሔረ ኦሪት (ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)፣ ከመሳፍንት፣ከሩት፣ ከመጽሐፈ መዝሙር ፣ ከኢሳይያስ፣ ከኤርምያስ፣ ከሰቈቃወ ኤርምያስና ከዘካርያስ መጻሕፍት አንዳንድ መረጃዎችን ወስዶአል፤ መጽሐፉ ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚጠቅሳቸው ሌሎች መጻሕፍትም ደግሞ አሉ፤ እነዚህም "የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ" (9፥1፤ 2ዜና 20፥34፤ ከ2ዜና 33፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፤ "የንጉሥ ዳዊት የታሪክ መጽሐፍ" (27፥24)፤ "የይሁዳና የእሥራኤል ነገሥታት መጽሐፍ" ወይም "የእስ ራኤልና የይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ" (2ዜና 16፥11፤ 25፥26፤ 27፥7፤ 28፥26፤ 32፥32፤ 35፥27፤36፥8)፤ "የነገሥታቱ መጽሐፍ" (2ዜና 24፥27) ናቸው:: እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት አንድን ምንጭ ይሁን የተለያዩ ምንጮችን ወይም ከሳሙኤልና ከነገሥት እንዲሁም በመጽሐፈ ነገሥት ላይ ከተጠቀሰው የቤተ መንግሥቱ ታሪክ ጋር ምን ዐይነት ግንኙነት ይኑራቸው በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም:: በተጨ ማሪም ጸሓፊው ብዙ የትንቢት መጻሕፍት ጠቅሶአል፤ እነዚህም የ"ባለ ራእዩ የሳሙኤል" (29፥29)፣ የ"ባለ ራእዩ አዶ" (2ዜና 29፥29፤12፥15፤13፥22)፣ የ"ነቢዩ ሸማያ" (2ዜና 12፥15)፣ የ"ነቢዩ ኢሳ ይያስ" (2ዜና 26፥22)፣ የ"ባለ ራእዩ" (2ዜና 33፥19) መጻሕፍት ናቸው:: ጥቂት ለውጥ በማድረግ ብቻ እነዚህን ሁሉ መጻሕፍት በትረካው ተጠቅሞባቸዋል:: ከምርኮ የተመለሰችው እስራኤል እንደ እግዚ አብሔር ሕዝብ ለመኖር በምትውተረተርበት ሰዓት፣ እስራኤል ትምህርት ልታገኝበት የምትችለውን ታሪክ ለማቅረብ ሲል ለታሪኩ ምንጭ የሆኑትን ነገሮች በመምረጥ፣ መልክ በማስያዝና በማቀናጀት ረገድ ልዩ ጥንቃቄ አድርጓል::

### ዐላማውና መሪ ሐሳቡ

የመጽሐፈ ሳሙኤልና የመጽሐፈ ነገሥት ጸሓፊዎች በምርኮ ላይ ለሚገኘው ኅብረተ ሰብ የእግዚ አብሔርን ሐሳብ ለማስተላለፍ የእስራኤልን ታሪክ መልክ እንዳስያዙና እንደ ተረጐሙ ሁሉ የመጽሐፈ ዜና መዋዕሉም ጸሐፊ ከምርኮ ለተመለሰው ኅብረተ ሰብ ይህን መጽሐፍ በዚህ ዐይነት ጽፎአል:: እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ የአሁኑን ታሪክ ከቀድሞው ታሪክ ጋር የማያያዙ ጉዳይ ነው፤ ይኸውም እግዚ አብሔር አሁንም ይወደናል ወይ? ኪዳኑ አሁንም ይሠራል ወይ? አሁን ከዳዊት ቤት የወጣ ንጉሥ የለንም፤ የፋርሶችም ባሪያ ነን፤ ታዲያ እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት የገባው ቃል ኪዳን ለእኛ ትርጒም ይኖረዋል? እግዚአብሔር ይህን ሁሉ መዐትና ቊጣ (ፍርድ) አምጥቶብን የዳዊት ቤት ከወደቀ፣ ሕዝቡ ከአገሩ ተነቅሎ ወደ ባቢሎን ከፈለሰ፣ ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ ከወደሙ በኋላ ከቀድሞዪቱ እስራ ኤል ጋር ያለን ዝምድና ምንድን ነው? እነዚህ ጥያቄዎች ናቸው በጸሓፊው መልስ ያገኙት::

1. የአሁኑ ትውልድ (ከምርኮ የወጣው ኅብረተ ሰብ) ከቀድሞው ትውልድ ጋር ዝምድና እንዳ ለው የተረጋገጠው ልዑል እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ አነሣሥቶ ዐዋጅ እንዲያስነግርና በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ እንደ ገና እንዲሠራ በማድረጉ ነው (2ዜና 36፥22-23):: የራሱ የሆነ ነጻ

መንግሥትና ከዳዊት ቤት የወጣ ንጉሥ ለሌለው ትውልድ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና አገልግሎቱ (የጸሎቱንና የምስጋናውን እንዲሁም የመዝሙራቱን መጽሐፍ ጨምሮ) በዳዊት ቤት አማካይነት ለእስራ ኤል የተሰጠ ታላቅ ገጸ በረከት መሆኑን ለማሳየት ጸሐፊው እጅግ ከፍ ያለ ጥረት አድርጎአል:: ከዚ ህም የተነሣ የዳዊትንና የሰሎሞንን ዘመነ መንግሥት አስመልክቶ የሚተርከው ዜና በአብዛኛው ዳዊት ለቤተ መቅደሱ ሥራ ያደረገውን ዝግጅትና ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን እንዴት አድርጎ እንደ ሠራ፣ ዳዊት ስለ ቤተ መቅደሱ አገልግሎት (የባለ ራእዩን የጋድንና የነቢዩ ዮናታንን 2ዜና 29፥25 እንዲ ሁም የሌዋውያኑን የአሳፍን፣ የኤማን፣ የኤዶታምን 2ዜና 35፥15) ምክር መሠረት በማድረግ የፈ ጸማቸውን ድርጊቶች የሚያወሣ ነው:: የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የአሳን፣ የኢዮሣፍጥን፣ የኢዮአስን፣ የሕ ዝቅያስንና የኢዮአስን ዘመነ መንግሥት አስመልክቶ የጻፈውን ታሪክ ይመ:: በጥንቷ ቅድስት ከተማ በኢየሩሳሌም የቆመው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና (መጽሐፈ መዝሙርን ጨምሮ) በዚያ የሚከናወ ነው አገልግሎት፣ ከምርኮ ለተመለሰው ኅብረተሰብ ከዳዊት ቤት የተሰጡ ታላቅ የመታሰቢያ ቅርሶች ናቸው::

2. ጸሐፊው የእነዚህን ቅርሶች ፋይዳ ሊያሳየን የሞከረው እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን በጎ ዐላማ ይበልጥ ያስመሰከረው በሉዓላዊ ምርጫው አማካይነት መሆኑን በአጽንኦት በመናገር ነው:: ይህንንም፣ (1) የሌዊን ነገድ በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት እንዲያገለግል (15፥2፤23፥24-32 ይመ)፣ (2) ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን (28፥4፤ 2 ዜና 6፥6)፣ (3) ልጁ ሰሎሞን ንጉሥ እንዲሆንና ቤተ መቅደሱን እንዲሠራ (28፥5-6:10፤29፥1)፣ (4) ኢየሩሳሌም (2ዜና 6፥6:34:38፤12፥13፤ 33፥7) እንዲሁም (5) የእግዚአብሔር ስም በሕዝቡ መካከል ይኖር ዘንድ ቤተ መቅደሱ የተመረጠ ቦታ እንዲሆን (2ዜና 7፥12:16፤ 33፥7) በማድረግ አሳይቷል:: ይህ መለኮታዊ ሥራ ለድኅረ-ምርኮ እስራኤላውያን መተማመኛ የሚሰጥ ነው፤ ይኸውም ቤተ መቅደሱ በኢየሩሳሌም መገንባቱና ዘለቄታ ያለው ሥርዐተ አምልኮ መካሄዱ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናቸውንና የእግዚአብሔርም ምርጫ እንዳልፈረሰ የሚያሳይ ነው::

3. ከቤተ መቅደሱም በተጨማሪ፣ እስራኤል ሕጉና ነቢያት አሏት፤ እነርሱም የሚናገሩት እስራ ኤል በዳዊት ቤት አመራር ሥር ስላላት ኪዳናዊ ሕይወት ነው:: የዳዊት ሥርወ መንግሥትም ሆነ ቤተ መቅደሱ ለእስራኤል ሰላምና በረከት ዋስትና መሆን አይችሉም:: እነዚህ ሁሉ እስራኤልና ነገሥታቷ ሕጉን በታማኝነት ለመጠበቅ በሚያሳዩት ታዛዥነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው (28፥7፤2ዜና 6፥16፤ 7፥17፤ 12፥1፤ 33፥8):: በዜና መዋዕሉ ጸሐፊ አስተያየት ከዳዊት ቤት የሚወጣ ማንኛውም ንጉሥ ሕጉን የመጠበቅና በሕጉ መሠረት የመኖር ኀላፊነት አለበት:: እነዚህም ዳዊት (6፥49፤ 15፥13:15፤ 16፥40፤ 22፥12-13፤ 29፥19)፤ አሳ (2ዜና 14፥4፤15፥12-14)፤ ኢዮሣፍጥ (2ዜና 17፥3-9፤19፥8-10)፤ ኢዮአስ (2ዜና 24፥6:9)፤ ሕዝቅያስ (2ዜና 29፥10:31፤ 30፥15-16፤ 31፥3-4:21)፤ ኢዮስያስ (2ዜና 34፥19-21:29-33፤5፥ 6:12:26) ናቸው:: እንዲሁም እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት የተናገረውን ቃል በልባቸው የመሰወር ግዴታም አለባቸው:: እንደ ዳዊት፣ አሳ፣ ኢዮሣፍጥ፣ ሕዝቅያስ፣ ኢዮስያስ ያሉት ታማኝ ነገሥታትና እንደ ሮብዓምና (2ዜና 11፥4፤ 12፥6) አሜስያስ ያሉት እንኳ ሳይቀሩ (2ዜና 25፥7-10) ለሕጉ ያላቸውን አክብሮት ገልጸዋል:: ታማኝ ሆነው ያልተገኙ ነገሥታት ደግሞ ናቁት፤ ይህም ለጥፋታቸው ምክንያት ሆነ፤ እነዚህም ኢዮርብዓም (2ዜና 21፥12-19)፤ ኢዮአስ (2ዜና 24፥19-25)፤ አሜስያስ (2ዜና 25፥15-16:20)፤ ምናሴ (2ዜና 20፥20) ናቸው:: የመጽሐፈ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ከሳሙኤልና ከነገሥት ጸሐፊ ይልቅ የብዙዎቹን ነቢያት አገልግሎት በስፋት ዘግቦአል:: ኢዮሣፍጥ ለእስ ራኤል ሕዝብ የተናገረው ቃል ይህን አባባል በሚገባ ይገልጸዋል፣ "በአምላካችሁ በእግዚአብሔር እመኑ፤ ትጸኑማላችሁ፤ በነቢያቱ ምእመኑ ይሳካላችኋል" (2ዜና 20፥20):: በዜና መዋዕሉ ጸሐፊ አተራ ረክ መሠረት እስራኤል በነገሥታት ትገዛ በነበረበት ጊዜ፣ የሕጉንና የነቢያቱን ትምህርት አሜን ብላ የመቀበሏ ነገር ከነገሥታቱ አገዛዝ ይልቅ ወሳኝነት ነበረው::

እንደ ቤተ መቅደሱ ሁሉ ሕጉና ነቢያቱም፣ ነገሥታት ከመኖራቸውና ካለመኖራቸው ይልቅ እስ ራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ስላላት ዘላቂ ግንኙነት ወሳኝ ነገሮች ናቸው፤ የዳዊት ሥርወ መንግሥት ራሱ ለእነዚህ ነገሮች ምስክር ሊሆን ይችላል::

4.ከዚህ በተጨማሪ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለሕጉና ለነቢያቱ ቃል መታዘዝ እጅግ አስፈላጊ መሆኑንና ቢታዘዙ ወዲያውኑ በረከት የሚያገኙበት፣ ቢያምጹ ደግሞ ወዲያውኑ ቅጣት የሚቀበሉበት መሆኑን በአጽንዖት ገልጾአል:: ዳዊት (28፥9)፣ እግዚአብሔርና (2ዜና 7፥14) ነቢያት (2ዜና 12፥5፤ 15፥2:7፤ 16፥7:9፤ 19፥2-3፤ 21፥14-15፤ 24፥20፤ 25፥15-16፤ 28፥9፤ 34፥24-28) የተናገሩትን የዐደራ ቃል ይመ:: ጸሐፊው የእያንዳንዱን ንጉሥ የአገዛዝ ዘመን ታሪክ በሚጽፍበት ጊዜ አለመታዘዝና ኀጢ አት የሚያስከትለውን የራብና የቸነፈር፣ ወይም የጦርነትና የመከራ ወይም ደግሞ ከበደልና ከክፋት በንስሓ መመለስ፣ መታዘዝና በእግዚአብሔር መታመን የሚያመጣውን ሰላም፣ ድልና ብልጽግና ለማ ሳየት ከፍተኛ ጥረት አድርጎአል::

5. የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለዳዊት የተሰጠውን ቃል ኪዳን (2ሳሙ 7) ለእርሱ ቅርብ የሆኑትን ሐጌን፣ ዘካርያስን ሚልክያስን ጨምሮ የነቢያቱን ማረጋገጫ ቃል መሠረት በማድረግ የእስራኤል ተስፋ እንደለመለመ እንዲቈይ ያለውን ፍላጎት ይገልጣል:: እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን የተስፋ ቃል በሚገባ ያሳስባል (1ዜና ምዕ 17):: ይህንንም ለማስረዳት ሲል ብዙ ማስረጃዎችን ያቀርባል (እዚህ ላይ

በተለይ ስለ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የተተረከውን እንዲሁም 2ዜና 13፥5፤21፥7፤23፥3 ይመ):: እዚህ ላይ ጸሐፊው ይበልጥ የሚጨነቀው ለዳዊት፣ ለሰሎሞን፣ ለአሳ፣ ለኢዮሣፍጥ፣ ለሕዝቅያስና ለኢዮስያስ ሊሰጣቸው ስለፈለገው ስፍራ ነው:: ታሪካቸው በተለየ መንገድ የተነገረው ነገሥታት፣የመሲሑን ማንነት እንዲያሳዩ ሆነው ቀርበዋል፤ በዚህ ምድር የእግዚአብሔር አገልጋይ በመሆናቸው እግዚአብሔርን እየፈሩና ቃል ኪዳኑንም እየጠበቁ በመኖር ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ሕዝቡን ጽኑ መሠረት ላለው ድል፣ ትድግናና ብልጽግና ያበቁት ዘንድ የእግዚአብሔርን ሞገስ አክሊል ተቀዳጅተዋል:: ከዚህም በላይ "በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ተቀምጠዋል" (29፥23፤28፥5፤ 2ዜና9፥8 ይመ)፤ የእግዚአብሔርንም መንግሥት ገዝተዋል (17፥14፤ 2ዜና 13፥8)፤ በዚህ ዐይነት ወደፊት ስለሚመጣው ዳዊት ምሳሌና ጥላ ሆኑ፤ ተስፋ መቍረጥ በሰፈነበት ስፍራ መታሰቢያቸው ለመለመ (የሚልክያስን መጽሐፍ እንዲሁም ከዚህ ክፍል "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል" የሚለውን ይመ)::

6. ሌላው የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ዐቢይ ትኵረት "እስራኤል ሁሉ" የሚለው አነጋገር ነው (ለምሳሌ 9፥1፤ 11፥1-4፤ 12፥38-40፤ 16፥1-3፤ 18፥14፤ 21፥1-5፤ 28፥1-8፤ 29፥21-26፤ 2ዜና 1፥1-3፤7፥8-10፤ 9፥30፤ 10፥1-3፡16፤ 12፥1፤ 18፥16፤ 28፥23፤ 29፡24፤ 30፥1-13፡23-27፤ 34፥6-9፡30):: በእርግጥም ከምርኮ የተመለሰውን ማኅበረሰብ የሚመለከተው የሰሜኑና የደቡብ ብሎ በመነጠል ሳይሆን፣ ባጠቃላይ የመላው እስራኤል ቅሬታ አድርጎ ነው (9፥2-3):: ታሪኩ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች ከእስራኤል ወደ ይሁዳ ያደረጉትን ጕዞ በተለየ መንገድ አቅርቧል:: የመጀመሪያዎቹ መጪዎች ሌዋውያን ሲሆኑ፣ የመጡትም በሮብዓም ዘመነ መንግሥት ነው (2ዜና 11፥14):: ሌሎቹ መጪዎች ደግሞ በአሳ ዘመነ መንግሥት ከኤፍሬምና ከምናሴ ነገድ መጡ (2ዜና 15፥9):: አሦራውያን የሰሜኑን መንግሥት ከደመሰሱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሕዝቅያስ ባስተላለፈው ጥሪ መሠረት ብዙዎቹ ከዚሁ ከጠፋው አገር ወደ ይሁዳ መጥተው ተቀመጡ (2ዜና 30)፤ ሕዝቅያስ ላዘጋጀው ለትልቁ የፋሲካ በዓል የመጡት ሁሉ እዚሁ ቀርተዋል ማለት አይቻልም፤ ይሁን እንጂ ብዙ ቍጥር ያለው ሕዝብ በዚህ ጊዜ መጥቶ የኢየሩሳሌምን አካባቢ አጥለቅልቆት እንደ ነበር የሥነ ቅርስ ጥናቶች ያረጋግጣሉ:: የዜና መዋዕሉ ጸሐፊም ይህንኑ ለይቶ "በይሁዳ ከተሞች የተቀመጡ...የእስራኤል ሰዎች" ብሎ ይጠቅሳቸዋል (2ዜና 31፥6):: እንዲሁም በኢዮስያስ ዘመን ቤተ መቅደሱን ለማደስ (2ዜና 34፥39) "የይሁዳን፣ የብንያምንና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች" የተቀላቀሏቸው "የምናሴ፣ የኤፍሬምና የእስራኤል ሕዝብ ቅሬታዎች በሙሉ" ብሎ ያውሣቸዋል፤ እነዚህም እንደዚሁ በኢዮስያስ የፋሲካ በዓል ላይ ተገኝተው ነበር (2ዜና 35፥17-18):: ስለዚህ የይሁዳ መንግሥት ከሰሜኑ መንግሥት ብዙዎቹን በየጊዜው እየዋጠ በዚያው አስቀርቶአቸው ነበር፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊም ከሰማርያ ውድቀት ጀምሮ ያለውን ይህን ታሪክ የሚመለከተው እንደ እስራኤል ቅሬታ አድርጎ ነው::

7. የትውልድ ሐረጎችም እንደዚሁ የአሁኑን ትውልድ ወስደው ከጥንቱ ጋር በማያያዝ ከዚያ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑን ያሳያል:: "እግዚአብሔር አሁንም ስለ እኛ ይገደዋል ወይ?" ተብሎ ለሚቀርብ ጥያቄ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ "እንዴታ! ዘወትር እንጂ" የሚል መልስ ይሰጣል:: እግዚአብሔር ከምርኮ ለተመለሰው ሕዝቡ ፍቅሩንና ጸጋውን መግለጽ የጀመረው ከዳዊት ወይም ከኢያሱ (ከነዓን በሚወርሱበት ጊዜ) ወይም ከግብፅ ከወጡበት ዘመን ጀምሮ ሳይሆን፣ ከፍጥረት ዘመን ጀምሮ ነው (ዘፍ1፥1):: የትውልድ ሐረግ የሚለውን ይመ::

8. ጸሐፊው በመጽሐፈ ሳሙኤልና ነገሥት ውስጥ የማይገኙ ንግግሮችን በታሪኩ ውስጥ አውሥቷል፤ ይህንንም ያደረገው በአጽንዖት ለመናገር የሚፈልገውን ነገር በሚገባ እንዲሉለት ፈልጎ ነው:: በመጽሐፈ ዜና ውስጥ ከምናገኛቸው 165 አጫጭርና ረጃጅምና ንግግሮች መካከል በመጽሐፈ ሳሙኤልና ነገሥት ተጓዳኝ ክፍሎች ውስጥ የምናገኘው 95 ብቻ ነው፤ ለምሳሌ የአብያ (2ዜና 13፥4-12)፣ የአሳና (2ዜና 14፥11) የኢዮሣፍጥ (2ዜና 20፥5-12) ንግግሮች ናቸው::

**የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል**

የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በአብዛኛው የሚያተኵረው በዳዊትና (ም 11-29) በሰሎሞን (2ዜና 1-9) ታሪክ ላይ ነው:: የእነዚህ ሁለት ነገሥታት ገጸ ባሕርይ አሣሣል ልዩ ከመሆኑም በላይ፣ ጸሐፊው ሥራዬ ብሎ ለተነሣበት ጕዳይ ቍልፍ ሚና አላቸው::

1. የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለዳዊትና ለሰሎሞን የሚሰጠው ቦታ የላቀ ነው:: ለታሪኩ ምንጭ አድርጎ በተጠቀመባቸው መጻሕፍት (ሳሙኤልና ነገሥት) እነዚህን ነገሥታት በተመለከተ የሚናገሩት ነገር ደብዛዛ ሲመስለው እነዚያን ነገሮች ሆን ብሎ ትቷቸዋል:: ሁለቱ መንግሥታት አንድ ከመሆናቸው በፊት በኬብሮን የነበረውን የሰባቱን ዓመት ዘመነ መንግሥት፤ በሳኦልና በዳዊት ቤት መካከል የነበረውን ጦርነት፣ ከአበኔር ጋር የተደረገውን ስምምነት፣ በዳዊት ሚስት በሜልኮል የተከሠተው ችግር ወይም የአበኔርንም ሆነ የኢሽቦሽቴን መገደል (2ሳሙ 1-4) አያወሳም:: የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ሳኦል እንደ ሞተ ዳዊት ወዲያውኑ ተቀብቶ በመላው እስራኤል ላይ መንገሡና (ም11) የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍ ማግኘቱን (11፥10-12፥40፤ የ31፥9 ማብ ይመ) ጽፎአል:: በዳዊት ላይ በተከታታይ የደረሱ ችግሮች ቢኖሩም፣ ጸሐፊው ግን አልጠቀሳቸውም:: ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር የሠራው ኀጢአት፣ የአምኖን ወንጀልና ሞት፣ አቤሴሎም ወንድሙን መግደሉና በአባቱ ላይ መዶለቱ፣ ዳዊት ከኢየሩሳሌም ሸሽቶ መውጣቱ፣ የሼባና የሽማይ ዐመፅ እንዲሁም የዳዊትን አገዛዝ የሚያጨልሙ ድርጊቶች ፈጽሞ አልተወ

ሡም (2ሳሙ 11-20)። ዳዊት በዜና መዋዕሉ ብርዕ ምንም በደል እንዳልፈጸመ ሰው ሆኖ ቀርቦአል፤ በእርሱ ላይ በደል ሆኖ የታየበት ነገር ቢኖር፣ ሕዝቡ እንዲቈጠር ማድረጉ ነበር (የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የሕዝቡን ቈጠራ በመጽሓፉ ውስጥ ያስገባበት የተለየ ምክንያት አለው ም 21 እና ማብ ይመ)።

የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ሰሎሞን የሚጽፈውም በተመሳሳይ መንገድ ነው። ሰሎሞን በዳዊት እግር እንደሚተካ አምላካዊ ትንቢት ተነግሮለታል (22፥7-10፤ 28፥6)። በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠውም እርሱ መሆኑን አባቱ ዳዊት በአደባባይ መስክሮለታል፤ ይህም በመላው የእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ አድርጎአል (ም 28-29)። ዳዊት የዐልጋ ቍራኛ መሆኑ ፈጽሞ አልተወሳም፤ ዳዊት በመጨረሻው ሰዓት በልጁ በሰሎሞን ዙፋን ላይ አዶንያስ የጠነሰሰውን ሤራ ማክሸፍ ነበረበት። እንዲሁም የሰራዊቱ አዛዥ ኢዮአብና ሊቀ ካህኑ አብያታር አዶንያስን እንደ ገደለ ፈጽሞ አልተጠቀሰም (1ነገ 1)። ሰሎሞን በዳዊት ላይ በደል የፈጸሙትን ሰዎች በሞት ቢቀጣ ቸውም ፣ይህ ግን በዜና መዋዕሉ ጸሓፊ አልተጠቀሰም። ሰሎሞን ሥልጣን የጨበጠው ያለ አንዳች ተቀናቃኝና ተቃውሞ ነው። የአገዛዙም ዘመን ሙሉ በሙሉ የዋለው በቤተ መቅደሱ ሥራ ላይ ነው (2ዜና 2-8)፤ ውድቀቶቹ ግን ከቶ አልተወሡም። ባዕድ ማምለኩ፣ የአሕዛብን ሴቶች ማግባቱ ወይም በመንግሥቱ ላይ ተነሥቶ ስለነበረው ዐመፅ የተነገረ ነገር የለም። ሌላው ቀርቶ መንግሥቱ ከሁለት ሊከፈል የቻለበት ምክንያት የተሳበበው በሰሎሞን ላይ ሳይሆን (1ነገ 11፥26-40፤12፥1-4)፣ በሮብዓም ላይ ነው። በዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ተስሎ የምናየው የሰሎሞን ገጽታ በአብዛኛው የሚያምረውን የአባቱን የዳዊትን መልክ ይዞ ነው (2ዜና 11፥17)።

የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በብርዑ አሳምሮ የሚያቀርባቸው ዳዊትና ሰሎሞን በታሪክ መዝገብ በሚገባ የሚታወቁት ዳዊትና ሰሎሞን ብቻ ሳይሆኑ፣ ራሱ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በተስፋ የሚጠብቀውን መሲሓዊ ንጉሥ አምሳያ የሚያሳዩም አድርጎ ነው።

2. የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዳዊትንና ሰሎሞንን የመሲሑ አገዛዝ አምሳል ብቻ ሳይሆን፣ የሙሴና የኢያሱ አመራር በዳዊትና በሰሎሞን እንደተደገመም አድርጎ ይመለከተዋል፤

ሀ) ዳዊትና ሙሴ ካሰቡት ግብ ሳይደርሱ ቀርተዋል፤ የአንዱ ምኞት ቤተ መቅደሱን መሥራት ነበር፤ የሌላው ምኞት ደግሞ ወደ ተስፋዪቱ ምድር መግባት ነበር። የሁለቱም ምኞትና ዐላማ እውን የሆነውና ከፍጻሜ ሊደርስ የቻለው በእግራቸው በተተኩት በኢያሱና በሰሎሞን ነው (ዘዳ 1፥37-38፤31፥2-8፤ 1ዜና 22፥5-23፤ 28፥2-8)።

ለ) ሰሎሞንና ኢያሱ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ዕረፍት ሊያመጡ ችለዋል (22፥8-9፤ ኢያ 11፥23፤ 21፥44)።

ሐ) ሰሎሞንና ኢያሱ ሹመት ሲቀበሉ የተነገረላቸው ነገር በብዙ ረገድ ተመሳሳይ ነው (22፥11-13፡16፤28፥7-10፡20፤ 2ዜና 1፥1፤ን ከዘዳ 31፥5-8፡23፤ ከኢያ 1፥5፡7-9 ጋር ያነጻጽሩ)።

መ) ኢያሱ በሙሴ፣ ሰሎሞን ደግሞ በዳዊት እግር በተተኩ ጊዜ ለሁለቱም በግልም ሆነ (22፥6፤ ዘዳ 31፥23) በይፋ (28፥8፤ ዘዳ 31፥7 "በሕዝበ እስራኤል ሁሉ ፊት") የተነገረላቸው ነገር አለ።

ሠ) ሁለቱም የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍ ወዲያውኑ አግኝተዋል (29፥23-24፤ ዘዳ 34፥9፤ ኢያ 1፥16-18)።

ረ) እግዚአብሔር ሰሎሞንንና ኢያሱን "ከፍ ከፍ" ወይም "ታላቅ ሰው" እንዳደረጋቸው ሁለት ጊዜ ተጠቅሶአል።

የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የዳዊትንና የሰሎሞንን ገጸ ባሕርይ በሚሥልበት ጊዜ ከአምስቱ ብሔረ ኦሪት ላይ (የሙሴ መጻሕፍት) ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ወስዶአል። እንደ ሙሴ ሁሉ ዳዊትም የቤተ መቅደሱን ንድፍ ከእግዚአብሔር ተቀብሎአል (28፥11-19፤ ዘጸ 25፥9)፤ እንደ ሙሴ ሁሉ ዳዊትም ለቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ ሕዝቡ በገዛ ፈቃዱ ስጦታ እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፎአል (29፥1-9፤ ዘጸ 25፥1-7)። ሰሎሞን ከጢሮሳዊው የእጅ ባለሙያ ከኪራምአቢ ጋር የነበረው ግንኙነት (2ዜና 2፥13-14) ባስልኤልና ኤልያብ ከመገናኛው ድንኳን ጋር የነበራቸውን ግንኙነት (ዘፀ 35፥36-37) ያስተጋባል። የ2ዜና 1፥5 ማብ ይመ።

## ትውልድ ሐረግ

በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የምናገኛቸው የትውልድ ሐረጎች የተለያየ አገልግሎት አላቸው። አንዳንዶቹ የትውልድ ሐረጎቹን ሲዘረዝሩ የሚመሩበት ልዩ ልዩ መርሕ ሲኖራቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ በቅርጽ (ዝርዝርና ጥቅል የትውልድ ሐረጎችን በመዘርዘር)፣ በጥልቀት (ብዙ የትውልድ ሐረጎችን በመጥቀስ)፣ በባሕርይ (በየጊዜው የሚለዋወጡ የትውልድ ሐረጎች ብዛት)፣ ተለይተው ይታወቃሉ።

የትውልድ ሐረጎቹ የሚያገለግሉበት ሦስት መንገዶች አሉ፤ እነዚህም ቤተ ሰባዊ ወይም አካባቢያዊ፣ ሕጋዊ ወይም ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ናቸው። በቤተ ሰባዊ መንገድ ሲዘረዝር አንድ ግለሰብ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለው ደረጃ፣ የሚያገኘው ጥቅምና የሚፈጽመው ግዴታ በትውልዱ ሐረግ ቅደም ተከተል ውስጥ በተሰጠው ስፍራ ይንጸባረቃል (7፥14-19 ይመ)። ይህን ለማወቅም ለበኵር ልጅ የሚሰጠውን መብትና ከቁባት የሚወለዱት ልጆች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው። በፖለቲካው መንገድ የታየ እንደ ሆነ ደግሞ የትውልድ ሐረጉ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የገዥነት ሥልጣን እንዳለው የሚያረጋግጥ ጠንካራ ማስረጃ በመምዘዝ መብቱና ሥልጣኑ የእኔ ነው ባይ ቢነሣም አፉን የሚያሲዝ ኀይል አለው። የመሬት ድልድልና የርስት አከፋፈል የሚከናወነው ነገድንና

የትውልድ ሐረግን ተከትሎ ነው:: መሬቱ ለዐሥራ ሁለቱ ነገድ የተከፈለው በዚሁ መሠረት መሆኑን እዚህ ላይ እንደ ምሳሌ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል:: በእስራኤል ወታደር የሚመለመለውና የሚዘምተው በየትውልድ ሐረጉ እየተቈጠረ ነው:: በዜና መዋዕል መጽሐፍ ላይ የሚገኘው አብዛኛው የትውልድ ሐረግም የወታደር ምልመላንና ግዳጅን ያንጸባርቃል (5፥1-26፤ 7፥1-12:30-40፤8፥1-40):: በሃይማኖት ረገድ ሲታይ የትውልድ ሐረጉ የካህናቱንና የሌዋውያኑን አገልግሎት አስቀድሞ በመመ ደብ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጎአል::

ቅርጹን በተመለከተ አንዳንዱ የትውልድ ሐረግ ዝርዝር ብዙ ቅርንጫፍ ይዞ የሚወርድ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ የአንዱን ትውልድ ሐረግ ቀጥታ መስመር ብቻ ይዞ ይወርዳል::

የአንዱ ነገድ ወይም ቤተ ሰብ የትውልድ ሐረግ ከሌላው ጋር በሚነጻጸርበት ጊዜ ያልታሰበና ያልታለመ ልዩነት ይታያል:: የዝርዝሩ ፍሰት የተለያየ ጠቀሜታ አለው፤ ነገር ግን አንዳንዴ በዘርአ ትውልድ ውስጥ የሰዎችን ስም በመለወጥ ደረጃን (ማዕረግን) እና በማኅበረ ሰቡ ውስጥ ያለውን ግንኙነት መለወጥ ይቻላል (1፥35-42፤ 6፥22:27 ይመ)፤ ወይም በዘርአ ትውልዱ መስመር ውስጥ ስሞችን ወይም የትውልድ ቅርንጫፎችን በመጨመር (5፥11-22፤ 6፥27፤ 7፥6-12 ይመ) ለውጡን ማካሄድ ይቻላል:: የተለመደው የዝርዝር ፍሰት የስሞች መዘለል ከምን ምክንያት የተነሣ እንደ ሆነ የሚያስተምረው ነገር አለ:: አንዱን ግለ ሰብ ሁነኛ ከሆነው ሰው ጋር ለማቈራኘት ወይም ደግሞ በትውልደ ሐረጉ ውስጥ የተፈለጉ ስሞችን ለማግባት ሲባል ይኼን ያህል ታዋቂነት የሌላቸው ስሞች እንዲወጡ ይደረጋል፤ ለምሳሌ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትውልደ ሐረጎች ስሞችን (ሐረጉን) በሰባት ለማብዛት እንዲቻል አንዳንድ ስሞችን ይዘሉ ነበር፤ ለምሳሌ:- ማቴዎስ ከዳዊት እስከ ግዞት ዘመን ድረስ 14 ትውልደ ሐረጎችን (2x7) ሲያቀርብ፣ ሉቃስ ደግሞ 21 ትውልደ ሐረጎችን (3x7) ይጠቅሳል:: እነዚሁ ጸሐፍያን ከግዞት ዘመን እስከ ኢየሱስ ድረስ የ7 ብዜቶችን ይሰጣሉ (ማቴ 1፥1-17፤ ሉቃ 3፥23-38)::

በዜና መዋዕል መጻሕፍት ውስጥ ከላይ በተመለከትናቸው ምክንያቶች የተለያዩ የትውልድ ሐረጎች ዘገባ ያቀርባል:: አብዛኛውን ጊዜ የትውልድ ሐረጎቹ ጸሓፊው ለምን ዐላማ አስቦ እንዳቀረባቸው ከአደራደራቸው መረዳት ይቻላል::

**አስተዋፅኦ**

1. ትውልደ ሐረግ፤ ከዘፍጥረት እስከ ምርኮ መልስ (1ዜና 1-9)::
   - ሀ) ርእሳን አበው (ም1)
   - ለ) ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ/የእስራኤል ልጆች (2፥1-2)
   - ሐ) የይሁዳ ቤተ ሰብ (2፥3-4፥23)
   - መ) የስምዖን ወንዶች ልጆች (4፥24-43)
   - ሠ) ሮቤል፣ ጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ (ም5)
   - ረ) ሌዊና ቤተ ሰቦቹ (ም6)
   - ሰ) ይሳኮር፣ ብንያም፣ ንፍታሌም፣ ምናሴ፣ ኤፍሬምና አሴር (ም 7-9)
2. የዳዊት ዘመነ መንግሥት (1ዜና 10-29)
   - ሀ) የሳኦል መሞት (ም10)
   - ለ) የኢየሩሳሌም መያዝ፤ የዳዊት ከተማና ኀያላኑ (11-12)
   - ሐ) የታቦቱ መመለስ፤ የዳዊት መንግሥት መመሥረት (ም13-16)
   - መ) ለዘሩ የተሰጠ ተስፋ (ም17)
   - ሠ) ዳዊት የተጐናጸፋቸው ድሎች (ም 18-20)
   - ረ) የሕዝብ ቈጠራ (ም21)
   - ሰ) ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት (ም22)
   - ሸ) የቤተ መቅደሱ አገልግሎት አደረጃጀት (ም 23-26)
   - ቀ) የመንግሥቱ አስተዳደር መዋቅር (ም27)
   - በ) ዳዊት ወራሲ መንግሥቱንና ቤተ መቅደሱን በተመለከተ ያደረገው የመጨረሻ ዝግጅት (ም28፥1-29፥20)
   - ተ) ሰሎሞን ዙፋኑን ወረሰ፤ የዳዊት መሞት (29፥21-30)
3. የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት (2ዜና 1-9)
   - ሀ) ጥበብን መታደል (ም 1)
   - ለ) የቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ (2፥1-5፥1)
   - ሐ) የቤተ መቅደሱ ምረቃ (5፥2-7፥22)
   - መ) ሰሎሞን ያከናወናቸው ሌሎች ተግባራት (ም 8)
   - ሠ) የሰሎሞን ጥበብ፣ ገናናነትና ሞት (ም 9)
4. የእስራኤል መንግሥት ከሁለት መከፈልና የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ (2ዜና 10-36)
   - ሀ) ሮብዓም (ም 10-12)

ለ) አቢያ (13፥1-14፥1)
ሐ) አሳ (14፥2-16፥14)
መ) ኢዮሣፍጥ (17፥1-21፥3)
ሠ) ኢዮራምና አካዝያስ (21፥4-22፥9)
ረ) ኢዮአስ (22፥10-24፥27)
ሰ) አሜስያስ (ም25)
ሸ) ዖዝያን (ም26)
ቀ) ኢዮአታም (ም27)
በ) አካዝ (ም28)
ተ) ሕዝቅያስ (ም29-32)
ቸ) ምናሴ (33፥1-20)
ኀ) አሞን (33፥21-25)
ነ) ኢዮስያስ (34፥1-36፥1)
ኘ) የኢዮስያስ ወራሾች (36፥2-14)
አ) የባቢሎን ምርኮና ከምርኮ መልስ (36፥15-23)

## ከአዳም እስከ አብርሃም ያለው የትውልድ ሐረግ

### እስከ ኖኅ ልጆች

1 አዳም፣ሴት፣ ሄኖስ፣ 2ቃይናን፣ መላልኤል፣
ያሬድ፣ 3ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣ ላሜሕ፣ ኖኅ።
4የኖኅ ወንዶች ልጆች[ሀ]፤
ሴም፣ ካም፣ ያፌት።

### ያፌታውያን

1፥5-7 ተጓ ምብ - ዘፍ10፥2-5

5የያፌት ወንዶች ልጆች፤[ለ]
ጋሜር፣ ማጎግ፣ ማዴ፣ያዋን፣
ቶቤል፣ ሞሳሕ፣ ቴራስ።
6የጋሜር ወንዶች ልጆች፤
አስከናዝ፣ ሪፋት፣ ቴርጋማ።
7የያዋን ወንዶች ልጆች፤
ኤሊሳ፣ ተርሴስ፣ ኪቲም፣ ሮድኢ።

### ካማውያን

1፥8-16 ተጓ ምብ - ዘፍ 10፥6-20

8የካም ወንዶች ልጆች፤
ኩሽ፣ ምጽራይም፣[ሐ] ፉጥ፣ ከነዓን።
9የኩሽ ወንዶች ልጆች፤
ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታ፣ ራዕማ፣
ሰብቃታ።
የራዕማ ወንዶች ልጆች፤
ሳባ፣ ድዳን።
10ኩሽ ናምሩድን ወለደ፤
እርሱም በምድር ላይ የመጀመሪያው
ኀያል ጦረኛ ሆነ።
11ምጽራይም የሉዲማውያን፣ የዐናማውያን፣
የላህባማውያን፣ የነፍተሂማውያን፣ 12የፈ
ትሩሲማውያን፣ የፍልስጥኤማውያን
ቅድመ አባቶች የሆኑት የከስሉሂማው
ያንና የከፍቶሪማውያን ነገዶች አባት[መ]
ነው።
13ከነዓን የበኵር ልጁ የሆነው የሲዶን[ሠ]
እንዲሁም የኬጢያውያን፣ 14የኢያቡሳ
ውያን፣ የአሞራውያን፣ የጌርጌሳውያን፣
15የኤዊያውያን፣ የዐርካውያን፣ የሲኒው
ያን፣ 16የአራዴዎያውያን፣ የሰማርያ
ውያን፣ የአማቲያውያን አባት ነው።

### ሴማውያን

1፥17-23 ተጓ ምብ – ዘፍ 10፥21-31፤11፥10-27

17የሴም ወንዶች ልጆች፤
ኤላም፣ አሦር፣ አርፋክስድ፣ ሉድ፣አራም።
የአራም ወንዶች ልጆች፤[መ]
ዑፅ፣ ሁል፣ ጌቴር፣ ሞሳሕ።
18አርፋክስድ ሳላን ወለደ፤
ሳላም ዔቦርን ወለደ።
19ዔቦር ሁለት ወንዶች ልጆች ወለደ፤
በዘመኑ ምድር ስለተከፈለች፣
የአንደኛው ስም ፋሌቅ[ረ] ተብሎ ተጠራ፤
ወንድሙም ዮቅጣን ተባለ።
20ዮቅጣንም፡
አልሞዳድን፣ ሣሌፍን፣ ሐስረሞትን፣
ያራሕን፣21ሀዶራምን፣ አውዛልን፣ ደቅላን፣

1፥1 ዘፍ5፥1-32፤ ሉቃ 3፥36-38
1፥2 ዘፍ5፥9:12:15
1፥3 ዘፍ5፥18:21:25:29፤ይሁ1፥14
1፥4 ዘፍ5፥32፤ 6፥10፤10፥1

[ሀ]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ የኖኅ ወንዶች ልጆች የሚለውን አይጨምርም።
[ለ]5 *ወንዶች ልጆች* ማለት ዘር ወይም ሕዝብ ማለት ነው፤ እንዲሁም ቍ 6-10፤ 17 እና 20
[ሐ]8 "*ግብፅ*" ናት፤ እንዲሁም ቍ 11
[መ]12 *አባት* ማለት *ቅድመ አያት ወይም አንጃላት ወይም መሠረት* ማለት ነው፤ እንዲሁም ቍ 16
[ሠ]13 ወይም፣ *የሲዶናውያን አለቃ*
[ረ]19 *ፋሌቅ* ማለት *መከፈል* ማለት ነው

*1፥1-9፥44፤* ይህ የትውልድ ሐረግ ከምርኮ የተመለሰው ማኅበረ ሰብ፣ ከጥንቱ የትውልድ ሐረግ የቀጠለ መሆኑን ቍልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ከዳዊት መንሣት በፊት ለእስራኤል ያደረጋቸው ታላላቅ ታምራት በዚህ ክፍል አልተወሱም፤ ይሁን እንጂ የእስራኤል መኑብኘት በእግዚአብሔር መለኮታዊ ዕቅድ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለው መሆኑን እንዲገነዘቡ፣ ከአዳም ጀምሮ (ቍ1) የቀረበው የትውልድ ሐረግ ዝርዝር እግዚአብሔር በየዘመናቱ ያደረገላቸውን የሚያሳስብ ነው። እንዲሁም ይህ የትውልድ ሐረግ እዚህ ላይ የተዘረዘረው እግዚአብሔር በእስራኤል ታሪክ ውስጥ አሁንም የሚሠራው ነገር እንዳለ ትምህርት ለመስጠት ነው። ይህም የሕዝቡ ምግባራዊና መንፈሳዊ (ሃይማኖታዊ) ንጽሕና ሊታደስ የሚችል መሆኑን አመልካች ነው። እንዲሁም ከምርኮ መልስ በተሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥ ስለሚሆነው የሌዋውያን ሕጋዊ የክህነት አገልግሎትና የንጉሣዊው ሐረግ ቀጣይነት የሚያስገነዝብ ነው።

*1፥1-2፥1፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በዚህ ክፍል ከአዳም ጀምሮ እስከ ያዕቆብ ያሉትን ዘመናት አካቷል። ለዚህም እንደ ምንጭ የተጠቀመው የዘፍጥረትን መጽሐፍ ነው። አነስተኛ ግምት የሚሰጣቸው የዘር ሐረጎች በመጀመሪያ ቀርበዋል። ያፌትና ካም (ቍ 5-16) ከሴም ነገድ የትውልድ ሐረግ በፊት ቀርበዋል (ቍ 17-27)። በአብርሃም የትውልድ ሐረግ ውስጥ ያልተጠቀሱት ሌሎቹ የሴም ወንዶች ልጆች (ቍ 17-23) ማለትም የአብርሃም ቁባቶች ልጆች (ቍ 28-33) ከይስሐቅ የዘር ሐረግ በፊት፣ (ቍ34)፣ የዔሳው ዘሮችና የኤዶማውያን አለቆች የትውልድ ሐረግ (ቍ 35-54) ከእስራኤል ወንዶች ልጆች (2፥1) በፊት ተጠቅሰዋል። እንግዲህ እግዚአብሔር የመረጠው የትውልድ ሐረግ/ መስመር መጨረሻ ላይ ቀርቦ እናገኘዋለን።

አብዛኛው የዚህ ትውልድ ሐረግ ዋና ዋና ባሕርያት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ካሉት ተመሳሳይ ታሪኮች ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሚያስደንቅ ነው። የትውልድ ሐረጉ የሚጀምረው ያለምንም መግቢያ ነው። ሁለቱ የትውልድ ሐረጎች የስም ዝርዝር ብቻ እንጂ ትውልዶቹ የሥጋ ዝምድና የላቸውም። ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሦስት ስሞች (ቍ 1-4 እንዲሁም የቍ 4 ማብ ይመ) እንዲሁም ቍ 24-27። በቍ 5-16 (ከዚያም ቍ 27 ላይ) የሥጋ የዝምድና ያላቸው ትውልዶች ተጠቅሰዋል። በዚህ ውስጥ ብዙ የዘር ሐረጎችን የሚጠቅሱና አንድ የዘር ሐረግ ብቻ የሚጠቅሱ ትውልዶች ተካተዋል። ልክ ይህን የመሰለ የዘር ሐረግ አወቃቀር የአሦራውያንን ነገሥታት ስም ዝርዝር በያዘው መዝገብ ላይ ተገኝቷል። እንደ ዜና መዋዕሉ ሁሉ ይሄም መዝገብ መግቢያ የለውም፤ ጸሐፊው ድንቱን ከላይ ወደ ታች በማስመር አራት ቦታ ከከፈለው በኋላ፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች ውስጥ የሥጋ ዝምድና የሌላቸውን የትውልድ ሐረጎች ይዘረዝራል፤ በቀሩት ሁለት ክፍሎች ደግሞ የሥጋ ዝምድና ያላቸውን የትውልድ ሐረጎች ይመዘግባል። ይህ የሚያመለክተው የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ይህን መጽሐፍ የጻፈው በዘመኑ ታዋቂ የነበረውን የአጻጻፍ ስልት ተከትሎ መሆኑን ነው።

*1፥1-4፤* ከፍጥረት መጀመሪያ እስከ ጥፋት ውሃ ማለት ነው፤ ይህ ዝርዝር የተወሰደው ከዘፍ 5፥1-32 ላይ ነው (የዚያን ማብ ይመ)። የቃየልና የአቤል ስም አለመጠቀስ የሚያሳየው የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ሥራዬ ብሎ ለመጻፍ የተነሣው እግዚአብሔር ላቀደው ዐላማ የመረጠውን የዘር ሐረግ መስመር ብቻ መሆኑን ነው (ዘፍ 4፥17-25)።

1፥4 *የኖኅ ወንዶች ልጆች፤* ይህ ሐረግ በዕብራይስጡ የዜና መዋዕል መጽሐፍ ላይ አይገኝም (*አማራጭ ትርጉሙን ይመ*)። ይህም ከአሦር ነገሥታት ስም ዝርዝር አጻጻፍ ጋር (የ1፥1-2፥1 ማብ ይመ) ተጓዳኝ ነው። ስማቸው እዚህ ላይ በግልጽ ተጽፎ ባይገኝም፣ የዜና መዋዕል ተደራስያን፣ ያለ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ እነዚህ የኖኅ ልጆች መሆናቸውን ያውቃሉ። የሰብዓ ሊቃናት ትርጒምና በርካታ የዘመኑ ትርጒሞች ዝምድናውን በግልጽ ለማሳየት ሲሉ ይህን ሐረግ አስገብተዋል።

*1፥5-23፤* ይህ የትውልድ ሐረግ የተወሰደው በዘፍ 10፥2-29 ላይ ከሚገኘው የሕዝቦች ስም ዝርዝር ነው (የዚያን ማብ ይመ)። የትውልድ ሐረጉ በዚህ መልክ የተቀናጀው ሥጋዊ ዝምድናን ሳይሆን መልክዐ ምድራዊና ባህላዊ ነገሮችን መሠረት በማድረግ

22ያባልን፣[ሀ] አቢማኤልን፣ ሳባን፣ 23ኦፊርን፣
ኤውላጥን፣ ዮባብን ወለደ፤ እነዚህ
ሁሉ የዮቅጣን ወንዶች ልጆች ናቸው።
24ሴም፣ አርፋክስድ[ለ]፣ ሳለ፣
25ዔቦር፣ ፋሌቅ፣ ራግው፣
26ሴሮሕ፣ ናኮር፣ ታራ፣
27እንዲሁም በኋላ አብርሃም የተባለው አብራም።

1፥24 ዘፍ10፥21-25፤ ሉቃ3፥34-36
1፥32 ዘፍ10፥7፤22፥24
1፥34 ዘፍ17፥5፤ ማቴ 1፥2፤ ሉቃ3፥34፤ሐሥ 7፥8
1፥35 ዘፍ36፥4:19
1፥36 ዘፀ17፥14
1፥37 ዘፍ36፥17
1፥40 ዘፍ36፥2
1፥45 ዘፍ36፥11

## የአብርሃም ቤተ ሰብ

28የአብርሃም ወንዶች ልጆች፤
ይስሐቅ፣ እስማኤል።

## የአጋር ዘሮች

1፥29-31 ተጓ ምብ - ዘፍ 25፥12-16

29የእነዚህ ዘሮች የሚከተሉት ናቸው፤
የእስማኤል በኵር ልጅ ነባዮት፣ ቄዳር፣ ነብ
ዳኤል፣ መብሳም፣ 30ማስማዕ፣ ዱማ፣ ማሣ፣
ኩዳን፣ ቴማን፣ 31ኢጡር፣ ናፌስ፣ ቄድማ፤
እነዚህ የእስማኤል ወንዶች ልጆች ናቸው።

## የኬጡራ ዘሮች

1፥32-33 ተጓ ምብ - ዘፍ 25፥1-4

32የአብርሃም ቁባት ኬጡራ የወለደቻ
ቸው ወንዶች ልጆች ዘምራን፣ ዮቅ
ሳን፣ ሜዳን፣ ምድያም፣ የስቦቅና፣ ስዌሕ
ናቸው።
የዮቅሳን ወንዶች ልጆች፤
ሳባ፣ ድዳን።
33የምድያም ወንዶች ልጆች፤
ጌፌር፣ ዔፌር፣ ሄኖኅ፣ አቢዳዕ፣ ኤልዳዓ፤
እነዚህ ሁሉ የኬጡራ ዘሮች ናቸው።

## የሣራ ዘሮች

1፥35-37 ተጓ ምብ - ዘፍ 36፥10-14

34አብርሃም ይስሐቅን ወለደ።
የይስሐቅ ወንዶች ልጆች፤
ዔሳው፣ እስራኤል።

## የዔሳው ወንዶች ልጆች

35የዔሳው ወንዶች ልጆች፤
ኤልፋዝ፣ ራጉኤል፣የዑስ፣ የዕላም፣ ቆሬ።
36የኤልፋዝ ወንዶች ልጆች፤
ቴማን፣ አማር፣ ስፎ[†]፣ ጎቶም፣
ቄኔዝ፣ ቲምናዕ፣ አማሌቅ።
37የራጉኤል ወንዶች ልጆች፤
ናሖት፣ ዛራ፣ ሣማ፣ ሚዛህ።

## በኤዶም የሚኖሩ የሴይር ሰዎች

1፥38-42 ተጓ ምብ - ዘፍ 36፥20-28

38የሴይር ወንዶች ልጆች፤
ሎጣን፣ ሦባል፣ ጽብዖን፣ ዓና፣
ዲሶን፣ ኤጽር፣ ዲሳን።
39የሎጣን ወንዶች ልጆች፤
ሖሪ፣ ሄማም፤ ቲሞናዕ የሎጣን እኅት
ነበረች።
40የሦባል ወንዶች ልጆች፤
ዓልዋን፣ ማኔሐት፣ ዔባል፣ ስፎ፣ አውናም።
የጽብዖን ወንዶች ልጆች፤
አያ፣ ዓና።
41የዓና ወንድ ልጅ፤
ዲሶን።
የዲሶን ወንዶች ልጆች፤
ሔምዳን[ሀ]፣ ኤስባን፣ ይትራን፣ ክራን።
42የኤጽር ወንዶች ልጆች፤
ቢልሐን፣ዛዕዋን፣ ዓቃን።
የዲሳን ወንዶች ልጆች፤
ዑፅ፣ አራን።

## የኤዶምያስ ነገሥታት

1፥43-54 ተጓ ምብ - ዘፍ 36፥31-43

43በእስራኤል አንድም ንጉሥ ገና ሳይነ
ግሥ[†] በኤዶም ምድር የነገሡ ነገሥ
ታት እነዚህ ናቸው፤ የቢዖር ልጅ ባላቅ፤
ከተማዪቱም ዲንሃባ ትባል ነበር።
44ባላቅ ሲሞትም የባሶራ ሰው የሆነው
የዛራ ልጅ ኢዮባብ በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ።
45ኢዮባብ ሲሞት የቴማን አገር ሰው
የሆነው ሑሳም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
46ሑሳም ሲሞት በሞዓብ ምድር ምድያ
ምን ድል ያደረገው የባዳድ ልጅ በእግሩ
ተተክቶ ነገሠ። የከተማዪቱም ስም ዓዊት

[ሀ]22 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሱርስቱ ትርጉም (እንዲሁም ዘፍ 10፥28 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ ዔባል ይላሉ።
[ለ]24 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ግን፣ *አርፋክስድ፣ ቃይናም* ይላሉ (የዘፍ 11፥0 ማብ ይመ)።
[†]36 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞችና የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም ዘፍ 36፥11 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ጼፊ* ይላሉ
[ሀ]41 ብዙ የዕብራይስጥና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞች (እንዲሁም ዘፍ 36፥26) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ሐምራን* ይላሉ።
[†]43 ወይም፣ *እስራኤላዊ የሆነ ንጉሥ ገና በእነርሱ ላይ ከመንገሡ በፊት*

ነው። የፍልስጥኤማውያንን ነገድ በመተው (ቍ 14) በድምሩ የ70 ሕዝቦች ዝርዝር ተጠቅሶአል፤ እነዚህም የያፌት 14፣ የካም 30፣ የሴም 26 ናቸው (የዘፍ 10፥2 ማብ ይመ)።

*1፥24-27፤* የ1፥1-2፥1፡ ማብ ይመ። እንዲሁም ዘፍ 11፥10-26 ይመ።

*1፥28-34፤* የዘፍ 25፥1-18 ማብ ይመ።

*1፥35-42፤* ዘፍ 36፥10-28 እና ማብ ይመ።

1፥36 ***የኤልፋዝ ወንዶች ልጆች፤*** ይህ ክፍል ከዘፍ 36፥11-12 ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይሁን እንጂ አንድ ችግር አለበት። የዜና መዋዕል የዕብራይስጡ ቅጅ ቲምናዕ የኤልፋዝ ወንድ ልጅ እንደ ሆነ ሲያወሳ፣ ዘፍ 36፥12 ግን ቲምናዕ የኤልፋዝ ቁባትና የአማሌቅ እናት እንደ ሆነ ያወሳል። የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ቲምናዕ የአማሌቅ እናት እንጂ የኤልፋዝ ወንድ ልጅ መሆኑን አይናገርም። እዚህ ላይ እንደ መፍትሔ የተሰጠው ሐሳብ የዕብራይስጡ ቅጅ ተሳስቷል፣ አልያም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ሥጋ ዝምድና የሚናገሩ መጠሪያዎችን ሆን ብሎ ትቷቸዋል የሚል ነው (የ1፥1-2፥1ማብ ይመ)። ሌሎች ደግሞ ከአንዳንድ ምክንያቶች የተነሣ የትውልድ ሐረጎችን የመለወጥ ልማድ እንዳለ ይናገራሉ (በመግቢያው ላይ "የትውልድ ሐረጎች" የሚለውን ይመ)። ቲምናዕ የሚለው ስም በኤዶም ሰዎች ዘንድ የአንድ ነገድ ስም መጠሪያ) ለመሆን በመብቃቱ (ቍ51፤ ዘፍ 36፥40) ከጊዜ በኋላ ቲምናዕ በኤዶማውያን የትውልድ ሐረግ ውስጥ "የክብር ስፍራ" አግኝቶ የኤልፋዝ ልጅ፣ የአማሌቅ ወንድም እስከ መባል ደርሶአል።

*1፥43-54፤* ዘፍ 36፥31-43 ይመ። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ኤዶም በሰፋት መተረኩን ይቀጥላል። ይህም የቃየንን የትውልድ ሐረግ ሳይጠቅስ የእስማኤልን የትውልድ ሐረግ በመጠኑ ጠቃቅሶ ከማለፉ ጋር ሲነጻጸር የሚያስደንቅ ነው። ይህ ምናልባት በዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዘመን ኤዶማውያን ታላቅ ሕዝቦች እንደ ነበሩ ያመለክታል (18፥11-13፤2ዜና 8፥17፤21፥8፤ 25፥20፤ 28፥17)።

ተባለ።
47ሃዳድም ሲሞት የመሥሬቃ ሰው የሆ
ነው ሠምላ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
48ሠምላም ሲሞት በወንዙ[ሠ] አጠገብ ያለ
ችው የረኆቦት ሰው የሆነው ሳኡል
በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
49ሳኡልም ሲሞት የዓክቦር ልጅ የሆነው
በአልሐናንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
50በአልሐናን ሲሞት ሀዳድ በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ። ከተማውም ፋዑ ትባል
ነበር፤ ሚስቱ መሄጣብኤል ትባላ
ለች፤ እርሷም የሜዛሃብ ልጅ የመ
ጥሬድ ልጅ ነበረች። 51ሀዳድም ሞተ።

ዋና ዋናዎቹ የኤዶም ሕዝብ አለቆች እነ
ዚህ ነበሩ፤
ቲምናዕ፣ ዓልዋ፣ የቴት፣ 52አህሊባማ፣
ኤላ፣ ፊኖን፣ 53ቄኔዝ፣ ቴማን፣ሚብሳር፣
54መግዲኤል፣ዒራም። እነዚህ የኤዶም
አለቆች ነበሩ።

## የእስራኤል ወንዶች ልጆች

2፥1-2 ተጓ ምብ - ዘፍ 35፥23-26

2 የእስራኤል ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤
ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣
ዛብሎን፣ 2ዳን፣ ዮሴፍ፣ ብንያም፣ ንፍታሌም፣
ጋድ፣ አሴር።

## ይሁዳ

2፥5-15 ተጓ ምብ - ሩት 4፥18-22፤ ማቴ 1፥3-6

## እስከ ኤስሮን ወንዶች ልጆች

3የይሁዳ ወንዶች ልጆች፤
ዔር፣ አውናን፣ ሴሎም፤ እነዚህን ሦስቱን
ከከነዓናዊት ሚስቱ ከሴዋ ወለደ። የበኵር
ልጁ ዔር በእግዚአብሔር ፊት ክፉ
ሰው ሆነ፤ እግዚአብሔርም ቀሠፈው።
4የልጁም ሚስት የነበረችው ትዕማር
ፋሬስንና ዛራን ወለደችለት፤ ይሁዳም
ባጠቃላይ አምስት ወንዶች ልጆች
ነበሩት።
5የፋሬስ ወንዶች ልጆች፤
ኤስሮም፣ ሐሙል።
6የዛራ ወንዶች ልጆች፤
ዘምሪ፣ ኤታን፣ ሄማን፣ ከልኮል፣ ዳራ[ረ]፤
ባጠቃላይ አምስት ናቸው።
7የከርሚ ወንድ ልጅ አካን[ሰ]፤
እርሱም ፈጽሞ መደምሰስ የነበረበትን
ነገር ሰርቆ በእስራኤል ላይ ጥፋት[ሸ]
እንዲመጣ ያደረገ ነው።
8የኤታን ወንድ ልጅ፤
አዛርያ።
9የኤስሮም ወንዶች ልጆች፤
ይረሕምኤል፣ አራም፣ ካሌብ።[ቀ]

## ከኤስሮም ልጅ ከአራም ጀምሮ ያለው የትውልድ ሐረግ

10አራም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብም የይሁዳ ሕዝብ መሪ የሆነውን
ነአሶንን ወለደ፤11ነአሶን ሰልሞንን[በ]

2፥3 ዘፍ29፥35፤ 38፥2-10፤ ዘኁ26፥19
2፥5 ዘፍ46፥12፤ ዘኁ26፥21
2፥7 ኢሱ6፥18፤7፥1
2፥9 ዘኁ26፥21
2፥10 ዘፀ6፥23፤ ዘኁ1፥7፤ሉቃ3፥32-33

[ሠ]48 ምናልባት *ኤፍራጥስን* ነው።
[ረ]6 አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራይስጥ፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የሱርስቱ ቅጆች (እንዲሁም 1ነገ 4፥31 ይመ) ግን፣ *ዳርዳ* ይላሉ።
[ሰ]7 *አካን* ማለት፣ *ችግር ወይም፣ መከራ* ማለት ነው።
[ሸ]7 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል።
[ቀ]9 ዕብራይስጡ፣ *ክሉባይ* ይላል፤ ይኸውም፣ *ካሌብ* ማለት ነው።
[በ]11 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (እንዲሁም ሩት 4፥21) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ሳልማ*

*2፥1-2፤* ምንም እንኳ በብሉይ ኪዳን ስለ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ስም ዝርዝር የያዙ ብዙ ክፍሎች ቢኖሩም፣ የትውልድ ሐረጎቹን በቅደም ተከተል ያቀረቡት አራቱ ብቻ ናቸው (1) ዘፍ29፥31-30፥24፤ 35፥16-20፤ (2) ዘፍ35፥22-26፤ (3) ዘፍ46፥8-27፤ (4) በዚህ ክፍል የነገዶቹ ስም ዝርዝር በ12፥24-37፤ 27፥16-22፤ ዘፀ፡1፥2-5፤ ዘዳ 27፥12-13፤ 33፤ ሕዝ 48፥31-34 ላይ ተገልጾአል። በሌሎቹ የስም ዝርዝሮች ውስጥ የሌዊ ነገድ አልተጠቀሰም፤ የዮሴፍን ነገድ ኤፍሬምና ምናሴ በማለት ሁለት ቦታ ከፍለው የእስራኤልን ነገድ ቍጥር ዐሥራ ሁለት ያደርሱታል። (ዘኁ1፥5-15፤1፥20-43፤2፥3-31፤7፥12-83፤10፥14-28፤13፥4-15፤26፥5-51)። እዚህ ላይ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የሚከተለው ዘፍ 35፥22-26 ይመስላል፤ ሆኖም የዳንን ነገድ ተራ ከዘጠኝ ወደ ሰባት አውርዶታል። እዚህ ላይ ጸሐፊው የሌሎቹን ነገዶች ስም ዝርዝር አልጠቀሰም፤ ይልቁንም የጽሑፉ ዐላማ ወደ ሆነው ወደ ዳዊት የዘር ሐረግና ወደ ይሁዳ ነገድ በቀጥታ ያመራል (2፥3-4፥23)፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የነገዶቹን ስም በሚዘረዝርባቸው ምዕራፎች ውስጥ ቍጥር "12"ን ጠብቋል፤ ቅደም ተከተላቸው ግን ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ይሁዳ፣ ስምዖን፣ ሮቤል፣ ጋድ፣ የምናሴ ነገድ እኩሌታ፣ ሌዊ፣ ይሳኮር፣ ብንያም፣ ንፍታሌም፣ ኤፍሬም፣ምናሴና አሴር፤ ዛብሎንና ዳን ግን በዝርዝሩ ውስጥ አልተጠቀሱም።

*2፥3-9፤* የይሁዳ ትውልድ ሐረግ የሚወርደው በኤስሮም ወንዶች ልጆች በኩል ነው (ቍ9)፤ የእነዚህም የዘር ሐረግ በ2፥10-3፥24 ላይ ተጽፎአል። ከይሁዳ አምስት ወንዶች ልጆች መካከል ሁለቱ (ዔርና አውናን) የሞቱት በዘፍ 38 ላይ በተጠቀሰው ኀጢአታቸው ምክንያት ነው። የሦስተኛው ልጅ ማለትም የሴሎም ትውልድ ሐረግ በ4፥21 ላይ ተወሥቶአል፤ ይህ ክፍል የሚያተኩረው በቀሩት በሁለቱ ላይ ነው (ዘፍ46፥12፤ዘኁ26፥19-22)።

2፥6 *ኤታን፣ሄማን፣ከልኮል፣ዳራ፤* እነዚህ በቀጥታ ከዛራ የተወለዱ አይደሉም፤ ነገር ግን በሰሎሞን ዘመን የተወለዱ የልጅ ልጆች ናቸው (1ነገ4፥31)። ሄማንና ኤታን የዳዊት መዘምራን ነበሩ (15፥19፤ የመዝ 88-89 ርእስ ይመ)፤ ይሁን እንጂ እዚህ ላይ የተጠቀሱት እነርሱ ይሁኑ ወይም ሌሎች ሰዎች በውል አይታ ወቅም። እንደ ተባለው እነዚህ ራሳቸው ከሆኑ በ6፥33-42 እና በ15፥19 ላይ ሄማንና ኤታን በሌዊ ነገድ ውስጥ ገብተዋል ወይም ተደልድለዋል ማለት ነው፤ ይህም የትውልድ ሐረጋቸው ከአንዱ ነገድ ወደ ሌላው እንዲገቡና የዜማ መሣሪያ የመጫወት ችሎታቸውም ወደ ሌዊ የዘር ሐረግ እንዲገቡ አድርጎአቸዋል ማለት ነው፤ ወይም ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ሆኖአል፤ ሌዋውያን ከይሁዳ ጋር ኅብረት ስላላቸው፣ በዚህ ነገድ ውስጥ ተደምረዋል።

2፥7 *አካን፤* የስሙ ትርጕም "ችግር" ማለት ነው።

*2፥10-3፥24፣* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለይሁዳ የትውልድ ሐረግ ትኵረት የሰጠበት ምክንያት የዳዊትን የዘር መስመር ለማስጨበጥ በመሆኑ ይህ የቀረበው ዝርዝር የዘር ሐረጉን ግልባጭ የሚያሳይ ነው።
የአራም ዘሮች (የዳዊት ቅድመ አያቶች፤2፥10-17)
የካሌብ ዘሮች (2፥18-24)
የይረሕምኤል ዘሮች (2፥25-33)
ይረሕምኤልን በተመለከተ የተጨመሩ (2፥34-41)
ካሌብን በተመለከተ የተጨመሩ (2፥42-55)
አራምን (የዳዊትን ዘሮች) በተመለከተም የተጨመሩ (ም 3)
ጸሐፊው ይህን የይሁዳን ትውልድ ሐረግ መካከለኛ ክፍል ያዋቀረው የዳዊትን ቅድመ አያቶችና የእርሱን ዘሮች አጕልቶ ለማሳየት ነው። ይህም ጸሐፊው በዚህ ታሪክ ውስጥ ዳዊት ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን ለማሳየት የተጠቀመበት መንገድ ነው።

*2፥10-17፤* ቍ 10-12 የሚያሳየው ከአራም እስከ እሴይ ያለውን የትውልድ ሐረግ ሲሆን፣ ከዚያም የእሴይ ትውልድ ሐረግ በንኡስ ሐረጎች ተከፋፍሎአል። ይህም በ1ሳሙ 16፥1-13)

ወለደ፤ ሰልሞን ቦዔዝን ወለደ፡፡ 12ቦዔዝ
ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድ እሴይን
ወለደ፡፡
13የእሴይ ወንዶች ልጆች፤
የበኵር ልጁ ኤልያብ፣ ሁለተኛ ልጁ
አሚናዳብ፣ ሦስተኛ ልጁ ሣማ፣ 14አራ
ተኛ ልጁ ናትናኤል፣ አምስተኛ ልጁ
ራዳይ፣ 15ስድስተኛ ልጁ አሳም፣ ሰባ
ተኛ ልጁ ዳዊት፡፡ 16እኅቶቻቸውም
ጽሩያና አቢግያ ነበሩ፡፡ የጽሩያ ሦስት
ወንዶች ልጆች አቢሳ፣ኢዮአብና አሣ
ኤል ነበሩ፡፡ 17አቢግያ አሜሳይን ወለ
ደች፤ አባቱም ዬቴር የተባለ እስማኤ
ላዊ ነበረ፡፡

## የኤስሮም ልጅ ካሌብ

18የኤስሮም ልጅ ካሌብ ከሚስቱ ከዓዙ
ባና እንዲሁም ከይሪዖት ወንዶች
ልጆች ወለደ፤ ከዓዙባ የተወለዱት
ወንዶች ልጆች እነዚህ ናቸው፤ ያሳር፣
ሶባብ፣ አርዶን፡፡ 19ዓዙባ ስትሞት
ካሌብ ኤፍራታን አገባ፤ እርሷም ሆርን
ወለደችለት፡፡ 20ሆር ኡሪን ወለደ፤
ኡሪም ባስልኤልን ወለደ፡፡
21ከዚያም በኋላ ኤስሮም ሥልሳ ዓመት
ሲሆነው የገለዓድን አባት የማኪርን
ልጅ አገባ፤ እርሷም ሠጉብን ወለደ
ችለት፡፡ 22ሠጉብም ኢያዕርን ወለደ፤ እር
ሱም በገለዓድ ምድር ሃያ ሦስት ከተሞች
ያስተዳድር ነበር፡፡ 23ይሁን እንጂ ጌሹ
ርና አራም፣ ቄናትንና በዙሪያዋ የሚ
ገኙትን ሥልሳ መንደሮች ጨምሮ
የኢያዕርን ከተሞች ነጠቁት፡፡ እነዚህ
ሁሉ የገለዓድ አባት የማኪር ዘሮች
ነበሩ፡፡ 24ኤስሮም በካሌብ ኤፍራታ ከሞተ
በኋላ፣ ሚስቱ አቢያ የቴቁሔን አባት*
አሽሑርን ወለደችለት፡፡

## የኤስሮም ልጅ ይረሕምኤል

25የኤስሮም የበኵር ልጅ የይረሕምኤል
ወንዶች ልጆች፤ የበኵር ልጁ ራም፣
ቡናህ፣ አሬን፣ አጼም፣ አኪያ፡፡ 26ይረሕ
ምኤል ዓጣራ የተባለች ሌላ ሚስት
ነበረችው፤ እርሷም የኦናምን እናት ነበረች፡፡
27የይረሕምኤል የበኵር ልጅ የራም ወንዶች፤
መዓስ፣ ያሚን፣ ዔቄር፡፡
28የኦናም ወንዶች ልጆች፤
ሸማይና ያዳ፡፡
የሸማይ ወንዶች ልጆች፤
ናዳብና አቢሱር፡፡
29የአቢሱር ሚስት አቢካኢል ትባላለች፤
እርሷም አሕባንንና ሞሊድ የተባሉ
ልጆች ወለደችለት፡፡
30የናባድ ወንዶች ልጆች፤
ሴሌድ፣ አፋይም፤ ሴሌድ ወንድ ልጅ ሳይ
ወልድ ሞተ፡፡
31የአፋይም ወንድ ልጅ፤
ይሽዒ፡፡ ይሽዒም ሶሳን ወለደ፡፡
ሶሳን አሕላይን ወለደ፡፡
32የሸማይ ወንድም የያዳ ወንዶች ልጆች፤
ዬቴር፣ ዮናታን፤ ዬቴርም ልጅ ሳይወልድ
ሞተ፡፡
33የዮናታን ወንዶች ልጆች፤
ፌሌት፣ ዛዛ፡፡
እነዚህ የይረሕምኤል ዘሮች ነበሩ፡፡
34ሶሳን ሴቶች ልጆች እንጂ ወንዶች
ልጆች አልነበሩትም፡፡ እርሱም ኢዮ
ሄል የተባለ ግብፃዊ አገልጋይ ነበረው፡፡
35ሶሳን ልጁን ለአገልጋዩ ለኢዮሄል ሚስት
ትሆነው ዘንድ ሰጠው፤ እርሷም ዓታይ
የተባለ ወንድ ልጅ ወለደችለት፡፡
36ዓታይ ናታንን ወለደ፤
ናታንም ዛባድን ወለደ፤
37ዛባድ ኤፍላልን ወለደ፤
ኤፍላል ዖቤድን ወለደ፤
38ዖቤድ ኢዩን ወለደ፤
ኢዩ ዓዛርያስን ወለደ፤
39ዓዛርያስ ኬሌስን ወለደ፤
ኬሌስ ኤልዓሣን ወለደ፤
40ኤልዓሣ ሲስማይን ወለደ፤
ሲስማይ ሰሎምን ወለደ፤
41ሰሎም የቃምያን ወለደ፤
የቃምያም ኤሊሳማን ወለደ፡፡

2፥12 ሩት2፥1፤4፥ 17
2፥13ሩት4፥17፤ 1ሳሙ16፥6
2፥16 1ሳሙ 26፥6 ሳሙ2፥13:18
2፥17 2ሳሙ17፥25
2፥19 ቍ42:50
2፥20 ዘፀ31፥2
2፥21 ዘኍ27፥1
2፥23 ዘኍ32፥41፡ 42፤ዘዳ3፥14
2፥24 1ዜና4፥5
2፥36 1ዜና11፥41

*23 ወይም፣ የኢያዕርን መንደሮች ከተማ
*24 በዚህም ሆነ በቍጥር 42፡45፡ 49 - 52 ላይ፣ አባት ማለት፣ የአገር ሽማግሌ ወይም፣ የጦር መሪ ማለት ነው፡፡

ላይ ዳዊት ለንጉሥነት እንደ ተቀባ የሚናገረውን ታሪክ ያስታውሰናል፡፡ ለአብዛኛው የዘር ሐረግ ምንጩ ሩት (4፥19-22) ነው፡፡ በ1ሳሙ 16፥10-13 ላይ ተጽፎ እንደምናገኘው፣ ዳዊት በሳሙኤል ፊት ከቀረቡት የእሴይ ልጆች የመጨረሻው ትንሹ ስምንተኛው ልጅ ነው፡፡ እዚህ ላይ ግን የተጠቀሱት ሰባት ብቻ ሲሆኑ፣ ይህም ዳዊት ሰባተኛው ልጅ ተገቢ የሆነውን ቦታ እንዲይዝ ያደርገዋል (ቍ15፤ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "የትውልድ ሐረግ" የሚለውን ይመ)፡፡ ዳዊት የጀግኖቹ (ተዋጊዎች) የአቢሳይ፣ የኢዮአብ፣ የአሣሄልና የአሜሳያ አጎት ነው (11፥6፡ 20፡ 26፤ 2ሳሙ 2፥13:18፤17፥25፤19፥13)፡፡

*2፥18-24፤* እዚህ ላይ ጸሐፊው ትልቅ ግምት የሰጠው ስም ከካሌብ የትውልድ ሐረግ ውስጥ የባስልኤልን ነው (ቍ20)፡፡ እርሱም የመገናኛውን ድንኳን ሥራ እየተቈጣጠረ በኀላፊነት ያሠራ ጠቢብ ባለሙያ ነበር (ዘጸ31፥1-5)፡፡ የዚህ ሰው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ የምናገኘው በዘፀአትና በዜና መዋዕል ላይ ነው፡፡ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በዚህ ክፍል የቤተ መቅደሱን ሥራ በተመለከተ (የ2ዜና:1፥5 ማብ ይመ) ለሰሎሞንና ለኪራምአቢ እንደ ምሳሌ አድርጎ ያቀረባቸው ባስልኤልንና ኤልያብን ነው (ዘፀ31፥1-5)፡፡ የምስክሩን ድንኳን በረቀቀ ብልኀት የሠራውን ሰው እዚህ ላይ አምጥቶ ከዳዊት ትውልድ ሐረግ ጋር በማያያዝ (ቍ10-17) የንጉሡንና የቤተ መቅደሱን ዐላማና ፍሬ ሐሳብ ጐን ለጐን ለማሳየት ሞክሯል፤ ይህን ያደረገውም ታሪኩን በዝርዝር ለማቅረብ ስለሚጠቅመው ነው፡፡

*2፥25-33፤* ይህ ክፍል ተለይቶ የሚታወቀው እንደ መግቢያና እንደ መደምደሚያ አድርጎ በሚጠቀምባቸው "የይረሕምኤል ልጆች" (ቍ25) እንዲሁም "የይሕረምኤል ዘሮች" ናቸው በሚለው ነው (ቍ33)፡፡ የይሕረምኤል ትውልድ ሐረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ የሚገኘው በቍ25-41 ላይ በዚህ ክፍል ብቻ ነው፡፡ 1ኛ ሳሙ 27፥10 እና 30፥27-29 ላይ እነዚህ ሰዎች የሰፈሩት በነጌብ እንደ ሆነ ተመልክቷል፡፡

*2፥34-41፤* በሶሳን ትውልድ ሐረግ (ቍ31) ላይ የተጨመረ ነው፡፡ ይህም እስከ 13 ትውልድ ዘልቆ የሚወርድ የትውልድ ሐረግ ነው፡፡ የኤሊሳማ ትውልድ (ቍ:41) ከይሁዳ ጀምሮ ሲቈጠር ሃያ ሦስተኛ ይሆናል፡፡ በመካከሉ የተዘለሉ ስሞች ባይኖሩ ኖሮ፣ ይህን ያህል በትክክል የምናውቀው ነገር አይኖርም ነበር፤ ዳዊትና ኤሊሳማ በአንድ ዘመን ሳይኖሩ እንዳልቀሩ መገመት ይቻላል፡፡

## የካሌብ ጐሣዎች

42የይረሕምኤል ወንድም የካሌብ ወንዶች
ልጆች፤
የበኵር ልጁ ሞሳ ሲሆን፣ እርሱም ዚፍን
ወለደ፤ ዚፍም መሪሳን° ወለደ፤ መሪ
ሳም ኬብሮንን ወለደ።
43የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤
ቆሬ፣ ተፉዋ፣ ሬቄም፣ ሽማዕ። 44ሽማዕ
ረሐምን ወለደ፤ ረሐምም ዮርቅዓምን
ወለደ። ሬቄም ሸማይን ወለደ፤ 45ሸማ
ይም ማዖንን ወለደ፤ ማዖንም ቤት
ጹርን ወለደ።
46የካሌብ ቁባት ዔፉ ሐራንን፣ ሞጻን፣
ጋዜዝን ወለደች። ሐራንም ጋዜዝን
ወለደ።
47የያህዳይ ወንዶች ልጆች፤
ሬጌም፣ኢዮታም፣ ጌሻን፣ ፋሌጥ፣ ዔፋ፣
ሸዓፍ።
48የካሌብ ቁባት ማዕካ ሼቤርን፣ ቲርሐናን
ወለደችለት። 49እንዲሁም የመድማናን
አባት ሸዓፍን፣ የመክቢናንና የጊብዓን
አባት ሱሳን ወለደች። ካሌብ ዓክሳ
የተባለች ልጅ ነበረችው። 50እነዚህ ሁሉ
የካሌብ ዘሮች ነበሩ።

የኤፍራታ የበኵር ልጅ የሑር ወንዶች
ልጆች፤
ሦባል የቂርያትይዓሪም አባት፤ 51ሰል
ሞን የቤተልሔም አባት፤ ሐሬፍ የቤት
ጋዴር አባት።
52 የቂርያትይዓሪም አባት የሦባል ዘሮች፤
የመናሕታውያን ነዋሪዎች እኩሌታ፣ ሀሮኤ፤
53እንዲሁም የቂርያትይዓሪም ጐሣዎች፤ ይት
ራውያን፣ ፉታውያን፣ ሹማታውያን፣ ሚሽ
ራውያን፣ ጾርዓውያንና ኤሽታኦላውያን ከእ
ነዚህ የመጡ ጐሣዎች ነበሩ።
54የሰልሞን ዘሮች፤
ቤተልሔም፣ ነጦፋውያን፣ ዓጥሮትቤት
ዮአብ፣ የመናሕታውያን እኩሌታ፣ ጾርዓ
ውያን። 55በያቤጽ የሚኖሩ የጸሐፍት
ጐሣዎች፡ ቲርዓውያን፣ ሺምዓታውያን፣
ሡካታውያን። እነዚህ ከሬካብ ቤት አባት
ከሐማት የመጡ ቄናውያን ናቸው።

## የዳዊት ወንዶች ልጆች

3፥1-4 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 3፥2-5
3፥5-8 ተጓ ምብ -2 ሳሙ 5፥14 -16 ፤ 1ዜና 14፥4 -7

3ዳዊት በኬብሮን ሳለ የወለዳቸው ወን
ዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤
ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆም የተወ
ለደው የበኵር ልጁ አምኖን፣ ሁለተ
ኛው ከቀርሜሉሳዊቷ ከአቢግያ የተወ
ለደው ዳንኤል፣
2ሦስተኛው ከጌሹር ንጉሥ ከተልማይ
ልጅ ከመዓካ የተወለደው አቤሴሎም፣
አራተኛው የአጊት ልጅ አዶንያስ፣
3አምስተኛው የአቢጣል ልጅ ሰፋጥያስ፣
ስድስተኛው ከሚስቱ ከዔግላ የተወለ
ደው ይትረኃም።
4እነዚህ ስድስቱ የተወለዱት ዳዊት
በኬብሮን ሆኖ ሰባት ዓመት ተኩል
በገዛበት ጊዜ ነበር።
ዳዊት በኢየሩሳሌም ሠላሳ ሦስት ዓመት
ነገሠ፤ 5በዚያም የወለዳቸው ልጆች እነዚህ
ነበሩ፤
ሳሙስ፣ᵖ ሶባብ፣ ናታን፣ ሰሎሞን፤ እነ
ዚህ አራት ወንዶች ልጆች ከዓሚኤል
ልጅ ከቤርሳቤህ የተወለዱ ናቸው። 6እን
ዲሁም ሌሎች ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
ስማቸውም ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣ ኤሊ
ፋላት፣ 7ኖጋ፣ ናፌቅ፣ ያፍያ፣ 8ኤሊሳማ፣
ኤሊዳሄ፣ ኤሊፋላት ይባላል፤ ባጠቃላይ
ዘጠኝ ነበሩ። ከቁባቶቹ ከወለዳቸው
ወንዶች ልጆች ሌላ እነዚህ ሁሉ ልጆቹ
ነበሩ፤ እነዚህም ትዕማር የምትባል እኅት
ነበረቻቸው።

°42 የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።
ᵇ55 ወይም፣ "ሰፍራውያን"
ᵖ5 ዕብራይስጡ፣ "ሺማ" ይላል፤ "ሻሙአ" ከሚለው ጋር አንድ ነው።

2፥45 ኢሱ 15፥55፡ 58
2፥49 ኢሱ15፥16፡31
2፥50
ቍ19፤ 1ዜና 4፥4
2፥53 2ሳሙ23፥38
2፥54 ዕዝ2፥22፤
ነህ 7፥26፤12፥28
2፥55 ዘፍ15፥19፤
ኢሱ19፥35፤መሳ4፥11፤
2ነገ10፥15፡23፤
ኤር35፥2-9
3፥1ኢሱ15፥56፤
1ሳሙ25፥42፡43፤
1ዜና14፥3፤28፥5
3፥2 1ነገ2፥22
3፥4 2ሳሙ5፥4፡5፤
1ዜና29፥27
3፥5 2ሳሙ11፥3
3፥9 2ሳሙ13፥1፤
1ዜና14፥4

*2፥42-55፤* በቍ25 እና 33 ላይ እንዳየነው ሁሉ እዚህ በቍጥር 42 እና 50 ላይ "የካሌብ ወንዶች ልጆች... የካሌብ ዘሮች እነዚህ ናቸው" የሚሉትን ሐረጐች በመግቢያና በመደምደሚያ ላይ እናገኛቸዋለን። በዚህ ክፍል የተጻፈው የስም ዝርዝር የግለሰብንና የቦታን ስም ያደባልቃል። "አባት" የሚለው ሐረግ "ይህን ከተማ የቈረቈረው ወይም የዚህ ከተማ መሪ" ማለት መሆኑ መታወቅ አለበት።

*2፥50-55፤* የሑርን ዘሮች ትውልድ በመቀጠል ያቀርባል (ቍ:20)፤ እዚህም ላይ በቍ 25 እና 33 እንዲሁም በቍ 42 እና 50 ላይ የምናገኛቸው በቍ 50 እና 4፥4 ላይ ተዘርዝረዋል። በመግቢያውና በመደምደሚያው ላይ "የሑር ወንዶች ልጆች... የካሌብ ዘሮች እነዚህ ናቸው" የሚለው የእነዚህ ሐረጐች መኖር ይህ ክፍልና 4፥1-4 ቀድሞ የአንድ ዐውደ ምንባብ ክፍሎች ነበሩ ብለን እንድናስብ ያደርገናል። ጸሐፊው የዳዊትን ዘሮች (ም3) በእነዚህ በሌሎቹ የትውልድ ሐረጐች መካከል ጣልቃ አስገብቶታል፤ ይህን ያደረገውም በእነዚህ ክፍሎች ያመለከታቸውን የትውልድ ሐረጐች ዝርዝር ከዋነኛ ዐላማው ጋር ለማጣጣም ሲል ያደረገው መሆኑ መገመት ይቻላል። (የ2፥10-3፥24፤4፥1-23ማብ ይመ)። አለበለዚያ የተከፈለውን የሑር ትውልድ ሐረግ ጸሐፊው ምንጩ ባደረገው ክፍል ውስጥ ባስገባው ነበር።

2፥55 *ቲርዓውያን፣ ሺምዓታውያን፣ሡካታውያን፤* እዚህ ላይ እንደ ተተረጐመው ሦስት ቤተ ሰቦችን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ በሦስት በተለያየ ክፍል የተመደቡ ጸሓፍትን ማለትም የሚያነቡ፣ የሚገለብጡና ሥራው ደረጃውን መጠብቅ አለመጠበቁን የሚቈጣጠሩትን ሊያመለክት ይችላል። *ቄናውያን፤* በመሠረቱ እነዚህ ሌላ ሕዝብ ናቸው። ከቄናውያን አብዛኞቹ ከይሁዳ ሕዝብ ጋር በመቀላቀል አንድ ሆነዋል (ዘኍ10፥20-32፤ መሳ 1፥16፤4፥11)።

*3፥1-24፤* የ2፥10-3፥24 ማብ ይመ።

*3፥1-9፤* የዳዊትን ልጆች የሚያሳየው የስም ዝርዝር አብዛኛው የተወሰደው ከ2 ሳሙ 3፥2-5፤ 5፥13-16፤ 13፥1 ላይ ነው (የእነዚህን ማብ ይመ)። በኢየሩሳሌም የወለዳቸው ወንዶች ልጆቹ የስም ዝርዝር በ1 ዜና 14፥3-7 ተደግሞአል። ኤሊፋላት የሚለው ስም ሁለት ጊዜ ተወሥቶአል (ቍ6:8)፤ በምዕ 14፥5:7 ይህ ስም ሆህያቱ በተለያዩ ሁለት ስሞች ውስጥ ይገኛሉ። በ2 ሳሙ 5፥14-16 ግን በዚህ ስም የተወሣው አንድ ሰው ብቻ ነው። ዳዊት በኬብሮን ሰባት ዓመት የገዛው (ቍ4) በዚህ ጊዜ እንደ ነበረ፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ባይተርከም፣ በምዕ 29፥27 ላይ ተደግሞ ተወሥቶአል። አቤሴሎም፣ ትዕማር፣አዶንያስ፣አምኖን፣ ቤርሳቤህ የተባሉት ስሞች በሚወሡበት ጊዜ፣ ከእነዚህ ሰዎች የተነሣ በዳዊት ሕይወት ያጋጠሙን ከፉ ጊዜ (የሐዘን ጊዜ) የሚያስታውሱ በመሆናቸው፣ ጸሓፊው በቀጣይ ትረካው ውስጥ አልዘገበውም (2ሳሙ:11-15፤17-18፤1ነገ:1ይመ)።

## የይሁዳ ነገሥታት

10የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም ነበረ፤
የሮብዓም ልጅ አቢያ፣
የአቢያ ልጅ አሳ፣
የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ፣
11የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢዮራም፣
የኢዮራም ልጅ አካዝያስ፣
የአካዝያስ ልጅ ኢዮአስ፣
12የኢዮአስ ልጅ አሜስያስ፣
የአሜስያስ ልጅ ዓዛርያስ፣
የዓዛርያስ ልጅ ኢዮአታም፣
13የኢዮአታም ልጅ አካዝ፣
የአካዝ ልጅ ሕዝቅያስ፣
የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ፣
14የምናሴ ልጅ አሞጽ፣
የአሞጽ ልጅ ኢዮስያስ::
15የኢዮስያስ ወንዶች ልጆች፤
በኵሩ ዮሐናን፣
ሁለተኛ ልጁ ኢዮአቄም፣
ሦስተኛ ልጁ ሴዴቅያስ፣
አራተኛ ልጁ ሰሎም::
16የኢዮአቄም ዘሮች፤
ልጁ ኢኮንያ፣ ልጁ ሴዴቅያስ::

3፥10 1ነገ14፥21-31፤15፥1-8፡9-24፤ 2ዜና12፥16፤13፥1፤17፥1-21
3፥11 2ነገ8፥16-25፤10፥14፤11፥1-12፤12፥21፤2ዜና21፥1፤22፥1-10፤11-24፡27
3፥13 2ነገ16፥1-20፤18፥1-20፥21፤21፥1-18፤ 2ዜና 29፥1፤33፥1፤ኢሳ1፥1፤ኤር26፥19፤ሆሴ1፥1፤ሚክ1፥1
3፥14 2ነገ21፥19-26፤22፥1፤2ዜና33፥21፤34፥1፤ኤር1፥2፤3፥6፤25፥3፤ሶፎ1፥1
3፥15 2ነገ23፥31፡34፤ኤር37፥1
3፥16 2ነገ24፥6፡ 8፡18
3፥17 ዕዝ32
3፥18 ዕዝ1፥8፤ 5፥14፤ ኤር 22፥30
3፥19 ዕዝ2፥2፤3፥2፤5፥2፤ነህ7፥7
3፥22 ዕዝ8፥2-3

## ከምርኮ በኋላ የነበረው የነገሥታቱ የትውልድ ሐረግ

17የምርኮኛው የኢኮንያን ዘሮች፤
ልጁ ሰላትያል፣ 18መልኪራም፣
ፈዳያ፣ ሼናጻር፣ ይቃምያ፣ ሆሻማ፣ ነዳብያ::
19የፈዳያ ወንዶች ልጆች፤
ዘሩባቤል፣ ሰሜኢ::
የዘሩባቤል ወንዶች ልጆች፤
ሜሱላም፣ ሐናንያ፤
እኅታቸው ሰሎሚት ትባላለች::
20ሌሎችም አምስት ልጆች ነበሩ፤
እነርሱም ሐሹባ፣ ኦሄል፣ በራክያ፣
ሐሳድያ፣ ዮሻብሒሴድ::
21የሐናንያ ዘሮች፤
ፈላጥያ፣ የሻያ፤ እንዲሁም የረፋያ፣
የአርናን፣ የአብድዩና የሴኬንያ
ወንዶች ልጆች::
22የሴኬንያ ዘሮች፤
ሸማያና ወንዶች ልጆቹ፤
ሐጡስ፣ ይግአል፣ ባሪያሕ፣ ነዓርያ፣
ሻፋጥ፤ ባጠቃላይ ስድስት ነበሩ::
23የነዓርያ ወንዶች ልጆች፤
ኤልዮዔናይ፣ ሕዝቅያስ፣ ዓዝሪቃም፤
ባጠቃላይ ሦስት ነበሩ::

3፥10 *ሮብዓም፤* 2 ዜና 10-12 ይመ:: *የአቢያ፤* 2 ዜና 13፥1-14፥1 ይመ:: *አሳ፤* 2ዜና14-16 ይመ:: *ኢዮሣፍጥ፤* 1ነገ22 ይመ::

3፥11 *የኢዮራም፤* 2ዜና 21 ይመ::

3፥13 *የአካዝ፤* 2ዜና 28 ይመ *የሕዝቅያስ፤* 2ዜና 29-32 ይመ:: *የምናሴ፤* 2ዜና 33፥1-20 ይመ::

3፥14: *የአሞጽ፤* 2ዜና:33፥21-25 ይመ:: *ኢዮስያስ፤* 2 ነገ 22፥1-23፥30፤ 2ዜና 34፥1-36፥1 ይመ::

3፥15-16 "*በኵሩ ዮሐናን፤*" በሌላ ስፍራ አልተጠቀሰም:: ዮሐናን ምናልባት ከኢዮስያስ በፊት ሞቶ ይሆናል:: ትውልደ ሐረጉ በቍ10-14 ላይ እንደምናገኘው በቀጥታ ተያይዞ በመውረድ ፈንታ በንኡስ ዘርፎች ተከፋፍሎአል:: ይህም የኢዮስያስ ሦስት ሌሎች ልጆቹ በተከታታይ ዙፋኑን የሚወርሱ ስለ ሆነ፣አወራረሱ ቀጥታ መስመሩን ተከትሎ ከአባት ወደ ልጅ የሚወርድ አይደለም:: ኢዮአክስን (2ዜና36፥2-4፤ 2ነገ23፥30-35) የተካው ኢዮአቄም ነበረ (2ዜና36፥5-8፤ 2 ነገ 23፥34-24፥6)፤ የኢዮአ ቄምን ዙፋን ልጁ ዮአኪን ወረሰ (2ዜና36፥9-10፤ 2 ነገ 24፥8-16)፤ ዮአኪን በናቡከደነጸር ተማርኮ ወደ ባቢሎን ከተወሰደ በኋላ፣ የኢዮስያስ ሦስተኛ ልጁ ሴዴቅያስ (2ነገ24፥18-20፤ 2 ዜና 36፥11-14) የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ሆነ።

*3፥17-20፤* ዮአኪን ሰባት ወንዶች ልጆች እንዳሉት ተነግሮአል፤ ይሁን እንጂ አንዱም እንኳ በዙፋኑ አልተተካም (የቍ15-16፤ የኤር22፥30 ማብ ይመ):: ከናቡከደነጸር ዐሥረኛው እስከ ሠላሳ አምስተኛው ዘመነ መንግሥት (ከ595-570 ዓ.ቅ.ክ) ጊዜ ውስጥ የተገኙት የሸክላ ሰሌዳዎችና በባቢሎን ተይዘው ቀለብ የሚሰፈርላቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር የሚያወጣው ሰነድ የኢዮአቄምን አምስቱን ወንዶች ልጆቹንና የሌሎቹን አይሁድ ስም ይዞ ይገኛል:: ዮአኪን ከናቡከደነጸር ዐልጋ ወራሽ ከዮር ማሮዴቅ (562-560 ዓ.ቅ.ክ) ብዙ የተትረፈረፈ ሀብት በየጊዜው ይቀበል ነበር (2ነገ25፥27-30)::

3፥18 *ሼናጻር፤* ለሼሽባጻር ሌላው ስሙ ሊሆን ይችላል:: ይህም ትክክል ከሆነ፣ ወደ ይሁዳ ምድር የሚመለሰውን የቤተ መቅደስ ሀብት ንብረት እንዲያደርስ ኀላፊነት የተሰጠው (ዕዝ 1፥11) ለእርሱ ነበር ማለት ይቻላል:: እንዲሁም ለአጭር ጊዜ ከምርኮ በተመለሱት ላይ የመጀመሪያው አገረ ገዥ በመሆን አስተዳድሮአቸዋል፤ የቤተ መቅደሱንም የዳግም ግንባታ ሥራ (ዕዝ 5፥14-16) ለመጀመር ሙከራ ያደረገው እርሱ ነው:: ስለ እርሱ ብዙ የሚታወቅ ነገር የለም:: ከዚያም በዕዝራ፣ በሐጌና በዘካርያስ መጻሕፍት ስፈ ሽፋን ያገኘው የወንድሙ ልጅ ዘሩባቤል በእርሱ ቦታ በመተካቱ ፍጻሜው ምን እንደነበር እንኳ አይታወቅም (ከታሪክ ዕይታ ተሰውሮአል)፤ ይሁን እንጂ የዕዝ 1፥8 ማብ ይመ::

3፥19 *የፈዳያ፤* ሌሎች መጻሕፍት ሰላትያል (ቍ17) የዘሩባቤል አባት እንደሆነ ይናገራሉ (ዕዝ3፥2፥8፤ነህ12፥1፤ሐጌ1-12፡14፤ 2፥2፡23):: ይህን የተምታታ ሐሳብ ለመፍታት የቀረቡት መፍትሔዎች የሚከተሉት ናቸው:- (1) ሰላትያል ቀደም ብሎ ሳይሞት አይቀርም፤ ስለዚህም የቤተ ሰቡ ኀላፊነት በፈዳያ ላይ ሊወድቅ ችሎአል:: (2) ፈዳያ ዘር ሳይተካ የሞተውን የሰላትያልን ሚስት አግብቶ ይሆናል:: ከዚህም የተነሣ ዘሩባቤል በሙሴ ሕግ መሠረት የሰላትያል ልጅ እንደሆነ ይታሰባል (ዘዳ 25፥5-6):: በሉቃ3፥27 ላይ በዮአኪን ፈንታ (ቍ17) ኔሪ የሰላትያል አባት ተብሎአል:: ከፍ ብለው ለተጠቀሱት ለሌሎች ሐሳቦች ይህንኑ የመሰለ ነገር ማቅረብ ይቻላል:: በማቴ 1 እና በሉቃ 3 ላይ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ የሚናገረው ክፍል፣ ወደ ላይ ሲቈጠር ዘሩባቤልን ይጠቅሳል፤ ሆኖም ከእርሱ ቀጥሎ ያሉትን (ትውልድ) ዘሮች (ቍ19-24) የሚያወሣ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የለም::

3፥20 *ሌሎችም አምስት፤* እነዚህም የዘሩባቤል ልጆች ሳይሆኑ አይቀሩም፤ ሆኖም ዝምድናን የሚያሳዩ ቃላት አልተጠቀሰም፤ የሐናንያ ልጆች (ቍ19) በቍጥር 21 ላይ ከተዘረዘረ እነዚህ የሚሱላም ልጆች ሊሆኑ ይችላሉ (ቍ19)::

3፥21 *የረፋያ... የሴኬንያ ወንዶች ልጆች፤* እነዚህ ምናልባት በዘሩባቤል ጊዜ የነበሩ ሌላ የዳዊት ቤተ ሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ (ቍ9)፤ ወይም ደግሞ ፈላጥያ ወይም የሻያ የተባሉት ሳይሆኑ አይቀሩም:: እነዚህ እንግዲህ በዘሩባቤል ጊዜ የነበሩ ናቸው ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ፣ የትውልድ ሐረጉን ወደ ታች መቍጠር የምንችለው የልጆቹንና የልጅ ልጆቹን (ሁለት ትውልድ) ብቻ ይሆናል፤ የዜና መዋዕል መጽሐፍም የተጻፈው ከዚህ ቀደም ብሎ በ450 ዓ.ቅ.ክ ላይ ሳይሆን እንደማይቀር መገመት ይቻላል::

3፥22 *ስድስት፤* ሸማያ አምስት ወንዶች ልጆች እንዳሉት ግልጽ ቢሆንም፣ ባጠቃላይ ስድስት እንደ ሆኑ ተጽፎአል:: እዚህ ላይ የምንረዳው ነገር ቢኖር ከስድስቱ ልጆች የአንዱ ስም በሆነ ምክንያት ሳይጻፍ ቀርቶአል፤ አልያም ደግሞ ሸማያ ለአምስቱ ልጆች አባታቸው ሳይሆን ወንድማቸው ነው ለማለት ያስደፍራል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ስድስቱም የሴኬንያ ልጆች ናቸው ማለት ነው::

*4፥1-23፤* እዚህ ላይ የሰፈረው የይሁዳ ትውልድ ሐረግ በሌሎቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች አይገኝም:: ምንም እንኳ ይህ ክፍል የተለያዩ ማብራሪያዎችን ባልቃ ቢያስገባም፣ ጸሓፊው እዚህ ላይ የይሁዳን ትውልድ ሐረግ አቀማመጥ አገላብጦ መጻፉ ከዐላማው ጋር ለማስማማት ሲል ጥንቃቄ ማድረጉን ያሳያል:: ይህም

2፥3 ሴሎም
2፥4-8 ፋሬስ
2፥9-3፥24 ኤስሮን
4፥1-20 ፋሬስ
4፥21-23 ሴሎም ነው::

[24]የኤልዩዔናይም ወንዶች ልጆች፤
ሆዳይዋ፣ ኤልያሴብ፣ ፌልያ፣ ዓቁብ፣
ዮሐናን፣ ደላያ፣ ዓናኒ፤ ባጠቃላይ ሰባት
ናቸው።

## ሌሎቹ የይሁዳ ጐሣዎች

4 የይሁዳ ዘሮች፤
ፋሬስ፣ ኤስሮም፣ ከርሚ፣ ሆር፣ ሦባል።
[2]የሦባል ልጅ ራያ ኢኤትን ወለደ፤ኢኤት
ደግሞ አሑማይንና ላሃድን ወለደ፤ እነ
ዚህም የጾርዓውያን ጐሣዎች ናቸው።
[3]የኢጣም ወንዶች ልጆች[ሀ] እነዚህ ናቸው፤
ኢይዝራኤል፣ ይሽማ፣ ይደባሽ።
እኅታቸው ሃጽሌልፎኒ ትባላለች። [4]ፋኑ
ኤል ጌዶርን ወለደ፤ ኤጽር ደግሞ ሑሻ
ምን ወለደ[ለ]። እነዚህ የኤፍራታ የበኩር
ልጅና የቤተልሔም አባት የሆነው የሆር
ዘሮች ናቸው።
[5]የቴቁሔ አባት አሽሑር፣ ሔላና ነዕራ
የተባሉ ሁለት ሚስቶች ነበሩት።
[6]ነዕራም አሑዛምን፣ ኦፌርን፣ ቴምኒን፣
አሐሽታሪን ወለደችለት፤ የነዕራ ዘሮች
እነዚህ ነበሩ።
[7]የሔላ ወንዶች ልጆች፤
ዴሬት፣ ይጽሐር፣ ኤትናን ናቸው።
[8]የቆጽ ወንዶች ልጆች ደግሞም ዓኑብ፣
ጾቤባና፣ የሃሩም ናቸው።
[9]ያቤጽ ከወንድሞቹ ይልቅ የተከበረ ሰው
ነበረ፤ እናቱም "በጣር የወለድሁት" ስትል
ስሙን ያቤጽ አለችው። [10]ያቤጽም ወደ
እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ጮኸ፤ "አቤቱ፤
እንድትባርከኝና ግዛቴንም እንድታሰፋ እለ
ምንሃለሁ። እጅህ በእኔ ላይ ትሁን፤ ከሥቃ
ይና ከጉዳትም ጠብቀኝ።" እግዚአብሔርም
የለመነውን ሰጠው።
[11]የሹሐ ወንድም ክሉብ ምሒርን ወለደ፤
ምሒርም ኤሽቶን ወለደ። [12]ኤሽቶን
ቤትራፋንና ፋሴሐን ወለደ፤ የዒርናሐ
ሽን ከተሞች የቈረቈረ እርሱ ነው[ሐ]።
እነዚህ የሬካ ሰዎች ናቸው።
[13]የቄኔዝ ወንዶች ልጆች፤

4፥1 ዘፍ29፥35፤ ዘኍ26፥21፤ 1ዜና 2፥3
4፥4 ሩት 1፥19፤ 1ዜና2፥50
4፥5 1ዜና2፥24
4፥13 ኢሱ15፥17
4፥17 ዘፀ15፥20
4፥18 ኢሱ15፥34
4፥19 ዘዳ3፥14፤ ኢሱ1544
4፥21 ዘፍ38፥5

ጎቶንያል፣ ሠራያ።
የጎቶንያል ወንዶች ልጆች፤
ሐታት፣ መዮኖታይ[መ]። [14]መዮኖታይ ደግሞ
ዖፍራን ወለደ።
ሠራያ የኢዮአብ አባት ሲሆን፣ ኢዮአብ ጌሐራሺ
ምን[ሠ] ወለደ፤ የእደ ጥበብ ባለ ሙያዎች
ስለ ነበሩ ይህ ስም ተሰጣቸው።
[15]የዮፎኔ ልጅ የካሌብ ወንዶች ልጆች፤
ዒሩ፣ ኤላ፣ ነዓም።
የኤላ ልጅ፤
ቄኔዝ።
[16]የይሃሌልኤል ወንዶች ልጆች፤
ዚፍ፣ ዚፋ፣ ቲርያ፣ አሣርኤል።
[17]የዕዝራ ወንዶች ልጆች፤
ዬቴር፣ ሜሬድ፣ ዔፌር፣ ያሎን። ከሜ
ሬድ ሚስቶች አንዲቱ ማርያምን፣ ሸማ
ይንና የኤሽትምዓን አባት ይሽባን ወለ
ደች። [18]አይሁዳዊት ሚስቱም የጌዶርን
አባት ዮሬድን፣ የሦኮን አባት ሔቤ
ርን፣ የዛኖዋን አባት ይቁቲኤልን ወለ
ደች፤ እነዚህም ሜሬድ ያገባት የፈ
ርዖን ልጅ የቢትያ ልጆች ናቸው።
[19]የሆዲያ ሚስት የነሐም እኅት ወንዶች
ልጆች፤
የገርሚው የቅዒላ አባት፣ ማዕካታዊው
ኤሽትሞዓ።
[20]የሺሞን ወንዶች ልጆች፤
አምኖን፣ ሪና፣ ቤንሐናን፣ ቲሎን። የይ
ሺዒ ዘሮች፤ ዞሔትና ቤንዞሔት።
[21]የይሁዳ ልጅ የሴሎም ወንዶች ልጆች፤
የሌካ አባት ዔር፣ የመሪሳና በቤት
አሽቤዓ የበፍታ ጨርቅ ሠሪ የሆኑት
ጐሣዎች አባት ለዓዳ፣ [22]ዮቂም፣ የኮ
ዜባ ሰዎች፣ ኢዮአስ፣ ሞዓብን የገዛ ሣራ

[ሀ]3 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች (እንዲሁም ቩልጌት ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡን ግን፣ አባት ይላል
[ለ]4 ቃል በቃል ሲተረጐም አባት ሆነ ማለት ነው፤ ይህም ምናልባት፣ አባት ማለት፣ የጐሣው፣ አንዣላት፣ አንጆላት ወይም፣ መሥረት መሆኑን የሚያመለክት ነው
[ሐ]12 ወይም፣ የዒር ናሐሽ አባት ነው
[መ]13 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞችና የቩልጌት ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ መዮናታይ የሚለውን አይጨምርም።
[ሠ]14 ጌሐራሺም ማለት የእደ ጥበብ ሸለቆ ማለት ነው።

የይሁዳ የትውልድ ሐረግ በዚህ ክፍል እንደዚህ ተገላብጦ መቀ መጡ፣ ክፍሉ ጉላ አድርጎ ለማሳየት የፈለገው የኤስሮምንና የዳዊትን ቤት ስለሆነ ነው። የኤስሮም ትውልድ ሐረግ በተ ወጣበት ክፍል ልክ ይህንኑ የመሰለ አቀማመጥ ይታያል (የ2፥10 -3፥24 ማብ ይመ)። በወቅቱ በሕይወት የነበረው የይሁዳ የመጀመሪያ ልጅ የሴላ የዘር ሐረግ የይሁዳን የትውልድ ሐረግ አጠቃሉ የያዘ ነው።

4፥1፤ *የይሁዳ ዘሮች*፤ በመሠረቱ ከአብራኩ የተከፈለው ልጅ ፋሬስ ብቻ ሲሆን፣ ሌሎቹ ግን የልዩ ልዩ ጐሣ መሪ እንጂ ወን ድሞቹ አይደሉም። ሆኖም የዘር ሐረጋቸው ይገናኛል። *ከርሚ*፤ ይህ ስም ጥንቱንም ሲጻፍ የአጻጻፍ ስሕተት ሳይፈጸም አል ቀረም፤ ወይም ደግሞ ሌላው የካሌብ መጠሪያ ስም ሊሆን ይች ላል (2፥9)። ይህ ስሕተት የተፈጸመውም በ2፥7 ላይ ከተከሠ ተው ችግር የተነሣ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

4፥2 *ራያ*፤ የሀሮኤ ሌላው ስሙ (2፥52) ነው።

*4፥5-8*፤ ለ2፥24 ተጨማሪ ሆኖ የገባ ነው።

*4፥9-10*፤ በትውልድ ሐረግ ውስጥ አጫጭር ታሪካዊ ዘገባ ዎች ጣልቃ እያስገቡ መጻፍ በሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችና (ዘፍ4፥19-24፤10፥8፥12) ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ በሚ ገኙ በጥንት ቅርብ መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች የትውልድ ሐረግ አጻጻፍ ውስጥ የተለመደ ነበር።

4፥13 *ጎቶንያል*፤ የመጀመሪያው የእስራኤል መስፍን ነው (ኢሱ 5፥17፤ መሳ 1፥13፤3፥9-11)።

*4፥16-20*፤ በዚህ ስፍራ የሚገኘው የትውልድ ሐረግ ክፍል የሚያወሣው ከምርኮ በፊት የነበረውን ነው፤ ይህን ለማለት ምክ ንያት የሆነውም፣ ከተወሡት በታዎች አብዛኛዎቹ ከምርኮ በኋላ በነበረው የይሁዳ አውራጃ ውስጥ ስማቸው ስለማይገኝ ነው (ለምሳሌ ዚፍ፣ኤሽትሞዓ አልተጠቀሱም)።

4፥17 *ሜሬድ ያገባት*፤ ይህቺ ሴት ምናልባት የፈርዖን ልጅ ሳትሆን አትቀርም (ቍ 18)፤ ወይም ሜሬድ ማን መሆኑ በትክክል አይታወቅም። ሜሬድ በእርግጥ የፈርዖንን ልጅ ማግባቱ ትክክል ከሆነ፣ የተከበረ (የታወቀ) ሰው ነበር ለማለት ያስችላል።ይህም ድርጊት በዮሴፍ ዘመን እስራኤላውያን በግብፅ ምድር ከነበራቸው ብልጽግና ጋር የሚያያዝ ነው።

*4፥21-23*፤ ይህ ክፍል የጥንቱን መካከለኛ ምሥራቅ ማኅበረ ሰብ ሕይወት በትክክል የሚያሳይ ነው። በዚያ ዘመን እያንዳንዱ ጐሣ ተለይቶ የሚታወቀው በመኖሪያ አካባቢው ብቻ ሳይሆን፣ መተዳደሪያ አድርጎ በያዘውም ሙያ ጭምር ነበር፤ እነ ርሱም የተልባ እግር ልብስ ሠራተኞች (ቍ 21) የሸክላ ሠራተ ኞች (ቍ 23)፣ የመንግሥት ሠራተኞች (ቍ 23)፣ ጸሐፍት (ቍ 55) ነበሩ።

ፍና ያሹቢሌሔም። ታሪካቸውም ጥን
ታዊነት ያለው ነው። 23ሰዎቹ በነጣዒ
ምና በጋዴራ የሚቀመጡ ሸክላ ሠሪ
ዎች ነበሩ፤ በዚያ በመቀምጥ እየኖሩ
ለንጉሡ ሸክላ ይሠሩለት ነበር።

## ስምዖን

4፥28-33 ተጓ – ምብ ኢሱ 19፥2-10

24የስምዖን ዘሮች፤
ነሙኤል፣ ያሚን፣ ያሪን፣ ዛራ፣ ሳኡል፤
25ሰሎም የሳኡል ልጅ ነው፤ መብሳም
የሰሎም ልጅ ነው፤
ማስማዕ ደግሞ የመብሳም ልጅ ነው።
26የማስማዕ ዘሮች
ልጁ ሃሙኤል፣ ልጁ ዘኩር፣ ልጁ ሰሜኢ።
27ሰሜኢ ዐሥራ ስድስት ወንዶችና ስድ
ስት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ ወንድሞቹ ግን
ብዙ ልጆች አልነበሯቸውም፤ ስለዚህ ጐሣ
ቸው በሙሉ እንደ ይሁዳ ሕዝብ ብዙ አል
ነበረም። 28የኖሩባቸውም ቦታዎች እነዚህ
ናቸው፤ ቤርሳቤህ፣ ሞላደ፣ ሐጻርሹዓል፣
29ቢልሃ፣ ዔጼም፣ ቶላድ፣ 30ቤቱኤል፣ ሔርማ፣
ጺቅላግ፣ 31ቤትማርካቦት፣ ሐጻርሱሲም፣ ቤት
ቢሪ፣ ሽዓራይም፤ እስከ ዳዊት ዘመነ መንግ
ሥት ድረስ የኖሩት በእነዚህ ከተሞች
ነው። 32በአካባቢያቸው የሚገኙት መንደ
ሮች ደግሞ ኤጣም፣ ዓይን፣ ሬሞን፣
ቶኬን፣ ዓሻን የተባሉ አምስት ከተሞች
ናቸው፤ 33በእነዚህም ከተሞች ዙሪያ እስከ
በኣል የሚዘልቁ መንደሮች ነበሩ፤ መኖሪ
ያቸው በዚሁ ሲሆን፣ የትውልድ መዝገ
ብም አላቸው።
34ሞሾባብ፣ የምሌክ፣ የአሜስያስ ልጅ
ኢዮስያስ፣ 35ኢዮኤል፣ የዮሺብያ ልጅ፣
የሠራያ ልጅ፣ የዓሢኤል ልጅ ኢዩ 36እን
ዲሁም ኤልዮዔናይ፣ ያዕቆባ፣ የሾሐያ፣
ዓሣያ፣ ዓዲዔል፣ ዩሲምኤል፣ በናያስ፣
37የሺፊ ልጅ ዚዛ፣ የአሎን ልጅ፣ የይዳያ
ልጅ፣ የሺምሪ ልጅ፣ የሸማያ ልጅ፤
38እነዚህ ስማቸው ከላይ የተዘረዘረው
ሰዎች የየጐሣቸው መሪዎች ነበሩ፤ የየቤተ
ሰባቸውም ብዛት እጅግ በጣም እየጨመረ
ሄደ፤ 39እነርሱም ለከብቶቻቸው ግጦሽ
ፍለጋ ከሸለቆው በስተምሥራቅ እስካለው
እስከ ጌደር መግቢያ ድረስ ዘልቀው ሄዱ።
40በዚያም ለምለምና ያማረ የግጦሽ ቦታ
አገኙ፤ ምድሪቱም ሰፊ፣ ሰላምና ጸጥታ የሰ
ፈነባት ነበረች። በቀድሞ ዘመን በዚህ
ምድር ይኖሩ የነበሩት አንዳንድ የካም
ዘሮች ናቸው።
41እነዚህ ስማቸው ከላይ የተዘረዘረው
ወደዚህ ቦታ የመጡት በይሁዳ ንጉሥ በሕ
ዝቅያስ ዘመን ነበረ፤ እነርሱም በድንኳኖ
ቻቸው ውስጥ በነበሩት በካም ወገኖችና
በምዑናውያን ላይ አደጋ በመጣል ፈጽመው
አጠፉአቸው[ሙ]፤ ይህም እስከ ዛሬ ድረስ
በግልጽ ይታያል። ለመንጎቻቸው በቂ የግጦሽ
ቦታ ስላገኙም፣ በዚያ መኖር ጀመሩ።
42ከእነዚሁ አምስት መቶ የሚሆኑ የስምዖን
ወገኖች በይሽዒ ልጆች በፈላጥያ፣ በነዓ
ርያ፣ በረፋያና በዑዝኤል ተመርተው የሴ
ይርን ኮረብታማ አገር ወረሩ። 43አምልጠው
የቀሩትን አማሌቃውያን ፈጅተው እስከ ዛሬ
በዚያው ይኖራሉ።

## ሮቤል

5 የእስራኤል የበኵር ልጅ የሮቤል
ልጆች፤ ሮቤል የበኵር ልጅ ቢሆንም፣
የአባቱን መኝታ ስላረከሰ፣ የብኵርና መብቱ
ለእስራኤል ልጅ ለዮሴፍ ልጆች ተሰጥቶ
አል። ከዚህም የተነሣ ትውልዱ የበኵርነ
ቱን ተራ ይዞ ሊቈጠር አልቻለም። 2ይሁዳ
ከወንድሞቹ ይልቅ ብርቱ ነበረ፤ ገዥ የወ
ጣው ከእርሱ ቢሆንም፣ የብኵርና መብቱ
የተላለፈው ለዮሴፍ ነበረ። 3የእስራኤል
የበኵር ልጅ የሮቤል ወንዶች ልጆች፤
ሄኖኅ፣ ፋሉሶ፣ አስሮን፣ ከርሚ።
4የኢዩኤል ዘሮች
ልጁ ሸማያ፣ ልጁ ጎግ፣ ልጁ

4፥24 ዘፍ29፥33፤ ዘኍ 26፥12
4፥28 ዘፍ1፥14፤ ኢሱ 15፥26
4፥29 ኢሱ15፥29
4፥30 ዘኍ14፥45፤ ኢሱ15፥31
4፥31 ኢሱ15፥36
4፥32 ዘኍ 34፥11፤ ኢሱ15፥42
4፥39 ኢሱ15፥58
4፥40 መሳ18፥7-10
4፥41 2ዜና20፥1፤ 26፥7
4፥42 ዘፍ14፥6
4፥43 ዘፍ14፥7፤ አስ3፥1፤9፥16
5፥1 ዘፍ29፥32፤35፥22፤ 48፥5፡16፤49፥4፡26፤1 ዜና 26፥10
5፥2 ዘፍ25፥31፤ 49፥10፡12፤1ሳሙ9፥16፤12፥12፤ 2ሳሙ6፥21፤ 1ዜና11፥2፤ 2ዜና7፥18፤ማቴ 2፥6
5፥3 ዘፍ29፥32፤ 46፥9፤ዘፀ6፥14፤ ዘኍ26፥5-11

[ሙ]41 የዕብራይስጡ ቃል አንድን ሰው ወይም ነገር ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠትን ያመለክታል።

*4፥24-43፤* የስምዖን የትውልድ ሐረግ እንደዚሁ በዘፍ 46፥10፤ ዘፀ 6፥15፤ ዘኍ 26፥12-13 ላይ ተጽፎ ይገኛል። ስምዖን ከይሁዳ ግዛት በአንዱ ክፍል ተቀምጦ ነበር። የተያዙትን ከተሞች ዝርዝር ከኢያ 15፥26-32፡ 42፤19፥2-7 ጋር ያነጻጽሩ። ስምዖን የሰፈረበት ምድር ለይሁዳ በዕጣ በደረሰው አገር ላይ ስለሆነ፣ ይህ ነገድ በፖለቲካና በማናቸውም ረገድ ከይሁዳ ጋር በመቀላቀሉ በታሪክ ውስጥ የራሱን ማንነት በብዙ መንገድ አጥቶአል ለማለት ይቻላል (ዘፍ 34፥24-31፤49፥5-7 ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ 34፥25፤49፥7 ማብ ይመ)። በትውልድ ሐረጉም ውስጥ የመልክዐ ምድርና የታሪክ ዘገባዎች ዐልፎ ዐልፎ ጣልቃ ገብተዋል (የቍ9-10 ማብ ይመ)። እዚህ ላይ ሁለት የትውልድ ሐረግ መስመሮች በግልጽ ተለይተው ገብተዋል (ቍ24-33፤ "የታወቀ የትውልድ ሐረግ አላቸው" ብሎ በተለመደው ዐይነት ይደመድማል፤ በማስከተል ቍ 34-43 ይገኛል። የሕዝቡ ብዛት (ቍ 38) መጨናነቅን ስለፈጠረ፣ በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት (ቍ 39-43) ወደ ጌዶርና ወደ ኤዶም ምሥራቅ በኩል መስፋፋት ግድ ሆኖባቸዋል። በእስራኤልና በአማሌቃውያን መካከል ለረጅም ጊዜ ጸንቶ የነበረው ጠላትነት እንደገና ተቀስቅሷል (ቍ 43)፤ ከዘፀ 17፥8-16፤ ዘዳ 25፥17-19፤ 1 ሳሙ 15 ጋር ያነጻጽሩ፤ የመጽሐፈ አስቴርን መግቢያ ይመ)።

*5፥1-26፤* ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ያሉ ነገዶች ማለትም የምናሴ ነገድ እኩሌታ (ዘኍ 32፥33-42 ይመ)፣ የሮቤልና የጋድ የትውልድ ሐረግ ታሪክ ነው። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ "በመላው እስራኤል" ታሪክ ውስጥ እነዚህ ሦስቱ ነገዶች ከምርኮ ተመልሰው ወደ አገራቸው ከገቡ በኋላ፣ ይህን ያህል ከቍጥር የሚገባ ብዛት ባይኖራቸውም፣ የትውልድ ሐረጋቸውን ከሌሎች ነገዶች ጋር አግብቶ እያሰባጠረ መዝግቦታል። እነዚህ ነገዶች ለመጀመሪያ መናመን የበቀትም የአሦር መንግሥት እስራኤልን ወርሮ ድል ካደረገ በኋላ ተጠራርገው በመወሰዳቸው ነበር።

*5፥1-10፤* ሮቤል የብኵርና መብቱን የተገፈፈው ለምን እንደሆነ መግለጹ የግድ አስፈላጊ ነው (ስለ ሮቤል ኀጢአት ዘፍ 35፥22፤ 49፥4ይመ)፤ ጸሓፊው በመጀመሪያ ላይ መጻፍ የሚገባውን (ቍ1) ይዘልለውና ወደ ኋላ ይመለስበታል (ቍ3)። ምንም እንኳ ዮሴፍ የብኵርናውን መብት በዕጥፉ ያገኘ ቢሆንም፣ (በልጆቹ በኤፍሬምና በምናሴ ምክንያት) ጸሓፊው ለይሁዳ ከፍ ያለ ትኵረት እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው። በዕብራይስጡ ቋንቋ "ገዥ" ተብሎ የተተረጐመው ቃል (ቍ2) በ11፥2፤17፥7፤ 2ሳሙ5፥2፤ 6፥21፤ 7፥8 ላይ ለዳዊት የተነገረ ነው፤ ከ1ዜና 28፥4 ጋር ያነጻጽሩ። ወታደራዊ ማዕረጎች መጠቀሳቸውና (ቍ6-7) የጦርነት ታሪኮች መውሣታቸው (ቍ10) ለዚህ የትውልድ ሐረግ ምንጭ የሆነው ጽሑፍ የተዘጋጀው የውትድርና ተቋም ውስጥ ከውትድርና ግልጋሎት ጋር በተያያዘ ምክንያት ሳይሆን

ሰሜኢ፣ 5ልጁ ሚካ፣
ልጁ ራያ ፣ ልጁ ቢኤል፣
6የአሦር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር
ማርኮ የወሰደው ልጁ ብኤራ::
7የቤተ ሰቡ የዘር ትውልድ በየጐሣ በየጐ
ሣው ሲቈጠር እንደሚከተለው ነው፤
የጐሣ አለቃ የሆነው ኢዮኤል፣ ዘካ
ርያስ፣ 8የኢዮኤል ልጅ፣ የሽማዕ ልጅ፣
የያዛዝ ልጅ ቤላ፣ እነዚህ ከአሮዔር
እስከ ናባውና እስከ በኣልሜዎን ድረስ
በሚገኘው ምድር ላይ ሰፈሩ:: 9ከብቶቻ
ቸው በገለዓድ ምድር በዝተው ስለ
ነበር በምሥራቅ በኩል ወደ ኤፍራጥስ
ወንዝ እስከ ምድረ በዳው ዳርቻ ድረስ
የሚገኘውን ምድር ያዙ::
10በሳኦልም ዘመነ መንግሥት በእጃ
ቸው ተመትተው ድል ከተደረጉት አጋ
ራውያን ጋር ተዋጉ፤ በመላው የገለዓድ
ምሥራቃዊ ክፍል የሚገኙትን መኖሪያ
ዎቻቸውን ያዙ::

## ጋድ

11የጋድ ነገድ ደግሞ ከእነርሱ ቀጥሎ
እስከ ሰልካ ድረስ በሚገኘው በባሳን
ምድር ኖሩ፤
12አለቃው ኢዮኤል፣ ሁለተኛው ሳፋም
ከዚያም ያናይና ሰፋጥ ሆነው በባሳን
ተቀመጡ:: 13ቤተ ዘመዶቻቸውም በየ
ቤተ ሰቡ እነዚህ ነበሩ፤ ሚካኤል፣ ሜሱ
ላም፣ ሳባ፣ ዮራይ፣ ያካን፣ ዙኤ፣
ኦቤድ፤ ባጠቃላይ ሰባት ነበሩ:: 14እነ
ዚህ ደግሞ የቡዝ ልጅ፣ የዬዳይ ልጅ፣
የኢዬሳይ ልጅ፣ የሚካኤል ልጅ፣ የገ
ለዓድ ልጅ፣ የኢዳይ ልጅ፣ የሁሪ ልጅ፣
የሑሪ ልጅ፣ የአቢካኢል ልጆች ናቸው::
15የቤተ ሰባቸውም አለቃ የጉኒ ልጅ፣
የአብዲኤል ልጅ አሒ ነበረ::
16ጋዳውያንም በገለዓድ፣ በባሳንና እስከ

5፥6 ቍ26፤ 2ነገ 15፥19፤ 16፥10፤2ዜና28፥20
5፥7 ኢሱ13፥15-23
5፥8 ዘኍ32፥3:34፤ ኢሱ13፥17፤ መሳ 1 1፥26
5፥9 ዘፍ2፥14፤ ዘኍ 32፥26
5፥10 ቍ22፤1ዜና 27፥31
5፥11 ዘፍ30፥11፤ ዘኍ1፥25፤ ዘዳ3፥10፤ ኢሱ13፥24-28
5፥17 2ነገ14፥23፤ 15፥32
5፥18 ዘኍ1፥3
5፥19 ዘፍ25፥15
5፥20 ነገ8፥44፤2ዜና6፥34፤1 3፥14፤14፥11፤ መዝ20፥7-9፤22፥5፤ 26፥1፤ 37፥40፤46፥5 54፥4፤107፥6፤ ኢሳ26፥3፤ዳ36፥23
5፥22 ቍ10፤ ዘዳ 20፥4፤2ነገ15፥29፤ 2ዜና32፥8
5፥23 ዘዳ3፥8:9፤ 4፥8፤1ዜና7፥14
5፥25 ዘፀ34፥15፤ ዘሌ18፥3፤ዘዳ32፥15-18፤1ዜና9፥1፤10፥13፤ 2ዜና፤12፥2፤26፥16፤ 28፥19፤29፥6፤30፥7፤36፥14

ዳርቻዋ በሚገኙት መንደሮች እንዲ
ሁም በሳሮን በሚገኙ የግጦሽ ስፍራ
ዎች ሁሉና ከዚያም ወዲያ አልፈው
ተቀመጡ::
17እነዚህ ሁሉ በትውልድ መዝገብ የሰ
ፈሩት በይሁዳ ንጉሥ በኢዮአታምና በእስ
ራኤል ንጉሥ በኢዮርብዓም ዘመነ መንግ
ሥት ነው::
18የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩ
ሌታ አርባ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሥልሳ
ብቁ የጦር ሰዎች ነበሩአቸው:: እነርሱም
ጋሻ መያዝ፣ ሰይፍ መምዘዝና ቀስት መሳብ
የሚችሉ ጠንካራና በውጊያ የሠለጠኑ ናቸው::
19እነዚህም በአጋራውያን፣ በኢጡር፣ በናፌስ፣
በናዳብ ላይ ዘመቱ:: 20በጦርነቱም ላይ ወደ
እግዚአብሔር ጮኸው ስለ ነበር፣ በውጊያው
ረዳቸው፤ አጋራውያንንና የጦር አጋሮቻቸ
ውን ሁሉ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ስለ ታመኑብ
ትም ጸሎታቸውን ሰማ:: 21የአጋራውያን
ንም እንስሶች ማረኩ፤ እነዚህም አምሳ ሺ
ግመሎች፣ ሁለት መቶ አምሳ ሺ በጎችና
ሁለት ሺ አህዮች ነበሩ:: እንዲሁም አንድ
መቶ ሺ ሰው ማረኩ:: 22ውጊያው የእግዚ
አብሔር ስለ ነበር ሌሎችም ብዙ ሰዎች ተገ
ደሉ:: እስከ ምርኮ ጊዜ ድረስ ምድሪቱ በእ
ጃቸው ነበረች::

## እኩሌታው የምናሴ ነገድ

23የምናሴ ነገድ እኩሌታ ሕዝብ ቍጥር
ብዙ ነበረ፤ እነርሱም ከባሳን ጀምሮ እስከ
በኣልአርሞንዔም ድረስ ባለው ምድር ሰፈሩ፤
ይህም እስከ ሳኔር አርሞንዔም ተራራ ድረስ
ማለት ነው::
24የየቤተ ሰቡም አለቆች እነዚህ ነበሩ፤
ዔፌር፤ ይሽዒ፣ ኤሊኤል፣ ዓዝርኤል፣ ኤር
ምያ፣ ሆዳይዋ፣ ኢየድኤ፤ እነዚህ ጀግና
ተዋጊዎች፣ የታወቁ ሰዎችና የየቤተ ሰባ
ቸው አለቆች ነበሩ:: 25ይሁን እንጂ ለአባ

እንዳልቀረ ይገመታል (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "የትውልድ ሐረግ" የሚለውን ይመ):: ሮቤልን በተመለከተ እዚህ ላይ በከፊል ለተጻፉት ነገሮች ምንጫቸው (ዘኍ 26፥5-11) ነው:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በቆሬ ዐመፅ ምክንያት በሞት የተቀሠፉትን ኤልያብንና የሦስት ወንዶች ልጆቹን (ዘኍ 26፥8-10ይመ) ስም ሳያወሳ ማለፉ፣ ከጽሑፉ ዐላማ ጋር ግንኙነት ስላልነበራቸው ነው::

5፥6 *ቴልጌልቴልፌልሶር፤* ይህ የአሦር ንጉሥ በ745 -727 ዓ.ቅ.ክ እስራኤልን ወርሮ ነበር (ቍ26፤ 2ነገ15፥ 29)፤ ደግሞም የይሁዳም ንጉሥ አካዝን አስገብሮአል (2 ዜና 28፥19 -20፤ 2ነገ 16፥7-10)::

5፥10 *አጋራውያን፤* ቍ19-22 ይመ:: ከእስራኤል ጠላቶች እንደ አንዱ ሆነው የተቈጠሩት እነዚህ ሰዎች (መዝ 83፥6) ከእስ ማኤል እናት ከአጋር ጋር (ዘፍ 16) ዝምድና አላቸው:: ሆኖም የመዝ 83፥6 ማብ ይመ::

*5፥11-22፤* እዚህ ላይ የተመለከተው የጋድ ነገድ የስም ዝርዝር በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አይገኝም:: ሌሎች የጋድ የትውልድ ሐረጎች ዝርዝር የሰባቱን ልጆቹን ስም በመያዝ ተደራጅቶአል (ዘፍ 46፥16፤ ዘኍ 26፥15-18)፤ እዚህ ላይ በሌ ሎች የስም ዝርዝሮች ውስጥ የማይገኙ አራት ስሞች ተሰጥ ተዋል:: ይህ የትውልድ ሐረግ ዝርዝር የተላለፈው በይሁዳ ንጉሥ በኢዮኢታም (750-732 ዓ.ቅ.ክ.) እና በእስራኤል ንጉሥ በኢዮርብዓም (793-753 ዓ.ቅ.ክ.) ዘመነ መንግሥት መሆኑን የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ገልጾታል (ቍ17):: በመጽሐፉ ውስጥ የጦር አለቆች ማዕረግና ትረካዎች መገኘቱ (ቍ12:18-22) የዚህ የትውልድ ሐረግ ምንጩ ለውትድርና ግዳጅና አገ ልግሎት ቈጠራ በከፊል ከተዘጋጀው ጽሑፍ ላይ የተወሰደ እንደሆነ ያመለክታል:: የጋድ ምድር ዳር ድንበር ንድፍ በዘዳ 3፥12 ላይ ተገልጾአል::

*5፥18-22፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በዚህ ትረካው እንደ ዐቢይ ጉዳይ አድርጎ ለማሳየት የፈለገው የመጀመሪያው ምሳሌ ማና ቸውም ኀጢአት (ወዲያውኑ) ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን ነው (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "ዐላማና ርእስ" የሚለውን ይመ):: በጦ ርነቱ ድልን ለመጐናጸፍ የበቁትም ወደ እግዚአብሔር ካሶሙት ጩኸት የተነሣ ነው (ቍ 20፤ ከ2 ዜና 6፥24-25:34-39፤ 12፥7-12፤13፥13 -16፤ 14፥9-15፤18፥31፤ 20፥1-30፤32፥1-23 ጋር ያነጻጽሩ::)

*5፥23-26፤* ምናሴን በተመለከተ በ7፥14-19 ላይ በተጨ ማሪ የተወሳ ታሪክ አለ፤ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ስለተቀ መጠው ስለ ምናሴ ነገድ እኩሌታ እዚህ ላይ ተጽፎ የምናገኘው ግን ከሮቤልና ከጋድ ነገዶች ጋር የሚካፈለው (የሚጋራው) አንድ ዐይነት ዕጣ መኖሩን ስለሚያስረዳ፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የዐሥራ ሁለቱን ነገድ የትውልድ ሐረግ በአጠቃላይ ለመመዝገብ የነበረውን ፍላጎት ሊያሳይ ይችላል (የ2፥1-2 ማብ ይመ):: እን ዲሁም የአጸፋ ቅጣታቸውን ወዲያውኑ ሲቀበሉ እናያለን:: በእግ ዚአብሔር መታመን ድልን እንደሚያጐናጽፍ ሁሉ (ቍ 18-22)፣ በአንጻሩም ለእግዚአብሔር ታማኝ ባልሆኑት ሰዎች ላይ የሚደርስ ባቸው ሽንፈት ነው (ቍ25-26):: "አጸፋ ቅጣት" ዋና ሐሳብ ሆኖ በሁለቱም ታሪኮች ውስጥ ከዘር ትውልድ ታሪክ ጋር መጋጠሙ፣

ቶቻቸው አምላክ ታማኞች አልሆኑም፤ እግ
ዚአብሔር ከፊታቸው ያጠፋቸውን የምድሪ
ቱን አሕዛብ አማልክት በማምለክ አመነ
ዘሩ:: 26ስለዚህ የእስራኤል አምላክ የአ
ሦርን ንጉሥ የፎሐን መንፈስ ይኸውም
የቴልጌልቴልፌልሶርን መንፈስ አነሣሥቶ
የሮቤልን፣ የጋድንና፣ የምናሴን ነገድ እኩ
ሌታ ማርኮ እንዲወስድ አደረገ:: እነዚህ
ንም ወደ አላሔ፣ ወደ አቦር፣ ወደ ሃራና
ወደ ጎዛን ወንዝ ዳርቻ አፈለሳቸው፤ እነር
ሱም እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ ይገኛሉ::

## ሌዊ

6 የሌዊ ወንዶች ልጆች፤
ጌድሶን፣ ቀዓት፣ ሜራሪ::
2የቀዓት ወንዶች ልጆች፤ እንበረም፣ ይስዓር፣
ኬብሮን፣ ዑዝኤል::
3የእምበረም ልጆች፤
አሮን፣ ሙሴ፣ ማርያም::
የአሮን ወንዶች ልጆች፤
ናዳብ፣ አብዮድ፣ አልዓዛር፣
ኢታምር::
4አልዓዛር ፊንሐስን ወለደ፤
ፊንሐስ አቢሱን ወለደ፤
5አቢሱ ቡቂን ወለደ፤
ቡቂ ኦዚን ወለደ፤
6ኦዚ ዘራእያን ወለደ፤
ዘራእያ መራዮትን ወለደ፤
7መራዮት አማርያን ወለደ፤
አማርያ አኪጦብን ወለደ፤
8አኪጦብ ሳዶቅን ወለደ፤
9ሳዶቅ አኪማአስን ወለደ፤
አኪማአስ ዓዛርያስን ወለደ፤
ዓዛርያስ ዮሐናን ወለደ፤
10ዮሐናን ዓዛርያስን ወለደ፤
እርሱም ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ባሠራው
ቤተ መቅደስ በክህነት ያገለገለ ነበር፤
11ዓዛርያስ አማርያን ወለደ፤
አማርያም አኪጦብን ወለደ፤
12አኪጦብ ሳዶቅን ወለደ፤
ሳዶቅ ሰሎምን ወለደ፤
13ሰሎም ኬልቅያስን ወለደ፤
ኬልቅያስ ዓዛርያስን ወለደ፤
14ዓዛርያስ ሠራያን ወለደ፤
ሠራያ ኢዮሴዴቅን ወለደ::
15እግዚአብሔር የይሁዳና የኢየሩሳሌም
ሕዝብ በናቡከደነፆር እጅ ተማርከው
እንዲወሰዱ ባደረገ ጊዜ ኢዮሴዴቅም
አብሮ ተማርኮ ሄደ::
16የሌዊ ወንዶች ልጆች፤
ጌድሶን፣ ቀዓት፣ ሜራሪ::
17የጌድሶን ወንዶች ልጆች፤
ሎቤኒ፣ ሰሜኢ::
18የቀሃት ወንዶች ልጆች፤
እምበረም፣ ይስዓር፣ ኬብሮን፣
ዑዝኤል::
19የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤
ሞሖሊ፣ ሙሲ::
በየአባቶቻቸው ቤተ ሰብ የተቈጠሩት
የሌዊ ጐሣዎች የሚከተሉት ናቸው፤

5፥26 ቊ6፤2ነገ15፥19:29፤ 17፥6፤ኢሳ37፥7
6፥1 ዘፍ29፥34፤ ዘኍ3፥17
6፥2 ዘፀ6፥18
6፥3 ዘፀ6፥23፤15፥20፤ ዘሌ10፥1-20
6፥4 ዕዝ7፥5
6፥8 2ሳሙ8፥17፤ 1ዜና12፥28፤ዕዝ7፥2
6፥10 1ነገ4፥2
6፥13 2ነገ22፥1-20፤2ዜና34፥9፤35፥8
6፥14 2ነገ25፥18፤ዕዝ2፥2
6፥15 ነህ12፥1፤ ሐጌ1:1:14፤ 2፥2:4፤ዘካ6፥11
6፥16 ዘፍ29፥34፤ ዘኍ3፥17-20፤26፥57
6፥17 ዘፀ6፥17
6፥18 ዘፀ6፥18
6፥19 ዘፍ46፥11፤ ዘፀ6፥19፤1ዜና23፥21፤ 24፥26

ዜና መዋዕሉቹ የአንድ ክፍል መጻሕፍት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: እዚህም ላይ የቀረበው የስም ዝርዝር በትክክል የትውልድ ሐረግን የሚያወሣ ሳይሆን፣ የየጐሣን ስም የያዘ ነው:: እነዚህም በተደረገው ጦርነት ላይ በጀግንነት መዋጋታቸው በሚገባ የተገለጸ ቢሆንም (ቊ 24-26)፣ ይህ ክፍል የተወሰደው ውትድርናን በተመለከተ ከተዘጋጀ የስም ዝርዝር መዝገብ ላይ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል (የ1-10 ማብ ይመ፤ እንደዚሁም 2 ነገ 15፥19:29፤17፥6፤18፥11 ይመ)::

5፥26 *የፎሐ*፣ ቴልጌልቴልፌልሶር ከመንገሡ በፊት ባቢሎናውያን ይጠሩ የነበረው በዚህ ስም ሳይሆን አይቀርም::

*6፥1-81*፤ ይህ ምዕራፍ የሌዊን ነገድ ብቻ ያካተተ ሲሆን፣ የዚህን ነገድ አባቶችና ዝርያቸውን የስም ዝርዝር ያቀርባል:: የመጀመሪያው ክፍል (ቊ 1-15) እስከ ባቢሎን ምርኮ ያለውን የካህናቱን አለቆች የትውልድ ሐረግ ያዘለ ነው:: ከዚያም የሌዊ ነገድ ጐሣዎች ዝርዝር ይቀጥላል (ቊ 16-30):: እንዲሁም ዳዊት ቤተ መቅደሱን በዝማሬ እንዲያገለግሉ የመደባቸው የሦስቱ የሌዊ ነገዶች ማለትም የጌድሶን፣ የቀዓትና የሜራሪ ዘሮች ስም ዝርዝር ይከተላል (ቊ 31-47):: በአሮንና በአኪማአስ መካከል ላሉት ትውልዶች የስም ዝርዝር የተለየ ቦታ ተሰጥቶአቸዋል (ቊ 49-53)፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ካህናቱና ሌዋውያኑ የተለያየ ተግባር ያላቸው መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት ነው (የዘፀ 32፥26 ማብ ይመ):: ምዕራፉ በሌሎቹ ነገዶች መካከል ለሌዋውያን የተመደቡትን ይዞታዎች (ከቊ 54-81) በመዘርዘር ይደመድማል::

*6፥1-3*፤ ዋና ዋናዎቹ የሌዊ የትውልድ ሐረግ ግንዶች ስም በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተካተተ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ ግን የሌዊ ነገድ ይጠብና የአልዓዛርን የትውልድ ሐረግ ይዞ ወደ ታች ይወርዳል:: የሊቀ ካህንነቱን ስፍራ በተርታ የሚይዙትም የእርሱ ዘሮች ናቸው (ቊ 4-15):: የሌዊ ወንዶች ልጆች (ቊ 1) ምን ጊዜም ቢሆን በዚህ ሁኔታ የዕድሜአቸውን ቅደም ተከተል ሥርዐት ይጠብቃል (ቊ 16፤ዘፍ46፥11፤ ዘፀ 6፥16 ዘኍ 3፥17፤26፥57):: የአሮንን አራት ወንዶች ልጆች በተመለከተም (ቊ 3) ሁለቱ ወንድማማቾች የእግዚአብሔርን ሕግ ተላልፈው የማይገባቸውን ሥራ ስለሠሩ ተቀሥፈው ለመሞት በቅተዋል (ዘሌ 10፥2፤ዘኍ 26፥61)፤ ከዚያ በኋላ በተከታታይ የተነሣው የካህናት ትውልድ እስከ አልዓዛር ወይም እስከ ኢታማር ድረስ የሚዘልቅ የዘር ሐረግ ነው::

*6፥4-15*፤ አልዓዛር ከነበረበት ዘመን አንሥቶ እስከ ምርኮው ዘመን ድረስ የነበረው ይህ የሊቀ ካህናቱ ስም ዝርዝር በዚህ ክፍል ጉልቶ ይታያል:: በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሚገባ የሚታወቁትና ከዚህ የሚከተሉት ሊቀ ካህናት፣ ስማቸው በእነዚህ ቍጥሮች አልተጠቀሰም:: ዮዳሄ (2 ነገ12፥2)፣ ኦርያ (2 ነገ16፥10-16)፣ ምናልባትም አዛርያ በሚል ስም የሚታወቁ ሌሎች ሁለት ሊቀ ካህናት ኖረው ይሆናል:: (2ዜና 26፥17:20፤31፥10-13) እነርሱም ኤሊና፣ (1ሳሙ 1፥9፤14፥3) አብያታር (2ሳሙ 8፥ 17):: የእነዚህ ስም ዝርዝር ጥቂት ለውጥ ተደርጎበት በመጽሐፈ ዕዝራ ተደግሞ ተጽፎአል::

6፥8 *አኪጦብ ሳዶቅን ወለደ*፤ ይህ ሳዶቅ ከዳዊት ሁለት ካህናት መካከል አንዱ ነበር (18፥16፤2ሳሙ8፥17):: ሌላው የዳዊት ካህን አብያታር (የቊ 4-15 ማብ ይመ) የአዶንያስን ዐመፅ ሲደግፍ፣ ሳዶቅ ግን ሰሎሞንን ደገፈ (1 ነገ1):: አብያታር ከተባረረ በኋላ (1ነገ2፥26-27) ሳዶቅ ወደ ልጆቹ የተላለፈውን (1ነገ 4፥2) የሊቀ ካህንነት አገልግሎት ብቻውን ይዞ ነበር (1ዜና 29፥22):: በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው አኪጦብ ከዔሊ የልጅ ልጅና (1ሳሙ14፥3) ከአብያታር ቅድመ አያት ስም (1ሳሙ 22፥20) ጋር መምታታት የለበትም:: የሳዶቅ የክህነት ሐረግ የዔሌን ተክቶአል (1ሳሙ2፥27-36፤ 1ነገ2፥26-27):: የሳዶቅ የዘር ሐረግ (ስለ ነበረው ከፍተኛ ቦታ ለመረዳት ሕዝ 40፥46፤ 43፥19፤ 44፥15፤48፥11 ይመ)፤ ዕዝራ ሆን ብሎ የራሱን የካህናት ሐረግ ለማመልከት ፈልጉአል (ዕዝ 7፥1-5)::

6፥13 *ኬልቅያስ*፤ በኢዮስያስ ዘመን የሕጉን መጽሐፍ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያገኘው እርሱ ነበር (2፥ነገ:22፤ 2፥ዜና:34)::

6፥14 *ሠራያ*፤ኢየሩሳሌም በ586 ዓ.ቅ.ክ. ከተማረከች በኋላ በባቢሎናውያን ተገድሏል (2ነገ25፥18-22) *ኢዮሴዴቅ*፤ በመጀመሪያ ከምርኮ በተመለሰው ትውልድ መካከል የነበረ የታላቁ ካህን የኢያሱ አባት ነው (ዕዝ3፥2፤5፥2፤10፥18፤ ሐጌ1፥1፤2፥2፤ ዘካ3፥1፤6፥11፤) “ኢዮሳዳቅ” በሚል ስምም ተጠርቷል::

*6፥16-19* ከዘፀ 6፥16-19፤ ዘኍ 3፥17-20፤ 26፥57-61 ላይ የተወሰደ ነው::

20 ከጌርሶን፤
ልጁ ሎቤኒ፣ ልጁ ኢኤት፣
ልጁ ዛማት፣ 21 ልጁ ዮአክ፣
ልጁ አዶ፣ ልጁ ዛራ፣ ልጁ ያትራይ።
22 የቀዓት ዘሮች፤
ልጁ አሚናዳብ፣ ልጁ ቆሬ፣ ልጁ አሴር፣
23 ልጁ ሕልቃና፣ ልጁ አቢሳፍ፣ ልጁ
አሴር፣ 24 ልጁ ኢኢት፣ ልጁ ኡርኤል፣
ልጁ ዖዝያ፣ ልጁ ሳውል።
25 የሕልቃና ዘሮች፤
አማሢ፣ አኪሞት።
26 ልጁ ሕልቃና፣[a] ልጁ ሱፊ፣ ልጁ ናሐት፣
27 ልጁ ኤልያብ፣ ልጁ ይሮሐም፣
ልጁ ሕልቃና፣ ልጁ ሳሙኤል[b]።
28 የሳሙኤል ወንዶች ልጆች፤
የበኵር ልጁ ኢዮኤል[c]፣
ሁለተኛው ልጁ አብያ።
29 የሜራሪ ዘሮች፤
ሞሖሊ፣ ልጁ ሎቤኒ፣ ልጁ ስሜኢ፣
ልጁ ዖዛ፣
30 ልጁ ሳምዓ፣ ልጁ ሐግያ፣ ልጁ ዓሣያ።

## የቤተ መቅደሱ መዘምራን

6፥54-80 ተጓ ምብ - ኢሱ21፥4-39

31 ታቦቱ ከገባ በኋላ፣ ዳዊት የመዘምራን
አለቃ አድርጎ *በእግዚአብሔር* ቤት የሾማ
ቸው ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ 32 እነርሱም ሰሎ
ሞን *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ በኢ
የሩሳሌም እስኪሠራ ድረስ፣ በማደሪያው
ድንኳን በመገናኛው ድንኳን ፊት ሆነው
እየዘመሩ ያገለግሉ ነበር፤ አገልግሎታቸውንም
የሚያከናውኑት በወጣላቸው ደንብ መሠረት
ነው።
33 ከወንዶች ልጆቻቸው ጋር ሆነው ያገለ
ገሉ ሰዎች እነዚህ ናቸው፤
ከቀዓታውያን ልጆች፤ ዘማሪው ኤማን፣
የኢዮኤል ልጅ፣ የሳሙኤል ልጅ፣
34 የሕልቃና ልጅ፣ የይሮሐም ልጅ፣ የኤሊ
ኤል ልጅ፣ የቶዋ ልጅ
35 የሱፍ ልጅ፣ የሕልቃና ልጅ፣ የመሐት
ልጅ፣ የአማሢ ልጅ፣
36 የሕልቃና ልጅ፣ የኢዮኤል ልጅ፣ የዓዛር
ያስ ልጅ፣ የሶፎንያስ ልጅ፣
37 የታሐት ልጅ፣ የአሴር ልጅ፣ የአብያ
ሳፍ ልጅ፣ የቆሬ ልጅ፣
38 የይስዓር ልጅ፣ የቀዓት ልጅ፣ የሌዊ ልጅ፣
የእስራኤል ልጅ።
39 እንዲሁም የሔማን ወንድም አሳፍ በስተ
ቀኙ ሆኖ ያገለግል ነበር፤
አሳፍ የበራክያ ልጅ፣ የሳምዓ ልጅ፣
40 የሚካኤል ልጅ፣ የበዓሤያ ልጅ፣
የመልክያ ልጅ፣ 41 የኤትኒ ልጅ፣
የዛራ ልጅ፣ የዓዳያ ልጅ፣
42 የኤታን ልጅ፣ የዛማት ልጅ፣ የሰሜኢ
ልጅ፣ 43 የኢኤት ልጅ፣ የጌድሶን ልጅ፣
የሌዊ ልጅ፤
44 በስተግራቸው በኩል አብረዋቸው ያሉት
የሜራሪ ልጆች፤ የቂሳ ልጅ ኤታን፣
የአብዲ ልጅ፣ የማሎክ ልጅ፣ 45 የሐሸ
ብያ ልጅ፣ የአሜስያስ ልጅ፣ የኬልቅ
ያስ ልጅ፣
46 የአማሲ ልጅ፣ የባኒ ልጅ፣ የሴሜር
ልጅ፣ 47 የሞሖሊ ልጅ፣ የሙሲ ልጅ
የሜራሪ ልጅ፣ የሌዊ ልጅ፣
48 ሌዋውያን ወንድሞቻቸው ግን የእግዚ
አብሔርን ቤት የማደሪያ ድንኳን ተግባር እን

6፥22 ዘፀ6፥24
6፥24 1ዜና15፥5
6፥27 1ሳሙ1፥1፡20
6፥28 ቍ33፤1ሳሙ8፥2
6፥31 1ዜና9፥33፤15፥19፤25፥1፤2ዜና29፥25-26፤ዕዝ3፥10፤ነህ12፥45፤መዝ68፥25
6፥33 ቍ28፤ 1ነገ4፥31፤1ዜና15፥17፤25፥1
6፥34 1ሳሙ1፥1
6፥37 ዘፀ6፥24
6፥38 ዘፀ6፥21
6፥39 1ዜና15፥17፤25፥1፡9፤2ዜና29፥13፤ነህ11፥17
6፥44 1ዜና15፥17
6፥48 1ዜና23፥32

[a]26 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕምና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ኪሞትና 26 ሕልቃና፤ የሕልቃና ወንዶች ልጆች፤*
[b]27 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ሳሙ 19፡20 እና 1 ዜና 6፥33፡34 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ልጁ ሳሙኤል* የሚለውን ሐረግ አይጨምርም
[c]28 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና ሱርስቱ (እንዲሁም 1 ሳሙ8፥2 እና 1 ዜና 6፥33 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ኢዮኤል* የሚለውን ስም አይጨምርም።

6፥22-23 *አሴር...ሕልቃና...አቢሳፍ፤* እነዚህ የቆሬ ልጆች እንደ ሆኑ በዘፀ 6፥24 ላይ ተገልጾአል። እዚህ ላይ ግን አንድ ቀጥተኛና የሚወርድ የትውልድ ሐረግ ክፍል አድርጎ አቅርቦ አቸዋል (ቍ 20-21፡25-26፡29-30)፤ ይህ አንድም የትውልድ ሐረጉ ሳይቋረጥ ተያይዞ መውረዱን እንደ ምሳሌ የሚያሳይ፣ አለበለዚያም "ልጁ" የሚለው ቃል በቀጥታ እንደ አባት ሆኖ ስሙ የተጠቀሰውን ቀዓትን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

6፥22 *አሚናዳብ፤* በዚሁ ምዕራፍ በሚገኘው ተመሳሳይ የትውልድ ሐረግ ይስዓር በአሚናዳብ ቦታ ተተክቶ እናገኘዋለን። አሚናዳብ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የቀዓት ልጆች የስም ዝርዝር በተጠቀሰበት ቦታ ሁሉ ስሙ ተጽፎ ቢገኝም፣ በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከቀዓት ልጆች እንደ አንዱ ሆኖ አልተጠቀሰም (ቍ 2፡37-38፤ ዘፀ 6፥18፡21)። እንግዲህ አሚና ዳብ ማን እንደ ሆነ በትክክል መናገር ስለማይቻል፣ አሚናዳብ የሚለው ስም የይስዓር ሌላው መጠሪያው ሊሆን ይችላል። አለበለዚያም አሚናዳብ ይህን ያህል ዕውቅና የሌለው ልጅ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ይህ ከላይ ተያይዞ ሳያቋርጥ የመጣው የዘር ሐረግ፣ ሌዋውያን ከይሁዳ ነገድና ከዳዊት ቤት ጋር የተጠ ገናኙበትን መስመር የሚያሳይ ሊሆን ይችላል (ሩት 4፥18-22 ይመ፤ እንዲሁም ማቴ 1፥4፤ ሉቃ 3፥33 ይመ)። እዚህ ላይ አሮን ከይሁዳ ነገድ የሆነውን የአሚና ዳብን ልጅ ማግባቱን ከዚህ ጋር ማገናዘቡ ጠቃሚ ነው (ዘፀ 6፥23 እንዲሁም 1ዜና 2፥10 ይመ)።

6፥24 *ኡርኤል፤* ቀዓታውያንን በዳዊት ዘመን በአለቅነት የመራቸው ሰው ሊሆን ይችላል (15፥5)።

6፥26-27 *ሱፊ...ናሐት...ኤልያብ፤* ምናልባት ሱፍ፣ ቶዋና ኤሊኤል፣ የሚጠሩበት ተለዋጭ ስሞች ሊሆኑ ይችላሉ (ቍ 34-35)።

6፥27 *ሳሙኤል፤* የትውልድ ሐረጉ በ1ሳሙ 1፥1 ላይ የተጠቀሰው ሲሆን፣ ከኤፍሬም ቤተ ሰብ እንደሆነም ተገልጾአል። ሳሙኤል ወደ መገናኛው ድንኳን መግባቱና (1ሳሙ 3) የሥርዐተ ክህነቱንም አገልግሎት ማከናወኑ ከላይ ተያይዞ የመጣ (9፥22፤ 1ሳሙ 2፥18፤3፥1) የትውልድ ሐረግ ስላለው ይሆናል፤ ከሌዋውያን ጋር አብሮ እንዲያገለግል አስችሎታል። ወይም ደግሞ "ኤፍሬማዊ" የሚለው ቃል የዘር መስመርን (ግንድን) ሳይሆን፣ የመኖሪያ ስፍራን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

*6፥31-48፤* ከሌዊ ነገድ ሦስት ጐሣዎች እያንዳንዳቸው ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት የዜማ መሣሪያ ተጫዋቾችን በማ ቅረብ አስተዋፅኦ አድርገዋል። የመዘምራኑ አለቆች ሔማን ከቀዓት፣ አሳፍ፣ ከጌድሶን፣ ኤታም ከሜራሪ ጐሣዎች የተገኙ ናቸው። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዳዊት በልዩ ልዩ የዜማ መሣሪያዎች የሚያገለግሉ መዘምራንን መድቦ እንደ ነበር ደጋግሞ በማውሳቱና (15፥16፡27፤25፥1-31፤ 2ዜና 29፥25-26፤ እንዲሁም ነህ12፥45-47 ይመ) የሌዋውያኑን ተግባር በጥሩ ሁናቴ ተደጋግሞ በመጻፉ፣ ምናልባት ጸሐፊው ከመዘምራኑ አንዱ ሳይሆን እንደማይቀር የሚ ገምቱ አሉ፤ በሌላ በኩል በዚያን ዘመን በከነዓናውያን አብያተ ጣዖታት ውስጥ በልዩ ልዩ የዜማ መሣሪያዎች እንዲያገለግሉ የተ መደቡት መዘምራን እንደ ነበሩ ሌሎች የጽሑፍ ሰነዶች ይመሰክ ራሉ። ከምርኮ የተመለሱት ሌዋውያን ተግባር ሕጋዊነት ባለው መልኩ ምን ይመስል እንደ ነበር ይህ የትውልድ ሐረግ ያሳያል (ዕዝ2፥40-41፤ ነህ7፥43-44፤ 10፥9-13፡ 28-29፤11፥15-18፤ 12፥24-47)።

ዲያከናውኑ ተመድበው ነበር:: 49የእግዚአብሔር
ባሪያ ሙሴ ባዘዘው መሠረት ስለ እስራ
ኤል ማስተስረያ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ
የሚከናወነውን ተግባር ሁሉ፣ በመሠዊያው
ላይ የሚቃጠል መሥዋዕትና በዕጣኑ መሠ
ዊያ ላይ የሚቀርበውን መሥዋዕት የሚያቀ
ርቡት ግን አሮንና ዘሮቹ ብቻ ነበሩ::
50የአሮን ዘሮች እነዚህ ነበሩ፤
ልጁ አልዓዛር፣ ልጁ ፊንሐስ፣ ልጁ አቢሱ
51ልጁ ቡቂ፣ ልጁ ኦዚ፣ ልጁ ዘራእያ፣
52ልጁ መራዮት፣ ልጁ አማርያ፣ልጁ
አኪጦብ፣ 53ልጁ ሳዶቅ፣ ልጁ አኪማአስ::
54መኖሪያዎቻቸው እንዲሆኑ የተመደቡ
ላቸው ቦታዎች እነዚህ ናቸው፤ የመጀመሪ
ያው ዕጣ የእነርሱ ስለ ሆነ፣ ከቀዓት ጐሣ
ለሆኑት ለአሮን ዘሮች የተመደቡላቸው
መኖሪያዎች እነዚህ ነበሩ::

55ለእነርሱም በይሁዳ ምድር የምትገ
ኘው ኬብሮንና በዙሪያዋ ያለው የግ
ጦሽ ቦታ ተሰጠ፤ 56በኬብሮን ዙሪያ
የሚገኙት የዕርሻ ቦታዎችና መንደ
ሮች ግን ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ተሰጡ::
57ለአሮን ዘሮች የመማፀኛ ከተሞች
የሆኑትን ኬብሮንን፣ ልብናን፣ የቲ
ርን፣ ኤሽትሞዓን፣ 58ሖሎንን፣ ዳቤርን፣
59ዓሳንን፣ ዮታን[ᐨ]፣ ቤትሳሚስን ከነ
መሰማሪያዎቻቸው ሰጡ:: 60ከብንያም
ነገድ ድርሻ ላይ ገባያንን፣[T] ጌባን፣
ጋሌማን፣ ዓናቶትን ከነመሳሪያዎቻቸው
ሰጡ:: ለቀዓት ዘሮች የተከፋፈሉት
እነዚህ ከተሞች ባጠቃላይ ዐሥራ
ሦስት ናቸው::
61ለቀሩት የቀዓት ዘሮች ደግሞ ከም
ናሴ ነገድ እኩሌታ ድርሻ ዐሥር ከተሞች
ተሰጧቸው::
62ለጌድሶን ነገድ በየጐሣቸው ከይሳኮር፣
ከአሴር፣ ከንፍታሌምና በባሳን ከሚገኘው
ከምናሴ ነገድ ድርሻ ላይ ዐሥራ ሦስት ከተ
ሞች ተመደቡላቸው::
63ለሜራሪ ዘሮች በየጐሣቸው ከሮቤል፣
ከጋድና ከዛብሎን ድርሻ ላይ ዐሥራ ሁለት
ከተሞች ተመደቡላቸው::
64እስራኤላውያንም ከተሞቹን በዚሁ ሁኔታ
መድበው ከነመሰማሪያዎቻቸው ለሌዋው
ያኑ ሰጧቸው:: 65ቀደም ብለው የተጠቀሱ
ትንም ከተሞች ከይሁዳ፣ ከስምዖንና ከብን
ያም ነገድ ላይ ወስደው መደቡላቸው::
66ለአንዳንድ የቀዓት ጐሣዎችም ከኤፍ
ሬም ነገድ ድርሻ ላይ የሚኖሩበት ቦታ
ተሰጣቸው::

67በኰረብታማው በኤፍሬም ምድር
የሚገኙትን የመማፀኛ ከተሞች ሴኬ
ምን፣ ጌዝርን፣ 68ዮቅምዓምን፣ ቤትሖ
ሮን፣ 69ኤሎንንና ጋትሪሞን ከነመሰማ
ሪያዎቻቸው ሰጧቸው::
70እንዲሁም እስራኤላውያን ከምናሴ
ነገድ እኩሌታ ድርሻ ላይ ዓኔርና ቢል
ዓም የተባሉትን ከተሞች ከነመሰማሪ
ያዎቻቸው ወስደው ለቀሩት የቀዓት
ጐሣዎች ሰጧቸው::
71ጌድሶናውያን ከዚህ የሚከተሉትን ከተ
ሞች ወሰዱ፤
ከምናሴ ነገድ እኩሌታ፣
በባሳን የሚገኘውን ጎላንና አስታሮትን
ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤
72ከይሳኮርም ነገድ፣
ቃዴስን፣ ዳብራትን 73ራሞትንና ዓኔምናን
ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤
74ከአሴር ነገድ
መዓሳልን፣ ዓብዶን፣ 75ሑቆቅንና፣ ረአብን
ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ፤
76ከንፍታሌም ነገድ
በገሊላ የሚገኘውን ቃዴስን፣
ሐሞንንና፣ ቂርያታይምን ከነመሰማሪያ
ዎቻቸው ወሰዱ::
77ከሌዋውያን የቀሩት የሜራሪ ጐሣዎች
ደግሞ ከዚህ የሚከተለውን ወሰዱ፤
ከዛብሎን ነገድ ዮቅኒዓምን፣ ቀርታህን፣[υ]
ሬሞንና፣ታቦርን ከነመሰማሪያዎቻቸው
ወሰዱ::
78ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ኢያሪኮ በስተ
ምሥራቅ ከሚገኘው ከሮቤል ነገድ፣
በምድረ በዳ የሚገኘውን ቦሶርን፣ ያሳን፣
79ቅዴሞትንና ሜፍዓትን ከነመሰማሪ
ያዎቻቸው ወሰዱ፤
80ከጋድ ነገድ በገለዓድ የምትገኘውን ሬማ
ትን፣ መሃናይምን፣81ሐሴቦንና ኢያዜርን
ከነመሰማሪያዎቻቸው ወሰዱ::

## ይሳኮር

7 የይሳኮር ወንዶች ልጆች፤
ቶላ፣ ፉዋ፣ ያሱብ፣ ሺምሮን፤ ባጠቃ
ላይ አራት ናቸው::
2የቶላ ወንዶች ልጆች፤
ኦዚ፣ ረፋያ፣ ይሪኤል፣ የሕማይ፣ ይብ
ሣም፣ ሽሙኤል፤ እነዚህ የየቤተ ሰባ

6፥49 ዘፀ27፥1-8፤30፥7፤2ዜና26፥18
6፥53 2ሳሙ8፥17
6፥54 ዘኍ31፥10
6፥56 ኢሱ14፥13፤15፥13
6፥57 ዘኍ33፥20፤ ኢሱ15፥48
6፥58 ኢሱ10፥3
6፥59 ኢሱ15፥42
6፥60 ኤር1፥1
6፥64 ዘኍ35፥1-8
6፥67 ኢሱ10፥33
6፥68 ኢሱ10፥10፤ 1ነገ4፥12
6፥69 ኢሱ10፥12፤ ኢሱ19፥45
6፥71 ኢሱ20፥8፤1ዜና23፥7
6፥72 ኢሱ19፥12
6፥74 ኢሱ19፥28
6፥75 ዘኍ13፥21፤ ኢሱ19፥34
6፥76 ዘኍ32፥37፤ ኢሱ 19፥28
6፥78 ኢሱ20፥8
6፥79 ዘዳ2፥26
6፥80 ዘፍ32፥2፤ ኢሱ20፥8
6፥81 ዘኍ21፥32፤ 2ዜና11፥14
7፥1 ዘፍ30፥18፤46፥13

[ᐨ]59 የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም የሰብዓ ሊቃናትና ኢሱ 21፥16) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ "ዮታን" የሚለውን ስም አይጨምርም::
[T]60 ኢሱ 21፥17 ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን "ገባዖን" የሚለውን ስም አይጨምርም::
[υ]77 የሰብዓ ሊቃናት ትርጉምንና ኢሱ 21፥34 ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ "ዮቅኒዓምን፣ ቀርታህን" የሚለውን አይጨምርም::

*6፥49-53፤* ይህ ክፍል ቍ4-8ን ይደግማል፤ ይሁን እንጂ ይህ የሆነበት ምክንያት የተለየ ነው፤ ይኸውም ወደ ኋላ ሲቈጠር እስከ ሰሎሞን ዘመን ድረስ በተከታታይ ሲያገለግል የነበረው የሳዶቅ የዘር (ትውልድ) ከሌዋውያን ሁሉ ተለይቶ መሥዋዕት ለማቅረብ ብቸኛ ሥልጣን የተሰጠው ዘር መሆኑን ለማሳየት ነው::

*6፥54-81፤* ይህ የሌዋውያኑን ይዞታ የሚያመለክተው ዝርዝር ከኢያሱ 21 የተወሰደ ሲሆን፣ ልዩነቱ ጥቂት ነው (ያንኑ ማብ ይመ):: ሌዋውያኑ እንደ ሌሎቹ ነገዶች ሁሉ የራሳቸው የሆነ የነገድ ርስት ተለይቶ ስላልተሰጣቸው፣ በእያንዳንዱ የእስራ ኤል ነገድ መካከል ይኖሩ ነበር::

*7፥1-5፤* ምንም እንኳ ስለ አብዛኞዎቹ ስሞች ግልጽ የሆነ ማስረጃ ማቅረብ ባይቻልም፣ የይሳኮር የትውልድ ሐረግ የተወሰደው ከዘፍ 46፥13፤ ከዘኍ 1፥28፤26፥23-25 ላይ ነው:: ይህ የየጐሣዎቹ ስም ዝርዝር በዳዊት ዘመን (ቍ2) ለውትድርና አገልግሎት ብቁ የሆኑትን ሰዎች ብዛት ለማወቅ ከተደረገው ቈጠራ ጋር ይመሳሰላል (ቍ 2፡4-5)፤ ምናልባትም በም21 እና በ2ሳሙ 24 ላይ እንደ

ቸው አለቆች ናቸው፤ በዳዊት ዘመነ
መንግሥት ከቶላ ዘሮች፣ በየትው
ልድ ሐረጋቸው የተቈጠሩት የቶላ
ዘሮች ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ፤ ቍጥራ
ቸውም ሃያ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ
ነበረ።
3የኦዚ ወንድ ልጅ፤
ይዝረሕያ።
የይዝረሕያ ወንዶች ልጆች፤
ሚካኤል፣ አብድዩ፣ ኢዩኤል፣ ይሺያ፤
አምስቱም አለቆች ነበሩ። 4ብዙ ሚስ
ቶችና ልጆች ስለ ነበሩአቸው፣ ከቤተ
ሰባቸው የትውልድ ሐረግ ለውጊያ
ብቁ የሆኑ ሠላሳ ስድስት ሺህ ሰዎች
ነበሩአቸው።
5ከይሳኮር ጐሣዎች ሁሉ የተመዘገቡት
ተዋጊዎች የቤተ ሰቦቹ ትውልድ ቍጥር
ባጠቃላይ ሰማንያ ሰባት ሺህ ነበሩ።

## ብንያም

6ሦስቱ የብንያም ወንዶች ልጆች፤
ቤላ፣ቤኬር፣ ይዲኤል።
7የቤላ ወንዶች ልጆች፤
ኤሴቦን፣ ኦዚ፣ ዑዝኤል፣ ኢያሪሙት፣
ዒሪ፤ ባጠቃላይ አምስት ሲሆኑ፣ የቤተ
ሰብ አለቆች ናቸው፤ በትውልድ ሐረግ
መዝገባቸው ሃያ ሁለት ሺህ ሠላሳ አራት
ተዋጊ ሰዎች ተመዝግበዋል።
8የቤኬር ወንዶች ልጆች፤
ዝሚራ፣ ኢዮአስ፣ አልዓዛር፣ ኤልዮዔናይ፣
ዖምሪ፣ ኢያሪሙት፣ አብያ፣ ዓናቶት፣
ዓሌሜት፤ እነዚህ ሁሉ የቤኬር ልጆች
ነበሩ። 9በትውልድ ሐረግ መዝገባቸ
ውም ውስጥ የየቤተ ሰባቸው አለቆችና
ሃያ ሺህ ሁለት መቶ ተዋጊዎች ተመዝግ
በዋል።
10የይዲኤል ልጅ፤
ቢልሐን።
የቢልሐን ወንዶች ልጆች፤
የዑስ፣ ብንያም፣ ኤሁድ፣ ክንዓና፣
ዜታን፣ ተርሴስ፣ አኪሳአር፤ 11እነዚህ
ሁሉ የይዲኤል ልጆች የየቤተ ሰቡ
አለቆች ነበሩ፤ እነርሱም ለውጊያ ብቁ
የሆኑ ዐሥራ ሰባት ሺህ ተዋጊዎች
ነበሯቸው።
12ሳፊንና ሑፊም የዒር ዘሮች ሲሆኑ፣
ሑሺም ደግሞ የአሔር ዘር ነው።

## ንፍታሌም

13የንፍታሌም ወንዶች ልጆች፤
ያሕጽኤል፣ ጉኒ፣ ዬጽር፣ ሺሌም፤ እነ
ዚህ የባላ ዘሮች ናቸው።

## ምናሴ

14የምናሴ ዘሮች፤
ሶርያዊት ቁባቱ የወለደችለት ልጁ
አሥርኤል ነው። እርሷም የገለዓድን
አባት ማኪርን የወለደች ናት፤ 15ማኪ
ርም ከሑፊምና ከሳፊም ወገኖች
ሚስት አገባ። እኅቱም መዓካ ትባል
ነበር።
ሌላው ዘሩ ሰለጰዓድ ሲሆን፣ እር
ሱም ሴቶች ልጆች ብቻ ነበሩት።
16የማኪር ሚስት መዓካ ወንድ ልጅ
ወለደች፤ ስሙንም ፋሬስ አለችው።
የወንድሙም ስም ሱሮስ ይባላል፤ ወን
ዶች ልጆቹም ኡላምና ራቄም ነበሩ።
17የኡላም ወንድ ልጅ፤
ባዳን፤
እነዚህ የምናሴ ልጅ፣ የማኪር ልጅ፣
የገለዓድ ወንዶች ልጆች ናቸው፤ 18እኅቱ
መለኬት ኢሱድን፣ አቢዔዝርንና መሕ
ላን ወለደች።
19የሸሚዳ ወንዶች ልጆች ደግሞ እነዚህ ነበሩ፤
አሒያን፣ ሴኬም፣ ሊቅሒ፣ አኒዓም።

## ኤፍሬም

20የኤፍሬም ዘሮች፤
ሹቱላ፣ ልጁ ባሬድ፣ ልጁ ታሐት፣ ልጁ
ኤልዓዳ፣ ልጁ ታሐት፣21 ልጁ ዛባድ፣ ልጁ
ሹቱላ። ኤድርና ኤልዓድ ከብቶች ለመ
ስረቅ በወረዱ ጊዜ፣ የአገሩ ተወላጆች
በሆኑት በጌት ሰዎች ተገደሉ። 22አባ
ታቸውም ኤፍሬም ብዙ ቀን አለቀሰ
ላቸው፤ ዘመዶቹም መጥተው አጽናኑት።
23ከዚያም ወደ ሚስቱ ገብቶ ተኛ፤ እር
ሷም ፀነሰች፤ ወንድ ልጅም ወለደች፤
በቤተ ሰቡ ላይ ከደረሰው መከራ የተ
ነሣ ስሙን በሪዓ አለው። 24ሴት ልጁ

7፥6 ዘኍ26፥38
7፥13 ዘፍ30፥8
7፥14 ዘፍ41፥51፤ዘኍ26፥30፤ ኢሱ17፥1፤ 1ዜና 5፥23
7፥15 ዘኍ26፥33፤ 36፥1-12
7፥17 ዘኍ26፥30
7፥18 ኢሱ17፥2
7፥19 ኢሱ17፥2
7፥20 ዘፍ41፥52፤ዘኍ1፥33
7፥24 ኢሱ10፥10

ተመለከተው በዳዊት ዘመን ቍ2 የተደረገውን የሕዝብ ቈጠራ የሚያንጸባርቅ ሳይሆን አይቀርም።

*7፥6-12፤* የብንያምን ወንዶች ልጆች ስም ዝርዝር በተ መለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጕልህ ልዩነቶች ይታያሉ። ይህ ዝርዝር የሦስቱን ወንዶች ልጆች ስም ይሰጣል፤ ዘፍ46፥2፤ ዐሥሩን መዝግቦአል፤ ዘኍ 26፥38-39 እና 1ዜና8፥1-2 አምስቱን መዝ ግቦአል፤ በእነዚህ ሁሉ ምንጮች ተመዝግቦ የሚገኘው የበኵሩ ልጅ የቤላ ስም ብቻ ነው። የልዩነቱም መንሥኤ እነዚህ የትው ልድ ሐረጎች የተለያዩ ምንጮችና የተለያዩ ተግባራት ያላቸው መሆኑን የሚያንጸባርቁ ናቸው። በዚህ ስፍራ ያለው ዝርዝር የሚያ ሳየው በውትድርናው ዓለም ያለውን ተግባር ነው (ቍ7:9:11)

*7፥13፤* ዘፍ 46፥24ን ዘኍ 26፥48-50ን እዚህ ላይ ይደ ግማቸዋል። *የባላ ዘሮች፤* ዳንና ንፍታሌም በትክክል የያዕ ቆብ ቁባት የባላ ወንዶች ልጆች (ዘፍ:30፥3-8)፤ ስለሆኑ የንፍታ ሌም ወንዶች ልጆችም የባላ "ዘሮች" ናቸው ማለት ነው።

*7፥14-19፤* የ5፥23-26 ማብ ይመ። የዚህ የትውልድ ሐረግ ምንጮች ዘኍ 26፥29-34፤ ኢሱ 17፥1-18 ናቸው። የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች (ቍ15) ሴቶች የውርስ መብት እንዲያገኙ ምክንያት ሆነዋል (ዘኍ 26፥29-34፤ 27፥1-11፤36፥1-12፤ ኢሱ 17፥3-4)። በእነዚህ የትውልድ ሐረጎች ከሚገኙት (ከታወቁት) ዐሥራ ሦስት የተለያዩ ጐሣዎች መካከል ሰባቱ፣ 65 ጽሑፎችን ካካተተውና ስለ ወይን ጠጅ፣ ዘይት፣ ገብስና ስለ ሌሎችም የቤት ዕቃዎች በሚና ገረው "ሰማሪያ እስትራካ" በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰ ዋል። ሴቶች በዘር ግንድ ስማቸው መጠቀሱ በዚያ ዘመን ያል ተለመደ ነገር ነው። ምናልባት ከእስራኤል ውጭ ባለው ዓለም ውስጥ የሴቶች መብት ቢያንስ በሕገ መንግሥት ውስጥ ሰፍሮ ይሆናል።

*7፥20-29፤* የኤፍሬም የትውልድ ሐረግ የተወሰደው ከዘኍ26፥35 ላይ ነው። ፋሬ(ቍ25) የኤፍሬም የልጁ ልጅ ከሆነ፣ ከኤፍሬም እስከ ኢያሱ ዐሥር ትውልድ ተመዝግቦአል ማለት ነው፤ ይህም እስራኤላውያን በምድረ ግብፅ ከነበሩበት አራት መቶ ዓመት ጋር የሚጣጣም ነው። ኢያሱ ከኤፍሬም የዘር ግንድ መሆኑም በዘኍ13፥8 ላይ ተጠቅሷል፤ ስሙን ግን "አውሴ" ይለዋል (ዘኍ13፥16ይመ)። ጌት የተወረረችው (ቍ21-22) የከነዓን ምድር ከመያዟ በፊት ገና በግብፅ ሳሉ መሆን አለበት። ገብተው የሰፈሩባቸውም ቦታዎች ስም ዝር

ስሟ ሲአራ ይባላል፤ እርሷም የታችኛ
ውንና የላይኛውን ቤት ሖሮንንና
ኡዜን ሼራን የተባሉትን ከተሞች የቈ
ረቈረች ናት።
25ልጁ ፋሬ፣ ልጁ^ ሬሴፍ፣ ልጁ ቴላ፣
ልጁ ታሐን፣ 26ልጁ ለአዳን፣ ልጁ
ዓሚሁድ፣ ልጁ ኤሊሳማ፣ 27ልጁ ነዌ፣
ልጁ ኢያሱ።
28ምድራቸውና መኖሪያቸው ቤቴልንና
በዙሪያዋ የሚገኙትን ከተሞች፣ በስተምሥ
ራቅ ነዓራን፣ በስተ ምዕራብ ጌዝርንና መን
ደሮቿን፣ እንዲሁም ሴኬምንና መንደሮቿን፣
ከዚያም አልፎ ዓያንና መንደሮቿን በሙሉ
ያጠቃልል ነበር። 29በምናሴም ወሰን ላይ
ቤትሳን፣ ታዕናክ፣ መጊዶና ዶር ከነመንደ
ሮቻቸው ነበሩ። በእነዚህም መንደሮች የእ
ስራኤል ልጅ የዮሴፍ ዘሮች ይኖሩ ነበር።

### አሴር

30የአሴር ወንዶች ልጆች፤
ዪምና፣ የሱዋ፣ የሱዊ፣ በሪዓ፤ እኅታቸ
ውም ሤራሕ ትባል ነበር።
31የበሪዓ ወንዶች ልጆች፤
ሐቤርና የቢርዛዊት አባት መልኪኤል።
32ሔቤርም ያፍሌጥን፣ ሳሜርን፣ ኮታም
ንና እኅታቸውን ሶላን ወለደ።
33የያፍሌጥ ወንዶች ልጆች፤
ፋሴክ፣ ቢምሃል፣ ዓሲት፤
የያፍሌጥ ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ።
34የሳሜር ወንዶች ልጆች፤
አኪ፣ ሮኦጋ፣^ ይሑባ፣ አራም።
35የወንድሙ የኤላም ወንዶች ልጆች፤
ጾፋ፣ ይምና፣ ሰሌስ፣ ዓማል።
36የጾፋ ወንዶች ልጆች፤
ሱዋ፣ ሐርኔፍር፣ ሦጋል፣ ቤሪ፣ ይምራ፣
37ቤጼር፣ ሆድ፣ ሳማ፣ ሰሊሳ፣ ይትራን፣
ብኤራ።
38የዬቴር ወንዶች ልጆች፤
ዮሮኒ፣ ፊስጳ፣ አራ።
39የዑላ ወንዶች ልጆች፤
ኤራ፣ ሐኒኤል፣ ሪጽያ።
40እነዚህ ሁሉ የአሴር ዘሮች ናቸው፤ እነ
ርሱም የቤተ ሰብ አለቆች፣ ምርጥ ሰዎች፣
ብርቱ ተዋጊዎችና ድንቅ መሪዎች ነበሩ።
በትውልድ መዝገባቸው እንደተጻፈው ለው
ጊያ ብቁ የሆኑት ወንዶች ቍጥር ሃያ ስድ
ስት ሺህ ነበር።

7፥28 ኢሱ10፥33
7፥29 ኢሱ11፥2፤17፥11
7፥30 ዘኍ1፥40
8፥1 ዘፍ46፥21
8፥3 ዘፍ46፥21
8፥4 2ሳሙ23፥9
8፥6 መሳ3፥12-30
8፥12 ዕዝ2፥33፤ ነህ6፥2፤7፥37፤11፥35
8፥13 ኢሱ10፥12፤11፥22

## የብንያማዊው የሳኦል ትውልድ ሐረግ

8፥28-38 ተጓ ምብ - 1 ዜና 9፥34-44

8 ብንያም የበኵር ልጁን ቤላን፣
ሁለተኛ ልጁን አስቤልን፣
ሦስተኛ ልጁን አሐራን፣ 2አራተኛ ልጁን
ኖሐን፣ አምስተኛ ልጁን ራፋን ወለደ።
3የቤላ ወንዶች ልጆች እነዚህ ነበሩ፤
አዳር፣ ጌራ፣ አቢሁድ፣^ 4አቢሱ፣ ናዕ
ማን፣ አሖዋ፣ 5ጌራ፣ ሰፉፋ፣ ሒራም።
6በጌባ ይኖሩ የነበሩትና በኋላም በምርኮ
ወደ መናሐት የተወሰዱት የኤሁድ
ዘሮች እነዚህ ናቸው፤ 7ናዕማን፣ አኪያ፣
ጌራ፤ በምርኮ ጊዜ እየመራ የወሰዳቸው
የዖዛና የአሒሑድ አባት ጌራ ነበረ።
8ሸሐራይም ሚስቶቹን ሑሺምንና በዕራን
ከፈታ በኋላ በሞዓብ ምድር ወንዶች
ልጆች ወለደ። 9ከሚስቱ ከሖዴሽ ዮባ
ብን፣ ዲብያን፣ ማሴን፣ ማልካምን፣
10ይዑጽን፣ ሻክያንና ሚርማን ወለደ፤
እነዚህም የቤተ ሰብ አለቆች የነበሩ
ልጆቹ ናቸው። 11ሑሺም ከተባለች
ሚስቱ አቢጡብና ኤልፍዓል የተባሉ
ወንዶች ልጆች ነበሩት።
12የኤልፍዓል ወንዶች ልጆች፤
ዔቤር፣ ሚሻም እንዲሁም ኦኖንና ሎድ
የተባሉ ከተሞችን ከነመንደሮቻቸው የቈ
ረቈረ ሻሜድ፣ 13በኤሎን ይኖሩ ለነ
በሩ ቤተ ሰቦች አለቆችና የጋት ነዋሪዎ
ችን አስወጥተው ያሳደዱ በሪዓና ሽማዕ።
14አሒዮ፣ ሻሻቅ፣ ይሬምት፣ 15ዝባድያ፣
ዓራድ፣ ዔድር፣ 16ሚካኤል፣ ይሽጳና
ዮሐ የበሪዓ ወንዶች ልጆች ነበሩ።
17ዝባድያ፣ ሜሱላም፣ ሕዝቂ፣ ሔቤር፣
18ይሽምራይ፣ ይዝሊያና ዮባብ የኤል
ፍዓል ወንዶች ልጆች ነበሩ።
19ያቂም፣ ዝክሪ፣ ዘብዲ፣ 20ኤሊዔናይ፣
ጺልታይ፣ ኤሊኤል፣ 21ዓዳያ፣ ብራያና፣
ሺምራት የሰሜኢ ወንዶች ልጆች ነበሩ።
2ይሽጳን፣ ዔቤር፣ ኤሊኤል፣ 23ዓብዶን፣
ዝክሪ፣ ሐናን፣ 24ሐናንያ፣ ኤላም፣ ዓን
ቶትያ 25ይፍዴያና ፋኑኤል የሶሴቅ
ወንዶች ልጆች ነበሩ።

^25 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ "ልጁ" የሚለውን ቃል አይጨምርም
^34 ወይም፣ *"ወንድሙ ሳሜር፤ ሮኦጋ"*
^3 ወይም፣ *"የሁድ አባት ጌራ"*
^29 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (1 ዜና 9፥35 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *ይዒኤል* የሚለውን አይጨምርም

ዝር (ቍ 28-29) ኢያ16-17 ላይ ያለውን አሳጥሮ የያዘ ነው።

*7፥30-40*፤ ከአሴር የትውልድ ሐረግ የመጀመሪያው ሦስት ተከታታይ ትውልድ ዘፍ 46፥17ን ይከተላል። እንዲሁም "የሱዋ" የሚለው ስም ከመዘለሉ በስተቀር (ቍ 30) ከዘኍ 26፥44-46 ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህም የትውልድ ሐረግ ለውትድርና ተግባር ሲባል የተደረገውን የሕዝብ ቈጠራ የሚያንጸባርቅ ነው (ቍ 40)።

*8፥1-40*፤ ሁለተኛውን ከዚያም አልፎ ተርፎ የሚገኘውን የብንያምን የትውልድ ሐረግ በዚህ ክፍል ማካተቱ (የ6-12 ማብ ይመ) የነገዱን ስፍራና የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ስለ ሳውል ያለውን ከፍተኛ ግምት ያንጸባርቃል። የደቡብ መንግሥት የይሁዳ፣ የስምዖንና የብንያም ነገድ እኩሌታ ስብስብ ነው። (1ነገ 12፥1-21)፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በነበረበት ዘመን ግዛታቸው ባብዛኛው ከምርኮ መልስ የነበረውን የአይሁድ አውራጃ የሚያካትት ነበር፤ የብንያም የትውልድ ሐረግ ይሁዳንና ሌዊን ሳይጨምር፣ ከቀሩት ነገዶች ሁሉ ይበልጥ የሰፋ ነበር። የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ለሳኦልም የዘር ግንድ እንደዚሁ ትኩረት ሰጥቶታል (ቍ 29-38)። ይህን የፈለገውም የዘመነ መንግሥቱ ፍጻሜ ወደሚቀጥለው አዲስ ታሪክ ለመሸጋገሪያነት ሊጠቀምበት ፈልጎ ነው (ም 10)። የሳኦል የትውልድ ሐረግ በ9፥35-44 ላይ ተደግሞ ተጽፎአል። ይህ የትውልድ ሐረግም በውትድርና ክልል ውስጥ እንደ ተመሠረተ አንዳንድ ምንጮች ይናገራሉ (ቍ6:10: 13:28:40)።

*8፥1-5*፤ ከ7:6-12፤ ዘፍ 46፥21-22፤ ዘኍ 26፥38-41 ጋር ያነጻጽሩ።

*8፥6-27*፤ በዜና መዋዕል መጽሐፍ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው።

26 ሽምሽራይ፣ ሸሃሪያ፣ ጎቶልያ፣ 27 ያሬ
ሽያ፣ ኤልያስና፣ ዝክሪ የይሮሐም ወን
ዶች ልጆች ነበሩ።
28 እነዚህ ሁሉ በየትውልድ ሐረጋቸው
የተቈጠሩ አለቆችና የቤተ ሰብ መሪዎች
ሲሆኑ፣ የሚኖሩትም በኢየሩሳሌም ነበረ።
29 የገባዖን አባት[ሙ] ይዒኤል[ረ] በገባዖን ኖረ፤
ሚስቱ መዓካ ትባል ነበር። 30 የበኵር
ልጁም አብዶን ይባል ነበር፤ የእርሱም
ተከታዮች ዱር፣ ቂስ፣ በአል፣ ኔር፣[ሰ]
ናዳብ፣ 31 ጌዶር፣ አሒዮ፣ ዛኩርና 32 የሺ
ምዓ አባት ሚቅሎት ነበሩ። እነዚህም
ከሥጋ ዘመዶቻቸው ጋር በኢየሩሳሌም
ከተማ አቅራቢያ ይኖሩ ነበር።
33 ኔር ቂስን ወለደ፤ ቂስ ሳኦልን ወለደ፤
ሳኦልም ዮናታንን፣ ሜልኪሳን፣ አሚና
ዳብን፣ አስበአልን[ሸ] ወለደ።
34 የዮናታን ወንድ ልጅ
መሪበኣል[ቀ]፤ እርሱም ሚካን ወለደ።
35 የሚካ ወንዶች ልጆች፤
ፒቶን፣ ሜሌክ፣ ታሬዓ፣ አካዝ።
36 አካዝ ይሆዓዳን ወለደ፤ ይሆዓዳም ዓሌሜ
ትን፣ ዓዝሞትን፣ ዘምሪን ወለደ፤
ዘምሪም ሞጻን ወለደ። 37 ሞጻ ቢንዓን
ወለደ፤ ቢንዓ ረፋያን ወለደ፤ ረፋያ
ኤልዓሣን ወለደ፤ ኤልዓሣም ኤሴልን
ወለደ።
38 ኤሴል ስድስት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
ስማቸውም፦
ዓዝሪቃም፣ ቦክሩ፣ እስማኤል፣ ሸዓ
ርያ፣ አብድዩ፣ ሐናን ይባላል፤ እነዚህ
ሁሉ የኤሴል ልጆች ነበሩ።
39 የወንድሙ የኤሴቅ ወንዶች ልጆች፤
የበኵር ልጁ ኡላም፣ ሁለተኛ ልጁ ኢያስ፣
ሦስተኛ ልጁ ኤሊፋላት። 40 የኡላም
ልጆች በቀስት መንደፍ የሚችሉ ብርቱ
ተዋጊዎች ነበሩ፤ እነርሱም ባጠቃላይ
ቍጥራቸው አንድ መቶ ሃምሳ ወን
ዶች ልጆችና የልጅ ልጆች ነበሯ
ቸው፤ እነዚህ ሁሉ የብንያም ትውል
ዶች ነበሩ።

8፥29 ኢሱ9፥3
8፥33 1ሳሙ9፥1፤14፥49፤28፥19፤2ሳሙ2፥8
8፥34 2ሳሙ4፥4፤9፥12፤21፥7-14
8፥40 ዘኍ26፥38
9፥1 ዘጸ21፥10፤1ዜና5፥25፤11፥1:10፤12፥38፤14፥8፤15፥3:28፤18፥14፤19፥17፤21፥5፤28፥4:8፤29፥21:23፤2ዜና1፥2፤5፥3፤7፥8፤10፥3:16፤12፥1፤13፥4:15፤18፥16፤24፥5፤28፥23፤29፥24፤30፥1
9፥2 ኢሱ9፥27፤ ዕዝ2፥43: 58:70፤8፥20፤ነህ7፥60
9፥4 ዘፍ38፥29፤46፥12

9 እስራኤል ሁሉ በየትውልድ ሐረጋቸው
ተቈጥረው ስማቸው በእስራኤል ነገሥ
ታት መዝገብ ላይ ሰፈረ።

### የኢየሩሳሌም ከተማ ሕዝብ

9፥1-17 ተጓ ምብ - ነህ 11፥3-19

የይሁዳ ሕዝብ ከፈጸሙት በደል የተነሣ
ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። 2 በመጀ
መሪያ በየርስታቸውና በየከተሞቻቸው ተመ
ልሰው የሰፈሩት ጥቂት እስራኤላውያን፣
ካህናት፣ ሌዋውያንና በቤተ መቅደሱ ውስጥ
የጕልበት ሥራ የሚሠሩ አገልጋዮች ነበሩ።
3 በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ የይሁዳ፣ የብ
ንያም፣ የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች የሚ
ከተሉት ናቸው፤
4 ከይሁዳ ልጅ፣ ከፋሬስ ዘሮች፣ የባኒ
ልጅ፣ የአምሪ ልጅ፣ የዖምሪ ልጅ፣
የዓሚሁድ ልጅ ዑታይ።
5 ከሴሎናውያን፦
የበኵር ልጁ ዓሣያና ወንዶች ልጆቹ።
6 ከዛራውያን፦
ይዑኤል፤
የሕዝቡ ቍጥር ስድስት መቶ ዘጠና
ነበረ።
ከይሁዳ ነገድ የሰው ቍጥር ስድስት
መቶ ዘጠና ነበር።
7 ከብንያማውያን፦
የሐስኑአ ልጅ፣ የሆዳይዋ ልጅ፣ የሜ
ሱላም ልጅ ሰሉ። 8 የይሮሐም ልጅ
ብኔያ፤ የሚክሪ ልጅ፣ የኦዚ ልጅ ኤላ፤
የይብንያ ልጅ፣ የራጉኤል ልጅ፣ የሰፋ
ጥያ ልጅ ሜሱላም። 9 በትውልድ ሐረግ
መዝገቡ ላይ በተጻፈው መሠረት ከብ
ንያም ነገድ የሕዝቡ ቍጥር ዘጠኝ መቶ
ሃምሳ ስድስት ነበረ፤ እነዚህ ሁሉ
ወንዶች የቤተ ሰብ አለቆች ነበሩ።

[ሙ]29 አባት ማለት፣ የማኅበረሰብ መሪ ወይም የጦር መሪ ማለት ነው።
[ሰ]30 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞች (እንዲሁም 1ዜና 9፥36 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ኔር የሚለውን ስም አይጨምርም
[ሸ]33 ኢሽ ቦሼት በመባልም ይታወቃል
[ቀ]34 ሜፊቦስቴ በመባልም ይታወቃል

*8፥29-38*፤ በመሠረቱ በ9፥35-44 ላይ ከተጠቀሰው የስም ዝርዝር ጋር አንድ ነው።

*8፥33*፤ የሳዖልን ወንዶች ልጆች በተመለከተ 1 ሳሙ 14፥49፤31፥2 ይመ። ***ዮናታን***፤ የሳኦል የበኵር ልጁ ነው። ዮናታን ተወዳዳሪ በሌለው ጀግንነቱና ከዳዊት ጋር ባለው ጽኑ ፍቅር በእጅጉ የታወቀ ነበር (1ሳሙ13-14፤18፥1-4፤19፥1-7፤ 20፥1-42፤ 23፥16-18፤ 2ሳሙ21፥13-14)። ***አስበኣል***፤ የ2 ሳሙ 2፥8 ማብ ይመ።

8፥34 ***መሪበኣል***፤ አማራጭ ትርጕሙን ይመ። የ2ሳሙ 4፥4 እንዲሁም ማብ ይመ።

9፥1 ***እስራኤል ሁሉ***፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የተለያዩ የትውልድ ሐረጎችን በመጽሐፉ ውስጥ ማካተቱ "እስራኤል ሁሉ" ለሚለው ሐረግ የተለየ ትኵረት እንደሚሰጠው የሚያመለክት ነው (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ዓላማውና መሪ ሐሳቡ የሚለውን ይመ)።

*9፥2-34*፤ ይህ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ስም የያዘው ዝርዝር በጸሐፊው ዘመን የነበረውን ሥርዐተ ደንብ በተለይም የኀላፊነቱን ቦታ የያዙት ወገኖች ሕጋዊ ሥልጣን ምን እንደ ነበረ የሚያንጸባርቅ ነው። በቍ 3-9 ላይ የተራውን ሕዝብ ("እስራኤላውያን" ቍ 2)፣ በቍ 10-13 ላይ የካህናቱን፣ በቍ 14-34 ላይ የሌዋውያኑን ስም ዘርዝሮአል። እንደዚሁም ከምርኮ ተመላሾች መካከል አራተኛ መደብ የሆኑትን የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ጠቅሷል፤ እነዚህም በቤተ መቅደሱ ውስጥ የጕልበት ሥራ በመሥራት የሚያገለግሉ ናቸው (ቍ 2) ፤ ይሁን እንጂ የስም ዝርዝራቸውን ለብቻ አይጽፈውም። እነዚህ ጥንቱኑ ባዕዳን ሆነው ሳለ፣ ከሌዋውያኑ ጋር የተቀላቀሉ ሳይሆኑ አልቀሩም (ኢያ 9፥23፤ዕዝ 8፥20)። ስለዚህም ዝርዝራቸው ከሌዊ ነገድ ውጭ ራሱን ችሎ አልተጻፈም። ተመሳሳይ ነው የአገልግሎት ድርሻ በጥንቱ የዑጋሪት ቤተ ጣዖት ውስጥም ነበር። እዚህ ላይ የተሰጠው ዝርዝር በነህ11 ላይ ከተጻፈው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ሆኖም በሁለቱ ቦታዎች አንድ ዐይነት የሆኑት የስም ዝርዝሮች ከግማሽ በታች ናቸው።

9፥3 ***የኤፍሬምና የምናሴ***፤ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ "እስራኤል ሁሉ" የሚለውን ሐረግ እንደገና በማንጸባረቅ፣ ከምርኮ የተመለሱት የይሁዳና የብንያም ነገዶች ብቻ ሳይሆኑ ከሰሜኑ ነገዶችም መካከል እንዳሉ ያሳያል።

*9፥4-6*፤2፥3-6፤4፥21 ይመ። ከምርኮ፣ የተመለሱትን የይ

10ከካህናቱ:-
ዮዳኤ፣ ዮአሪብ፣ ያኪን፤
11የእግዚአብሔር ቤት አለቃ የሆነው የአ
ኪጦብ ልጅ፣ የመራዮት ልጅ፣ የሳ
ዶቅ ልጅ፣ የሜሱላም ልጅ፣ የኬልቅ
ያስ ልጅ ዓዛርያስ።
12የመልክያ ልጅ፣ የጳስኮር ልጅ፣ የይ
ሮሐም ልጅ ዓዳያ፤ የኢሜር ልጅ፣
የምሺላሚት ልጅ፣ የሜሱላም ልጅ፣
የየሕዜራ ልጅ፣ የዓዲኤል ልጅ መዕሣይ።
13የቤተ ሰብ አለቃ የነበሩት ካህናት ቍጥር
አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሥልሳ ነበረ፤ እነዚ
ህም በእግዚአብሔር ቤት ለሚከናወነው አገ
ልግሎት ብቁ ሰዎች ነበሩ።
14ከሌዋውያን ወገን:-
ከሜራሪ ዘሮች የአሳብያ ልጅ፣ የዓዝሪ
ቃም ልጅ፣ የአሱብ ልጅ ሸማያ፣
15በቅበቃር፣ ኤሬስ፣ ጋላልና የአሳፍ
ልጅ፣ የዝክሪ ልጅ፣ የሚካ ልጅ መታ
ንያ። 16የኤዶታም ልጅ፣ የጋላል ልጅ፣
የሰሙስ ልጅ አብድያ። እንዲሁም በነ
ጦፋውያን ከተሞች የኖረው የሕልቃና
ልጅ፣ የአሳ ልጅ በራክያ።
17የቤተ መቅደሱ በር ጠባቂዎች:-
ሰሎም፣ ዓቁብ፣ ጤልሞን፣ አሒማንና
ወንድሞቻቸው፤ አለቃቸውም ሰሎም
ነበረ፤ 18እርሱም በስተ ምሥራቅ በሚገ
ኘው በንጉሡ በር እስካሁን ድረስ ተመ
ድቦአል። እነዚህም የሌዋውያኑ ሰፈር
በር ጠባቂዎች ነበሩ። 19የቆሬ ልጅ
የአብያሳፍ ልጅ፣ የቆሬ ልጅ ሰሎምና
ከእርሱም ቤተ ሰብ የሆኑት ቆሬያ
ውያን ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ[n] የሚያ
ስገባውን በር ይጠብቁ እንደ ነበር
ሁሉ፣ እነዚህም ወደ ቤተ መቅደሱ
የሚያስገባውን በር ይጠብቁ ነበር።
20በቀድሞ ጊዜ የበር ጠባቂዎቹ አለቃ
የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ነበረ፤ እግዚአ
ብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ። 21ወደ መገ
ናኛው ድንኳን የሚያስገባውን በር
የሚጠብቀው ደግሞ የሜሱላም ልጅ ዘካ
ርያስ ነበረ።
22መግቢያ በሮቹን እንዲጠብቁ የተመ
ረጡት ባጠቃላይ ሁለት መቶ ዐሥራ ሁለት
ነበሩ። እነርሱም በትውልድ ሐረጋቸው መሠ
ረት በሚኖሩባቸው መንደሮች ተቈጥረው
ተመዘገቡ፤ በር ጠባቂዎቹን በዚያ ቦታ ላይ
የመደቡአቸው ዳዊትና ባለ ራእዩ ሳሙኤል
ነበሩ። 23የማደሪያውን ድንኳን ማለትም
የእግዚአብሔርን ቤት የሚጠብቁትም እነ
ርሱና ዘሮቻቸው ነበሩ። 24በር ጠባቂዎቹም
በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜንና፣ በደቡብ
በሚገኙት በአራቱም ማዕዘኖች ላይ ነበሩ።
25ወንድሞቻቸውም በየመንደሮቻቸው ሆነው
በየጊዜው እየወጡ የጥበቃውን ሥራ ሰባት
ሰባት ቀን ያግዙአቸው ነበር። 26ሌዋውያን
የነበሩት አራቱ የበር ጠባቂ አለቆች ግን
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚገኙትን ክፍሎ
ችና ግምጃ ቤቶች በኀላፊነት ይጠብቁ
ነበር። 27የጥበቃውን ሥራ የሚያከናውኑት
እነርሱ በመሆናቸው የሚያድሩትም በዚ
ያው በእግዚአብሔር ቤት አካባቢ ነበረ፤ ጠዋት
ጠዋትም ደጆቹን የሚከፍቱት እነርሱ
ነበሩ። 28ከእነርሱም አንዳንዶቹ ለቤተ መቅ
ደሱ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን በኀላ
ፊነት ይጠብቁ ነበር፤ ዕቃዎቹም በሚገቡበ
ትና በሚወጡበት ጊዜ ሁሉ ይቈጥሩ ነበር፤
29ሌሎቹ ሌዋውያን ደግሞ ዕቃዎቹንና
የቤተ መቅደሱን ንዋያተ ቅድሳት፣ ዱቄቱን፣
የወይን ጠጁን፣ የወይራ ዘይቱን፣ ዕጣኑን፣ የሽ
ቱውን ቅመማ ቅመም እንዲጠብቁ ተመ
ድበው ነበር። 30ከካህናቱም አንዳንዶቹ
የሽቱውን ቅመማ ቅመም ይለውሱና ያዘጋጁ
ነበር። 31የቆሬያዊው የሰሎም በኵር ልጅ ሌዋ
ዊው ማቲትያ የቍርባኑን እንጀራ የመጋገር
ኀላፊነት ተሰጥቶት ነበር። 32በየሰንበቱ
ለሚዘጋጀው ገጸ ኅብስትም ኀላፊነቱ የተ
ሰጠው ከቀዓታውያን ወንድሞቻቸው መካ
ከል ለአንዳንዶቹ ነበር።
33የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለቆች የነበሩት
መዘምራኑ ደግሞ በቤተ መቅደሱ ክፍሎች
ውስጥ እንዲኖሩና ከሌላው ሥራ ሁሉ ነጻ
እንዲሆኑ ተደርጎ ነበር፤ ምክንያቱም ቀንና
ሌሊት የሚሠሩት ሥራ ነበራቸው።
34እነዚህ ሁሉ የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለ
ቆች ሲሆኑ፣ በትውልድ ሐረጋቸው መሠረት
ተመዘገቡ፤ የሚኖሩትም በኢየሩሳሌም ነበረ።

[n]19 በዚህ በቍጥር 21 እና 23 ላይ ቤተ መቅደሱን ያመለክታል።

9፥12 ዕዝ2፥38፤10፥22፤ ነህ10፥3፤ኤር21፥1፤38፥1
9፥15 2ዜና20፥14፤ነህ11፥22
9፥16 ነህ12፥28
9፥17 ቍ22፤1ዜና26፥1፤ 2ዜና8፥14፤31፥14፤ ዕዝ2፥42፤ነህ7፥45
9፥18 1ዜና26፥14፤ ሕዝ43፥1፤46፥1
9፥19 ኤር35፥4
9፥20 ዘኍ25፥11
9፥21 1ዜና26፥2፡14
9፥22 ቍ17፤1ሳሙ9፥9
9፥25 2ነገ11፥5
9፥26 1ዜና26፥22
9፥27 ዘኍ3፥38፤ ኢሳ22፥22
9፥29 ዘኍ3፥28፤ 1ዜና23፥29
9፥30 ዘፀ30፥25
9፥32 ዘሌ24፥5-8፤1ዜና23፥29፤ 2ዜና13፥11
9፥33 1ዜና6፥31፤25፥1-31፤2ዜና5፥12፤ መዝ134፥1

ሁዳ ዘሮች ወደ ኋላ በመቍጠር እስከ ፋሬስ ዛራና ሴሎም ያደርሳቸዋል። ይህም "ሴሎናውያን" የሚለው ቃል (ቍ5) "ሴሎማውያን" ተብሎ የሚነበብ ከሆነ (ዘኍ 26፥20) ማለት ነው። አሁንም ሴሎናውያን የሚለው እንዳለ የሚጠበቅ ከሆነ፣ የሚያመለክተው ሴሎን ይሆናል፤ ሴሎም የታወቀች ቅድስት ከተማ ነበረች (መሳ 18፥31፤ኤር 7፥12-14፤26፥9)።

*9፥10-13፤* የካህናቱ የስም ዝርዝር ከነህ 11፥10-14 ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይህም ቀደም ሲል ከነበረው የካህናቱ የትውልድ ሐረግ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ (6፥1-15፡50-53) የዚያን ጊዜዋ እስራኤል ታሪኳ ከቀድሞው የቀጠለ መሆኑን ያሳያል።

9፥15-16 *የአሳፍ... የኤዶታም፤* በተለያዩ የዜማ መሣሪያዎች የሚያገለግሉ የመዘምራን አለቆች ናቸው (6፥39፤16፥41)። የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በመቀጠልም የመዘምራኑን ስም (ም25) ከበር ጠባቂዎች አስቀድሞ (ም26) ይዘረዝራል።

9፥16 *በነጦፋውያን፤* የነህ12፥28 ማብ ይመ።

*9፥17-21፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ አራቱን የበር ጠባቂዎች ስም ሲያወሳ ነህምያ ግን (ነህ11፥19) ሁለቱን ስም ብቻ ነው የጠቀሰው። ንጉሡ የሚወጣ የሚገባበትን በር የመጠበቅ ኀላፊነት የተሰጠው ለዘበኞች አለቃ ነው (ሕዝ 46፥1-2)። የበር ጠባቂዎች ስም በም 26 እና በዕዝ 2፥42 ላይም በዝርዝር ተጽፎአል።እነዚህም የትውልድ ሐረጋቸውን ወደ ኋላ በመቍጠር እስከ ፊንሐስ ያደርሳቸዋል (ቍ20፤6፥4፤ዘኍ3፥32፤25፥6-13)።

*9፥22-27፤* ቀንና ሌሊት በሦስት ፈረቃ የሚጠበቁ ሃያ አራት የዘብ ቦታዎች ነበሩ። ለአንድ ሳምንት የሚመደቡትም ሰዎች ሰባ ሁለት ሲሆኑ ባጠቃላይ ለሦስት ሳምንት ጥበቃ የሚያስፈልገው የሰው ኀይል ከሞላ ጐደል ሁለት መቶ ዐሥራ ሁለት ነበር (26፥12-18)።

*9፥28-34፤* የሌዋውያኑ ኀላፊነት የቤተ መቅደሱን ምድረ ግቢ በመጠበቅና በሮቹን ጠዋት ጠዋት በመክፈት ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ በግቢው ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ክፍሎችና የዕቃ ቤቶቹን (23፥28፤ 26፥20-29) እንደዚሁም የተለያዩ መገልገያ ዕቃዎችን፣ ምግቦችን፣ የአላቂና የቋሚ ዕቃዎች ማከማቻ

## የሳኦል ትውልድ ሐረግ

9፥34-44 ተጓ ምብ - 1 ዜና 8፥28-38

[35]የገባዖን አባት[+] ይዒኤል የሚኖረው በገ
ባዖን ነበረ፤
የሚስቱም ስም መዓካ ይባላል:: [36]የበኵር
ልጁ ዓብዶን ሲሆን፣ የእርሱም ተከታ
ዮች ጹር፣ ቂስ፣ በአል፣ ኔር፣ ናዳብ፣
[37]ጌዶር፣ አሒዮ፣ ዘኩር፣ ሚቅሎት ነበሩ::
[38]ሚቅሎት ሳምአን ወለደ፤ እነርሱም
ከዘመዶቻቸው ጋር በኢየሩሳሌም አቅ
ራቢያ ይኖሩ ነበር::
[39]ኔር ቂስን ወለደ፤ ቂስ ሳኦልን ወለደ፤ ሳኦል
ዮናታን፣ ሜልኪሳን፣ አሚናዳብን፣ አስ
በኣልን[‡] ወለደ::
[40]የዮናታን ወንድ ልጅ፤
መሪበኣል[†] ነው፤ መሪበኣል ሚካን
ወለደ::
[41]የሚካ ወንዶች ልጆች፤
ፒቶን፣ ሜሌክ፣ ታሬዓ፣ አካዝ::
[42]አካዝ የዕራን ወለደ፤ የዕራም ዓሌሜ
ትን፣ ዓዝሞትን፣ ዘምሪን ወለደ፤ ዘም
ሪም ሞጻን ወለደ:: [43]ሞጻም ቢንዓን
ወለደ፤ ልጁ ረፋያ ነበረ፤ ልጁ ኤልዓሣ፣
ልጁ ኤሴል::
[44]ኤሴል ስድስት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤
ስማቸውም:-
ዓዝሪቃም፣ ቦክሩ፣ እስማኤል፣ ሸዓርያ፣
አብድዩ፣ ሐናን እነዚህ የኤሴል ወን
ዶች ልጆች ናቸው::

## ሳኦል ራሱን ገደለ

10፥1-12 ተጓ ምብ - 1ሳሙ 31፥1-13፤ 2ሳሙ 1፥4-12

**10** ከዚህ በኋላ ፍልስጥኤማውያን እስ
ራኤልን መውጋት ጀመሩ፤ እስራ
ኤላውያንም ከፊታቸው ሸሹ፤ ብዙዎች በጊ
ልቦዓ ተራራ ላይ ሞቱ:: [2]ፍልስጥኤማውያን
ሳኦልንና ልጆቹን ይበልጥ አሳደዱአቸው፤
የሳኦልንም ልጆች ዮናታንን፣ አሚናዳብ
ንና ሜልኪሳን ገደሉ፤ [3]ሳኦል በተሰለፈበት
ግንባር ውጊያው በረታ፤ ቀስተኞችም አግ
ኝተው አቈሰሉት::
[4]ሳኦል ጋሻ ጃግሬውን፣ "እነዚህ ሸለፈታ
ሞች መሳለቂያ እንዳያደርጉኝ ሰይፍህን
መዝዘህ ውጋኝ" አለው::
ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ስለ
ነበር አልደፈረም፤ ስለዚህ ሳኦል በገዛ ሰይፉ
ላይ ወድቆ ሞተ:: [5]ጋሻ ጃግሬውም ሳኦል
መሞቱን ሲያይ፣ እርሱም በሰይፉ ላይ
ወድቆ ሞተ:: [6]ስለዚህ ሳዖልና ሦስት ልጆቹ
ሞቱ፤ ቤተ ሰዎቹም ሁሉ አብረው ሞቱ::
[7]በሸለቆው ውስጥ የነበሩት እስራኤላው
ያን ሁሉ ሰራዊቱ እንደ ሸሸ፣ ሳኦልና ልጆ
ቹም እንደ ሞቱ ባዩ ጊዜ ከተሞቻቸውን
ለቀው ሸሹ፤ ፍልስጥኤማውያንም መጥተው
ከተሞቹን ያዙ::
[8]በማግሥቱ ፍልስጥኤማውያን የሞቱትን
ለመግፈፍ ሲመጡ፣ ሳኦልና ልጆቹ በጊ
ልቦዓ ተራራ ላይ ወድቀው አገኙአቸው::
[9]ሳኦልን ከገፈፉ፣ ራሱን ከቈረጡና መሣሪ
ያውንም ከወሰዱ በኋላ፣ ለአማልክቶቻቸ
ውና ለሕዝቡ የምሥራቹን እንዲነግሩ ወደ
መላው የፍልስጥኤም ምድር መልክተኞ
ችን ላኩ:: [10]ከዚያም መሣሪያውን በአማል
ክቶቻቸው ቤተ ጣዖት አኖሩ፤ ራሱንም በዳ
ጎን ቤተ ጣዖት ውስጥ አንጠለጠሉት::
[11]የኢያቢስ ገለዓድ ነዋሪዎች ሁሉ ፍልስ
ጥኤማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን በሰሙ
ጊዜ፣ [12]ብርቱ የሆኑ ሰዎች ሄደው የሳኦል
ንና የልጆቹን ሬሳ አንሥተው ወደ ኢያቢስ
አመጡ፤ ዐጽማቸውንም ኢያቢስ ውስጥ
በሚገኘው ትልቁ ዛፍ ሥር ቀበሩ፤ ከዚያም
ሰባት ቀን ጾሙ::
[13]ሳኦል *እግዚአብሔርን* ስላልታዘዘ ሞተ፤
*የእግዚአብሔርን* ቃል አልጠበቀም፤ ይል
ቁንም ከሙታን ጠሪ ምክርን ጠየቀ፤ [14]ይህን
*ከእግዚአብሔር* አልጠየቀም፤ ስለዚህ *እግዚአ
ብሔር* ገደለው፤ መንግሥቱንም ወደ እሴይ
ልጅ ወደ ዳዊት እንዲተላለፍ አደረገ::

## ዳዊት በእስራኤል ላይ ነገሠ

11፥1-3 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 5፥1-3

**11** እስራኤል ሁሉ በኬብሮን ወደ ዳዊት
መጥተው እንዲህ አሉት፤"እነሆ፤
እኛ የገዛ ሥጋህና ደምህ ነን፤ [2]በቀደመው
ዘመን ሳኦል ንጉሥ ሆኖ ሳለ እስራኤልን
ወደ ጦርነት የምትመራ አንተ ነበርህ፤ *እግ
ዚአብሔር* ስምላክህም፣ 'ሕዝቤን እስራኤልን

9፥35 1ዜና8፥29
9፥39 1ሳሙ9፥1፤ 13፥22፤ 2ሳሙ2፥8፤1ዜና8፥33
9፥40 2ሳሙ4፥4
10፥10 መሳ16፥23
10፥11 መሳ21፥8
10፥13 ዘሌ19፥31፤20፥6፤ ዘዳ18፥9-14፤ 1ሳሙ 13፥13፤ 2ሳሙ1፥11፤ ዜና5፥25
10፥14 1ሳሙ13፥14፤ 1ዜና12፥23
11፥1 ዘፍ13፥18፤23፥19፤ 1ዜና9፥1
11፥2 1ሳሙ18፥5:16፤1ዜና 5፥2፤መዝ78፥1፤ ማቴ2፥6

[+]35 *አባት ማለት፣ የማኅበረሰብ መሪ ወይም፣ የጦር መሪ ማለት ነው::*
[‡]39 *ኢሽበሼት* በመባልም ይታወቃል::
[†]40 *ሜፊቦስቴ* በመባልም ይታወቃል::

ክፍሎችን (28፥13-18፤ዕዝ1፥9-11) መጠበቅ እንዲሁም ዕቃዎችን የማቅረብና የማሳመር ኀላፊነት ሌዋውያኑን የሚመለከት ነበር:: በተጨማሪም የሚጋገረውን ኃገረው የሚያዘጋጁትም (ዘጸ 25፥30፤ ሌዋ 2፥5-7፤7፥9) እነርሱ ነበሩ:: መልካም መዓዛ ያለ ውን ዘይትና ሽቶዎች ግን የሚያዘጋጁት ካህናቱ ብቻ ነበሩ::

*9፥35-44፤* እዚህ ላይ የሳኦል የትውልድ ሐረግ እንዳለ ተደግሞ ተጽፎአል (8፥29-38 ይመ)፤ ይህ የሆነበትም ምክንያት የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በም10 ላይ መጻፉ ለፈለገው ታሪክ አጭር መግቢያ እንዲሆነው አስቦ ነው::

*10፥2፤* በጦርነት ውስጥ እንዴትና ለምን ንጉሡን እንዳሳ ደዱት ለማስተዋል የ1ነገ 22፥31 ማብ ይመ::

10፥6 *ሦስት ልጆቹ፤* ቍ2 ይመ (አሽቦሼት ግን ከሞት አምልጦአል የ1ሳሙ 31፥2 ማብ ይመ):: ቤተ ሰዎቹም ሁሉ፤ ሦስት ወንዶች ልጆቹንና ሹማምቱን ለማለት እንጂ ዘሮቹን በሙሉ ማለቱ አይደለም (8፥33-34 እና ማብ ይመ፤ 1ሳሙ31፥6)::

*10፥13-14፤* እነዚህ ቍጥሮች በመጽሐፈ ሳሙኤል ላይ ከተጻፈው ታሪክ ጋር አንድ አይደሉም:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ቍጥሮቹን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያካተተው፣ ወዲያውኑ ስለ ሚፈጸመው የአጻፉ ቅጣት ለመናገር ካለው ትልቅ ፍላጎት አኳያ ነው:: (በመግቢያው ላይ "ዐላማና መሪ ሐሳቡ" የሚለውን ይመ):: ሙታን ጠሪዎችን መጠየቅ የተከለከለ ነው (ዘዳ 18፥9-14)፤ ይህም በሳኦል ላይ ሞት አስከትሎበታል:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የጻፈው መጽሐፈ ሳሙኤልንና መጽሐፈ ነገሥትን ጠንቅቆ (አሳምሮ) ለሚ ያውቃቸው አንባቢ መሆኑንና እርሱም ቢሆን ይህንን እንደ ሚያውቅ መገንዘብ ይቻላል:: እዚህ ላይ ሳኦል የእንዶሯን ሙታን ጠሪ ምክር ስለመጠየቁ፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ተመልክቶ አል:: ሆኖም የድርጊቱን ዝርዝር አፈጻጸም በድጋሚ አልጻፈም (1 ሳሙ 28 ይመ)::

*11፥1-2 ዜና 9፥3፤* በመግቢያው ላይ "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል የሚለውን ይመ::

የምትጠብቅ አንተ ነህ፤ ንጉሣቸውም ትሆና
ለህ' ብሎሃል"።
3የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ ንጉሥ
ዳዊት ወዳለበት ወደ ኬብሮን መጡ፤ ዳዊ
ትም በኬብሮን *በእግዚአብሔር* ፊት ከእነ
ርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባ። *እግዚአብሔር*
በሳሙኤል አማካይነት በሰጠው ተስፋ መሠ
ረት ዳዊትን ቀብተው በእስራኤል ላይ አነ
ገሡት።

## ዳዊት ኢየሩሳሌምን ድል አደረገ

11፥4-9 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 5፥6-10

4ዳዊትና እስራኤላውያን ሁሉ ኢያቡስ
ወደምትባለው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። በዚ
ያም የሚኖሩ ኢያቡሳውያን 5ዳዊትን "ወደ
ዚህ ፈጽሞ አትገባም" አሉት፤ ዳዊት ግን
የጽዮንን ምሽግ ያዘ፤ እርሷም የዳዊት ከተማ
ናት።
6ዳዊትም፣ "ኢያቡሳዊያንን ቀድሞ የሚ
ወጋ ሰው የሰራዊቱ አዛዥ ይሆናል" አለ፤
ስለዚህ የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ በመጀመሪያ
ወጣ፤ እርሱም አዛዥ ለመሆን በቃ።
7ከዚያም ዳዊት መኖሪያውን በዐምባዪቱ
ውስጥ አደረገ፤ ከዚህም የተነሣ የዳዊት
ከተማ ተባለች። 8ዳዊትም ከሚሎ ጀምሮ
የከተማዪቱን ዙሪያ ቅጥር ሠራ፤ ኢዮአብ
ደግሞ የቀረውን የከተማዪቱን ክፍል መልሶ
ሠራ። 9*እግዚአብሔር* ጸባኦት ከእርሱ ጋር
ስለ ነበር ዳዊት በየጊዜው እየበረታ ሄደ።

## የዳዊት ኀያላን ሰዎች

11፥10-41 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 23፥8-39

10የዳዊት ኀያላን ሰዎች አለቆች እነዚህ
ናቸው፤ እነርሱም *እግዚአብሔር* በሰጠው
ተስፋ መሠረት መንግሥቱ በምድሪቱ ሁሉ
ትሰፋ ዘንድ ከሌሎቹ እስራኤላውያን ጋር
ሆነው ለመንግሥቱ ብርቱ ድጋፍ ሰጡ። 11የዳ
ዊት ኀያላን ሰዎች ስም ዝርዝር ይህ ነው፤
ሐክሞናዊው ያሾብዓም የጦር መኮንኖቹ
አለቃ' ነበረ፤ እርሱም ጦሩን አንሥቶ በአ
ንድ ጊዜ ሦስት መቶ ሰው ገደለ።
12ከእርሱም ቀጥሎ ከሦስቱ ኀያላን አንዱ
የሆነው የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ አልዓዛር
ነው፤ 13እርሱም ፍልስጥኤማውያን ለጦርነት
በተሰበሰቡ ጊዜ በፈስደሚም ከዳዊት ጋር
አብሮ ነበረ፤ ገብስ በሞላበት የእርሻ ቦታ
ወታደሮቹ ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ፤

11፥3 1ሳሙ 16፥1-13
11፥4 ዘፍ10፥16፤15፥18-21፤ኢሱ3፥10፤15፥8
11፥6 2ሳሙ 2፥13
11፥8 2ሳሙ 5፥9፤2ዜና32፥5
11፥9 አስ 9፥4
11፥10 ቍ11፤1ዜና12፥23
11፥11 2ሳሙ 17፥10
11፥14 ዘፀ14፥30፤ 1ሳሙ 1113
11፥15 1ዜና14፥9፤ ኢሳ 17፥5
11፥16 2ሳሙ 5፥17
11፥18 ዘጸ12፥16
11፥20 1ሳሙ 26፥6
11፥22 ኢሱ15፥21፤ 1ሳሙ 17፥36
11፥23 1ሳሙ 17፥7

14ይሁን እንጂ በእርሻው መካከል ቦታ
ይዘው ስለ ነበረ ፍልስጥኤማውያንን ገደሉ፤
*እግዚአብሔርም* ታላቅ ድል ሰጣቸው።
15ከፍልስጥኤማውያን ሰራዊት ጥቂቱ በራ
ፋይም ሸለቆ ሰፍሮ ሳለ፣ ከሠላሳዎቹ አለ
ቆች ሦስቱ ዳዊትን ለመገናኘት በዓዶላም
ዋሻ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ዐለቱ ወረዱ።
16በዚያን ጊዜ ዳዊት በምሽጉ ውስጥ ነበረ፤
የፍልስጥኤማውያን ሰራዊት ደግሞ በቤተ
ልሔም ነበረ። 17ዳዊትም ውሃ ፈልጎ ነበ
ርና፣ "ከቤተ ልሔም በር አቅራቢያ ከሚገ
ኘው ጕድጓድ የምጠጣው ውሃ ማን ባመጣ
ልኝ!" አለ። 18በዚህ ጊዜ ሦስቱ የፍልስጥኤ
ማውያንን ሰራዊት ጥሰው በማለፍ በቤተ
ልሔም በር አጠገብ ከሚገኘው ጕድጓድ
ውሃ ቀድተው ለዳዊት አመጡለት፤ እርሱ
ግን ሊጠጣው ስላልፈለገ *በእግዚአብሔር*
ፊት አፈሰሰው፤ 19ከዚያም "ይህን ከማድረግ
እግዚአብሔር ይጠብቀኝ፤ ይህ በሕይወታቸው
ቈርጠው የሄዱትን የእነዚህን ሰዎች ደም
እንደ መጠጣት አይደለምን?" አለ። ይህን
ለማምጣት በሕይወታቸው ቈርጠው ስለ
ነበር፣ ዳዊት ሊጠጣው አልፈለገም።
ሦስቱ ኀያላን ሰዎች የሠሩት ይህንን ነበር።
20የኢዮአብ ወንድም አቢሳ የሦስቱ
አለቃ ነበረ። እርሱም ጦሩን አንሥቶ
ሦስት መቶ ሰዎች ገደለ፤ ከዚህም የተነሣ
እንደ ሦስቱ ሁሉ ዝነኛ ሆነ። 21ከሦስቱ
አንዱ ሆኖ ባይቈጠርም እንኳ፣ እጥፍ ክብር
አገኘ፤ አዛዣቸውም ሆነ።
22ከቀብስኤል የመጣውና ታላቅ ጀብዱ የሠ
ራው የዮዳሄ ልጅ በናያስ ብርቱ ተዋጊ
ነበረ። እርሱም እጅግ የታወቁ ሁለት የሞ
አብ ሰዎችን ገደለ። እንዲያውም አንድ ጊዜ
በረዶ ምድርን በሸፈነበት ቀን ወደ አንድ
ጕድጓድ ወርዶ አንበሳ ገደለ። 23ደግሞም
ቁመቱ አምስት ክንድ[ፕ] የሆነ አንድ ግብፃዊ
ገደለ፤ ግብፃዊው የሸማኔ መጠቅለያ የመ
ሰለ ጦር በእጁ ቢይዝም፣ በናያስ ግን
ቆመጥ ይዞ ገጠመው፤ ከግብፃዊው እጅ
ጦሩን ነጥቆ በገዛ ጦሩ ገደለው። 24የዮዳሄ
ልጅ በናያስ የፈጸመው ጀብዱ ይህ ነበር፤
እርሱም እንደ ሦስቱ ኀያላን ዝነኛ ሆነ።
25ከሠላሳዎቹም ይልቅ የበለጠ ክብር ተጐና

'11 *ሠላሳ* ወይም እንደ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች፣ *ሦስት* (እንዲሁም 2ሳሙ 23፥8 ይመ) ይላሉ።
[ፕ]23 2.3 ሜትር ያህል ነው።

*11፥1-3፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ "እስራኤል ሁሉ" (ቍ 1) ለዳዊት በሰጠው ሕዝባዊ ድጋፍ ላይ ትኵረት ማድረጉን ለማመልከት በሌላ መልክ ከማቅረቡ በስተቀር በዚህ ስፍራ የተዘገበው በ2ሳሙ 5፥1-3 ላይ ካለው ጋር የሚመሳሰል ነው፤ ኢያቡስ ከመሞቱ አስቀድሞና ከስሜኑ ነገዶች ጋር ቃል ኪዳን ከመደረጉ በፊት (3፥4፤29፥27)፣ ዳዊት በኬብሮን መንገሡን የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሁለት ጊዜ ያወሳል። በመጽሐፉ የትረካ ክፍል ውስጥ እነዚህ ድርጊቶች አልተካተቱም። እጅግ የሚያስደንቀው ግን በ2ሳሙ 5፥4-5 ላይ የተወሳው ታሪክ እዚህ ላይ ሳይገባ መቅረቱ ነው። ይልቁንም ጸሓፊው ዳዊት ኢየሩሳሌምን ወዲያውኑ ድል አድርጎ ከያዘ በኋላ ወዲያው በማስከተል በመላው እስራኤል ላይ መንገሡን በሥዕላዊ መልክ አሳምሮ አስቀምጦታል (በመግቢያው ላይ "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል" የሚለውን ይመ።

*11፥4-9፤* 2ሳሙ 5፥6-10 እና ማብ ይመ። በቍ 4 ላይ "እስራኤል ሁሉ" የሚለው ሐረግ በ2 ሳሙ 5፥6 ላይ "ንጉሡና ሰዎቹ" የሚለውን ለመተካት ገብቶአል።

*11፥10-41(ሀ)፤* 2ሳሙ 23፥8-39 እና ማብ ይመ። ይህ የዳዊት ኀያላን ሰዎች ስም ዝርዝር በመጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ የምናገኘው በዘመነ መንግሥቱ መጨረሻ አካባቢ ነው። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን የስም ዝርዝሩን ወደ ዘመነ መንግሥቱ መጀመሪያ ላይ በማምጣት አስፋፍቶ ጽፎታል (11፥41ለ-12፥40)፤ "እስራኤል ሁሉ" የሚለውን ሐረግ የዳዊትን ንጉሥነት አጕልቶ (ከፍ አድርጎ) እንዲያሳይ ተጠቅሞበታል (ቍ 10)።

*11፥12-14፤* 2ሳሙ 23፥9ለ-11ሀ ይመ።

*11፥15-19፤* ኀያላኑ በሕይወታቸው ቈርጠው ሄደው ያመጡለትን ውሃ ለመጠጣት የተገባ ሰው አለመሆኑን በማ

ኢፊ፤ ይሁን እንጂ ከሦስቱ አንዱ አልነበረም፤
ዳዊትም የክብር ዘቡ አዣዥ አደረገው።
26 ኀያላኑም እነዚህ ነበሩ፤
የኢዮአብ ወንድም አሣሄል፣
የቤተ ልሔሙ የዱዲ ልጅ ኤልያናን፣
27 ሃሮራዊው ሳሞት፣ ፊሎናዊው ሴሌድ፣
28 የቴቁሔ ሰው የሆነው የዒስካ ልጅ፣
ዒራስ፣የዓናቶቱ ሰው አቢዔዜር፣
29 ኩሳታዊው ሴቤካይ፣
አሆሃዊው ዔላይ፣
30 ነጦፋዊው ማህራይ፣
የነጦፋዊው የበዓና ልጅ ሔሌድ፣
31 ከብንያም ወገን የጊብዓ ሰው የሆነው
የሪባይ ልጅ ኤታይ፣
ጲርዓቶናዊው በናያስ፣
32 የገዓስ ሸለቆዎች ሰው የሆነው ኡሪ፣
ዓረባዊው አቢኤል፣
33 ባሕሩማዊው ዓዝሞት፣
ሰዓልቦናዊው ኤሊያሕባ፣
34 የጊዞናዊው የአሳን ልጆች፣
የሃራራዊው የሻጌ ልጅ ዮናታን፣
35 የሃራራዊው የሳኮር ልጅ አሒአም፣
የኡር ልጅ ኤሊፋል፣
36 ምኬራታዊው ኦፌር፣
ፍሎናዊው አኪያ፣
37 ቀርሜሎሳዊው ሐጽሮ፣
የኤዝባይ ልጅ ነዕራይ፤
38 የናታን ወንድም ኢዮኤል፣
የሃግሪ ልጅ ሚብሐር፣
39 አሞናዊው ጼሌቅ፣
የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ጋሻ ጃግሬ
ቤሮ ታዊው ነሃራይ፣
40 ይትራዊው ዒራስ፣
ይትራዊው ጋሬብ፣
41 ኬጢያዊው ኦርዮ፣
የአሕላይ ልጅ ዛባድ፣
42 የሮቤላዊው የሺዛ ልጅ ዓዲና፤
እርሱም የሮቤላውያንና አብረውት
ለነበሩት የሠላሳ ሰዎች አለቃ ነበረ።
43 የማዕካ ልጅ ሐናን፣
ሚትናዊው ኢዮሣፍጥ፣
44 አስታሮታዊው ያዝያ፣ የአሮዔራዊው
የኮታም ልጆች ሻማና ይዒኤል፣
45 የሺምሪ ልጅ ይዲኤል፣
ወንድሙም ቴጻዊው ዮሐ፣
46 መሐዋዊው ኤሊኤል፣
የኤልነዓም ልጆች ይሪባይና ዮሻውያ፣
ሞዓባዊው ይትማ፣
47 ኤሊኤል፣ ዖቤድና ምጸባዊው
የዕሢኤል።

11፥26 2ሳሙ 2፥18
11፥27 1ዜና 27፥8
11፥28 1ዜና 27፥12
11፥29 ሳሙ 21፥18
11፥31
መሳ 12፥13፤1ዜና 27፥14
11፥41
2ሳሙ 11፥6፤1ዜና 2፥36
11፥44 ዘዳ 1፥4

12፥1 ኢሱ 15፥31
12፥2
መሳ 3፥15፤2ሳሙ 3፥19
12፥4 ኢሱ 15፥36
12፥7 ኢሱ 15፥58
12፥8
ዘፍ 30፥11፤2ሳሙ 2፥1
8፤17፥10
12፥14
ዘሌ 26፥8፤
ዘዳ 32፥30
12፥15 ኢሱ 3፥15
12፥16 2ሳሙ 3፥19

## ከዳዊት ጋር የተቀላቀሉ ተዋጊዎች

12 ዳዊት ከቂስ ልጅ ከሳኦል ፊት ሸሽቶ
በጺቅላግ ሳለ ወደ እርሱ የመጡት
ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ እነርሱም በጦርነቱ
ላይ ከረዱት ተዋጊዎች መካከል ነበሩ።
2 ሰዎቹ ቀስተኞች ሲሆኑ፣ በቀኝም ሆነ በግራ
እጃቸው ፍላጻ መወርወርና ድንጋይ መወን
ጨፍ የሚችሉ ነበሩ፤ እነርሱም ከብንያም
ነገድ የሆነው የሳኦል ሥጋ ዘመዶች ነበሩ፤
3 አለቃቸው አሒዔዝር ነበረ፤ ከእር
ሱም በኋላ ኢዮአስ ነበረ፤ ሁለቱም
የጊብዓዊው የሸማዓ ልጆች ነበሩ፤ የዓዝ
ሞት ልጆች ይዝኤልና ፋሌጥ፤ በራኪያ፣
ዓናቶታዊው ኢዩ፤ 4 ገባዖናዊው ሰማያስ
ከሠላሳዎቹ መካከል ኀያልና የሠላ
ሳዎቹም መሪ ነበረ፤ ኤርምያስ፣ የሕዚ
ኤል፣ ዮሐናን፣ ገድሮታዊው ዮዛባት፣
5 ኤሉዛይ፣ ኢያሪሙት፣በዓልያ፣ ሰማራያ፣
ሐሩፋዊው ሰፋጥያስ፣ 6 ቆሬያውያኑ
ሕልቃና፣ ይሺያ፣ ዓዛርኤል፣ ዮዛር፣
ያሾብዓም፤ 7 የጌዶር ሰው ከሆነው ደግሞ
የይሮሐም ልጆች ዮዔላና ዝባድያ።

8 ዳዊት በምድረ በዳ በሚገኘው ምሽጉ
ውስጥ ሳለ፣ ከጋድ ነገድ የሆኑ ሰዎች መጥ
ተው የእርሱን ሰራዊት ተቀላቀሉ፤ እነር
ሱም ለውጊያ የተዘጋጁ ጋሻና ጦር ለመያዝ
የሚችሉ ብርቱ ተዋጊዎች ነበሩ፤ ፊታቸው
እንደ አንበሳ ፊት የሚያስፈራና በየተራራውም
ላይ እንደሚዘል ሚዳቋ ፈጣኖች ነበሩ።
9 የእነዚህም አለቃ ዔጼር ነበረ፤
ሁለተኛው አዛኸ አብድዩ፣ ሦስተኛው
ኤልያብ፣
10 አራተኛው መስመና፣ አምስተኛው ኤር
ምያስ፣
11 ስድስተኛው ዓታይ፣ ሰባተኛው ኢሊኤል፣
12 ስምንተኛው ዮሐናን፣
ዘጠነኛው ኤልዛባድ፣
13 ዐሥረኛው ኤርምያስ፣ ዐሥራ አንደ
ኛው መክበናይ።
14 እነዚህ ጋዳውያን የጦር አዛዦች ነበሩ፣
ከእነርሱ ታናሽ የሆነው እንደ መቶ፣ ታላቅ
የሆነው ደግሞ እንደ ሺህ አለቃ ይቈጠር
ነበር። 15 በመጀመሪያው ወር የዮርዳኖስ
ወንዝ ከአፍ እስከ ገደፍ ሞልቶ ሳለ፣ ወን
ዙን ተሻግረው በስተ ምሥራቅና በስተ ምዕ
ራብ ሸለቆዎች ይኖሩ የነበሩትን ሁሉ ከዚያ
ያባረሩት እነዚህ ሰዎች ነበሩ።
16 ሌሎች ከብንያምና ከይሁዳም ወገን የሆኑ
ሰዎች ዳዊት ወደሚገኝበት ምሽግ መጡ።

መን የመጠጥ ቍርባን አድርጎ ለእግዚአብሔር አቀረበው (ዘፍ 35፥14፤2 ነገ 16፥13፤ ኤር 7፥18፤ሆሴ 9፥4 ይመ)።

*11፥41(ለ)-12፥40፤* የቍ 10-41 (ሀ)ን ማብ ይመ። በ2ሳሙ 23 የተጻፈው የስም ዝርዝር የሚዘጋው በኬጢያዊው በኡሪያ ስም ነው (2ሳሙ 11)። በተጨማሪ ስለ ተጻፉት ስለ ሌሎቹ ስሞች ግን ምንም አይታወቅም። አጽንዖቱ "እስራኤል ሁሉ" ለሚለው ዋና ሐሳብ ድጋፍ መስጠቱን እንደቀጠለ ነው፤ የሳኦል ቤተ ዘመዶች እንኳ ገና ሳኦል ከመሞቱ በፊት ለዳዊት ንጉሥነት ሕጋዊ ነት ዕውቅና ሰጥተውት ነበር (12፥1-7፤16-18:23:29)።

*12፥11* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ታሪኩን የሚያነቡት ሰዎች በጺቅላግ ስለ ተፈጸመው ድርጊት ዕውቀት እንዳላቸው ያምናል (1ሳሙ 27)፤ ቍ 19-20 ይመ።

*12፥8-15፤* የጋድ ሰዎች ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ (በስተምሥ ራቅ) የመጡ ነበሩ። በሰሜኑ ክፍል የቀለጠው በረዶ በዓመቱ የመጀመሪያ ወር (ከመጋቢት -ሚያዝያ ማለት ነው) ላይ እነርሱ በሚሻገሩበት ጊዜ የዮርዳኖስን ወንዝ ሞልቶ ወደ ዳር እንዲፈስ አድርጎት ነበር (ቍ15)፤ ይህ ሁኔታ የተፈጸመበት ትክክለኛ

17ዳዊትም እነዚህን ሰዎች ሊቀበል ወጥቶ
እንዲህ አላቸው፤ “የመጣችሁት ልትረዱኝና
በሰላም ከሆነ፣ ከእኔ ጋር እንድትሰለፉ ልቀ
በላችሁ ዝግጁ ነኝ፤ ነገር ግን እጄ ከበደል
ንጹሕ ሆኖ ሳለ፣ ለጠላቶቼ አሳልፋችሁ
ልትሰጡኝ ከሆነ፣ የአባቶቻችን አምላክ ይመ
ልከተው፤ ይፍረደውም”።
18ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በሠላ
ሳዎቹ አለቃ በዓማሣይ ላይ ወረደ፤ እር
ሱም እንዲህ አለ፤
“ዳዊት ሆይ፤ እኛ የአንተ ነን፤
የእሴይ ልጅ ሆይ፤ እኛ ከአንተ ጋር ነን፤
ሰላም ፍጹም ሰላም ለአንተ ይሁን፤
አንተን ለሚረዱም ሁሉ ሰላም ይሁን፤
አምላክህ ይረዳሃልና”።
ስለዚህ ዳዊት ተቀበላቸው፤ የሰራዊቱም
አለቃ አደረጋቸው።
19ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተባብሮ
ሳኦልን ለመውጋት በሄደ ጊዜ፣ ከምናሴ
ነገድ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ከድተው ከዳዊት
ሰራዊት ጋር ተቀላቀሉ። እርሱ ግን ርዳታ
አላደረገላቸውም፤ ምክንያቱም የፍልስጥኤ
ማውያን ገዦች ምክር ካደረጉ በኋላ እንዲህ
ሲሉ ልከውት ነበር፤ “ከድቶ ወደ ጌታው
ወደ ሳኦል ቢሄድ እኛን ያስጨርሰናል”።
20ዳዊት ወደ ጺቅላግ በሄደ ጊዜ ከድተው
ወደ እርሱ የተቀላቀሉ የምናሴ ነገድ ሰዎች
እነዚህ ነበሩ፤ ዓድና፣ ዮዛባት፣ ይዲኤል፣
ሚካኤል፣ ዮዛባት፣ ኤሊሁ፣ ጺልታይ፤ እነ
ዚህ በምናሴ ግዛት ሳሉ የሻለቆች ነበሩ።
21ሁሉም ብርቱ ተዋጊዎችና በዳዊትም ሰራ
ዊት ውስጥ አዛዦች ስለ ነበሩ፣ አደጋ ጣዮ
ችን በመውጋት ረዱት። 22ሰራዊቱም እንደ
እግዚአብሔር ሰራዊት^ እስኪሆን ድረስ፣ ዳዊ
ትን ለመርዳት በየዕለቱ ብዙ ሰዎች ይጎ
ርፉ ነበር።

## ሌሎችም በኬብሮን የዳዊትን ሰራዊት ተቀላቀሉ

23እግዚአብሔር ለዳዊት በገባለት ቃል
ኪዳን መሠረት የሳኦልን መንግሥት አንሥ
ተው ለእርሱ ለመስጠት ዳዊት ወደሚገኝ
በት ወደ ኬብሮን የመጡት ሰዎች ቍጥር
ይህ ነው፤
24ጋሻና ጦር አንግበው ለጦርነት የተዘጋ
ጁት የይሁዳ ሰዎች ስድስት ሺህ ስም
ንት መቶ፤
25ከስምዖን ነገድ ለጦርነት ዝግጁ የሆኑ
ሰባት ሺህ አንድ መቶ።
26ከሌዊ ነገድ አራት ሺህ ስድስት መቶ፤
27የአሮን ቤተ ሰብ መሪ የሆነውን ዮዳ
ሄን ጨምሮ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ
ሰዎች፤ 28ወጣቱ ብርቱ ተዋጊ ጻዶቅና
ከቤተ ሰቡ ሃያ ሁለት የጦር አለቆች፤
29የሳኦል ሥጋ ዘመድ የሆኑ የብንያም ሰዎች
ሦስት ሺህ፤ ከእነዚህም አብዛኞቹ እስ
ከዚያች ጊዜ ድረስ ለሳኦል ቤት ታማኝ
ነበሩ፤
30ከኤፍሬም ሰዎች በጐሣዎቻቸው ዘንድ
ታዋቂ የሆኑ ብርቱ ተዋጊዎች ሃያ ሺህ
ስምንት መቶ፤
31ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ዐሥራ ስምንት
ሺህ ሰዎች፤ እነርሱም ዳዊትን ለማን
ገሥ በየስማቸው ተጽፈው የመጡ ነበሩ።
32ዘመኑን የተረዱና እስራኤላውያንም ምን
ማድረግ እንደሚገባቸው የተገነዘቡ የይ
ሳኮር ሰዎች ሁለት መቶ አለቆች፤
በእነርሱም ሥር ሆነው የሚታዘዙ ዘመ
ዶቻቸው።
33ልምድ ያላቸው፣ በሁሉም ዐይነት መሣ
ሪያ ለመዋጋት የተዘጋጁና ዳዊትን
ለመርዳት የመጡት መንታ ልብ የሌ
ላቸው የዛብሎን ሰዎች ሃምሳ ሺህ፤
34ከንፍታሌም ሰዎች አንድ ሺህ የጦር
አለቆች፤ ከእነርሱም ጋር ጋሻና ጦር
የያዙ ሠላሳ ሰባት ሺህ ሰዎች፤
35ከዳን ሰዎች ለጦርነት የተዘጋጁ ሃያ
ስምንት ሺህ ስድስት መቶ፤
36ከአሴር ሰዎች ልምድ ያላቸውና ለጦርነት
የተዘጋጁ ወታደሮች አርባ ሺህ፤
37ከምሥራቅ ዮርዳኖስ ከሮቤል፣ ከጋድና
ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ልዩ ልዩ ዐይ
ነት መሣሪያ የታጠቁ አንድ መቶ ሃያ
ሺህ ሰዎች።
38እነዚህ ሁሉ በሰራዊቱ ውስጥ ለማገልገል

12፥18 መሳ3፥10፤1ሳሙ25፥5-6፤2ሳሙ17፥25፤1ዜና28፥12፤2ዜና15፥1፤፥20፥14፤24፥20
12፥19 1ሳሙ29፥2-11
12፥20 1ሳሙ27፥6
12፥23 1ሳሙ16፥1፤ 2ሳሙ3፥4፤ 1ዜና10፥14፤11፥10
12፥28 1ዜና6፥8፤15፥11፤16፥39፤27፥17
12፥29 2ሳሙ2፥8-9፤3፥19
12፥32 አስ1፥13
12፥38 1ዜና9፥1

^22 ወይም፣ *ታላቅና ኀያል ሰራዊት*

ወቅትም ዳዊት በሙት ባሕር አካባቢ በተንከራተተበት ጊዜ ነበር (1 ሳሙ 23፥14፤24፥1፤25፥1፤26፥1)።

*12፥23-37፤* “እስራኤል ሁሉ” የሚለው አጽንዖት እዚህም ላይ ይቀጥላል (ቍ 38)። የዐሥራ ሦስት ነገዶች ስም የተጠቀሰ ቢሆንም፣ የተለመደውን “ዐሥራ ሁለት ቍጥር” ለመጠበቅ ሲባል (የ2፥1-2 ማብ ይመ) የመጨረሻዎቹን አጣምሮአቸዋል። ብዙ ቍጥር ያለውን የሰው ኀይል ለዳዊት የላኩት (ቍ 33-37) በሰሜን ሩቅና ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ በስተምሥራቅ የሚገኙት ነገዶች ናቸው፤ እነዚህም ዳዊት በይሁዳና በብንያም ምድር ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎቹም ነገዶች ከፍተኛ ድጋፍ እንዲያገኝና ኀይሉን በማጠናከር ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እዚህ ላይ የተጠቀሰው ቍጥር እጅግ ከፍ ያለ ይመስላል። በመሠረቱ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሁለት አመለካከቶች ቀርበዋል፤ እነዚህም (1)ከፍተኞቹን ቍጥሮች በመግለጽ አነስተኛውን ቍጥር ለማግኘት ይቻላል የሚል ነው። በዕብራይስጡ “አንድ ሺህ” የሚለው ቃል በአንድ ነገድ ውስጥ የራሱ የሆነ አዛዥ ያለውን አንዱን ክፍል ያመለክታል (13፥1፤ እንዲሁም ዘኍ 31፥14፤48፡52፡54 ይመ)። በዚህ ሁኔታ ሲታይ ቍጥሮቹ መነበብ ያለባቸው እንደ ጠቅላላ ቍጥር ተወስደው ሳይ ሆን፣ የጦር አዛዦችን ቍጥር እንደሚወክሉ ሆነው ነው፤ ለም ሳሌ ከይሁዳ 6,800 (ቍ 24) ሲል አንድም ስድስት የአንድ ሺህ ወታደር አዛዦችና ስምንት የመቶ ወታደር አዛዦች (13፥1 ይመ) ማለት ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ስድስት የሺህ ስምንት መቶ ወታደር አዛዦች ማለትም ሊሆን ይችላል። ቍጥሮቹን በዚህ መልክ መቀነሱ ነገሩን ከ13፥1 ጋር፣ ከሳዶቅ ቤተ ሰብ አዛዦች ስም ዝርዝር ጋር (ቍ 28)፣ እንዲሁም ከይሳኮር ነገድ ጋር ለማያያዝ ያመቻል (ቍ 32)። ቍጥሮቹን እንዳሉ በቀጥታ ወስዶ መደመሩ ለበዓሉ ግብዣ በኬብሮን የተገኘውን ሰው ብዛት (ቍጥር) ወደ ሦስት መቶ አርባ ሺህ ስምንት መቶ ከፍ እንዲያደርገው ያስገድዳል። (2) ሌላው አመለካከት ደግሞ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ “እንደ እግዚአብሔር ሰራዊት” ብሎ ብዛቱን በማጋነን ከፍ ያደረገውን (ቍ 22) መቀበልና በዚሁ መልክ ማየቱ ነው። ይህም አመለካከት የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የዳዊትን ክብርና ከዚያ የሚቀጥለውን የግብዣውን ታላቅነት ለማሳየት ያደረገውን ጥረት የተሳካ ያደርገዋል።

*12፥38-40፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የዳዊትን ገጽታ በሚያሳይበት ጊዜ በተስፋ ስለሚጠበቀው መሲሕ የነበረው አመለካከት

ልገል ፈቃደኞች የሆኑ ተዋጊዎች ናቸው፤
ወደ ኬብሮን የመጡትም ዳዊትን በእስራ
ኤል ሁሉ ላይ ለማንገሥ ወስነው ስለ
ነበር ነው። የቀሩትም እስራኤላውያን
ሁሉ ዳዊትን ለማንገሥ በአንድ ሐሳብ
ጸኑ። 39የሚያስፈልጋቸውንም ቤተ ሰቦቻ
ቸው አዘጋጅተውላቸው ስለ ነበር፣ ሰዎቹ
እየበሉና እየጠጡ ከዳዊት ጋር ሦስት ቀን
ቈዩ። 40እንዲሁም ሩቅ ከሆነው ከይሳኮር፣
ከዛብሎንና ከንፍታሌም አገር ሳይቀር
ጎረቤቶቻቸው በአህያ፣በግመል፣ በበቅሎና
በበሬ ጭነው ምግብ አመጡላቸው፤ በእስ
ራኤል ታላቅ ደስታ ስለ ሆነ ዱቄት፣ የበ
ለስና የዘቢብ ጥፍጥፍ፣ የወይን ጠጅ፣ የወ
ይራ ዘይት፣ የቀንድ ከብትና በጎች በገፍ
ቀርበው ነበር።

## የታቦቱ መመለስ

13፥1-14 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ6፥1-11

13 ዳዊትም ሻለቆችና መቶ አለቆች
ከሆኑት የጦር ሹማምቱ ሁሉ ጋር
ተማከረ። 2ከዚያም ለመላው የእስራኤል ማኅ
በር እንዲህ አለ፤ "እንግዲህ ነገሩ መልካም
መስሎ ከታያችሁና የአምላካችን የእግዚአ
ብሔር ፈቃድ ከሆነ፣ በእስራኤል ግዛት
ሁሉ ለሚኖሩ በሩቅም ሆነ በቅርብ ላሉት
ለቀሩት ወንድሞቻችን እንዲሁም በየራሳ
ቸው ከተሞችና መሰማሪያዎች የሚኖሩ ካህ
ናትና ሌዋውያን መጥተው ከእኛ ጋር እን
ዲሰባሰቡ እንላክባቸው። 3በሳኦል ዘመነ
መንግሥት ሳንፈልገው[ሀ] የነበረውን የአምላ
ካችንን ታቦት መልሰን ወደ እኛ እናምጣ"።
4ነገሩም በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ ተቀባይነት
ስላገኘ መላው ማኅበር ይህንኑ ለማድረግ
ተስማማ።
5ስለዚህ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት ከቂ
ርያትይዓሪም ለማምጣት ከግብፅ ወንዝ ከሺ
ሖር ጀምሮ እስከ ሐማት መተላለፊያ[ሠ]
ድረስ የሰፈሩትን እስራኤላውያን ሁሉ ሰበ
ሰበ። 6ዳዊትና እስራኤላውያን ሁሉ በኪሩብና
በኪሩብ መካከል የተቀመጠውን ስሙም
በእርሱ የተጠራውን፣ የእግዚአብሔር አምላ
ካክን ታቦት ከዚያ ለማምጣት በይሁዳ ወዳ
ለችው ቂርያትይዓሪም ወደ ተባለችው
ወደ በኣላ ሄዱ።
7የእግዚአብሔርንም ታቦት ከአሚናዳብ ቤት
በአዲስ ሠረገላ ላይ አድርገው አመጡት፤
ሠረገላውን ይነዱ የነበሩትም ዖዛና አሒዮ
ነበሩ። 8ዳዊትና እስራኤላውያን ሁሉ በእግዚ
አብሔር ፊት ሆነው በቅኔና በበገና፣ በመ
ሰንቆና በከበሮ፣ በጸናጽልና በመለከት በሙሉ
ኀይላቸው በዓሉን በደስታ ያከብሩ ነበር።
9ወደ ኪዶን ዐውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ
አደናቅፏቸው ስለ ነበር፣ ዖዛ ታቦቱን ለመ
ደገፍ እጁን ዘረጋ። 10ታቦቱን በእጁ ስለ ነካ፣
የእግዚአብሔር ቍጣ በዖዛ ላይ ነደደ፤ ስለዚ
ህም በዚያው በእግዚአብሔር ፊት ሞተ።
11የእግዚአብሔር ቍጣ ዖዛን በድንገት ስለ
ቀሠፈው ዳዊት አዘነ፤ ያም ቦታ እስከ ዛሬ
ድረስ የዖዛ ስብራት[ፀ] ተብሎ ይጠራል።
12ዳዊት በዚያን ዕለት እግዚአብሔርን ስለ
ፈራ፣ "ታዲያ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ እኔ

12፥39 · 2ሳሙ3፥20፤ ኢሳ25፥6-8
12፥40 1ሳሙ25፥18፤ 2ሳሙ16፥1፤17፥29፤ 1ዜና29፥22
13፥3 1ሳሙ7፥1-2፤ 2ዜና 1፥5
13፥5 ዘኍ13፥21፤ ኢሱ13፥3፤1ሳሙ7፥2፤ 1ዜና11፥1፤15፥3
13፥6 ዘፀ25፥22፤ ኢሱ15፥9፤25፤19፥15
13፥7 1ሳሙ7፥1
13፥8 1ዜና15፥16፤19፤24፤2 ዜና5፥12፤መዝ92፥3
13፥10 ዘሌ10፥2፤1ዜና15፥13
13፥11 1ዜና15፥13፤መዝ7፥11

[ሀ]3 ወይም፣ ቸላ ብለን [ሠ]5 ወይም፣ እስከ ሌቦ ሐመት
[ፀ]11 ወይም፣ ፔሬዝ ዖዛ

ተጽዕኖ ያሳደረበት ይመስላል (በመግቢያው ላይ "ዐላማና መሪ ሐሳቡ" የሚለውን ይመ)። ዳዊት በነገሠ ጊዜ ለሩብ ሚሊዮን ሕዝብ (የቍ 23-37 ማብ ይመ) ያደረገው ግብዣ ወደፊት መሲሑ ለሚያደርገው ግብዣ ምሳሌ ነው (ኢሳ 25፥6-8)። የመሲሑ ግብዣ ምሳሌ በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል በነበሩት ዘመናት በተጻፉት ጽሑፎች ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ተሰጥቶታል (መጽሐፈ ባሮክ 29፥4-8፤ ሄኖክ 62፥14)፤ እንዲሁም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ዐቢይ ስፍራ ተሰጥቶታል (ማቴ፡8፥11-12፤ ሉቃ13፥28-30፤ ማቴ22፥1-10፤ሉቃ 14፥16-24፤ ደግሞም ማቴ 25፥1-13፤ ሉቃ 22፥28-30፤ ራእ 19፥7-9 ይመ)። የጌታ እራት ወደፊት የሚሆነውን የበጉን ሰርግ ግብዣ የሚያመላክት ነው (ማቴ26፥29፤ ማር14፥25፤ ሉቃ22፥15-18፤1ቆሮ11፥23-26)።

*13፥1-14፤* 2ሳሙ6፥1-11 እና ማብ ይመ። እዚህ ላይ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በ2ሳሙ 5-6 ላይ የተመለከተውን የጊዜ ቅደም ተከተል በመቀየር ስለ ቤተ መንግሥቱ ሕንጻ ሥራና ስለ ፍልስጥኤማውያን ዘመቻ የጀመረውን ዘገባ ወደ ኋላ ያቈይና (ም 14) ታቦቱ ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ስፍራ የመዛወሩን ታሪክ ያስቀድማል። ይህም ስለ ዳዊት በሚናገረው ታሪክ ውስጥ የተካተተ ነው። ዳዊት ስለ ታቦቱ ምን ያህል እንደሚገደው የተገለጸው ወዲያውኑ በነገሠበት ጊዜ ነው። ከመሪዎቹ ጋር ያደረገውም ምክክር ለንግሥና በዓሉ በተዘጋጀው ግብዣ ውስጥ የተካተተ ይመስላል (12፥38-40)።

*13፥1-4፤* እነዚህ ቍጥሮች በመጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ አይገኙም፤ የሚያንጸባርቁትም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ "እስራኤል ሁሉ" ያለውን አትኵሮት ነው። በ2ሳሙ 6፥1 ላይ እንደ ተጻፈው ታቦቱን ለማስመለስ የተደረገው ከፊል ወታደራዊ ዘመቻ፣ ካህናቱንና ሌዋውያኑን ጨምሮ "በግዛቶቹ ሁሉ" (ቍ 2) የሚገኘው "መላው የእስራኤላውያን ማኅበረ ሰብ" እዚህ ላይ መከሮና ዘክሮ ድጋፉን ሰጥቶት ይገኛል። ታቦቱን እንዲያንቀሳቅሱ የተፈቀደው ከዚያ በኋላ ስለ ሆነ፤ ይህ ለዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እጅግ ጠቃሚ ነጥቡ ነበር (15፥2፡13፤23፥25-27፤ ዘዳ 10:8)።

*13፥3 በሳኦል ዘመነ መንግሥት ሳንፈልገው የነበረውን፤* 1ሳሙ 4፥18 በሌላ ስፍራ የማይገኝ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አማራጭ ትርጕሙን ይመ።

*13፥5-6፤* አጽንዖቱ "እስራኤል ሁሉ" በሚዋሃዱበት ተግባር ላይ ያረፈ ነው። እስራኤላውያንም አደጋ ሊያስከትል በሚችለው በዚህ ተግባር ላይ ተካፋይ ለመሆን በስተሰሜን ካለው ከሐማት መተላለፊያ አንሥቶ በስተ ደቡብ እስከሚገኘው እስከ ሺሖር ወንዝ ድረስ ካለው ምድር ሁሉ ተሰበሰቡ።

13፥5 *ከሺሖር፤* የግብፃውያን ቃል ሲሆን፣ ትርጕሙም "የሆሩስ ኩሬ" ማለት ነው። ምናልባትም ይህ የዐባይ ወንዝ አንዱ ክፍል ወይም ደግሞ ከዐባይ ዋና ዋና የመስኖ ቦዮች የአንዱ መጠሪያ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ (ኢሱ13፥3፤ ኢሳ 23፥3፤ ኤር 2፥18 እና ማብ ይመ)።

*13፥6 በኣላ፤* ይህን ከነዓናውያን ቂርያትይዓሪም ብለው የሚጠሩት ሲሆን፣ "ቂርያት በአል" ኢሱ 18፥14 በመባልም ይታወቃል። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የመጽሐፉ ተደራስያን ታቦቱ ወደ ቂርያትይዓሪም የመምጣቱን ታሪክ እንደሚያውቁት ይገምታል (1ሳሙ፡6፥1-7፥1)

13፥7 *ዖዛና አሒዮ፤* የአሚናዳብ ወንዶች ልጆች ወይም ዘሮች ናቸው (2ሳሙ 6፥3)።

*13፥10 ታቦቱን በእጁ ስለ ነካ፤* በጕንና በጕኑ ላይ ባሉት ቀለበቶች መሎጊያ አስገብተው ታቦቱን ከቦታ ቦታ እንዲያንቀሳቅሱ የተፈቀደላቸው ሌዋውያን ብቻ ነበሩ (ዘጸ 25፥12-15)። ማናቸውም ንዋየ ቅድሳት ቢነካ በሞት ያስቀጣ ነበር (ዘኍ 4፥15)፤ ይህ ፍርድ በሁለተኛውና ስኬታማ በነበረው ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም በማጓጓዝ ተግባር ላይ ታይቶአል (15:1-15) ዖዛና አሒዮ ሌዋውያን መሆን አለመሆናቸው በውል ተለይቶ አይታወቅም፤ ሆኖም ተመሳሳዩን ታሪክ በዘገባው የመጽሐፈ ሳሙኤል ክፍል ውስጥ ሌዋውያን መኖራቸው አልተወሳም፤ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን በዚህኛው ጕዞአቸው የሌዋውያኑን ስም በጥንቃቄ ማስገባቱ ሁለቱ ሰዎች ሌዋውያን ለመሆናቸው ፍንጭ የሚሰጥ ነው (የቍ 1-4 ማብ ይመ)። ያም ሆነ ይህ ፍልስጥኤማው

እንዴት ማምጣት እችላለሁ?" አለ:: 13ስለዚህ
ታቦቱን ወደ ዳዊት ከተማ በመውሰድ
ፈንታ የጋት ሰው ወደ ሆነው ወደ አቢዳራ
ቤት ወሰደው:: 14የእግዚአብሔርም ታቦት በአቢ
ዳራ ቤት ከቤተ ሰቡ ጋር ሦስት ወር ተቀ
መጠ፤ እግዚአብሔርም ቤተ ሰቡንና ያለው
ንም ሁሉ ባረከ::

## የዳዊት ቤትና ቤተ ሰቡ

14፥1-7 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 5፥11-16 1ዜና3፥5-8

14 በዚህ ጊዜ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም
ለዳዊት ቤተ መንግሥት እንዲሠሩ
መልክተኞችን፣ ድንጋይ ጠራቢዎችንና አናጢ
ዎችን ከዝግባ ዕንጨት ጋር ላከ:: 2ዳዊትም
እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ አንግሦ እንዳ
ጸናውና ስለ ሕዝቡም ስለ እስራኤል ሲል
መንግሥቱን ከፍ ከፍ እንዳደረገለት አስተዋለ::
3ዳዊትም በኢየሩሳሌም ብዙ ሚስቶች
አገባ፤ ከእነርሱም ወንዶችንና ሴቶች ልጆ
ችን ወለደ:: 4በዚያ ሳለ የወለዳቸው የል
ጆቹ ስም ይህ ነው፤ ሳሙስ፣ ሶባብ፣ ናታን፣
ሰሎሞን፣ 5ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣ ኤሊፋላት፣
6ኖጋ፣ ናፌቅ፣ ያፍያ፣ 7ኤሊሳማ፣ ኤሊዳሄ፣
ኤሊፋላት::

## ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረገ

14፥8-17 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 5፥17-25

8ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ተቀብቶ
መንገሡን ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣
እርሱን ፍለጋ በሙሉ ኀይላቸው ወጡ፤
ዳዊት ይህን ሰምቶ ስለ ነበር ሊገጥማቸው
ወጣ:: 9በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን መጥ
ተው የራፋይምን ሸለቆ ወረሩ:: 10ስለዚህ
ዳዊት፣ "ወጥቼ በፍልስጥኤማውያን ላይ
አደጋ ልጣልን? አንተስ በእጄ አሳልፈህ ትሰ
ጣቸዋለህን? ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ::
እግዚአብሔርም፣ "አዎን ውጣ! በእጅህ አሳ
ልፌ እሰጣቸዋለሁ" ብሎ መለሰለት::
11ስለዚህ ዳዊትና ሰዎቹ ወደ በኣልፐራሲም
ወጡ፤ በዚያም ድል አደረጋቸው:: ዳዊትም፣
"ውሃ ነድሎ እንደሚወጣ ሁሉ እግዚአብሔ
ርም ጠላቶቼን በእጄ አፈረሳቸው" አለ፤ ከዚ
ህም የተነሣ ያን ቦታ "በኣልፐራሲም" ብለው
ሰየሙት:: 12ፍልስጥኤማውያን አማልክቶቻ
ቸውን በዚያው ጥለዋቸው ስለ ነበር፣ ዳዊት
በእሳት እንዲያቃጥሏቸው አዘዘ::
13ፍልስጥኤማውያን ሸለቆውን እንደ ገና ወረሩ፤
14ዳዊትም እንደ ገና እግዚአብሔርን ጠየቀ:: እግዚ
አብሔርም እንዲህ ሲል መለሰለት "ዙሪያውን
ከበህ በሾላው ዛፍ ፊት ለፊት አደጋ ጣል
ባቸው እንጂ በቀጥታ ወደ ላይ አትውጣ፤ 15በሾ
ላው ዐናት ላይ የሰልፍ ድምፅ ስትሰማ
ወዲያውኑ ለጦርነት ውጣ፤ ይህም የፍልስ
ጥኤማውያንን ሰራዊት ለመምታት እግዚአ
ብሔር በፊትህ መጥቶአል ማለት ነውና::"
16ስለዚህ ዳዊት እግዚአብሔር እንዳለው አደ
ረገ፤ ከገባዖን ጀምሮ እስከ ጌዝር ድረስ ፍል
ስጥኤማውያንን መቷቸው::
17ከዚህም የተነሣ የዳዊት ዝና በየአገሩ
ሁሉ ተሰማ፤ እግዚአብሔርም መንግሥታት
ሁሉ እንዲፈሩት አደረገ::

## ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተወሰደ

15፥25-16፥3 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 6፥12-19

15 ዳዊት በስሙ በተጠራችው ከተማ
ለራሱ ቤቶችን ሠራ፤ ለእግዚአብሔር

13፥13 1ዜና15፥18:24፤ 16፥38፤26፥4-5:15
13፥14 2ሳሙ6፥11
14፥1 1ነገ5፥6፤ 1ዜና17፥6፤22፥4፤ 2ዜና2፥3፤ ዕዝ3፥7፤ሐጌ1፥8
14፥2 ዘኍ24፥7፤ዘዳ26፥19
14፥3 1ዜና3፥1
14፥4 1ዜና3፥9
14፥8 1ዜና11፥1
14፥9 ቍ13፤ ኢሱ15፥8፤ 1ዜና11፥15
14፥11 መዝ94፥16፤ ኢሳ 28፥21
14፥12 ዘፀ32፥20፤ኢሱ7፥15
14፥13 ቍ9
14፥16 ኢሱ9፥3፤10፥33
14፥17 ዘፀ15፥14-16፤ዘዳ2፥25፤ ኢሱ6፥27፤መዝ2፥1-12
15፥1 2ሳሙ6፥17፤1ዜና16፥1፤17፥1፤መዝ132፥1-18

ያን እንዳደረጉት (1ሳሙ 6) ታቦቱ በሠረገላ ላይ ሆኖ መጓዝ ወይም መነካት አልነበረበትም::

*13፥13 አቢዳራ፤* ምናልባትም በ15፥18:21:24 ላይ ስሙ ከተጠቀሰው ሰው ጋር አንድ ሳይሆን አይቀርም:: አቢዳራን በባ ረከው ጊዜ ብዙ ወንዶች ልጆችንም እንደሰጠው በ26፥4 ላይ ተጽፎአል:: አቢዳራ ሌዋዊ መሆኑንና ታቦቱንም በጥንቃቄ መጠ በቁን ይህ ጥቅስ ያስገነዝባል::

*14፥1-17፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በዚህ ክፍል የተ ጨመሩ ሐሳቦችን ወደ ኋላ በመሄድ ከ2ሳሙ 5 ወስዶአል (የ13፥1-4 ማብ ይመ):: ታቦቱ.. በአቢዳራ ቤት በቈዩበት ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ (13፥14) እግዚአብሔር ዳዊትን በሙ ላት እንደባረከው የሚያሳዩ ብዙ ነገሮች አሉ፤ ቤተ መንግሥቱን ሠርቶአል (ቍ 1-2)፤ የቤተሰቡ ቍጥር ጨም ሮአል (ቍ 3-7)፤ በጦር ሜዳ ድልን ተቀዳጅቶአል (ቍ 8-16):: ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር ስለ ባረከው ነው::

*14፥1-2፤* 2ሳሙ5፥11-12 እና ማብ ይመ::

14፥1 *ኪራም፤* ዳዊት ከሞተ በኋላ ለቤተ መቅደሱ ሥራ የሚያስፈልገውን ዕቃና የሰው ኀይል በርዳታ ሰጥቶአል (2ዜና ም 2):: ስሙ እዚህ ላይ የተጠቀሰበት ምክንያት ዳዊት በእስ ራኤል ላይ መንገሡ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ዕውቅና ማግኘቱንና በዳዊትና በኪራም መካከል የቃል ኪዳን ውል ስምምነት መፈ ጸሙን ለማሳየት ነው::

*14፥3-7፤3፥5-9፤* 2 ሳሙ 5፥13-16 ይመ:: ዳዊት በኬብ ሮን ሳለ የወለዳቸው ልጆች ስማቸው አልተጠቀሰም (3፥1-4፤ 2ሳሙ 3፥2-5፤ እንዲሁም የ11፥1-3 ማብ ይመ)::

14፥7 *ኤሊዳሄ፤* ሌላው ስሙ ኤሊያድ ነው:: ከ2ሳሙ 5፥16 ይመ::

*14፥8-12፤* 2ሳሙ 5፥17-21 እና ማብ ይመ::

14፥11፤ *በኣልፐራሲም... ነድሎ እንደሚወጣ፤* እግዚአ ብሔር ፍልስጥኤማውያንን በመምታቱ በዕብራይስጥ ለዚህ ቦታ የተሰጠው ስያሜ እግዚአብሔር ዖዛን በመታው ጊዜ (13፥11) ከተጠቀሰው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው::

*14፥12 በእሳት እንዲያቃጥሏቸው አዘዘ፤* 2ሳሙ5፥21 ዳዊትና ሰዎቹ አማልክቱን መውሰዳቸውን እንጂ ማቃጠላ ቸውን አይናገርም:: እዚህ ላይ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ይህን ለውጥ ያደረገው፣ የዳዊትን ድርጊት የአሕዛብን አማልክት በእሳት እንዲቃጠሉ ከሚጠይቀው (ዘዳ7፥5፥25) የሙሴ ሕግ ጋር ለማጣ ጣም እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ:: ይሁን እንጂ አንዳንድ በሰባ ሊቃናት የተተረጐሙ የሳሙኤል መጽሐፍ ቅጆች እንደ ዜና መዋዕሉ ሁሉ፣ ዳዊት እነዚያን የጣዖት አማልክቶች ማቃጠሉን በሚመለከት ተመሳሳይ ነገር ይናገራሉ:: ይህም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የሥነ መለኮት ትምህርት እንዳይናጋ ሌላ አዲስ ነገር መጻፍ ወይም የነበረውን መለወጡ ሳይሆን፣ ከመደበኛው የዕብራ ይስጡ የሳሙኤል መጽሐፍ ቅጅ ከሚለየውና በፊቱ ከነበረው ቅጅ ተጠንቅቆ ያዘጋጀው (የወሰደው) መሆኑን ያሳያል::

*14፥13-16፤* 2ሳሙ 5፥22-25 እና ማብ ይመ::

14፥17 *እግዚአብሔርም መንግሥታት ሁሉ እንዲፈሩት አደረገ፤* እዚህም ሆነ በሌላ ስፍራ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሰው በፍ ርሃት እንዲዝል በሚያደርጉ ኀይለ ቃላት ደጋግሞ ሲጠቀም ይታያል፤ ይህም የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲል ራሱን በአስፈሪ ኀይሉ እንደሚገልጥ ለማመልከት ነው (ዘዳ15፥16):: ዳዊትም በአካባቢው አሕዛብ ዘንድ እንደ እግዚአ ብሔር ባለሟል ይቈጠር ነበር (በተመሳሳይ ሁኔታ አሳ 2ዜና 14፥14፤ ኢዮሳፍጥ 2ዜና 17፥10፤20፥29 ይመ)::

*15፥1-16፥3፤* ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ የተደረገውን ስኬታማ ውጤት የሚያወሣው ይህ ታሪክ ከዚህ ክፍል ይልቅ በ2ሳሙኤል መጽሐፍ ውስጥ ተስፋፍቶ ቀርቦአል:: ይህም በ15፥25-16፥3 ላይ ካለው ጋር ይመሳሰላል (2ሳሙ 6፥12-19):: የቀረው ግን የራሱ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሲሆን፣ የራሱን ፍላጎት በተለይም ስለ ሌዋውያኑና ስለ መዘምራኑ ያለ ውን አመለካከት ያንጸባረቀበት ነው (ቍ 3-24) "በመጽሐፉ መግቢያ፣ "ዐላማውና መሪ ሐሳቡ" የሚለውን ይመ):: እንዲሁም መዝ 132 ይመ::

*15፥1 ለራሱ ቤቶችን ሠራ...፤* 14፥1-2 እና የ13፥1-14

ታቦት ቦታ አዘጋጅቶ ድንኳን ተከለ። 2ከዚ
ያም ዳዊት፣ "የእግዚአብሔርን ታቦት እንዲሸ
ከሙና ለዘላለም በፊቱ እንዲያገለግሉ እግዚ
አብሔር ከመረጣቸው ከሌዋውያን በቀር፣
*የእግዚአብሔርን* ታቦት ማንም አይሸከም"
ሲል አዘዘ።

3ዳዊት *የእግዚአብሔን* ታቦት ወደዘጋጀለት
ስፍራ እንዲያመጡ እስራኤልን ሁሉ በኢየሩ
ሳሌም ሰበሰበ። 4የአሮንን ዘሮችና ሌዋውያኑንም
በአንድነት ሰበሰበ፤

5ከቀዓት ዘሮች፣
አለቃውን ኡርኤልንና አንድ መቶ ሃያ
የሥጋ ዘመዶቹን፤
6ከሜራሪ ዘሮች፣
አለቃውን ዓሣያንና ሁለት መቶ ሃያ
የሥጋ ዘመዶቹን፤
7ከጌድሶን ዘሮች፣
አለቃውን ኢዮኤልንና አንድ መቶ ሠላሳ
የሥጋ ዘመዶቹን፤
8ከኤሊጻፋን ዘሮች፣
አለቃውን ሸማያንና ሁለት መቶ የሥጋ
ዘመዶቹን፤
9ከኬብሮን ዘሮች፣
አለቃውን ኤሊኤልንና ሰማንያ የሥጋ
ዘመዶቹን፤
10ከዑዝኤል ዘሮች፣
አለቃውን አሚናዳብንና አንድ መቶ ዐሥራ
ሁለት የሥጋ ዘመዶቹን።

11ከዚያም ዳዊት ካህናቱን ሳዶቅንና አብ
ያታርን፣ ሌዋውያኑን ኡርኤልን፣ ዓሣያን፣
ኢዩኤልን፣ ሸማያን፣ ኤሊኤልንና አሚና
ዳብን ጠርቶ፣ 12እንዲህ አላቸው፤ "እንግዲህ
እናንተ የሌዋውያን ቤተ ሰብ አለቆች ስለ
ሆናችሁ፣ እናንተና ወንድሞቻችሁ ሌዋ
ውያን ራሳችሁን ቀድሱ፤ ከዚያም የእስራ
ኤልን አምላክ *የእግዚአብሔርን* ታቦት ወዳ
ዘጋጀሁለት ቦታ አምጡ። 13የአምላካችን *የእ
ግዚአብሔር* ቍጣ በላያችን ላይ እንዲህ
የነደደው እናንተ ሌዋውያኑ ቀድሞም ስላ
ላመጣችሁት ነው፤ እኛም ብንሆን ምን
ማድረግ እንዳለብን በታዘዘው መሠረት
አልጠየቅነውም።"14ስለዚህ ካህናቱና ሌዋው
ያኑ የእስራኤልን አምላክ *የእግዚአብሔርን*
ታቦት ለማምጣት ራሳቸውን ቀደሱ።
15ሙሴ በእግዚአብሔር ቃል እንዳዘዘው፣ ሌዋ
ውያኑ የእግዚአብሔርን ታቦት በትከሻቸው ላይ
በመሎጊያዎች አድርገው ተሸከሙ።

16ዳዊትም በዜማ መሣሪያ ማለትም በመ
ሰንቆ፣ በበገናና በጸናጽል እየታጀቡ የደስታ
ዜማዎችን የሚያዜሙ መዘምራንን ከወንድ
ሞቻቸው መካከል እንዲሾሙ ለሌዋውያኑ
መሪዎች ነገራቸው።

17ስለዚህ ሌዋውያኑ የኢዮኤልን ልጅ ኤማ
ንን ሾሙ፤ ከወንድሞቹም የበራክያን ልጅ
አሳፍን፣ ከወንድሞቻቸው ከሜራሪ ዘሮች
የቂሳን ልጅ ኤታንን ሾሙ፤ 18ከእነርሱም
ጋር ወንድሞቻቸው በደረጃ ተሾሙ፤ እነር
ሱም ዘካርያስ[ዐ]፣ ያዝኤል፣ ሰሚራሞት፣ ይሒ
ኤል፣ ዑኒን፣ ኤልያብ፣በናያስ፣ መዕሤያን፣
መቲትያ፣ ኤሊፍሌሁ፣ ሚቅኔያ፣ ደግሞም
በር ጠባቂዎቹ ዖቤድኤዶምና ይዒኤል[ሀ] ነበሩ።

19መዘምራኑ ኤማን፣ አሳፍና ኤታን
በናስ ጸናጽል ድምፁን ከፍ አድርገው እንዲ
ያሰሙ ተሾሙ፤ 20ዘካርያስ፣ ዓዝኤል፣ ሰሚ
ራሞት፣ ይሒኤል፣ ዑኒ፣ ኤልያብ፣ መዕ
ሤያና በናያስ ደግሞ በአላሞት[ሠ] ቅኝት
መሰንቆ ይገርፉ ነበር። 21እንዲሁም መቲ
ትያ፣ ኤሊፍሌሁ፣ ሚቅኔያ፣ ዖቤድኤዶም፣
ይዒኤል፣ ዓዛዝያ፣ በሺሚኒት[ሠ] ቅኝት በገና
ይደረድሩ ነበር። 22የዝማሬው ኀላፊ ሌዋ
ዊው አለቃ ክናንያ ነበረ፤ ይህን ኀላፊነት
የወሰደው በዝማሬ የተካነ ስለ ነበር ነው።

23በራክያና ሕልቃና የታቦቱ በር ጠባ
ቂዎች ነበሩ፤ 24ካህናቱ ሰበኒያ፣ ኢዮሣ
ፍጥ፣ ናትናኤል፣ ዓማሣይ፣ ዘካርያስ፣ በና
ያስና አልዓዛር በእግዚአብሔር ታቦት ፊት
መለከት ይነፉ ነበር። ዖቤድኤዶምና ይሒያ
ደግሞ የታቦቱ በር ጠባቂዎች ነበሩ።

25ስለዚህ ዳዊት የእስራኤል ሽማግሌዎችና
የሻለቃው አዛዦች *የእግዚአብሔርን* የቃል
ኪዳኑን ታቦት ከዖቤድኤዶም ቤት በደስታ
ለማምጣት ሄዱ። 26የእግዚአብሔርን የቃል ኪ
ዳን ታቦት የተሸከሙትን ሌዋውያን እግዚ
አብሔር ረድቶአቸው ስለ ነበር፣ ሰባት ኮር
ማዎችና ሰባት አውራ በጎች ሠዉ። 27ታቦ
ቱን የተሸከሙት ሌዋውያን ሁሉ፣ መዘም
ራኑና የመዘምራኑ አለቃ ክናንያ የለበ
ሱትን ዐይነት ከቀጭን በፍታ የተሠራ
ልብስ ዳዊትም ለብሶ ነበር፤ እንዲሁም ከበ

[ዐ]18 ሦስት የዕብራይስጥ ቅጆችና በርካታ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች (እንዲሁም ቍ20 እና 1ዜና 165 ይመ)፤ በርካታ የዕብራይስጥ ቅጆች *"የዘካርያስ ልጅ ወይም ዘካርያስ፣ ቤን"* ይላሉ።
18ዘ ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም (እንዲሁም ቍ21) ግን *"ይዒኤልና ዓዛዝያ"* ይላል።
[ሠ]21፥22 ምናልባት የዜማ ስም ነው።

15፥2 ዘኍ3፥6፤4፥15፤ ዘዳ 10፥8፤31፥9፡25፤ 1ዜና16፥4፤23፥13፤ 2ዜና5፥5፤29፥11፤ 31፥2፤ መዝ134፥1፤ 135፥2
15፥3 1ዜና13፥5
15፥4 ዘኍ3፥17-20
15፥5 1ዜና6፥24
15፥8 ዘፀ6፥22
15፥9 ዘፀ6፥18
15፥11 1ሳሙ22፥20፤ዜና12፥28
15፥12 ዘፀ29፥1፤ 30፥19-21፡30፤ 40፥31-32፤ዘሌ11፥44
15፥13 ዘሌ5፥10፤1ነገ8፥4፤ 1ዜና13፥11
15፥15 ዘፀ25፥14፤2ሳሙ6፥7
15፥16 1ዜና6፥31፤13፥8፤23፥5፤2ዜና7፥6፤29፥26፤ ዕዝ2፥41፤ነህ11፥23፤ 12፥27፡36፤ ኢዮ21፥12፤መዝ 68፥25፤150፥5፤አሞ6፥5
15፥17 1ዜና6፥33፡39፡44
15፥18 2ሳሙ6፥10፤1ዜና26፥4-5
15፥19 1ዜና16፥41፤25፥6
15፥24 2ዜና5፥12፤7፥6፤29፥26
15፥25 2ዜና1፥4፤5፥2፤ኤር3፥16
15፥26 ዘኍ23፥1-4፡29
15፥27 1ሳሙ2፥18

ማብ ይመ።

*15፥2-3፤* የ13፥10 ማብ ይመ።

*15፥4-10፤* ሦስቱ የሌዊ ነገድ ጐሣዎች ቀዓት፣ ሜራሪና ጌድሶን በዘሮቻቸው በተለይ የቀዓት ልጆች ኤሊጻፉን፣ ኬብሮን፣ ኡርኤል እንደዚሁ በተወላጆቻቸው በኩል ተወክለዋል፤ ጠቅላላ ቍጥራቸውም 862 ነበር።

*15፥12 ራሳችሁን ቀድሱ፤* በሥርዐቱ መሠረት ታጥቦ መንጻትና ሕጉ ከሚከለክለው ነገር ሁሉ መጠበቅ ማለት ነው (ዘፀ 29፥1-37፤30፥19-21፤ 40፥31-32፤ ዘሌ 8፥5-35)።

*15፥13-15፤* የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ታቦቱን ወደ ሌላ ቦታ ለማዛወር የተደረገው የመጀመሪያ ሙከራ ለምን ሳይሳካ እንደቀረ ከነምክንያቱ አቅርቦአል። ሆኖም ይህ ገለጻ በመጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ አይገኝም (የ1ሳሙ13፥10 ማብ ይመ)።

15፥18፡21፡24 *ዖቤድኤዶምና፤* የ13፥13 ማብ ይመ።

15፥24 *ካህናቱ... መለከት ይነፉ ነበር፤* 16፥6፤ዘኍ 10፥1-10 ይመ።

*15፥27፤* ዳዊት ካህናቱ የሚለብሱትን (1ሳሙ2፥18፤ 22፥18) የበፍታ ኤፉድ ስለ መልበሱ በ2 ሳሙ፡6፥14 እና በዚህ ክፍል ተወሥቶአል። ይሁን እንጂ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ዳዊት የለበሰውን ከጥንቱ መንፈሳዊ ልብሰ ተክህኖ ጋር ይበልጥ ለማያያዝ ፈልጎ እንደ ቀሩት ሌዋውያን ሁሉ ያማረ ቀጭን በፍታ መልበሱን ጨምሮ ጽፎአል። እዚህ ላይ በግልጽ እንደሚታየው የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ዳዊትን የተመለከተው እንደ ክህነና ንጉሥ ተደርጎ ለሚጠበቀው መሲሕ ነው (መዝ 110፤ ዘካ 6፥9-15 ይመ)።

ፍታ የተሠራ ኤፉድ ለብሶ ነበር:: [28]በዚህ
ሁኔታ መላው የእስራኤል ሕዝብ በሆታ
ቀንደ መለከትና እምቢልታ እየተነፋ፣ ጸና
ጽል እየጸነጸሉ፣ መሰንቆና በገና እየደረደሩ
*የእግዚአብሔርን* የኪዳኑን ታቦት አመጡ::
[29]*የእግዚአብሔር* የኪዳኑ ታቦት ወደ ዳዊት
ከተማ ሲገባ የሳኦል ልጅ ሜልኮል በመስኮት
ሆና ተመለከተች፤ ንጉሡ ዳዊት ደስ ብሎት
ሲያሸበሽብ አይታ በልቧ ናቀችው::

**16** ከዚያም የእግዚአብሔርን ታቦት አም
ጥተው ዳዊት በተከለለት ድንኳን
ውስጥ አኖሩት፤ የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅ
ብረት መሥዋዕትም[a] በእግዚአብሔር ፊት አቀ
ረቡ:: [2]ዳዊት የሚቃጠለውን መሥዋዕትና
የኅብረቱን መሥዋዕት ከሠዋ በኋላ፣ ሕዝ
ቡን *በእግዚአብሔር* ስም ባረከ:: [3]ከዚያም
ለእስራኤል ሁሉ ለወንዱም ለሴቱም አንዳ
ንድ ሙልሙል ዳቦ፣ አንዳንድ ጥፍጥፍ
ተምር፣ ሙዳ ሙዳ ሥጋና አንዳንድ ጥፍጥፍ
ዘቢብ ሰጠ::
[4]*በእግዚአብሔር* ታቦት ፊት እንዲያገለ
ግሉና ለእስራኤል አምላክ *ለእግዚአብሔር*
ልመና፣ ምስጋናና ውዳሴ እንዲያቀርቡ
ከሌዋውያን ሰዎች ሾመ፤ [5]አለቃው አሳፍ
ነበረ፤ ከእርሱ ቀጥሎ ዘካርያስ ሁለተኛ ሆኖ
ተሾመ፤ ከዚያም ይዒኤል፣ ሰሚራሞት፣
ይሒኤል፣ መቲትያ፣ ኤልያብ፣ በናያስ፣
ዖቤድኤዶም፣ ይዒኤል ተሾሙ፤ እነርሱም
በመሰንቆና በበገና ይዘምሩ ነበር፤ አሳፍ
ደግሞ ጸናጽል የሚጸነጽል ሆኖ ተመደበ::
[6]እንዲሁም ካህናቱ በናያስና የሕዚኤል ዘወ
ትር በእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት ፊት መለ
ከት እንዲነፉ ተመደቡ::

## የዳዊት የምስጋና መዝሙር

16፥8-22 ተጓ ምብ - መዝ 105፥1-15
16፥23-33 ተጓ ምብ - መዝ 96፥1-13
16፥34-36 ተጓ ምብ - 106፥ 1:47-48

[7]በዚያም ቀን ዳዊት በመጀመሪያ ለአሳ
ፍና ለሥራ ጓደኞቹ ይህን *የእግዚአብሔር*
ምስጋና መዝሙር ሰጠ፤

[8]*ለእግዚአብሔር* ምስጋና አቅርቡ፤
ስሙንም ጥሩ፤
ለአሕዛብ ያደረገውን ሁሉ ንገሩ፤
[9]ዘምሩለት፤ ውዳሴም አቅርቡለት፤
ድንቅ ሥራውን ሁሉ ንገሩ፤
[10]በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ፤
*እግዚአብሔርን* የሚፈልጉ ሁሉ፣
ልባቸው ሐሤት ያድርግ::
[11]ወደ *እግዚአብሔርና* ወደ ኀይሉ
ተመልከቱ፤
ዘወትር ፊቱን ፈልጉ::
[12]ያደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች፣
ታምራቱንና የሰጠውንም ፍርድ አስታውሱ፤
[13]እናንተ የባሪያው የእስራኤል ዘሮች፣
እናንተ የተመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች::
[14]እርሱ *እግዚአብሔር* አምላካችን ነው፤
ፍርዱም በምድር ሁሉ ላይ ነው፤
[15]ኪዳኑን እስከ ዘላለም፣
ያዘዘውንም ቃል እስከ ሺህ ትውልድ
ያስባል::
[16]ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን፣
ለይስሐቅ የማለውን መሐላ::
[17]ይህንንም ለያዕቆብ ሥርዐት አድርጎ
አጸና፤
ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን
አደረገ፤
[18]እንዲህ ሲል፣ "የምትወርሰው ርስት
እንዲሆን፣
የከነዓንን ምድር ለአንተ እሰጣለሁ::"
[19]ቍጥራቸው ገና ጥቂት ሳለ፣
በእርግጥ ጥቂትና መጻተኞች ሳሉ፣
[20]ከአንዱ ሕዝብ ወደ ሌላው ሕዝብ፣
ከአንዱም መንግሥት ወደ ሌላው
መንግሥት ተንከራተቱ::
[21]ማንም እንዲጨቍናቸው
አልፈቀደም፤
ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ፤
[22]እንዲህ ሲል፤ "የቀባኋቸውን
አትንኩ፤
በነቢያቴ ላይ ክፉ አታድርጉ::
[23]ምድር ሁሉ *ለእግዚአብሔር* ዘምሩ፤
ማዳኑንም ዕለት ዕለት ዐውጁ::
[24]ክብሩን ለአሕዛብ ተናገሩ፤
ድንቅ ሥራዎቹን ለሕዝቦች ሁሉ ንገሩ::
[25]*እግዚአብሔር* ታላቅ ነው፤
ምስጋናውም ብዙ ነው፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ሊፈራ የሚገ
ባው ነው::
[26]የአሕዛብ ሁሉ አማልክት ጣዖታት
ናቸው፤
*እግዚአብሔር* ግን ሰማያትን ሠራ::
[27]በፊቱ ክብርና ሞገስ አለ፤

[a]1 በዚህና በቍጥር 2 ላይ በትውፊት *"የሰላም መሥዋዕት"* ይባላል::

15፥28 ዘፀ19፥13፤ 1ነገ1፥39፤1ዜና9፥1፤ ዘካ4፥7
16፥1 1ዜና15፥1
16፥2 ዘፀ39፥43፤ዘኍ 6፥23-27
16፥3 ኢሳ16፥7
16፥4 1ዜና15፥2
16፥7 መዝ47፥7
16፥8 ቈላ34፤2ነገ19፥19፤መዝ107፥1፤118፥1፤136፥1
16፥9 ዘፀ15፥1፤ መዝ7፥17
16፥10 መዝ8፥1፤29፥2፤66፥2
16፥11 ቈላ10፤ 1ዜና28፥9፤2ዜና7፥14፤14፥4፤15፥2፡12፤16፥12፤18፥4፤20፥4፤34፥3 መዝ24፥6፤27፥8፤105፥4፤119፥2፡58፤ ምሳ 8፥17
16፥12 ዘዳ4፥34 ፤መዝ77፥11፤78፥43
16፥14 ኢሳ4፥4፤26፥9
16፥15 ዘፍ8፥1፤ መዝ98፥3፤111፥5፤115፥12፤136፥23
16፥16 ዘፍ12፥7፤15፥18፤22፥16-18
16፥17 ዘፍ35፥9-12
16፥18 ዘፍ13፥14-17
16፥19 ዘዳ7፥7
16፥20 ዘፍ20፥13
16፥21 ዘፍ12፥17፤20፥3፤ ዘፀ7፥15-18፤መዝ9፥5
16፥22 ዘፍ20፥7
16፥24 ኢሳ42፥12፤66፥19
16፥25 ዘፀ18፥11፤ ዘዳ 32፥39፤2 ዜና 2፥5፤መዝ18፥3፤48፥1፤76፥7፤89፥7፤135፥5፤ ኢሳ40፥25
16፥26 መዝ8፥3፤102፥25

*15፥29፤* ከ2ሳሙ 6፥16 ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይሁን እንጂ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በዚያ የተመዘገበውን ቀሪውን የዚህን ድርጊት ተከታይ ታሪክ በዚህ ክፍል አልጠቀሰውም (2 ሳሙ 6፥20-23):: አንዳንድ ሊቃውንት የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ይህን ሳይጽፍ ያለፈበት ምክንያት ምናልባት ለዳዊት ካለው ቀና አመለካከት የተነሣ ነው ይላሉ:: በሌላም አንጻር ሲታይ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ተደራስያኑ ይህን ታሪክ ቀደም ሲል የሚያውቁት መሆኑን ስለተረዳ እዚህ ላይ ሳያወሳው ማለፉም የዚያኑ ያህል ትክክል ይመስላል (የ10፥13-14፤,11፥1-3፤12፥1፤13፥6 ማብ ይመ)::
*16፥1-3፤* ዳዊት መሥዋዕቱን በመቈጣጠርና ለካህናቱ ብቻ የሚገባውን ጉባኤውን የመባረክ ተግባር በማከናወን ከካህናቱ ጋር መሥራቱን ያመለክታል (ዘኍ 6፥22-27፤ የ15፥27 ማብ ይመ):: ዳዊት ለሕዝቡ እንዲታደል ያደረገው የተጋገረና የተቀቀለ ምግብ በሕጉ መሠረት ከኅብረት መሥዋዕት ቀጥሎ የሚበላ የመሥዋዕት ክፍል ነው (ዘሌ 3፥1-17፤7፥11-21፤28-36)::
*16፥8-36፤* ከተለያዩ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች ጋር የሚመሳሰል ነው:: ስለ ቍ8-22 መዝ105፥1-15፤ ስለ ቍ23-33 መዝ96፤ ስለ ቍ34-36፤ መዝ 106፥1:47-48ን ይመ:: ይህ መዝሙር በሳሙኤል መጽሐፍ አይገኝም:: ጸሐፊው ከመዝ 105 ላይ ወስዶ ለአብርሃም ለተሰጠው ተስፋ አጽንዖት በማድረግ ይህን ረጅም ታሪካዊ ክፍል በዚህ ማምጣት ያስፈለገበት ምክንያት በተለይ የዚህ ታሪክ ተደራስያን ወገኖች ከባቢሎን ምርኮ በቅርቡ የተመለሱ እግዚአብሔርም ለአባቶቻቸው የገባውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም በቃሉ የሚጸና አምላክ ስለ መሆኑ ራሳቸው የቅ

ብርታትና ደስታም በማደሪያው ስፍራ::
28የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር ስጡ፤
ክብርና ኀይልን ለእግዚአብሔር
አምጡ::
29ለስሙ የሚገባውን ክብር ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
መባ ይዛችሁ በፊቱ ቅረቡ፤
በቅድስናውም ክብሩ ለእግዚአብሔር[a]
ስገዱ::
30ምድር ሁሉ በፊቱ ትንቀጥቀጥ፤
ዓለም በጽኑ ተመሥርታለች፤
አትናወጥምም::
31ሰማያት ደስ ይበላቸው፤ ምድር ሐሤት
ታድርግ፤
በአሕዛብም መካከል፤ "እግዚአብሔር
ነገሠ!" ይበሉ::
32ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ ይናወጥ፤
ሜዳዎችና በእርሷ ላይ ያሉ ሁሉ
ሐሤት ያድርጉ::
33ያን ጊዜ የዱር ዛፎች በእግዚአብሔር
ፊት ደስ ይላቸዋል፤
በደስታ ይዘምራሉ፤
በምድረ በዳ ላይ ሊፈርድ ይመጣልና::
34ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ፍቅሩም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል::
35 "አዳኛችን እግዚአብሔር ሆይ ታደገን፤
ለቅዱስ ስምህ ምስጋና እንድናቀርብ፣
በምስጋናህም እንድንከብር ሰብስበን፤
ከአሕዛብም መካከል ታደገን"
ብላችሁ ጩኹ::
36ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር
ምስጋና ይሁን::
ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ፣ "አሜን፤ እግዚአብሔር
ይመስገን" አሉ::
37ዳዊትም ለእያንዳንዱ ቀን በተመደበው
መሠረት ዘወትር እንዲያገለግሉ አሳፍንና
የሥራ ባልደረቦቹን በዚያው በእግዚአብሔር
ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ተዋቸው::
38እንዲሁም የቤድኤዶምና ሥልሳ ስም
ንቱ የሥራ ባልደረቦቹ አብረዋቸው እንዲ
ያገለግሉ በዚያው ተዋቸው:: የኤዶታም ልጅ
የቤድኤዶምና ሖሳ የቅጥሩ በር ጠባቂዎች ሆኑ::
39ዳዊት ካህኑን ሳዶቅንና የሥራ ባልደረ
ቦቹን ካህናት በገባዖን ከፍተኛ ቦታ ላይ በሚ
ገኘው በእግዚአብሔር ድንኳን ተዋቸው፤ 40የ
ተዋቸውም ለእስራኤል በተሰጠው ትእዛዝ
መሠረት በእግዚአብሔር ሕግ እንደ ተጻ
ፈው ሁሉ በመሠዊያው ላይ የሚቀርበውን
የሚቃጠል መሥዋዕት ሧትና ማታ በየጊ
ዜው እንዲያቀርቡ ነው:: 41እንዲሁም "ፍቅሩ
ለዘላለም ነውና" እያሉ እንዲያቀርቡ ኤማ
ንና ኤዶታም እንዲሁም ተመርጠውና ስማ
ቸው ተመዝግቦ የተመደቡ ሌሎችም አብረ
ዋቸው ነበሩ:: 42ድምፀ መለከቱንና ጸናጽሉን
ለማሰማት፣ ደግሞም መንፈሳዊ መዝሙር
ሲዘመር ለሚጠቀሙባቸው ሌሎች መሣሪ
ያዎች ኀላፊዎቹ ኤማንና ኤዶታም ነበሩ፤
የኤዶታምም ልጆች በሩን እንዲጠብቁ
ተመድበው ነበር::
43ከዚያም ሕዝቡ ተነሣ፤ እያንዳንዱም
ወደየቤቱ ሄደ:: ዳዊትም ቤተ ሰቡን ለመ
ባረክ ወደ ቤቱ ተመለሰ::

16፥28 መዝ29፥1-2
16፥29 2ዜና20፥21፤ መዝ8፥1፤29፥1-2
16፥30 መዝ2፥11፤ 33፥8፤76፥8፤93፥11 99፥1፤114፥7
16፥31 መዝ9፥7፤ 47፥8፤93፥1፤97፥11 99፥1፤146፥10፤ ኢሳ44፥23፤49፥13፤ 52፥7፤ሰቆ5፥19
16፥32 ዘፀ20፥11፤ኢሳ42፥10
16፥33 1ሳሙ2፥10፤ መዝ7፥8፤96፥10፤ 98፥9፤110፥6፤ ኢሳ2፥4፤ 14፥8፤55፥12
16፥34 ቁ8፤ 2ዜና 5፥13፤7፥3፤ዕዝ3፥11፤ መዝ 25፥7፤ 34፥8፤ 100፥5፤105፥1፤ 135፥3 136፥1-26፤145፥9፤ ኢሳ12፥4፤ ኤር33፥11፤ናሆ1፥7
16፥35 ዘዳ32፥15፤መዝ18፥4 6፤38፥22፤ሚክ7፥7
16፥36 1ነገ8፥15፤ መዝ72፥18-19
16፥37 2ዜና8፥14
16፥38 1ዜና13፥13 ፤26፥4-5፡10፤
16፥39 ኢሱ9፥3፤ 1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ8፥ 17፤1ዜና12፥28፤ 2ዜና1፥3
16፥40 ዘፀ29፥38፤ ዘኍ28፥1-8
16፥41 1ዜና15፥19
16፥42 1ዜና25፥31 2ዜና7፥6
17፥1 1ዜና15፥1
17፥2 1ዜና22፥7፤ 28፥2፤2ዜና6፥7
17፥4 1ዜና22፥10፤28፥3
17፥6 1ዜና14፥1
17፥7 2ሳሙ6፥21

## እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው ተስፋ

17፥1-15 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 7፥1-17

17 ዳዊት በቤተ መንግሥቱ ተደላድሎ በተ
ቀመጠበት ጊዜ፣ ነቢዩ ናታንን "እነሆ
እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ውስጥ እኖራለሁ፤
የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት ግን በድንኳን
ውስጥ ይኖራል" አለው::
2ናታንም ለዳዊት፣ "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር
ስለ ሆነ፣ ያሰብከውን ሁሉ አድርግ" ሲል መለ
ሰለት::
3በዚያም ሌሊት የእግዚአብሔር ቃል ወደ
ናታን መጥቶ እንዲህ አለው፤
4"ሂድና ለባሪያዬ ለዳዊት እንዲህ
ብለህ ንገረው፤ 'እግዚአብሔር የሚለው
ይህን ነው፤ እኔ የምኖርበትን ቤት
የምትሠራልኝ አንተ አይደለህም::
5እስራኤልን ከግብፅ ካወጣሁበት ቀን
ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ፣ ከአንዱ ድን
ኳን ወደ ሌላው ድንኳን፣ ከአንዱ ማደ
ሪያ ወደ ሌላው ማደሪያ እሄድ ነበር
እንጂ፣ በቤት ውስጥ አልኖርሁም::
6ከእስራኤላውያን ጋር በሄድሁባቸው
ቦታዎች ሁሉ፣ ሕዝቤን እንዲጠብቁ
ላዘዝኋቸው መሪዎቻቸው[b] ከቶ፣ "ለምን
ከዝግባ ዕንጨት ቤት አልሠራችሁል
ኝም ያለሁበት ጊዜ አለን?"
7"እንግዲህ አሁንም ለባሪያዬ ለዳ
ዊት እንዲህ ብለህ ንገረው፤ 'የሰራዊት
ጌታ እግዚአብሔር የሚለው ይህን ነው፤
'የሕዝቤ የእስራኤል ገዥ እንድትሆን

[a]29 ወይም፣ "ከክብሩ ጋር ለእግዚአብሔር"

ርብ ምስክሮች መሆናቸውን ለማስገንዘብ ነው:: ከመዝ 106 ላይ መጥቀሱም ከተበተኑባቸው ሕዝቦች ተሰብስበው ነጻነታቸውን በቅርቡ ያገኙ በመሆናቸው የእግዚአብሔር ታማኝነት ለእነርሱ ወቅታዊ እውነት መሆኑን ለማሳሰብ ነው (ቍ:35)::

*16፥29 በቅድስናውም ክብሩ፤* የመዝ 29፥2 ማብ ይመ::

*16፥39 በገባዖን..በእግዚአብሔር ድንኳን፤* ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ያነጻው ቤተ መቅደስ ተሠርቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ (2ዜና 1፥13፡5፥5) የምስክሩ ድንኳን በገባዖን ተቀምጦ ነበር፤ ከዚያም ወደ ቤተ መቅደሱ ተዛውሮአል:: የእነዚህ የሁለቱ ቤተ መቅደሶች ማለት የምስክሩ ድንኳንና በኢየሩሳሌም የተሠራው ጊዜያዊ የታቦቱ ማረፊያ መኖር (ቍ:1) በአንድ ጊዜ ሁለት ሊቃነ ካህናት እንዲሾሙ ምክንያት ሆኖአል:: ስለዚህም ሳዶቅ በገባዖን፣ አብያታር በኢየሩሳሌም (18፥16፤27፥34፤ የ6፥8 ማብ ይመ) አገልግለዋል::

16፥42 *ድምፀ መለከቱንና..ለማሰማት፤* ዘኍ 10፥1-10 ይመ::

*17፥1-27* 2ሳሙ 7 እና ማብ ይመ

*17፥1፡10* በዚህ ክፍል ዳዊት ከጠላቶቹ ጋር ከመዋጋት ማረፉን የሚያመለክተውን ሐሳብ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እንዳለ ትቶታል (2ሳሙ7፥1፡11):: ለዚህም አያሌ ምክንያቶች አሉ፤ (1) የዳዊት ዋና ዋና የጦርነት ታሪኮች ገና ወደፊት የሚፈጸሙ ናቸው (ም 18-20)፤ እንደ ቅደም ተከተሉ ተራ ከሆነ ይህ ክፍል የጦርነቶቹን ታሪክ ተከትሉ መምጣት ነበረበት፤ ሆኖም ጸሓፊው ይህን እዚህ ላይ ያስገባው ስለ ታቦቱና ስለ ቤተ መቅደሱ ሕንጻ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ለመቀጠል ፍላጎት ስላለው ብቻ

በጎችን ከመጠበቅና ከመከተል አንሥቼ
ወሰድሁህ:: [8]በሄድህበት ሁሉ ከአንተ
አልተለየሁም፤ ጠላቶችህንም ሁሉ
ከፊትህ አጠፋሁልህ፤ አሁንም ስምህን
እንደ ምድር ታላላቅ ሰዎች ስም ገናና
አደርገዋለሁ:: [9]ለሕዝቤ ለእስራኤል
መኖሪያ ስፍራ እሰጠዋለሁ፤ የራሳቸ
ውም መኖሪያ ስፍራ እንዲኖራቸው
ከእንግዲህም በኋላ እንዳይናወጡ አደ
ርጋቸዋለሁ:: ክፉ ሰዎች በመጀመሪያ
እንዳደረጉት ሁሉ፣ ከእንግዲህ አይጨ
ቍኗቸውም፤ [10]ከዚህ ቀደም በሕዝቤ
በእስራኤል ላይ መሪዎች በሾምሁ ጊዜ
ጨቋኞቹ ያደረጉትን ዛሬ አያደርጉ
ትም፤ ጠላቶቻችሁን ሁሉ አዋርዳቸዋለሁ::
" 'እግዚአብሔር ቤት እንደሚሠራ
ልህ በግልጽ እነግርሃለሁ፤ [11]ዘመንህን
ጨርሰህ ወደ አባቶችህ በምትሄድበት
ጊዜ፣ ከአብራክህ ከተከፈሉት ልጆችህ
አንዱ በእግርህ እንዲተካ አደርጋለሁ፤
መንግሥቱንም አጸናለታለሁ፤ [12]ቤት
የሚሠራልኝም እርሱ ነው፤ እኔም ዙፋ
ኑን ለዘላለም አጸናለሁ:: [13]አባት እሆ
ነዋለሁ፤ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤ ጽኑ
ፍቅሬን ከአንተ በፊት ከነበረው ላይ
እንደወሰድሁ፣ ከእርሱ ላይ ከቶ አል
ወስድም:: [14]በቤቴና በመንግሥቴ ላይ
ለዘላለም አኖረዋለሁ፤ ዙፋኑም ለዘላ
ለም ይጸናል::" '
[15]ናታንም የዚህን ሁሉ ራእይ ቃል ለዳ
ዊት ነገረው::

### የዳዊት ጸሎት

17፥16-27 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 7፥18-29

[16]ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ገባ፤ በእግዚአ
ብሔር ፊት ተቀምጦም እንዲህ አለ፤
"እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ ለመሆኑ
እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ?
ቤተ ሰቤስ ምንድን ነው? [17]አምላክ
ሆይ፤ ይህ በፊትህ በቂ እንዳልሆነ ቈጥ
ረህ ስለ ወደፊቱ የባሪያህ ቤት ተናገ
ርህ:: እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ እኔ
ንም ከሰዎች ሁሉ እጅግ የከበረ ሰው
አድርገህ ተመለከትኸኝ::
[18]"ባሪያህን ስላከበርኸው፣ ዳዊት ከዚህ
በላይ ምን ማለት ይችላል? ባሪያህን
እኮ ታውቀዋለህ፤ [19]እግዚአብሔር ሆይ፤
ስለ ባሪያህ ብለህና እንደ ፈቃድህም
መሠረት ይህን ታላቅ ነገር አድርገሃል፤
እነዚህም ታላላቅ ተስፋዎች ሁሉ እንዲ
ታወቁ አደረግህ::
[20]"አቤቱ፤ እንደ አንተ ያለ የለም፤
በጆሮአችን እንደ ሰማነው ሁሉ ከአንተ
በቀር አምላክ የለም' [21]ከግብፅ ተቤዥተህ
እንዳወጣኸው እንደ ሕዝብህ እንደ እስ
ራኤል ያለ ማን አለ? እነርሱ እግዚ
አብሔር ለራሱ ሊቤዣቸው ከምድር ሕዝ
ቦች መካከል የመርጣቸው ናቸው፤ በሕ
ዝብህም ፊት ታላላቅና አስፈሪ ነገሮ
ችን በማድረግ መንግሥታትን በፊታቸው
አሳደድህ:: [22]ሕዝብህንም እስራኤልን ለዘላ
ለም የራስህ ሕዝብ አደረግኸው፤ እግዚአ
ብሔር ሆይ፤ አንተም አምላክ ሆንህለት::
[23]"እግዚአብሔር ሆይ፤ አሁንም ስለ
ባሪያህና ስለ ቤቱ የሰጠኸው ተስፋ
ለዘላለም የጸና ይሁን፤ የሰጠኸውንም
ተስፋ ፈጽም፤ [24]ይህም ስምህ ጸንቶ እን
ዲኖርና ለዘላለምም ታላቅ እንዲሆን
ነው:: ከዚያም ሰዎች "የእስራኤል አም
ላክ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር በእው
ነት የእስራኤል አምላክ ነው!" ይላሉ፤
የባሪያህ የዳዊትም ቤት በፊትህ የጸና
ይሆናል::
[25]"አምላኬ ሆይ፤ ቤት እንደምትሠራ
ለት ለባሪያህ ገልጸህለታል፤ ስለዚህ ባሪ
ያህ ወደ አንተ ለመጸለይ ድፍረት አገኘ::
[26]እግዚአብሔር ሆይ፤ በእውነት አንተ
አምላክ ነህ፤ ይህንንም መልካም ተስፋ
ለባሪያህ ሰጥተሃል:: [27]በፊትህ ለዘላለም
እንዲኖር አሁንም የባሪያህን ቤት ልት
ባርክ ወደሃል፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ የባ
ረክኸው አንተ ስለ ሆንህ፣ ለዘላለም
የተባረከ ይሆናል::"

17፥10 መሳ2፥16
17፥12 1ነገ5፥5፤1ዜና22፥10፤ 2ዜና7፥18፤13፥5
17፥13 1ዜና28፥6፤ሉቃ1፥32፤2ቆሮ6፥18፤ዕብ1፥5
17፥14 1ነገ2፥12፤1ዜና28፥5፤ 29፥23፤2ዜና9፥8፤ መዝ132፥11፤ ኢሮ33፥17
17፥19 2ሳሙ7፥16-17:25፤ 2ነገ20፥6፤ኢሳ9፥7፤ 37፥35፤55፥3
17፥20 ዘፀ8፥10፤ 9፥14፤15፥11፤ ኢሳ44፥6፤46፥9
17፥21 ዘዐ6፥6
17፥22 ዘፀ19፥5-6
17፥23 1ነገ8፥25
17፥27 መዝ16፥11፤21፥6

[x]በዚህና በቍጥር 10 ላይ በትውፊት፣ "መሳፍንት" ይባላል

ነው (ቍ 4-6:12)::(2) እንዲሁም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ "የሰላምና የዕረፍት ሰው" ከሆነውና (22፥9) ቤተ መቅደሱን ከሠራው (22፥10) ከሰሎሞን ጋር በማነጻጸር ዳዊትን የሚመለከተው ከዕድሜው አብዛኛውን ክፍል በውጊያ እንዳሳለፈ የጦር ሰው አድርጎ ነው (22፥6-8):: እንደ ዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዳዊት ከጠላቶቹ ዕረፍት ያገኘው በዕድሜው መጨረሻ ላይ ብቻ ነው (22፥ 18):: (3) ዳዊትንና ሰሎሞንን ከሙሴና ከኢያሱ ጋር ለማነጻጸር ስለፈለገም ሰሎሞን እንደ ኢያሱ ሁሉ ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው አሳርፎአቸዋል (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል" የሚለውን ይመ)::

*17፥12-14፤* በእዚህ ክፍል የተጻፉት ቃላት የሚያወሱት ስለ ሰሎሞን ቢሆንም፣ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ግን ለክርስቶስ ተጠቅመውበታል (ማር1፥11፤ሉቃ 1፥32-33፤ ዕብ1፥5)::

*17፥13፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሰሎሞን ቢያጠፋ በበትር ወይም በአለንጋ እንደሚቀጣ የታሪኩ ምንጭ በሆነው (2ሳሙ፡ 7፥14) ላይ የሚገኘውን ክፍል ሳይጠቀስ አልፎታል:: ምክንያቱም ሰሎሞንን የመሲሑ ምሳሌ ስላደረገውና፤ እንዲህ ያለውም ቅጣት ለመሲሑ ባሕርይ የማይስማማ መሆኑን ለማንጸባረቅ ነው (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል" ገጽታ የሚለውን ይመ)::

*17፥14፤* የታሪኩ ምንጭ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውንና "ቤትህና መንግሥትህ" የሚለውን (2ሳሙ:7፥16)፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን "ቤቴና መንግሥቴ" ብሎታል ይህ ሐረግ እግዚአብሔር የሕዝቡ ገዥ መሆኑን በአጽንዖት የሚያሳይ ነው፤ የሚገኘውም በዜና መዋዕል መጻሕፍት ብቻ ሲሆን በብዙ ቦታ ተጠቅሷል (28፥5-6፤29፥23፤ 2ዜና1፥11፤9፥8፤13፥4-8)::

17፥16 *ተቀምጦም፤* በ2ሳሙ 7፥18 ላይ ከሚገኘው ተመሳሳይ ታሪክ ውጭ እንዲህ ሆኖ ለጸሎት መቀመጥ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሰው በ1ነገ 19:4 ላይ ብቻ ነው

*17፥21-22* እዚህ ላይ የእስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት የመውጣት ታሪክ መጠቀሱ፣ የዜና መዋዕለ መጽሐፍ ተደራስያን ከምርኮ የተመለሰው ሕዝብ፣ታላቁንና ሁለተኛውን የመውጣት ታሪክ ከባቢሎን ምርኮ መላቀቃቸውን ለማሳሰብ ነው::

*18፥1-8፥20* ዳዊት ያደረጋቸውን ጦርነቶች የሚያወሣው ታሪክ በዘመነ መንግሥቱ እግዚአብሔር ያደረገለትን በረከት ለማሳየት የሚያገለግል ነው፤ ጠላቶቹ እንዲገዙለት በማድረግ እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን ተስፋ ጠብቆለታል (17፥10):: ይህ

## ዳዊት የተቀዳጃቸው ድሎች

18፥1-13 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 8፥1-14

**18** ከዚህ በኋላ ዳዊት ፍልስጥኤማው
ያንን ድል መትቶ ተገዥ አደረጋ
ቸው፤ ጌትንና በዙሪያዋም የሚገኙትን መን
ደሮች ከፍልስጥኤማውያን እጅ ወሰደ።
2እንዲሁም ዳዊት ሞዓባውያንን ድል አደ
ረጋቸው፤ እነርሱም ገባሮቹ ሆኑ፤ ግብርም
አመጡለት።
3ከዚህም በላይ ዳዊት በኤፍራጥስ ወንዝ
አጠገብ የነበረውን ግዛት ለመቈጣጠር በሄደ
ጊዜ፣ የሱባን ንጉሥ አድርአዛርን እስከ ሐ
ማት ድረስ ዘልቆ ወጋው። 4ዳዊትም አንድ
ሺህ ሠረገላ፣ ሰባት ሺህ ፈረሰኛና ሃያ ሺህ
እግረኛ ወታደር ማረከ፤ አንድ መቶ የሠረ
ገላ ፈረሶች ብቻ አስቀርቶ የቀሩትን ቋን
ጃቸውን ቈረጠ።
5ሶርያውያንም የሱባን ንጉሥ አድርአዛርን
ለመርዳት ከደማስቆ በመጡ ጊዜ፣ ከእነርሱ
ሃያ ሁለት ሺህ ሰው ገደለ። 6ከዚያም በሶ
ርያ ግዛት ውስጥ ባለችው በደማስቆ የጦር
ሰፈር አቋቋመ፤ ሶርያውያን ገባሮቹ ሆኑ፤
ግብርም አመጡለት። እግዚአብሔርም ዳዊ
ትን በሄደበት ሁሉ ድል አጐናጸፈው።
7ዳዊትም የአድርአዛር ጦር አለቆች ያነገቡ
ትን የወርቅ ጋሻ ወሰደ፤ ወደ ኢየሩሳሌምም
አመጣው። 8ዳዊት ከአድርአዛር ከተሞች ከጢ
ብሐትና ከኩን እጅግ ብዙ ናስ ወሰደ፤ ሰሎ
ሞን የናሱን ባሕር፣ ዐምዶቹንና ልዩ ልዩ
የናስ ዕቃዎቹን የሠራው በዚሁ ነበር።
9የሐማት ንጉሥ ቶዑ ዳዊት የሱባን ንጉሥ
የአድርአዛርን ሰራዊት ሁሉ ድል እንደ መታ
ሲሰማ፣ 10እጅ እንዲነሣውና ደስታውንም
እንዲገልጥለት ልጁን አዶራምን ወደ ንጉሥ
ዳዊት ላከው፤ ቶዑ ከአድርአዛር ጋር ብዙ
ጊዜ ጦርነት ገጥሞ ነበር። አዶራምም ከወ
ርቅ፣ ከብርና ከናስ የተሠሩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች
አመጣለት።
11ንጉሥ ዳዊት ከኤዶም፣ ከሞዓብ፣ ከአ
ሞናውያን፣ ከፍልስጥኤማውያንና ከአማሌ
ቃውያን ከእነዚህ ሁሉ መንግሥታት የማረ
ከውን ወርቅና ብር ከዚህ ቀደም እንዳደረ
ገው ሁሉ፣ እነዚህንም ዕቃዎች ለእግዚአ
ብሔር ቀደሰ።
12የጽሩያ ልጅ አቢሳ በጨው ሸለቆ ዐሥራ
ስምንት ሺህ ኤዶማውያን ገደለ። 13እርሱም በኤ
ዶም የጦር ሰፈሮች አቋቋመ፤ ኤዶማውያ
ንም ሁሉ ለንጉሥ ዳዊት ገባሮች ሆኑ።
እግዚአብሔርም ዳዊትን በሄደበት ሁሉ
ድል አጐናጸፈው።

## የዳዊት ሹማምት

18፥14-17 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 8፥15-18

14ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ፤
ለሕዝቡም ሁሉ ፍትሕንና ጽድቅን አሰፈነላ
ቸው። 15የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የሰራዊቱ
አዛዥ ነበረ፤ የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥ
ደግሞ የቤተ መዛግብቱ ኀላፊ ነበረ። 16የአ
ኪጦብ ልጅ ሳዶቅና የአቤሜሌክ ልጅ አብ
ያታር ካህናት ነበሩ፤ ሱሳ ደግሞ ጸሓፊ
ነበረ። 17የዮዳሄ ልጅ በናያስ የከሊታውያ
ንና የፈሊታውያን አዛዥ ነበረ። የዳዊት
ወንዶች ልጆቹ ደግሞ ከንጉሡ ቀጥሎ
የበላይ ሹማምት ነበሩ።

18፥2 ዘኍ 21፥29
18፥3 ዘፍ 2፥14፤1ዜና 19፥6
18፥4 ዘፍ 49፥6
18፥5 2ነገ 16፥9
18፥8 1ነገ 7፥23፤2ዜና 4፥2-5
18፥11 ዘኍ 24፥18፡20
18፥12 1ነገ 11፥15
18፥14 1ዜና 11፥1፤29፥26
18፥15 2ሳሙ 5፥6-8
18፥16 1ዜና 6፥8፤24፥6
18፥17 1ሳሙ 30፥14፤ 2ሳሙ 15፥18

ታሪክ በተለይም በድኅረ ምርኮ ነቢያት ዘመን እያደገ ከመጣው ዋና ሐሳብ ጋር የሚጣጣም ነው። ይኸውም የመንግሥታት ብርና ወርቅ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚጐርፉና ጠላት ከሆኑት ሕዝቦች በሚመጣው የግብር ገንዘብ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሚታነጽ የሚናገር ነው (18፥7-8፤ 11፤22፥2-5፡14-15፤ ከሐጌ 2፥1-9፤20-23፤ ዘካ 2፥7-13፤6፥9-15፤14፥12-14 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ምንባብ በአንድ በኩል እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን በረከት በግልጽ ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዘገባውን በማስከተል ዳዊት የጦር ሰው ስለነበር፣ ቤተ መቅደሱን መሥራት እንዳልቻለ ይገልጻል (22፥6-8፤28፥3)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እዚህ ላይ ለቀረበው ታሪክ ምንጩ ያደረገው መጽሐፈ ሳሙኤልን ነው። ዋናው ልዩነት የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በመጽሐፉ ውስጥ ያስገባቸው የተለወጡ ታሪኮች መኖራቸው ሳይሆን፣ በመጽሐፉ ውስጥ እንዲገቡ ስላልፈለገ የተዋቸው ነገሮች መኖራቸው ነው። በተለይ 2ሳሙ 9፤11፥2-12፥25 የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በመጽሐፉ ውስጥ ሊያሳይ ከፈለገው የዳዊት ገጽታ ጋር አብረው የማይሄዱለትን ታሪኮች እንዳለ ትቶአቸዋል።

*18፥1-13፤* 2ሳሙ 8፥1-14 እና ማብ ይመ።

*18፥2፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በ2ሳሙ 8፥2 ላይ በሞአባውያን ላይ ስለ ተፈጸመው የጭካኔ ተግባር የተጻፈውን አያወሳውም፤ ምክንያቱም እንዲህ ዐይነቱን የጭካኔ ተግባር መዘገቡን የተወው በጐ ገጽታውን ያጐድፍብኛል ብሎ ይሆናል።

18፥5 *ሶርያውያንም፤* ከሳኦል ጠላቶች መካከል አንዱ መሆናቸው ተጠቅሷል (1ሳሙ 14፥47 "ሱባ")። በዳዊት ዘመን ሰሜኑና (ሱባ) ደቡቡ (ቤት ሮዖብ) በአድርአዛር ሥር አንድ ሆነዋል (2ሳሙ 10፡6)። የሰሜኑ መንግሥት እንደ እነርሱ ከመውደቁ ጥቂት ቀደም ሲል (2ነገ 16፥7-9) በአሦራውያን እስከወደቀበት ጊዜ ድረስ ለሁለት መቶ ዓመት ያህል የእስራኤል ጠላት ሆነው ኖረዋል።

18፥8 *ከጢብሐትና ከኩን፤* በሊባኖስና በሊባኖስ ትይዩ የተራራ ሰንሰለቶች መካከል ባለው ረባዳ ስፍራ የነበሩ ከተሞች ናቸው። *ሰሎሞን...ልዩ ልዩ የናስ ዕቃዎቹን የሠራው፤* 2ዜና 4፥2-5፡18 ይመ።

18፥12 *አቢሳ፤* 2ሳሙ 8፥13 የሚናገረው ስለ ዳዊት ብቻ ነው (1ነገ 11፥15-16፤ የመዝ 60 ርእስ ይመ)።

*18፥15-17፤* የእነዚህ በዳዊት ቤተ መንግሥት የሚያገለግሉት የጦር መኰንኖች ማዕረግና ተግባር በግብጽ አገር ፈርዖንን እንዲያገለግሉ ከተመደቡት መኰንኖች አደረጃጀት የተቀዳ ሳይሆን አይቀርም።

*18፥15፤* ኢዮአብ የሰራዊቱ የጦር አለቃ ለመሆን እንዴት እንደቻለ ታሪኩን በ11፥4-6፤2ሳሙ 5፥6-8 ላይ ይመ።

18፥16 *ሳዶቅና.. የአቤሜሌክ፤ ልጅ አብያታር* የ6፥8፤ 16፥39 የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ።

*18፥17 የከሊታውያንና የፈሊታውያን፤* እነዚህ ለቤተ መንግሥቱ የክብር ዘብ ጥበቃ ከሌሎቹ ጋር የተመደቡ የውጭ ቅጥረኞች ናቸው (2ሳሙ 8፥18፤20፥23፤ የ1ሳሙ 30፥14 ማብ ይመ)። አቤሴሎም (2ሳሙ 15፥18) እና ሳቤዔ (2ሳሙ 20፡7) በዳዊት ላይ ዐምፀው በተነሡ ጊዜ እነዚህ ሰዎች ለዳዊት ታማኞች የነበሩ ሲሆኑ፣ ሰሎሞን የአባቱን ዙፋን በመተካት እንዳይነግሥ አዶንያስ በተቀናቀነው ጊዜም ረድተውታል (1ነገ 1፥38፡44) *የበላይ ሹማምት፤* ይህን ነጥብ በተመለከተ ጥንታዊው ታሪክ የተጠቀመበት ቃል ከመደበኛው የዕብራይስጥ ቋንቋ "ካህናት" ተብሎ የተተረጐመውን ነው (የ2ሳሙ 8፥18 ማብ ይመ)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ይህን ስያሜ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከማዋል ይልቅ ለሕዝባዊው አገልግሎት ተጠቅሞበታል፤ በመሠረቱ ለዚህ ክፍል ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች ቀርበዋል፤ እነዚህም (1) አንዳንድ ምሁራን የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እርሱ በነበረበት ዘመን ሁሉ፣ ሕጋዊ ሆኖ እንዲጠበቅለት የፈለገውን ካህንነት ለሌዋውያኑ ብቻ የተወሰነ ተግባር መሆኑን ማመልከቱ ነው ይላሉ። (2) ሌሎች ደግሞ በ2ሳሙ 8፥18 ላይ ያለው በዕብራይስጡ ቃል ካህን ከሚለው ቃል ሰፋ ያለ ትርጕም ስለ ነበረው፣ ለሌሎች ሹማምትም በጥቅም ላይ መዋሉን ይናገራሉ። (ከ2ሳሙ 20፥26፤ ከ1ነገ 4፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። በዘመኑ በዕብራይስጥ "ካህን" የሚለው ቃል

## ከአሞናውያን ጋር የተደረገ ጦርነት

19፥1-19 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 10፥1-19

19 ከዚህ በኋላ የአሞናውያን ንጉሥ
ናያስ ሞተ፤ ልጁም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ:: 2 ዳዊትም፣ “አባቱ ለእኔ በጎ ነገር
እንዳደረገልኝ እስቲ እኔም ለናያስ ልጅ
ለሐኖን በጎ ነገር ላድርግለት” ብሎ አሰበ::
ስለዚህ ዳዊት ስለ አባቱ ሞት ሐዘኑን ለመ
ግለጽ ወደ ሐኖን መልክተኞችን ላከ::
የዳዊት ሰዎች ሐዘናቸውን ለመግለጽ ሐኖን
ወደሚኖርበት ወደ አሞናውያን ምድር በመጡ
ጊዜ፣ 3 የአሞናውያን መኳንንት ለሐኖን
“ዳዊት ሐዘኑን ለመግለጽ ሰዎችን ወደ አንተ
የላከው አባትህን አክብሮ ይመስልሃልን? ሰዎቹ
ወደ አንተ የመጡት አገሪቱን ለመመርመር፣
ለመሰለልና ለመያዝ አይደለምን?” አሉት:: 4 ስለ
ዚህ ሐኖን የዳዊትን ሰዎች ይዞ ላጫቸው፤
ልብሳቸውንም እስከ መቀመጫቸው ድረስ
መኻል ለመኻል ቀዶ ሰደዳቸው::
5 በሰዎቹ ላይ የደረሰባቸውን ዳዊት በሰማ
ጊዜ እጅግ ዐፍረው ስለ ነበር፣ ወደ እነርሱ
መልክተኞችን ላከ፤ ንጉሡም፣ “ጢማችሁ እስ
ኪያድግ ድረስ በኢያሪኮ ቈዩና ከዚያ በኋላ
ትመጣላችሁ” አለ::
6 አሞናውያን በዳዊት ዘንድ እንደ ተጠሉ
ባወቁ ጊዜ፣ ሐኖንና አሞናውያን ከመስጴ
ጦምያ[1]፣ ከአራምመዓካና ከሱባ ሠረገሎች
ንና ፈረሰኞችን ለመከራየት አንድ ሺህ
መክሊት[መ] ብር ላኩ፤ 7 ከዚያም ሠላሳ ሁለት
ሺህ ሠረገሎችንና ፈረሰኞችን እንዲሁም
የመዓካን ንጉሥና ወታደሮች በገንዘብ ቀጠሩ፤
እነርሱም መጥ ተው በሜድባ አጠገብ ሲሰፍሩ፣
አሞናውያን ደግሞ ከየከተሞቻቸው ተሰብስ
በው ለጦርነት ወጡ::
8 ዳዊት ይህን ሲሰማ ኢዮአብንና መላውን
ተዋጊ ሰራዊት ላከ:: 9 አሞናውያንም መጥ
ተው ወደ ከተማቸው በሚያስገባው በር
ላይ ለጦርነት ተሰለፉ፤ የመጡት ነገሥታት
ደግሞ ብቻቸውን በሜዳው ላይ ነበሩ::
10 ኢዮአብም ከፊቱና ከኋላው ጦር መኖሩን
አየ፤ ስለዚህ በእስራኤል የታወቁትን ጀግ
ኖች መርጦ ሶርያውያንን እንዲገጥሙ አሰ
ለፋቸው:: 11 የቀሩትም ሰዎች በወንድሙ በአ
ቢሳ ሥር ሆነው አሞናውያንን እንዲገጥሙ
አሰለፋቸው:: 12 ኢዮአብም እንዲህ አለ፤
“ሶርያውያን ከበረቱብኝ አንተ ትረዳኛለህ፤
አሞናውያን ከበረቱብኝ ደግሞ እኔ እረዳ
ሃለሁ:: 13 እንግዲህ በርቱ፤ ስለ ሕዝባችንና ስለ
አምላካችን ከተሞች ብለን በጀግንነት እንዋጋ፤
እግዚአብሔርም ደስ ያሰኘውን ያድርግ::”
14 ከዚያም ኢዮአብና አብረውት ያሉት
ወታደሮች ሶርያውያንን ለመውጋት ወደ ፊት
ገሠገሡ፤ ሶርያውያንም ከፊታቸው ሸሹ:: 15 አሞ
ናውያንም ሶርያውያን መሸሻቸውን ሲያዩ፣ እነ
ርሱም ከወንድሙ ከአቢሳ ፊት ሸሽተው ወደ
ከተማዪቱ ገቡ፤ ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ተመለሰ::
16 ሶርያውያን በእስራኤል መሸነፋቸውን
ሲያዩ፣ መልክተኞችን ልከው ከኤፍራጥስ
ወንዝ ማዶ ያሉትን ሶርያውያን አስመጡ፤
እነዚህንም የሚመራቸው የአድርአዛር ሰራ
ዊት አዛዥ ሾፋክ ነበረ::
17 ዳዊት ይህን ሲሰማ፣ እስራኤልን ሁሉ
ሰብስቦ ዮርዳኖስን ተሻገረ፤ ወደፊት በመገ
ሥገሥም ከፊት ለፊታቸው የውጊያ መሥ
መሩን ያዘ:: ዳዊትም ሶርያውያንን ጦርነት
ለመግጠም ወታደሮቹን አሰለፈ፤ እነርሱም
ተዋጉት:: 18 ይሁን እንጂ ከእስራኤል ፊት
ሸሹ:: ዳዊትም ሰባት ሺህ ሠረገለኞችና አርባ
ሺህ እግረኛ ወታደሮች ገደለ:: የሠራዊታ
ቸው አዛዥ ሾፋክም በጦርነቱ ላይ ሞተ::
19 የአድአዛርም ሹማምት በእስራኤል መሸነ
ፋቸውን ሲያዩ፣ ከዳዊት ጋር ታረቁ፤ ገባሮ
ቹም ሆኑ::
ስለዚህ ሶርያውያን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ
አሞናውያንን ለመርዳት ፈቃደኞች አልሆኑም::

## የራባ ከተማ መያዝ

20፥1-3 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 11፥1፤12፥29-31

20 ነገሥታት ለጦርነት በሚሄዱበት በጸ
ደይ ወራት፣ ኢዮአብ የጦር ሰራዊቱን
እየመራ ሄዶ የአሞናውያንን አገር አጠፋ፤
ወደ ራባትም ሄዶ ከበባት፤ ዳዊት ግን ኢየሩ

19፥1 ዘፍ19፥38፤መሳ10፥1
7፤11፥33፤2ዜና20፥1-
2፤ሶፎ2፥8-11
19፥3 ዘኍ21፥32
19፥6 ዘፍ34፥30፤1ዜና18፥3
19፥7 ዘኍ21፥30
19፥11 1ሳሙ26፥6
19፥17 1ዜና9፥1
20፥1 ዘዳ3፥11፤ አሞ1፥13-15

[1] 6 ሰሜን ምዕራብ ባሕር መስጴጦምያ ነው
[መ] 6 34 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ የተመደበ ስለ ነበር፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ተመሳሳይ በሆነ ሌላ ቃል ተጠቅሞአል:: *የሰብዓ ሊቃናት* ትርጒም፣ ታርጒም የተሰኘው የአይሁድ፣ ትርጓሜ መጽሐፍ የጥንቱ ሮማይስጥና የሲፍ ወልደ ኮርዮን ይህን ቃል የተረጠ ጒሙት “ካህን” ከሚለው ቃል ይልቅ ሌላ ፍች በመ ስጠት ነው::

*19፥1-20፥31* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር የፈጸመውን ዝሙት (11፥2-12፥25) ሳይጠቀስ ከማለፉ በስ ተቀር፣ የተከተለው በ2ሳሙ10-12 የተጻፈውን ታሪክ ነው (የዚ ያኑ ማብ ይመ):: አሞናውያንና እስራኤላውያን የብዙ ዘመን ጠላ ቶች ነበሩ(2ዜና20፥1-2፡23፤7፥5፤መሳ3፥13፤10፥7-9፤10፥17-11፥33፤ 1ሳሙ11፥1-13፤14፥47፤2ነገ10፥32-33፤ኤር49፥1-6፤ሶፎ2፥8-11):: ከምርኮ መልስ በኋላም እንኳ አሞናዊው ጦብያ ኢየሩሳሌምን አውኮአት ነበር (ነሀ2፥19፤4፥3፡7፤6፥1፡12፡14፤13፥4-9)::

*19፥1 ናያስ፤* ምናልባት የሳኦል ጠላት የነበረው ሰው ወይም የዚያ ሰው ዝርያ ሳይሆን አይቀርም (1ሳሙ11፥1)::

19፥6 *ከመስጴጦምያ ከአራም መዓካና ከሱባ፤* 2ሳሙ 10፥6 ቤትሮዖብንና ጦብን ይጨምራቸዋል:: እነዚህ ሁሉ አገ ሮች የሚገኙት ከእስራኤል በስተሰሜንና በስተሰሜን ምሥራቅ ሲሆን፣ ከሁሌህ ምድር ሐይቅ አንሥቶ እስከ ሊባኖስ ትይዩ ድረስ ከዚያም ዐልፎ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ መውጫ መግ ቢያ በማሳጣት የማያፈናፍኑ ነበሩ::

*19፥7 በሜድባ፤* በሞዓብ ምድር የምትገኝ በአሞናውያን እጅ የነበረች መንደር ሳትሆን አትቀርም::

*19፥9 ከተማቸው፤* ራባት የምትባለዋ የመናገሻ ከተማቸው ስትሆን፣ በሚቀጥለውም ዓመት ኢዮአብ ከቦአታል (20፥1-3)::

19፥18 *ሰባት ሺህ፤* በ2ሳሙ10፥18 ላይ የተጻፈው ሰባት መቶ ተብሎ ነው:: ከአንዱ ጥቅልል ብራና ወደ ሌላው ሲገለበጥ በእጅ የገለበጠው ሰው ስሕተት መሥራቱ የተረጋገጠ ነው::

*20፥1 ነገሥታት ለጦርነት በሚሄዱበት፤* የጸደይ ወቅት አዝመራ እንደተሰበሰበ ወዲያውኑ የእርሻው ሥራ ጋብ ሲልና የሚንቀሳቀሰው ተዋጊ ሠራዊት የሚያስፈልገውን ምግብ እንደ ልብ ማግኘት የሚችልበት ወቅት ነው:: ረባትም፤ የ19፥9 ማብ ይመ:: ረባት ባሁኑ ጊዜ የዮርዳኖስ ዋና ከተማ አማን የተቈረቈ ረችበት ስፍራ ነው::

ሳሌም ቀርቶ ነበር። ኢዮአብም ራባትን
ወግቶ አፈራረሳት፤ 2ዳዊት የንጉሣቸውን
ዘውድ ከራሱ ላይ ወሰደ፤ ክብደቱም አንድ
መክሊት[መ] ወርቅ ነበረ፤ ይህንንም በዳዊት
ራስ ላይ ጫኑለት፤ እንዲሁም ከከተማዪቱ
እጅግ ብዙ ምርኮ ወሰደ። 3በዚያ የነበረ
ውንም ሕዝብ አውጥቶ መጋዝ፣ ዶማና
መጥረቢያ ይዘው እንዲሠሩ አደረጋቸው።
ዳዊት በሌሎቹም የአሞን ከተሞች ሁሉ
ይህንኑ አደረገ። ከዚያም ዳዊትና መላው
ሰራዊቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

## ከፍልስጥኤማውያን ጋር የተደረገ ጦርነት

2፥4-8 ተጓ ምብ - 2ሳሙ 21፥15-22

4ከዚያም በኋላ ከፍልስጥኤማውያን ጋር
በጌዝር ጦርነት ተደረገ፤ በዚያ ጊዜ ኩሳ
ታዊው ሴቦካይ የራፋይም ዘር የሆነውን ሲፋ
ይን ገደለ፤ ፍልስጥኤማውያንም ድል ተመቱ።
5ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሌላ ጦርነት
ተደረገ፤ የያዒር ልጅ ኤልያናን የጦሩ የቦ
ውፍረቱ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የሚያህለ
ውን የጌት ተወላጅ የሆነውን የጎልያድን
ወንድም ላሕሚን ገደለ።
6ደግሞም ጌት ላይ በተደረገ ሌላ ጦር
ነት፣ በእጆቹና በእግሮቹ ላይ ስድስት ስድ
ስት ጣት በድምሩ ሃያ አራት ጣት የነበሩት
አንድ ግዙፍ ሰው ነበረ፤ ይህም እንደዚሁ
ከራፋይም ዘር ነበረ። 7እርሱም እስራኤልን
በተገዳደረ ጊዜ የዳዊት ወንድም የሳምዓ
ልጅ ዮናታን ገደለው።
8በጌት የነበሩ የራፋይም ዘሮች እነዚህ
ናቸው፤ እነርሱም በዳዊትና በሰዎቹ እጅ
ወደቁ።

## ዳዊት ተዋጊ ሰራዊቱን ቈጠረ

21፥1-26 ተጓ ምብ - 2 ሳሙ 24፥1-25

20፥3 ዘዳ29፥11
20፥4 ዘፍ14፥5፤ ኢሱ10፥33
20፥5 1ሳሙ17፥7
21፥1 2ዜና14፥8፤18፥21፤2 5፥5፤መዝ109፥6
21፥2 1ዜና27፥23-24
21፥3 ዘዳ1፥11
21፥5 1ዜና9፥1
21፥9 1ሳሙ9፥9፤22፥5

21 1ሰይጣን በእስራኤል ላይ ተነሥቶ
ዳዊት የእስራኤልን ሕዝብ እንዲቈ
ጥር አነሣሣው። 2ዳዊትም ኢዮአብንና የሰራ
ዊቱን አዛዦች፣ "ሂዳችሁ ከቤርሳቤህ እስከ
ዳን ያሉትን እስራኤላውያን ቍጠሩ፤ ከዚ
ያም ምን ያህል እንደ ሆኑ አውቅ ዘንድ
ንገሩኝ" አላቸው።
3ኢዮአብ ግን፣ "እግዚአብሔር የእስራኤልን
ሰራዊት አሁን ካለው በላይ በመቶ እጥፍ ያብ
ዛው፤ ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ሁሉስ ቢሆኑ የጌ
ታዬ ተገዢዎች አይደሉምን? ታዲያ ጌታዬ
ይህን ማድረግ ለምን አስፈለገው? ለምንስ በእ
ስራኤል ላይ በደል ያመጣል?" አለ።
4ይሁን እንጂ የንጉሡ ቃል ኢዮአብን
አሸነፈው፤ ስለዚህ ኢዮአብ ወጣ፤ በመላው
እስራኤል ከተዘዋወረ በኋላ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ተመለሰ። 5ኢዮአብም የተዋጊዎቹን
ሰዎች ቍጥር ለዳዊት አቀረበ፤ እነዚህም
በመላው እስራኤል አንድ ሚሊዮን አንድ
መቶ ሺህ፣ በይሁዳ ደግሞ አራት መቶ ሰባ
ሺህ ሲሆኑ፣ ሁሉም ሰይፍ መምዘዝ የሚ
ችሉ ነበሩ።
6ኢዮአብ ግን የንጉሡ ትእዛዝ አስጸያፊ
ነበረና፣ የሌዊንና የብንያምን ነገድ ጨምሮ
አልቈጠረም። 7ይህ ትእዛዝ በእግዚአብሔር
ዘንድ የተጠላ ነበር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር
እስራኤልን ቀጣ።
8ከዚያም ዳዊት እግዚአብሔርን፣ "ይህን በማ
ድረጌ እጅግ በድያለሁ፤ የፈጸምሁትም የስ
ንፍና ሥራ ስለ ሆነ፣ የባሪያህን በደል እን
ድታስወግድ እለምንሃለሁ" አለ።
9እግዚአብሔርም የዳዊት ባለ ራእይ የሆነውን
ጋድን እንዲህ አለው፤ 10"ሂድና ለዳዊት እን

[መ] 2.34 ኪሎ ግራም ያህል ነው

*20፥2-3፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ፣ ተደራስያኑ በ2ሳሙ 12፥26-29 ላይ የተጻፈውን ታሪክ አሳምረው እንደሚያውቁ ስለ ተገነዘበ፣ በኢየሩሳሌም ቀርቶ የነበረው ዳዊት፣ (ቍ1) ወደ ረባት እንዴት እንደ መጣ ዘርዝሮ መጻፍ አላስፈለገውም።

*20፥4 ሴቦካይ፤* 11፥29፤27፥11 ይመ። የራፋይም ዘር የጥንት ሕዝቦች ሲሆኑ፣ የሚታወቁትም በሕዝብ ብዛታቸው ነው። (ዘፍ14፥5፤ ዘዳ2፥11፤ እንዲሁም የ2ሳሙ 21፥16 ማብ ይመ)።

*20፥5፤* የ2 ሳሙ21፥19 ማብ ይመ። *የሸማኔ መጠቅለያ፤* 11፥23፤ 1ሳሙ17፥7 ይመ።

*20፥6 ራፋይም፤* የ2ሳሙ 21፥16 ማብ ይመ።

*21፥1-22፥1፤* 2ሳሙ 24 እና ማብ ይመ። ዳዊት የሕዝብ ቈጠራ ስለማድረጉ የሚያወሳው ታሪክ በሁለቱም መጻሕፍት ፍጹም ተመሳሳይነት ያለው ቢመስልም፣ አቀራረቡ የተለያየ ነው። ይህ ታሪክ የመጽሐፈ ሳሙኤል (2ሳሙ21-24 ተቀጥላ ሲሆን፣ ታሪኩ የሚጀምረውም የሚጨርሰውም ከነገሥታቷ ክፉ ድርጊት የተነሣ የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራኤል ላይ መውረዱን በመግለጽ ነው (ስለ ሳኦል ድርጊት በም21፤ ስለ ዳዊት ድርጊት በም24 ተጠቅሷል)። የ2ሳሙ21፥1-24፥25 ማብ ይመ። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ቤተ መቅደሱ የሚሠራበትንም ቦታ ግዥ ታሪክ እዚህ ክፍል ውስጥ ጨምሮታል። በዜና መዋዕሉ መጽሐፍ የተጨመሩት አንዳንድ ነገሮች ግን በመጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ (21፥28-22፥1) እንደማይገኙ ይህ ክፍል ግልጽ ያደርገዋል። የሕዝብ ቈጠራው ታሪክ ዳዊት ቤተ መቅደስ ለመሥራት ላለው ዕቅድም እንደ መቅድም የሚቈጠር ነው (ም 22-29)።

*21፥1፤* የ2ሳሙ24፥1 ማብ ይመ። *ሰይጣን፤* የኢዮብ 1፥6 እና የዘካ3፥1 ማብ ይመ።

*21፥4፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ኢዮአብ በ2 ሳሙ 24፥4-8 በሰፊው የተጻፈውን ነገር እዚህ ላይ ባጭሩ ነው ያወሣው። የሕዝብ ቈጠራው ዘጠኝ ወር ከሃያ ቀን መፍጀቱን አልጠቀሰም (2ሳሙ 24፥8)።

21፥5 *በመላው እስራኤል...አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ... አራት መቶ ሰባ ሺህ፤* በ2ሳሙ 24፥9 ላይ የተጻፈው ግን ቍጥሩን በእስራኤል ስምንት መቶ ሺህ፣ በይሁዳ አምስት መቶ ሺህ ያደርገዋል፤ አምስት መቶ ሺህ የተባለው ግን ትክክለኛው ቍጥር አራት ሺህ ሰባት መቶ ነው። ዝቅ ያለ ውን ቁጥር አሟልቶ በአቅራቢያው ሙሉ ቁጥር በዐሥር ወይም በመቶ መጥራት የተለመደ ሊሆን ይችላል። ሆኖም በሁለቱ መጻሕፍት መካከል የቍጥር ልዩነት መኖሩ ለምን እንደሆነ በውል አይታወቅም፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ምናልባት የሕዝብ ቈጠራው ጠባይ እንደሚገባ ጥንቃቄ ተደርጎበት እስከ መጨረሻው ያልተከናወነና በባሕር መዝገብ ያልተመዘገበ ከመ ሆኑ የተነሣ ነው ብሎ ለመገመት ያስችል ይሆናል (27፡23-24ይመ)፤ በሕዝቡ መካከል የሚገኙት አንዳንድ ክፍ ሎች ወይም ነገዶች ቍጥር መጨመሩ ወይም አለመጨመሩ ከዚሁ ጋር የሚያያዝ ነው (ቍ6)። ከአንዱ ቅጅ ወደ ሌላው ቅጅ በእጅ እየተጻፈ ሲተላለፍ በጸሐፊዎቹ ስሕተት ምክንያት የተገደፈ ሊሆን ይችላል።

*21፥6፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ኢዮአብ ሌዊንና ብንያምን ሳይቈጥር ያለፈበትን ምክንያት ገልጾአል። እንዲሁም ይህን ተጨማሪ ማብራሪያ በዚህ ክፍል ማስገባቱ፣ ጸሓፊው ለሌዋውያንና ለእስራኤል ሕዝብ አምልኮ ያለውን ልዩ ግምት የሚያንጸባርቅ ነው። በገባዖን የተተከለው የምስክሩ ድንኳንና በኢየሩሳሌም የተቀመጠው ታቦት ሁለቱም የሚገኙት በብንያም ግዛት ውስጥ ነበር።

*21፥9 ጋድ፤* ዳዊት ከሳኦል ፊት ሸሽቶ ከተሰደደበት ጊዜ ጀምሮ ያልተለየው የብዙ ጊዜ ወዳጁ ነው (1ሳሙ22፥3-5፤ ከ1 ዜና29፥29፤ከ2ዜና 29፥25 ጋር ያነጻጽሩ)።

ዲህ ብለው ንገረው፤ ‘እግዚአብሔር የሚለው
ይህን ነው፤ እነሆ፣ ሦስት ምርጫ ሰጥቼሃለሁ፤
በአንተ ላይ እንዳደርስብህ አንዱን ምረጥ”
[11]ስለዚህ ጋድ ወደ ዳዊት ሄዶ እንዲህ
አለው፤ “እግዚአብሔር የሚለው ይህን ነው፤
‘በል እንግዲህ አንዱን ምረጥ፤ [12]የሦስት ዓመት
ራብ ወይስ ሦስት ወር በጠላቶችህ እጅ መጥ
ፋት ወይስ ሦስት ቀን የእግዚአብሔር ሰይፍ
መቅሠፍት በምድሪቱ ላይ ወርዶ የእግዚአብሔር
መልአክ እስራኤልን ሁሉ ያጥፋ?’ ለላከኝ ምን
እንደምመልስ ቊርጡን ንገረኝ::”
[13]ዳዊትም ጋድን፣ “እጅግ ተጨንቄአለሁ፤
ምሕረቱ ታላቅ ስለሆነ በእግዚአብሔር እጅ
መውደቅ ይሻለኛል፤ በሰው እጅስ አልው
ደቅ” አለ።
[14]ስለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ
መቅሠፍት ላከ፤ ከእስራኤልም ሰባ ሺህ
ሰው ዐለቀ:: [15]እንዲሁም እግዚአብሔር ኢየሩ
ሳሌምን እንዲያጠፋ መልአክ ላከ፤ መል
አኩ ሊያጠፋትም ሲል እግዚአብሔር አይቶ
ስለሚደርሰው ጥፋት አዘነ፤ ሕዝቡን የሚ
ያጠፋውንም መልአክ፣ "እጅህን መልስ”
አለው:: የእግዚአብሔርም መልአክ በኢያቡ
ሳዊው በኦርና ዐውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር::
[16]ዳዊት ቀና ብሎ ሲመለከት፣ የእግዚአ
ብሔር መልአክ በሰማይና በምድር መካ
ከል ቆሞ አየ፤ መልአኩም በኢየሩሳሌም
ላይ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ ይዞ ነበር፤ ከዚ
ያም ዳዊትና ሽማግሌዎቹ ማቅ እንደ ለበሱ
በግ ምባራቸው ተደፉ::
[17]ዳዊት እግዚአብሔርን፣ “ተዋጊዎቹ እንዲ
ቈጠሩ ያዘዝሁ እኔ አይደለሁምን? ኀጢ
አት የሠራሁትም ሆነ የበደልሁት እኔ ነኝ፤
እነዚህ እኮ በጎች ናቸው፤ ታዲያ እነርሱ
ምን አደረጉ? እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤
እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ትሁን እንጂ፣
መቅሠፍቱ በሕዝብህ ላይ አይውረድ” አለ::
[18]ከዚያም የእግዚአብሔር መልአክ ዳዊት
ወጥቶ በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ ላይ
ለእግዚአብሔር መሠዊያ ይሠራ ዘንድ እን
ዲነግረው ጋድን አዘዘው:: [19]ዳዊትም ጋድ
በእግዚአብሔር ስም በነገረው ቃል መሠ
ረት ለመፈጸም ወጣ::
[20]ኦርና ስንዴ በመውቃት ላይ ሳለ ዘወር
ሲል መልአኩን አየ፤ አብረውት የነበሩት
አራት ወንዶች ልጆቹም ተሸሸጉ:: [21]ዳዊት
ወደ እርሱ እየቀረበ መጣ፤ ኦርና ቀና ብሎ
ሲመለከት፣ ዳዊትን አየው፤ ከዐውድማውም
ወጥቶ መሬት ላይ ለጥ ብሎ በመደፋት
ለዳዊት እጅ ነሣ::
[22]ዳዊትም፣ “በሕዝቡ ላይ የወረደው
መቅሠፍት እንዲወገድ ለእግዚአብሔር መሠ
ዊያ እሠራ ዘንድ ዐውድማህን ልውሰደው፤
ሙሉውን ዋጋ እከፍልሃለሁ” አለው::
[23]ኦርናም ዳዊትን፣ “እንዲሁ ውሰደው፤
ጌታዬ ንጉሥ ደስ ያለውን ያድርግ፤ እነሆ፤
ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎቹን፣ መው
ቂያ በትሮቹን ለማቀጣጠያ ዕንጨት፣ ስን
ዴውን ደግሞ ለእህል ቊርባን እንዲሆን
እሰጣለሁ፤ ሁሉንም እኔ እሰጣለሁ::” አለ::
[24]ንጉሥ ዳዊት ግን ለኦርና “አይደረግም፤
ሙሉውን ዋጋ እኔ እከፍላለሁ፤ የአንተ የሆ
ነውን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ አልፈልግም፤
ዋጋ ያልከፈልሁበትንም የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጌ አላቀርብም’’ ሲል መለሰለት::
[25]ስለዚህ ዳዊት ለኦርና የቦታውን ዋጋ
ስድስት መቶ ሰቅል[a] ወርቅ ከፈለ:: [26]ዳዊ
ትም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠርቶ
የሚቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[b]
አቀረበ። እግዚአብሔርንም ጠራ፤ እግዚአብሔ
ርም የሚቃጠል መሥዋዕት በሚቀርብበት
መሠዊያ ላይ ከሰማይ በእሳት መለሰለት::
[27]ከዚያም እግዚአብሔር ለመልአኩ ተና
ገረ፤ መልአኩም ሰይፉን ወደ አፎቱ መለሰ::
[28]በዚያን ጊዜ ዳዊት፣ እግዚአብሔር በኢያ
ቡሳዊው በኦርና ዐውድማ ላይ እንደ መለሰ
ለት ሲያይ፣ በዚያው ቦታ መሥዋዕት ማቅ
ረብ ጀመረ:: [29]ሙሴ በምድረ በዳ የሠራው
የእግዚአብሔር ማደሪያ ድንኳንና የሚቃጠል
መሥዋዕት የሚቀርብበት መሠዊያ በዚያን
ጊዜ በገባዖን ኮረብታ ላይ ነበረ:: [30]ዳዊት
የእግዚአብሔርን መልአክ ሰይፍ ስለ ፈራ ወደ
ዚያ ሄዶ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ አልቻለም::

[a]25 7 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[b]26 በትውፊት፣ “የሰላም መሥዋዕት” ይባላል

21፥12 ዘፍ19፥13፤ዘዳ32፥24፤ሕዝ30፥25
21፥13 መዝ6፥4፤86፥15፤130፥4፡7
21፥14 1ዜና27፥24
21፥15 ዘፍ6፥6፤19፥13፤32፥1፤ዘፀ32፥14፤መዝ 125፥2
21፥16 ኢሱ7፥6፤ዘኍ14፥5
21፥17 2ሳሙ7፥8፤ዮና1፥12
21፥18 2ዜና3፥1
21፥20 መሳ6፥11
21፥26 መሳ19፥18፤መሳ6፥21
21፥29 ኢሱ9፥3

21፥12 *የሦስት ዓመት ራብ፤* የ2ሳሙ24፥13 ማብ ይመ::

21፥16፤ ይህ ቍጥር ከመደበኛው የዕብራይስጡ መጽሐፈ ሳሙኤል (2ሳሙ24) ጋር አይመሳሰልም፤ ስለዚህም አንዳንድ ምሁራን ከምርኮ መልስ መላእክትን በተመለከተ አድጐና ተስፋፍቶ ይሰጥ የነበረውን ሃይማኖታዊ ትምህርት ለማንጸባረቅ ሲል የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ራሱ የጨመረው ነው የሚል አስተያየት አላቸው፤ ይሁን እንጂ በሦስት መቶ ዓ.ቅ.ክ. ተጽፎ በቍምራን ገዳም በተገኘው መጽሐፈ ሳሙኤል ላይ ይህ ቍጥር ተጽፎ ይገኛል:: እንግዲህ ነገሩ ይህ ከሆነ፣ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ከሳሙኤል መጽሐፍ ቅጅ ላይ በጥንቃቄ ሳይገለብጥ እንዳልቀረ ይታመናል፤ ይህ ቅጂም በአንዳንድ ነገሮች አይሁድ እንደ መደበኛ መጽሐፍ አድርገው ከሚመለከቱት የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ሳይለይ አይቀርም:: የአይሁድን ታሪክ ጠንቅቆ የጻፈው ጆሲፈስ በመጽሐፉ የዘገበው ይህንኑ በሳሙኤል መጽሐፍ የሚገኘውን ታሪክ ነው:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊና፤ ጆሲፈስም፣ ምንጭ አድርገው የተጠቀሙበት የሳሙኤል መጽሐፍ ቅጅ ተመሳሳይ ነበር ለማለት ይቻላል::

*21፥20-21፤* ንጉሡ በዚያ ሲደርስ (አጠገቡ በደረሰ ጊዜ) ኦርና ስንዴ እየወቃ እንደ ነበር የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በመጽሐፉ አስፍሮአል፤ ይህ ግን በ2ሳሙ24፥20 ላይ አይገኝም:: ይሁን እንጂ ነገሩ የጆሲፈስ መጽሐፍና በቁምራን የተገኙት ቁርጥራጭ ጽሑፎች ይህንኑ ሐሳብ ጽፈውታል::

*21፥25 ስድስት መቶ ሰቅል ወርቅ፤* 2ሳሙ 24፥24 ግን ለቦታውና ለበሬዎቹ የተከፈለው አምሳ ሰቅል ጥሬ ብር ነው ይላል:: አንዳንዶች ይህን “የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዳዊትንና የቤተ መቅደሱን ክብርና ዝና አጕልቶ ለማሳየት ሲል የቈለለው ገንዘብ ነው” የሚል አመለካከት አላቸው:: ሆኖም ልዩነቱ ይሄን ያህል ከፍ ሊል የቻለው፣ ክፍያው የተፈጸመው ለራሱ ለዐውድማው ብቻ ሳይሆን፣ በዐውድማው ዙሪያ ለሚገኘው ቦታ ጭምር መሆኑን ለማሳየት፣ ሲል የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ “የቦታውን” የሚል ቃል መጨመሩ ይህንኑ ለማሳየት ሊሆን ይችላል::

21፥26 *ከሰማይ በእሳት፤* እግዚአብሔር መሥዋዕቱን እንደ ተቀበለለትና ቦታውም የተቀደሰ መሆኑን ያረጋግጣል (2ዜና 7፥1፤ ዘሌ 9፥24፤1ነገ፡18፥37-38)::

*21፥28-22፥11* ይህ ታሪክ በ2ሳሙ24 ላይ አይገኝም:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ሥራዬ ብሎ ለመጻፍ የተነሣለትን ጉዳይ ያንጸባርቃል (የ21፥1-22 ማብ ይመ)::

21፥30 *ወደዚያ፤* የመገናኛውን ድንኳን ነው::

**22** ከዚያም ዳዊት፣ "ከእንግዲህ የእግ
ዚአብሔር ስምባክ ቤት በዚህ ይሆ
ናል፤ እንዲሁም ስለ እስራኤል የሚቃጠል
መሥዋዕት የሚቀርብበት መሠዊያ በዚሁ
ይቆማል" አለ::

## ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት

2ስለዚህ ዳዊት በእስራኤል የሚኖሩ መጻ
ተኞች እንዲሰበሰቡ አዘዘ፤ ከመካከላቸውም
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚሠራበትን
ጥርብ ድንጋይ እንዲያዘጋጁ ጠራቢዎችን
መደበ:: 3ለቅጥር በሮቹ ምስማርና ማጠፊያ
የሚሆን ብዙ ብረትና ከብዛቱ የተነሣ ሊመ
ዘን የማይቻል ናስ አዘጋጀ:: 4እንዲሁም
ሲዶናውያንና ጢሮሳውያን በብዛት አምጥ
ተውለት ስለ ነበር፣ ስፍር ቍጥር የሌለው
የዝግባ ዕንጨት አሰናዳ::
5ዳዊትም፣ "ልጄ ሰሎሞን ወጣት ነው፤
ልምዱም የለውም፤ ለእግዚአብሔር የሚሠራው
ቤተ መቅደስ ደግሞ እጅግ የሚያምር፣
በአሕዛብም ሁሉ ዘንድ ዝናው የተሰማና
እጅግ የተዋበ መሆን አለበት፤ ስለዚህ ሁሉ
ንም እኔ አዘጋጃለሁ" አለ:: እንዳለውም
ዳዊት ከመሞቱ በፊት በብዛት አዘጋጀ::
6ከዚያም ልጁን ሰሎሞንን ጠርቶ ለእስራ
ኤል ስምባክ ለእግዚአብሔር ቤት እንዲሠራ
አዘዘው::
7ዳዊትም ሰሎሞንን እንዲህ አለው፤
"ልጄ ሆይ፤ በስምባኪ ለእግዚአብሔር ስም
ቤት ለመሥራት በልቤ አስብ ነበር፤ 8ነገር
ግን ከእግዚአብሔር እንዲህ የሚል ቃል
መጣልኝ፤ "አንተ ብዙ ደም አፍስሰሃል፤
ብዙ ጦርነትም አድርገሃል፤ በፊቴ በምድር
ላይ ብዙ ደም ያፈሰስህ ስለ ሆነ አንተ
ለስሜ ቤት አትሠራልኝም፤ 9ነገር ግን የሰ
ላምና የዕረፍት ሰው የሆነ ልጅ ትወልዳ
ለህ፤ በየአቅጣጫው ካሉ ጠላቶቹ ዐሳርፈዋ
ለሁ፤ ስሙም ሰሎሞን ይባላል:: በዘመኑም
ለእስራኤል ሰላምንና ጸጥታን እሰጣለሁ::
10ለስሜ ቤት የሚሠራልኝ እርሱ ነው::
እርሱ ልጅ ይሆነኛል፤ እኔም አባት እሆን
ዋለሁ:: ዙፋኑንም በእስራኤል ላይ ለዘላለም
አጸናለሁ::
11"አሁንም ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔር ከአ
ንተ ጋር ይሁን፤ እንድትፈጽመው በተናገረ
ውም መሠረት፣ ተሳክቶልህ የስምባክህን የእ
ግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት ያብቃህ::
12በእስራኤል ላይ አለቃ ባደረገህ ጊዜ፣ የስ
ምባክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትፈጽም
ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብንና ማስተዋልን
ይስጥህ:: 13እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት
ለእስራኤል የሰጠውን ሕጉንና ሥርዐቱን
ተጠንቅቀህ ብትጠብቅ ይሳካልሃል፤ አይ
ዞህ ጠንክር፤ በርታ፤ ተስፋም አትቍረጥ::
14"ለእግዚአብሔር ቤት እንዲሆንም
አንድ ሺህ መክሊት[ሌ] ወርቅ፣ አንድ ሚሊ
ዮን መክሊት[T] ብር፣ ከብዛቱ የተነሣ ሊመ
ዘን የማይቻል ናስና ብረት ለማዘጋጀት
በተቻለኝ ሁሉ ጥሬአለሁ:: በተረፈ አንተ
ጨምርበት:: 15ድንጋይ ጠራቢዎች፣ ግን
በኞች፣ አናጢዎች የሆኑ ብዙ ሠራተኞች፣
እንዲሁም በልዩ ልዩ ሙያ የተጠበቡ ሰዎች
አሉህ፤ 16እነዚህም ቍጥራቸው እጅግ የበዛ
የወርቅ፣ የብር፣ የናስና የብረት ሠራተኞች
ናቸው:: በል ሥራህን ጀምር፤ እግዚአብሔ
ርም ከአንተ ጋር ይሁን::"
17ከዚያም ዳዊት የእስራኤል መሪዎች
ሁሉ ልጁን ሰሎሞንን እንዲረዱት አዘዘ፤
18እንዲህም አለ፤ "እግዚአብሔር ስምባካችሁ
እስካሁን ከእናንተ ጋር አይደለምን? በየአቅ
ጣጫውስ ዕረፍትን ሰጥቷችሁ የለምን? የም
ድሪቱን ነዋሪዎች በእጄ አሳልፎ ሰጥቶኛል፤
ምድሪቱም ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ተገ
ዝታለች:: 19አሁንም እግዚአብሔር ስምባ
ካችሁን ለመፈለግ ልባችሁንና ነፍሳችሁን
ሰብስቡ:: የእግዚአብሔርን የኪዳኑን ታቦትና

22፥1 ዘፍ28፥17
22፥2 ዘፀ፥11፤ ዘዳ20፥11፤ 1ነገ5፥17-18፤2ዜና8፥10፤ ዕዝ3፥7፤ኢሳ56፥6
22፥3 1ነገ7፥47፤1ዜና29፥2-5
22፥4 1ነገ5፥6
22፥5 1ነገ3፥7፤ 1ዜና29፥1፤2ዜና2፥5
22፥6 ሐሥ7፥47
22፥7 ዘዳ12፥5:11፤1ነገ8፥17፤1ዜና17፥2
22፥8 1ነገ5፥3፤1ዜና28፥3
22፥9 ቍ18፤ኢሱ14፥15፤ 2ሳሙ12፥24፤1ነገ4፥20፤5፥4፤1ዜና23፥1:25፤ 2ዜና14፥6+7፤15፥15፤ 20፥30፤36፥21
22፥10 2ሳሙ7፥13:14፤ 1ነገ9፥5፤1ዜና17፥4:12፤2ዜና6፥15
22፥11 1ሳሙ16፥18፤18፥12
22፥12 1ነገ3፥11
22፥13 ዘዳ31፥6፤ 1ነገ2፥3፤1ዜና28፥7
22፥14 1ዜና29፥2-5:19
22፥15 ዕዝ3፥7
22፥16 2ዜና2፥7
22፥17 1ዜና28፥1
22፥18 ቍ9፤2ሳሙ7፥1
22፥19 2ዜና7፥14

[ሌ]14 3,450 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[T]14 34,500 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

*22፥1-29፥30፤* በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተካተቱት ታሪኮች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ሲሆን፣ እነርሱም የ ጸሐፊውን ትኩረት የሳቡ ርእሰ ጕዳዮች ናቸው:: እነርሱም ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገውን ዝግጅት፣ ካህናቱና ሌዋ ውያኑ በቤተ መቅደሱ አገልግሎት ውስጥ ያላቸውን ስፍራ፣ የንጉሡንና በእርሱ እግር የሚተካውን ሕጋዊ ወራሽ ዜና የያዙ ናቸው:: እንዲሁም ምዕራፎቹ ልክ ያን ጊዜ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን የነበረውን መለኮት ገዝ "መሲሓዊ" መንግሥት ያሳዩናል::

*22፥1፤* ዳዊት ይህን የገዛውን ቦታ ቤተ መቅደሱ እንዲሠራበት (ቍ2-6) ለእግዚአብሔር ቀድሶታል (21፥18-30)::

*22፥2-19፤* ሰሎሞን በአባቱ በዳዊት ፈንታ የተተካው ሁለት ነገሮች በቅድሚያ ከተፈጸሙ በኋላ ነበር፤ እነዚህም (1) እርሱ ባለበት ከጥቂት ባለሟሎቹ ጋር ነገሩ በምክር በመ ቈረጡ፤ (2) ሕዝቡ በይፋ (በአደባባይ) እንዲያውቀው በመደረጉ ነበር::

22፥2 *መጻተኞች...ድንጋይ...ጠራቢዎች፤* 2ሳሙ 20፥24 ሥራው በግዴታ እንዲሠራ ዳዊት ማዘዙን ያረጋግጣል:: ይሁን እንጂ እነዚህ የጕልበት ሠራተኞች መጻተኞች ይሁኑ እስራ ኤላውያን በግልጽ ለይቶ አያስቀምጥም፤ ሰሎሞን ግን እስራኤላ ውያን ተገድደው (የጕልበት ሥራ) እንዲሠሩ በሕግ ደንግጎአል (1ነገ5፥13-18፤9፥15-23፤11፥28)፤ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የዘገበው መጻተኞች ለመኖር ነጻነት የነበራቸው ቢሆንም፣ ስለመብታቸው አፋቸውን ሞልተው መናገር የሚችሉ ስላልነበሩ፣ ጕልበታቸው በቀላሉ ይበዘበዝ ነበር:: እርግጥ ብሉይ ኪዳን መጻተኞች እንዳ ይጨቈኑ አጥብቆ ያስጠነቅቃል (ዘፀ22፥21፤ 23፥29፤ ዘሌ19፥33፤ ዘዳ24፥14፤ ኤር7፥6፤ ዘካ7፥10):: ኢሳይያስ የቤተ መቅደሱ ቅጥር ወደ ፊት በሚሠራበት ጊዜ ባዕዳን በሥራው ላይ ተካፋይ እንደሚሆኑ ትንቢት ተናግሮአል (ኢሳ60፥10-12)::

*22፥3 ናስ፤* የ18፥8 ማብ ይመ::

*22፥5 ወጣት፤* ሰሎሞን በአባቱ ዙፋን ላይ ሲቀመጥ ዕድሜው ምን ያህል እንደነበረ በእርግጠኝነት አይታወቅም:: የነገሠው 970 ዓ.ቅ.ክ. ሲሆን የተወለደው ምናልባት በ991 ዓ.ቅ.ክ. ሳይሆን አይቀርም::

22፥8-9፤ የ17፥1 ማብ ይመ:: በ1ነገ 5፥3 ላይ ሰሎሞን አባቱ ዳዊት በጦርነት ብዛት ተወጥሮ ስለ ነበር ቤተ መቅደሱን ለመሥራት አለመቻሉን ማውሣቱ ተጽፎአል:: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ይህንኑ ታሪክ የሚገልጸው በተለየ መንገድ ነው፤ እንደ እርሱ አመለካከት ጦርነቱ ብዙውን ጊዜውን ስለ ወሰደበት ሳይሆን፣ አግባብ ባልሆነ መንገድ ደም በማፍሰሱ (በመግደሉ) ነው:: የሰሎሞንን ስም ግን በተለየ መንገድ ከመለኮታዊ ትንቢት ጋር ያያይዘዋል::

*22፥10፤* የ17፥12-14 ማብ ይመ::

*22፥12-13፤* በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል" የሚለውን ይመ::

*22፥19፤* 2ዜና 5፥7 ይመ::

ንዋያተ ቅድሳቱን ለእግዚአብሔር ስም ወደ
ሚሠራቸው ቤተ መቅደስ አምጥታችሁ
የሰምሳክን *የእግዚአብሔርን መቅደስ ሥሩ።"*

**ሌዋውያን**

**23** ዳዊት በሸመገለና ዕድሜው በገፋ ጊዜ፣
ልጁን ሰሎሞንን በእስራኤል ላይ
አነገሠው።
2እንዲሁም መላውን የእስራኤልን መሪ
ዎች፣ ካህናቱንና ሌዋውያኑን ሁሉ በአንድ
ነት ሰበሰበ። 3ዕድሜአቸው ሠላሳና ከዚያ
በላይ የሆኑ ወንዶች ሁሉ ተቈጠሩ፤ ቊጥ
ራቸውም በጠቅላላው ሠላሳ ስምንት ሺህ
ነበረ። 4ዳዊትም እንዲህ አለ፤ "ከእነዚህ
መካከል ሃያ አራቱ ሺህ *የእግዚአብሔርን*
ቤተ መቅደስ ሥራ ይቈጣጠሩ፤ ስድስቱ ሺህ
ደግሞ ሹሞችና ዳኞች ይሁኑ፤ 5አራቱ ሺህ
የቅጥሩ በር ጠባቂዎች ይሁኑ፤ አራቱ ሺህ
ደግሞ ለዚሁ ብዬ ባዘጋጀሁት የዜማ
መሣሪያ እግዚአብሔርን ያመስግኑ"።
6ዳዊትም ሌዋውያኑን በሌዊ ልጆች
በጌድሶን፣ በቀዓትና በሜራሪ በየጐሣቸው
መደባቸው።

**ጌድሶናውያን**

7ከጌድሶናውያን ወገን፤
ለአዳን፣ ሰሜኢ።
8የለአዳን ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ይሒኤል፣ ዜቶም፣
ኢዮኤል፤ ባጠቃላይ ሦስት ናቸው።
9የሰሜኢ ወንዶች ልጆች፤
ሰሎሚት፣ ሐዝኤል፣ ሐራን፤ ባጠቃ
ላይ ሦስት ናቸው። እነዚህ የለአዳን
ቤተ ሰብ አለቆች ናቸው።
10የሰሜኢ ወንዶች ልጆች፤
ኢኢት፣ ዚዛ፣ የዑስ፣ በሪዓ፤ እነዚህ
አራቱ የሰሜኢ ልጆች ናቸው።
11የመጀመሪያው ኢኢት፣ ሁለተኛው ደግሞ
ዚዛ[ሀ] ነበረ፤ የዑስና በሪዓ ግን ብዙ ወን
ዶች ልጆች አልነበሩአቸውም፤ ስለዚህ
የተቈጠሩት በሥራ መደብ እንደ አንድ
ቤተ ሰብ ሆነው ነው።

**ቀዓታውያን**

12የቀዓት ወንዶች ልጆች፤
እንበረም፣ ይስዓር፣ ኬብሮን፣
ዑዝኤል፤ ባጠቃላይ አራት ናቸው።
13የእንበረም ወንዶች ልጆች፤
አሮን፣ ሙሴ።
አሮን የተቀደሰ እንዲሆን ተለየ፤ እር
ሱና ዘሮቹ ለዘላለም ቅዱስ የሆኑትን
ነገሮች እንዲቀድሱ፣ *በእግዚአብሔር*
ፊት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፣ በፊቱ
እንዲያገለግሉና በስሙም ለዘላለም እን
ዲባርኩ ተለዩ። 14የእግዚአብሔር ሰው
የሙሴ ወንዶች ልጆችም እንደ ሌዊ
ነገድ ሆነው ተቈጠሩ።
15የሙሴ ወንዶች ልጆች፤
ጌርሳም፣ አልዓዛር።
16የጌርሳም ዘሮች፤
ሱባኤል።
17የአልዓዛር ዘሮች፤
የመጀመሪያው ረዓብያ ነበረ።
አልዓዛር ሌሎች ወንዶች ልጆች አል
ነበሩትም፤
የረዓብያ ወንዶች ልጆች ግን እጅግ
ብዙ ነበሩ።
18የይስዓር ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ሰሎሚት።
19የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ይሪያ፣ ሁለተኛው አማ
ርያ፣ ሦስተኛው የሕዚኤል፣ አራተኛው
ይቅምዓም ነበሩ።
20የዑዝኤል ወንዶች ልጆች፤
የመጀመሪያው ሚካ፣ ሁለተኛው ይሺያ
ነበሩ።

**ሜራሪያውያን**

21የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤
ሞሐሊ፣ ሙሲ።
የሞሐሊ ወንዶች ልጆች፤
አልዓዛርና ቂስ ነበሩ።
22አልዓዛር ወንድ ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤
ልጆቹ ሴቶች ብቻ ነበሩ፤ እነርሱንም
የአጎታቸው የቂስ ልጆች አገቡአቸው።
23የሙሲ ወንዶች ልጆች፤
ሞሐሊ፣ ዔደር፣ ኢያሪሙት ባጠቃላይ
ሦስት ናቸው።

[ሀ]11 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅ፣ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጉሞች (እንዲሁም ቍጥር 11 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ "ዚና" ይላሉ።

23፥1 1ነገ1፥30፤1ዜና22፥9፤28፥5፤29፥28፤2ዜና1፥8
23፥3 ዘኍ4፥3-49፤8፥24፤1ዜና21፥7
23፥4 1ዜና26፥29፤2ዜና19፥8፤34፥13፤ዕዝ3፥8፤ነህ4፥10፤ሕዝ44፥24
23፥5 1ዜና15፥16፤ነህ12፥45፤መዝ92፥3
23፥6 ዘኍ3፥17፤1ዜና24፥20፤2ዜና8፥14፤23፥18፥18፤29፥25
23፥7 1ዜና6፥71
23፥12 ዘፍ46፥11፤ዘፀ6፥18
23፥13 ዘፀ6፥20፤30፥7-10፤ዘኍ6፥23፤1ዜና15፥2
23፥14 ዘዳ33፥1
23፥15 ዘፀ18፥4
23፥16 1ዜና26፥24-28
23፥17 1ዜና24፥21
23፥18 1ዜና26፥25
23፥19 1ዜና24፥23፤26፥31
23፥21 ዘፀ6፥19፤1ዜና6፥19
23፥22 ዘኍ36፥8

*23፥1-27፥34፤* ዳዊት ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ያደረገው ዝግጅት ለሕንጻው ሥራ የሚያስፈልገውን ዕቃ በማከማቸት ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፤ የቤተ መቅደሱን የውስጥ አስተዳደርና ሥርዐተ አምልኮውንም በተመለከተ እንደዚሁ የሚያስፈልገውን ዝግጅት አድርጎአል። ራሱ እግዚአብሔር እንደ ንጉሣቸው ሆኖ ሕዝቡን በበላይነት ማስተዳደሩ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በነበረበትም ዘመን ትኩረት የሳበ ዋና ጉዳይ ነበር። እዚህ ላይ ጸሓፊው ትልቅ ግምት በመስጠት በዝርዝር የሚጽፈው ዳዊት የተሻለ የሕዝብ አስተዳደር ማደራጀቱን ከማ ሣየት ይልቅ (ም27) ከሃይማኖትና ከአምልኮ ሥርዐቶች ጋር ለተያያዙት ጉዳዮች ነው (ም23-26)።

23፥1 **ልጁን ሰሎሞንን... አነገሠው፤** ሰሎሞን የአባቱን ዙፋን የመውረሱ ታሪክ በም 28-29 የሚቀጥል ነው። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዙፋን ለመያዝ የተደረገውን ሽኩቻና በብዙ ደም መፍሰስ የጸናውን መንግሥት ታሪክ አልጻፈውም (1ነገ1-2 እንዲሁም የ28፥1-29፥30 ማብ ይመ)። ምክንያቱም የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ስለ ዳዊትና ስለ ሰሎሞን ከሚያቀርበው አጠቃላይ ታሪክ ጋር ስለ ማይጣጣም ነው (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል የሚለውን ይመ)።

*23፥2-5፤* እግዚአብሔርን ለቍጣ ባነሣሣው የሕዝብ ቈጠራ ሌዋውያኑ አልተቈጠሩም (21፥6-7)።

23፥3 *ዕድሜያቸው ሠላሳና ከዚያ በላይ የሆነ፤* የሌዋውያኑ ቈጠራ በሙሴ የሕግ መጻሕፍት በተደነገገው መሠረት (ዘኍ 4፥1-3) ቀደም ባለው ጊዜ ተከናውኖአል። ከዚህ ቈጠራ በኋላ ግን ዳዊት የአገልግሎት መጀመሪያው ዕድሜ ወደ ሃያ ዓመት ዝቅ እንዲል አዞአል (ቍ 24፡27)፤ ተመሳሳይ የሆነ የአገልግሎት መጀመሪያ ዕድሜ ወደ ሃያ አምስት ዓመት ዝቅ እንዲል ሙሴም ይህንኑ የመሰለ የዕድሜ ማስተካከያ አድርጎ ነበር (ዘኍ8፥23-24፤ ነገር ግን የዘኍ 8፥24 ማብ ይመ)።

*23፥6፤ በጌድሶን፣ በቀዓትና በሜራሪ፤* ሌዋውያኑ በሦስት ጐሣ ተደራጅተው ነበር (ም6፤ዘጸ6፥16-19፤ዘኍ3)፤ ይህ የስም ዝርዝር ከ6፥10-30፤ ከ24፥20-30 ጋር ተመሳሳይ ነው።

24እንግዲህ እነዚህ የቤተ ሰቡ አለቆች
ሆነው እያንዳንዳቸው በየስማቸው ተመዝግ
በው የተቈጠሩት የሌዊ ዘሮች ናቸው፤ ዕድሜ
አቸውም ሃያና ከዚያ በላይ የሆናቸው *በእግ
ዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያ
ገለግሉ ነበሩ። 25ዳዊት እንዲህ ብሎ ነበ
ርና፣ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ለሕዝቡ ዕረፍት ሰጥቷል፤ በኢየሩሳሌምም
ለዘላለም ለመኖር መጥቷል፤ 26ሌዋውያን
ከእንግዲህ ወዲህ ድንኳኑን ወይም የመገል
ገያ ዕቃውን ሁሉ መሸከም የለባቸውም።"
27ዳዊት በሰጠው የመጨረሻ መመሪያ
መሠረት የተቈጠሩት ሌዋውያን ዕድሜ
ያቸው ሃያና ከዚያ በላይ ነበረ።
28የሌዋውያኑ ተግባር *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ አገልግሎት የአሮንን ዘሮች
መርዳት፣ የቤተ መቅደሱን ቅጥር ግቢና
ክፍሎች መንከባከብ፣ የተቀደሱ ዕቃዎችን
ሁሉ ማንጻትና በእግዚአብሔር ቤት ያሉትን
ሌሎች ተግባሮች ማከናወን ነበር። 29እንዲ
ሁም መባ ሆኖ የሚቀርበውን ኅብስተ ገጽ፣
የእህል ቍርባኑን ዱቄት፣ ያለ እርሾ የሚ
ጋገረውን ቂጣ የሚጋግሩ፣ የሚያቦኩና የሚ
ስፈረውንም ሆነ የሚለካውን ሁሉ በኀላ
ፊነት የሚቈጣጠሩ እነርሱ ነበሩ። 30በየዕለ
ቱም *እግዚአብሔርን* ለማመስገንና ለመወደስ
ጠዋት ጠዋት ይቆሙ ነበር፤ ይህንንም ማታ
ማታ 31እንዲሁም በየሰንበቱ፣ በወር መባቻ
በዓልና በተደነገጉት በዓላት ሁሉ ይፈጽሙ
ነበር፤ በተወሰነላቸው ቍጥርና በተሰጠውም
መመሪያ መሠረት ዘወትር *በእግዚአብሔር*
ፊት ያገለግሉ ነበር።
32ስለዚህ ሌዋውያኑ ለመገናኛው ድንኳ
ንና ለመቅደሱ እንዲሁም በወንድሞቻቸው
በአሮን ዘሮች ሥር ሆነው *ለእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ ያለባቸውን ኀላፊነት ያከናውኑ
ነበር።

### የካህናት አመዳደብ

24 የአሮን ልጆች አመዳደብ እንደሚከ
ተለው ነበረ፤
የአሮን ልጆች ናዳብ፣ አብዩድ፣ አልዓ
ዛር፣ ኢታምር ነበሩ። 2ናዳብና አብዩድ
ግን ዘር ሳይተኩ ከአባታቸው በፊት ሞቱ፤
ስለዚህ አልዓዛርና ኢታምር ካህናት ሆነው
ያገለግሉ ነበር። 3ዳዊትም የአልዓዛር ዘር
የሆነው ሳዶቅና የኢታምር ዘር የሆነው
አቢሜሌክ እየረዱት እንደየአገልግሎታቸው
ሥርዐት እየለየ መደባቸው። 4ከኢታምር
ይልቅ በአልዓዛር ዘሮች መካከል ብዙ መሪ
ዎች ተገኙ፤ አከፋፈላቸውም እንደሚከተ
ለው ነበር፤ ከአልዓዛር ዘሮች ዐሥራ ስድስት
የቤተ ሰብ አለቆች፤ ከኢታምርም ዘሮች
ስምንት የቤተ ሰብ አለቆች። 5ከአልዓዛርና
ከኢታምር ዘሮች መካከል የመቅደሱ ሹማ
ምትና የእግዚአብሔር ሹማምት ስለ ነበሩ፣ ያለ
አድልዎ በዕጣ ለዩአቸው።
6የሌዋዊው የናትናኤል ልጅ ጸሓፊው ሸማያ
በንጉሡና በሹማምቱ፣ በካህኑ በሳዶቅ፣ በአ
ብያታር ልጅ በአቤሜሌክ እንዲሁም በካህ
ናቱና በሌዋውያኑ ቤተ ሰብ አለቆች ፊት
ስማቸውን ጻፈ፤ የጻፈውም አንዱን ቤተ
ሰብ ከአልዓዛር ሌላውን ደግሞ ከኢታምር
በመውሰድ ነው፤

7የመጀመሪያው ዕጣ ለዮአሪብ፣ ሁለተኛ
ውም ዕጣ ለዮዳዬ ወጣ፤
8ሦስተኛው ለካሪም፣ አራተኛው ለሥዖሪም፣
9አምስተኛው ለመልክያ፣ ስድስተኛው
ለሚያሚን፣
10ሰባተኛው ለአቆስ፣ ስምንተኛው ለአብያ፣
11ዘጠነኛው ለኢያሱ፣ ዐሥረኛው ለሴኬንያ፣
12ዐሥራ አንደኛው ለኤሊያሴብ፣ ዐሥራ
ሁለተኛው ለያቂም፣
13ዐሥራ ሦስተኛው ለኦፓ፣ ዐሥራ አራ
ተኛው ለየሼብአብ፣
14ዐሥራ አምስተኛው ለቢልጋ፣ ዐሥራ
ስድስተኛው ለኢሜር፣
15ዐሥራ ሰባተኛው ለኤዚር፣ ዐሥራ
ስምንተኛው ለሃፊጼጽ፣
16ዐሥራ ዘጠነኛው ለፈታያ፣ ሃያኛው
ለኤዜቄል፣

23፥24 ዘኍ4፥3
23፥25 1ዜና22፥9
23፥26 ዘኍ4፥5፡15፤17፥9፤ዘጸ10፥8
23፥28 2ዜና29፥15፤ነህ13፥9፤ሚል3፥3
23፥29 ዘፀ25፥30፤ዘሌ2፥4-7፤6፡20-23፤19፥35-36፤1ዜና19፥29፡32
23፥30 1ዜና9፥33፤መዝ134፥1
23፥31 ዘኍ28፥9-29፡39፤2ነገ4፥23፤ኢሳ1፥13-14፤ቈላ2፥16
23፥32 ዘኍ3፥6-8፡38፤1ዜና6፥48፤2ዜና23፥18፤31፥2፤ሕዝ44፥14
24፥1 ዘፀ6፥23፤ዘኍ3፥2-4፤1ዜና23፥6፤28፥13፤2ዜና5፥11፤8፥14፤23፥8፤31፥2 35፥4፡5፤ዕዝ6፥18
24፥2 ዘሌ10፥1-2
24፥3 2ሳሙ8፥17
24፥5 ቍ31፤1ዜና25፥8፤26፥13
24፥6 1ዜና18፥16
24፥7 ዕዝ2፥36፤ነህ12፥6
24፥8 ዕዝ2፥39፤10፥21፤ነህ10፥5
24፥10 ነህ12፥4፡17፤ሉቃ1፥5
24፥14 ዕዝ2፥37፤10፥20፤ኤር20፥1
24፥15 ነህ10፥20

*23፥24፡27 ዕድሜያቸውም ሃያና ከዚያ በላይ፤* የቍ3 ማብ ይመ።

*23፥28-32፤* የ9፥28-34 ማብ ይመ። የሌዋውያኑ ተቀዳሚ ተግባር ካህናቱን መርዳት ነው። በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ከሚያከናውኑት የጥበቃ ሥራ፣ ንዋያተ ቅድሳትንና ሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎችን በማግባት በማውጣት፣ በማቅረብና ከቦታ ቦታ በማዛወር፣ የሚጋገረውን በመጋገር የሚቀቀለውን በመቀቀል፣ እንዲሁም መዝሙር በመዘመር ከሚሰጡት አገልግሎት (እነዚህ ነገሮች የሌዋውያኑ ሥራ መሆናቸው በ9፥22-34 ላይ ተጠቅሰዋል) በተጨማሪም መሥዋዕት በሚቀርብበት ጊዜ ሌዋውያኑ ካህናቱን እንደሚረዷቸው የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በዝርዝር አስቀምጦታል።

*23፥30 ጠዋት... ማታ፤* ዘፀ29፥38-41 ዘኍ28፥3-8 ይመ።

*24፥1-19፤* እስራኤላውያን ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ የካህናትን ስም ዝርዝር የያዙ ብዙ ጽሑፎች ተዘጋጅተዋል (6፥3-15፤ 9፥10-13፤ ዕዝ2፥36-39፤ ነህ10፥1-8፤11፥10-12፤12፥1-7፡12-21)።

*24፥2 ናዳብና አብዮድ... ሞቱ፤* እዚህ ላይ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ በዘሌ10፥1-3 ላይ የተጻፈውን ማመልከቱ ነው።

24፥3 *ሳዶቅና... አቢሜሌክ፤* ሳዶቅና አብያታር በዳዊት ዘመን ሊቀካህናት ሆነው አገልግለዋል። ዳዊት ዕድሜው እየገፋ ከመጣ በኋላ የአቤሜሌክ ልጅ አብያታር አባቱ ከሚያከናውናቸው የአገልግሎት ሥራዎች አንዳንዱን ይሠራ ነበር፡ (የ6፥8 ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ።

*24፥4 ዐሥራ ስድስት... ስምንት፤* ባጠቃላይ በሃያ አራት ክፍል የተመደቡ አገልጋዮች በዕጣ ተለዩ። ይህም ግብፃውያን አስከሬን በሚቀመጥባቸው ቤተ ጣዖታት የሚያገለግሉ ካህናት እንደሚያደርጉት በወር ተረኛነት ምድብ በአዲስ ኪዳን ዘመን ይደረግ እንደነበረው በየዓመቱ የሁለት ሳምንት ተረኝነት ተደልድሎ ማገልገል ማለት ነው። ከእነዚህ ምድብ ተረኞችም መካከል የመጀመሪያው፣ የሁለተኛው፣ የአራተኛው የዘጠነኛውና የሃያ አራተኛው ምድብ ተረኞች ስም ዝርዝር በቍምራን በአራተኛው ዋሻ ውስጥ በተገኘው የሙት ባሕር ጥቅል ብራና ላይ ተጽፎ ተገኝቶአል።

*24፥7 ለዮአሪብ፤* ለእግዚአብሔር አምልኮ ቀንተው አንጥዮኩስ ላቆመው ምስል እንዳይሰገድ የተቃወሙት የመቃብያኑ አባት የሆነው ማትያስ በዮአሪብ ምድብ ተራ ውስጥ የተመደበ ካህን ነበር (መቃ2፥1)።

*24፥10 ለአብያ፤* የዮሐንስ መጥምቁ አባት ዘካርያስ በአብያ የክህነት ምድብ ውስጥ ነበር (ሉቃ1፥5)።

24፥15 *ለኤዚር፤* በዘመነ ብሉይና በዘመነ ሐዲስ (በኪዳናት) መካከል በነበረው ጊዜ ውስጥ የኤዚር ቤተ ሰብ ምድብ እጅግ የታወቀ ነበር፤ ስሙም ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ

[17]ሃያ አንደኛው ለያኪን፣ ሃያ ሁለተኛው
ለጋሙል፣
[18]ሃያ ሦስተኛው ለድላያ፣ ሃያ አራተኛ
ለመዓዝያ ወጣ::
[19]የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ባዘዘ
ውና ከቀድሞ አባታቸው ከአሮን በተሰጣ
ቸው መመሪያ መሠረት ወደ እግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ በሚገቡበት ጊዜ፣ የተወሰነላ
ቸው ሥርዐት ይህ ነበር::

### የተቀሩት ሌዋውያን

[20]ከቀሩት የሌዊ ዘሮች ደግሞ:-
ከእንበረም ወንዶች ልጆች፤ ሱባኤል፤
ከሱባኤል ወንዶች ልጆች፤ ዬሕድያ::
[21]ከረዓብያ ወንዶች ልጆች፤አለቃው ይሺያ::
[22]ከይስዓራውያን ወገን፤ ሰሎሚት
ከሰሎሚት ወንዶች ልጆች፤ ያሐት::
[23]የኬብሮን ወንዶች ልጆች፤ የመጀመሪ
ያው ይሪያ^፣ ሁለተኛው አማርያ፣ ሦስ
ተኛው የሕዚኤል፣አራተኛው ይቀምዓም::
[24]የዑዝኤል ልጅ፤ ሚካ::
ከሚካ ወንዶች ልጆች ሻሚር::
[25]የሚካ ወንድም ይሺያ፤
ከይሺያ ወንዶች ልጆች ዘካርያስ::
[26]የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤ ሞሖሊ፣ሙሲ::
የያዝያ ወንድ ልጅ በኖ::
[27]የሜራሪ ወንዶች ልጆች፤
ከያዝያ በኖ፣ ሾሃም፣
ዘኩር፣ ዔብሪ::
[28]ከሞሖሊ፤ አልዓዛር፤ ይህ ሰው ወንዶች
ልጆች አልነበሩትም::
[29]ከቂስ፤ የቂስ ወንድ ልጅ፤
ይረሕምኤል::
[30]የሙሲ ወንዶች ልጆች፤ ሞሖሊ፣
ዔዳር፣ኢያሪሙት::
እነዚህ እንግዲህ እንደየቤተ ሰባቸው የተ
ቈጠሩ ሌዋውያን ነበሩ:: [31]ወንድሞቻቸው
የአሮን ዘሮች እንዳደረጉት ሁሉ፣ እነዚህም
በንጉሥ ዳዊት፣ በሳዶቅ፣ በአቢሜሌክ እንዲ
ሁም የካህናቱና የሌዋውያኑ ቤተ ሰብ አለቆች
ባሉበት ዕጣ ተጣጣሉ፤ የበኵሩም ቤተ ሰቦች
እንደ ትንሹ ወንድም ቤተ ሰብ እኩል ዕጣ
ተጣለላቸው::

### የቤተ መቅደሱ መዘምራን

**25** ዳዊት ከሰራዊቱ አለቆች ጋር ሆኖ
በመሰንቆ፣ በበገናና በጸናጽል ድምፅ
እየታጀቡ ትንቢት የሚናገሩትን ከአሳፍ፣
ከኤማንና ከኤዶታም ቤተ ሰብ መካከል
መርጦ መደበ፤ ይህን አገልግሎት የሚያከና
ውኑትም ሰዎች ዝርዝር እንደሚከተለው ነው፤
[2]ከአሳፍ ወንዶች ልጆች፤
ዘኩር፣ ዮሴፍ፣ ነታንያ፣ አሸርኤላ::
የአሳፍ ልጆች በአሳፍ አመራር ሥር
ነበሩ፤ አሳፍም በንጉሡ አመራር ሥር
ነበረ::
[3]ከኤዶታም ወንዶች ልጆች፤
ጎዶልያስ፣ ጽሪ፣ የሻያ፣ ሰሜኢ^፣ ሐሸ
ብያ፣ መቲትያ:: እነዚህ ስድስቱ በመ
ሰንቆ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየ
ወደሰ ትንቢት በተናገረው አባታቸው
በኤዶታም አመራር ሥር ነበሩ::
[4]ከኤማን ወንዶች ልጆች፤
ቡቅያ፣ መታንያ፣ ዓዛርኤል፣ ሱባኤል፣
ኢያሪሙት፣ ሐናንያ፣ ሐናኒ፣ ኤልያታ፣
ጊዶልቲ፣ ሮማንቲዔዘር፣ ዮሽብቃሻ፣
መሎቲ፣ ሆቲር፣ መሐዝዮት:: [5]እነዚ
ህም ሁሉ የንጉሡ ባለ ራእይ የኤማን
ልጆች ነበሩ:: እርሱን ከፍ ከፍ እንዲ
ያደርጉትም እግዚአብሔር በገባለት ቃል
መሠረት ሰጡት~:: እግዚአብሔር ለኤ
ማን ዐሥራ አራት ወንዶችና ሦስት
ሴቶች ልጆች ሰጠው::
[6]እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ቤተ መቅ
ደስ በጸናጽል፣በመሰንቆና በበገና ድምፅ
ለሚቀርበው የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት
በአባቶቻቸው አመራር ሥር ነበሩ:: አሳፍ፣
ኤዶታምና ኤማን ደግሞ በንጉሡ የበላይ
አመራር ሥር ነበሩ:: [7]እነዚህም ከቤተ ዘመ
ዶቻቸው ጋር በመሆን ሁሉም ወደ እግዚአ
ብሔር በሚቀርበው ዜማ የሠለጠኑና የተ
ካኑ ነበሩ፤ ቍጥራቸውም ሁለት መቶ ሰማ
ንያ ስምንት ነበረ:: [8]የሥራ ድርሻቸውንም
ለመወሰን ወጣት፣ ሽማግሌ፣ መምህርም ሆነ
ደቀ መዝሙር ሳይባል እኩል ዕጣ ተጣጣሉ::
[9]የመጀመሪያው ዕጣ ከአሳፍ ወገን ለሆ
ነው ለዮሴፍ ወንዶች ልጆቹና ለቤተ

24፥20 1ዜና23፥6
24፥21 1ዜና23፥17
24፥23 1ዜና23፥19
24፥26 1ዜና6፥19
24፥31 ቍ5
25፥1 1ሳሙ10፥5፤2ነገ3፥15፤1ዜና6፥31:33፤15፥16፤16፥41:42፤2ዜና5፥12፤8፥14፤34፥12፤35፥15፤ዕዝ3፥10፤ነህ11፥17
25፥3 ዘፍ4፥21፤1ዜና16፥41-42፤መዝ33፥2
25፥6 1ዜና15፥16:19፤2ዜና23፥18፤29፥25
25፥8 1ዜና26፥13
25፥9 1ዜና6፥39

^23 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆችና ጥቂት የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1 ዜና23፥19 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *"የይሪያ ወንዶች ልጆች"* ይላሉ
^3 አንድ የዕብራይስጥ ቅጅና ጥቂት የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም ቍጥር17 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *"ሰሜኢ"* የሚለውን አይጨምሩም
~5 ዕብራይስጡ፤ *"ቀንዱ ከፍ ከፍ አለ"* ይላል

ባለው በቄድሮን ሸለቆ ከሚገኝ ከአንድ ትልቅ መቃብር ላይ ተጽፎ ይገኛል::

*24፥20-31፤* ይህ የስም ዝርዝር በ23፥7-23 ላይ የተጠቀሱትን አንዳንድ መስመሮች ሰፋ አድርጎ በማቅረብ ከዚያ ጋር የሚያያይዝ ነው::

25፥1 *ከሰራዊቱ አለቆች፤* ዳዊት አብዛኛውን ጊዜ የጦር መሪዎችን ምክር ይጠይቅ ነበር (11፥10፤12፥32፤28፥1)፤ ሌላው ቀርቶ የሥርዐተ አምልኮን ጉዳይ በሚመለከት እንኳ ያማክራቸው ነበር (13፥1፤15፥25):: *ከአሳፍ፣ ከኤማንና ከኤዶታም፤* የ6፥31 ማብ ይመ፤ የትንቢት አገልግሎት የአምልኮ አገልጋዮች "ነቢይ" ተብለው የተገለጹት በዜና መዋዕሉ መጻሕፍት ውስጥ ብቻ ሲሆን በብዙ ክፍሎች ውስጥ ተጠቅሰዋል:: እዚህ ላይ፤ 2ዜና 20፥14-17፤ 29፥30፤35፥15፤ ከ2ነገ23፥2 ከ2ዜና34፥30 ጋር ያነጻጽሩ:: ካህኑ ዘካርያስ ምንም እንኳ ነቢይ ተብሎ ባይጠራም የነቢይነትን አገልግሎት ሲያከናውን ይታያል:: (2ዜና24፥19-22):: ይህም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፣ ነቢይ፣ ካህንና ንጉሥ የሆነው መሲህ ይመጣል ብለው ሕዝቡ እንዴት ይጠብቁ እንደነበረ የሚያንጸባርቅ (የሚያመላክት) ነው:: በዜና መዋዕሉ መጻሕፍት ትንቢት የሚናገሩት ካህናት ብቻ ሳይሆኑ፣ ነገሥታቱም የካህናቱን ተግባር ያከናውኑ ነበር (የ15፥27፤የ16፥1-3 ማብ ይመ):: ዳዊት በቤተ መቅደስ እንዲያገለግሉ ያደራጃቸው መዘምራን፣ እርሱ ስለ መዝሙር የነበረውን ከፍተኛ ስሜት የሚያንጸባርቁ ናቸው (1 ሳሙ 16፥23፤18፥0፤19፥9፤2ሳሙ1፥17-27፤6፥5:14)::

*25፥5፡ ዐሥራ አራት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች፤* የልጆች ብዛት ከእግዚአብሔር በረከት የማግኘት ምልክት ነው:: (ኢዮ1፥2፤42፥13):: እግዚአብሔር ሔማንን ከፍ ከፍ ሊያደርገው እንደፈለገ የገባለትን ተስፋ እንደፈጸመለት ለማሳየት ነው 3፥1-9፤ 14፥2-7፤26፥4-5፤2ዜና፡11፥18-21፤13፥21፤21፥2፤ 24፥3፡ ይመ::

ጕበዝ የሆኑ አንድ ሺህ ሰባት መቶ
ሰዎች ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በሚ
ገኘው የእስራኤል ምድር ላለው *የእግ
ዚአብሔር ሥራና ለንጉሡም አገል
ግሎት* ኀላፊዎች ሆነው ተመደቡ::
[31]በኬብሮናውያን በኩል በቤተ ሰቦቻ
ቸው የትውልድ መዝገብ መሠረት
ይሪያ አለቃቸው ነበረ:: በዳዊት ዘመነ
መንግሥት *በአርባኛው ዓመት* መዛ
ግብቱ ተመርምረው ስለ ነበር፣በገለዓድ
ውስጥ ኢያዜር በተባለ ቦታ ከኬብሮና
ውያን መካከል ጠንካራ ሰዎች ሊገኙ
ችለዋል:: [32]ይሪያም ጠንካሮችና የቤተ
ሰባቸው አለቆች የሆኑ ሁለት ሺህ
ሰባት መቶ ሥጋ ዘመዶች ነበሩት::
ንጉሥ ዳዊትም እነዚህን የእግዚአብሔር
ለሆነውና የንጉሡም በሆነው ጕዳይ
ላይ ሮቤልን፣ ጋድንና የምናሴን ነገድ
እኵሌታ ኀላፊ አድርጎ ሾማቸው::

## የሰራዊቱ ዋና ዋና ክፍሎች

**27** የእስራኤል የቤተ ሰቡ አለቆች፣ የሻ
ለቆች፣ የመቶ አለቆች እንዲ
ሁም ዓመቱን ሙሉ በየወሩ የሚመደቡትን
ዋና ዋና ክፍሎች በተመለከተ ንጉሡን ያገ
ለገሉ አለቆቻቸው ዝርዝር ይህ ነው:: እያንዳ
ንዱ ዋና ክፍል ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረው::
[2]በመጀመሪያው ወር የመጀመሪያው ዋና
ክፍል የበላይ የዘብድኤል ልጅ ያሾ
ብዓም ሲሆን፣ በሥሩ የሚታዘዙ ሃያ አ
ራት ሺህ ሰዎች ነበሩ:: [3]እርሱም
የፋሬስ ዘር ሲሆን፣ በመጀመሪያው ወር
የሰራዊቱ ሹማምት ሁሉ የበላይ ነበር::
[4]በሁለተኛው ወር የክፍለ ጦሩ የበላይ
አዛዥ አሆሃዊው ዱዲ ሲሆን፣ የዚሁ
ክፍል መሪ ደግሞ ሚቅሎት ነው፤
በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ::
[5]በሦስተኛውም ወር የሦስተኛው ክፍለ
ጦር የበላይ አዛዥ የካህኑ የዮዳሄ ልጅ
በናያስ ነበረ፤ ዋናው እርሱ ሲሆን፣ በሥሩ
ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ:: [6]ይህም
ከሠላሳዎቹ ይልቅ ኀያል ሲሆን፣ የሠላ
ሳዎቹ የበላይ ነበረ፤ ልጁ ዓሚዛባድም
የክፍሉ ሰራዊት አዛዥ ነበረ::
[7]በአራተኛው ወር አራተኛው የበላይ
አዛዥ የኢዮአብ ወንድም አሣሄል ሲሆ
ን፣ በእግሩ የተተካውም ልጁ ዝባድያ
ነው፤ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው
ነበረ::
[8]በአምስተኛው ወር አምስተኛው የበላይ
አዛዥ ይዝራዊው ሸምሁት ሲሆን፣
በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ::
[9]በስድስተኛ ወር ስድስተኛው የበላይ
አዛዥ የቴቁሐዊው የዒስካ ልጅ ዒራስ
ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው
ነበረ::
[10]በሰባተኛው ወር ሰባተኛው የበላይ
አዛዥ የኤፍሬም ወገን የሆነው ፍሎና
ዊው ሴሌስ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት
ሺህ ሰው ነበረ::
[11]በስምንተኛው ወር ስምንተኛው የበላይ
አዛዥ ከካዛራውያን ወገን የሆነው ኩሳ
ታዊው ሲቦካይ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ
አራት ሺህ ሰው ነበረ::
[12]በዘጠነኛው ወር ዘጠነኛው የበላይ አዛዥ
ከብንያም ወገን የሆነው ዓናቶታዊው
አቢዔዜር ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ አራት
ሺህ ሰው ነበረ::
[13]በዐሥረኛው ወር ዐሥረኛው የበላይ
አዛዥ ከከዛራውያን ወገን የሆነው ነጦ
ፋዊው ኖኤሬ ሲሆን፣ በሥሩም ሃያ
አራት ሺህ ሰው ነበረ::
[14]በዐሥራ አንደኛው ወር ዐሥራ አንደ
ኛው የበላይ አዛዥ ከኤፍሬም ወገን
የሆነው ጲርዓቶናዊው በናያስ ሲሆን፣
በሥሩም ሃያ አራት ሺህ ሰው ነበረ::
[15]በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ ሁለ
ተኛው የበላይ አዛዥ ከጎቶንያል ቤተ
ሰብ የሆነው ነጦፋዊው ሔልዳይ ነበረ::

## የየነገዱ የጦር ሹማምት

[16]የየነገዱ የእስራኤል የጦር ሹማምት፤

በሮቤል ነገድ ላይ የተሾመው፣ የዝክሪ
ልጅ አልዓዛር፤
በስምዖን ነገድ ላይ የተሾመው፣ የመዓካ
ልጅ ሰፋጥያስ::

26፥31 2ሳሙ 5፥4፤1ዜና 23፥19
27፥2 2ሳሙ 23፥8
27፥4 2ሳሙ 23፥9
27፥5 2ሳሙ 23፥20
27፥7 2ሳሙ 2፥18
27፥8 1ዜና 11፥27
27፥9 2ሳሙ 23፥26
27፥10 2ሳሙ 23፥26
27፥11 2ሳሙ 21፥18
27፥12 2ሳሙ 23፥27
27፥13 2ሳሙ 23፥28
27፥14 1ዜና 11፥31
27፥15 ኢሱ 15፥17፤2ሳሙ 23፥29

*አገልግሎት... የእግዚአብሔር ለሆነውና የንጉሡም በሆነው ጕዳይ፤* እግዚአብሔር ራሱ ገዥ ሆኖ ሕዝቡን በሚያስተዳድርበት በሥጋዊውና በመንፈሳዊው አስተዳደር መካከል ልዩነት የለም፤ ሰማያዊውን አምላክና ምድራዊውን ንጉሥ በማገልገል ረገድ የሚፈጠር ምንም ዐይነት ጭንቀትና ውጥረት የለም (ከማቴ 22፥15-22፤ ከሉቃ 16፥10-13፤ ከሮሜ 13፥1-7፤ ከ1ጢሞ 2፥1-4፤ ከ1ጴጥ 2፥13-17 ጋር ያነጻጽሩ)::

*26፥31 በአርባኛው ዓመት፤* የዳዊት ዘመነ መንግሥት የመጨረሻው ዓመት ነው::

*27፥1-15፤* የዳዊት የጦር አዛገሮቹ ስም ዝርዝር ከእርሱ ኀያላን ስም ዝርዝር ጋር አንድ ነው (11፥11-47 ይመ፤ እንዲሁም 2ሳሙ 23፥8-39 እና ማብ ይመ):: ከሳኦል ሸሽቶ በሄደ ጊዜ ዳዊትን ያገለገሉት ሰዎች በመደበኛውም ተዋጊ ሠራዊት ውስጥ አዛገሮች የሆኑት እነርሱ ናቸው::

27፥1 *ሃያ አራት ሺህ፤* የ12፥23-37 ማብ ይመ:: መደበኛ ወታደሮች ያልሆኑ በውትድርና ሙያ የሠለጠኑ፣ ነገር ግን መደበኛ ወታደር ያልሆነው፣ በዐሥራ ሁለት ምድብ የተከፈለውና እያንዳንዱ ሃያ አራት ሺህ (ጠቅላላ ድምሩ ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ) ሠራዊት ይሆናል:: ከዚህ በመነሣት ቍጥሩ ተጋኖ አል ለማለት አይቻልም:: እዚህም ላይ በእያንዳንዱ ምድብ አዛዥ ውስጥ "አንድ ሺህ" ተብሎ የተጠቀሰው ቍጥር የሚያሳየው በዚህ ዐይነቱ ምድብ ውስጥ መከተት የሚገባውን ከፍተኛ ቍጥር ለማመልከት እንጂ፣ ያን ያህል ሰው ግድ መኖር እንዳለበት ለማሳየት አይደለም:: በዚህም መሠረት በሚቀጥሉት ቍጥሮች ውስጥ 24,000 የሚለውን ቍጥር ከመጠቀም ፈንታ "24 ምድብ (ክፍል)" ብሎ ማንበብ ይቻላል::

27፥2 *ያሾብዓም፤* 11፥11 ይመ::

*27፥4 ዱዲ፤* 11፥12 ይመ::

*27፥5 በናይስ፤* 11፥22-25፤18፥17 ይመ::

*27፥7 አሣሄል፤*11፥26፤2ሳሙ 2፥18-23 ይመ

*27፥9-15፤* የቀሩት አዛገሮች የተመረጡት ከሠላሳዎቹ መካከል ነበር (የስም ዝርዝራቸውን ከ11፥27-31 ውስጥ ይመ)::

*27፥16-22፤* "እስራኤል ሁሉ" ለሚለው ሐረግ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ ልዩ ትኵረት የሰጠው ሲሆን፣ ይህም በዐሥራ ሁለቱ

17በሌዊ ነገድ ላይ የተሾመው የቀሙኤል
ልጅ ሐሸብያ፤
በአሮን ነገድ ላይ የተሾመው፣ ሳዶቅ።
18በይሁዳ ነገድ ላይ የተሾመው፣
የዳዊት ወንድም ኤሊሁ፤
በይሳኮር ነገድ ላይ የተሾመው፣የሚካ
ኤል ልጅ ዖምሪ።
19በዛብሎን ነገድ ላይ የተሾመው፣ የአብ
ድዩ ልጅ ይሽማያ፤
በንፍታሌም ነገድ ላይ የተሾመው፣
የዓዝሪኤል ልጅ ኢያሪሙት።
20በኤፍሬም ነገድ ላይ የተሾመው፣ የዓዛ
ዝያ ልጅ ሆሴዕ፤
በምናሴ ነገድ እኩሌታ ላይ የተሾመው፣
የፈዳያ ልጅ ኢዩኤል።
21በገለዓድ ባለው የምናሴ ነገድ እኩሌታ
ላይ የተሾመው፣ የዘካርያስ ልጅ አዶ፤
በብንያም ነገድ ላይ የተሾመው፣ የአበ
ኔር ልጅ የዕሢኤል።
22በዳን ነገድ ላይ የተሾመው፣ የይሮሐም
ልጅ ዓዛርኤል፤
እንግዲህ የእስራኤል ነገድ አለቆች እነ
ዚህ ነበሩ።
23እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ ሰማይ
ከዋክብት እንደሚያበዛቸው ተስፋ ሰጥቶ ስለ
ነበር፣ ዳዊት ዕድሜያቸው ሃያና ከዚያ
በታች የሆነውን አልቈጠረም ነበር። 24የጽ
ሩያ ልጅ ኢዮአብ መቍጠር ጀመረ፤
ሆኖም አልፈጸመውም፤ መቈጠራቸው በእስ
ራኤል ላይ ቍጣ ስላመጣ፣ የተቈጠረውም
በንጉሡ ዳዊት መዝገብ አልገባም።

### ንጉሡ የሾማቸው የበላይ ተቈጣጣሪዎች

25የዓዲኤል ልጅ ዓዝሞት የቤተ መንግ
ሥቱ ዕቃ ቤት ኀላፊ ነበረ፤
የዖዚያ ልጅ ዮናታን በየአውራጃው በየ
ከተማው፣ በየመንደሩና በየቃፊር መጠበቂ
ያው ላሉት ዕቃ ቤቶች ኀላፊ ነበረ።
26የክሉብ ልጅ ዔዝሪ ምድሪቱን ለሚያር
ሱት ገበሬዎች ኀላፊ ነበረ።
27ራማታዊው ሰሜኢ የወይን ተክል ቦታ
ዎች ኀላፊ ነበረ፤ ሽፋማዊው ዘብዲ ይወ
ይን ጠጅ ዕቃ ቤት ኀላፊ ነበረ።
28ጌድራዊው በአልሐናን በምዕራባዊው ኰረ
ብታዎች ግርጌ ለሚገኙት የወይንና የወርካ
ዛፎች ጥበቃ ኀላፊ ነበረ።
29ሳሮናዊው ሰጥራይ በሳሮን ለሚሰማሩት
የከብት መንጋዎች ኀላፊ ነበረ፤
የዓድላይ ልጅ ሻፋጥ በሸለቆው ውስጥ
ላሉት የከብት መንጋዎች ኀላፊ ነበረ።
30እስማኤላዊው ኡቢያስ የግመሎች ኀላፊ
ነበረ።
ሜሮኖታዊው ዩሕድያ የአህዮች ኀላፊ ነበረ።
31አጋራዊው ያዚዝ የበግና የፍየል መን
ጋዎች ኀላፊ ነበረ።
እነዚህ ሁሉ የንጉሥ ዳዊት ንብረት
ኀላፊዎች ነበሩ።
32አስተዋይ የሆነው የዳዊት አጎት ዮና
ታን አማካሪና ጸሓፊ ነበረ፤ የሐክሞኒም
ልጅ ይሒኤል ደግሞ የንጉሡ ልጆች ሞግ
ዚት ነበረ።
33አኪጦፌል የንጉሡ አማካሪ ሲሆን፣ አር
ካዊው ኩሲ ደግሞ የንጉሡ ወዳጅ ነበረ።
34የበናያስ ልጅ ዮዳሄና አብያታር በአኪ
ጦፌል እግር ተተኩ።
ኢዮአብም የንጉሡ የክብር ዘብ አዛዥ ሆነ።

### ዳዊት ስለ ቤተ መቅደሱ ያወጣው ዕቅድ

28 ዳዊት በኢየሩሳሌም እንዲሰበሰቡ
የነገዱን የጦር አለቆች፣ ንጉሡን
የሚያገለግሉትን የክፍለ ጦር አዛዦች፣ የሻ
ለቆቹን፣ የመቶ አለቆቹን፣ የንጉሡና የል

27፥17
2ሳሙ8፥17፤1ዜና12፥
28፤26፥30
27፥23
ዘፍ12፥2፤2ሳሙ24፥1
፤1ዜና21፥2-5
27፥24
2ሳሙ24፥15፤
1ዜና21፥14
27፥28 1ነገ10፥27
27፥29 መሐ2፥1፤
ኢሳ33፥9፤35፥2፤
65፥10
27፥31 1ዜና5፥10
27፥33
2ሳሙ15፥12:37
27፥34 1ሳሙ22፥20
፤2ሳሙ2፥13
28፥1
1ዜና22፥17፤
1ዜና27፥1-31፤29፥6

ነገድ ላይ በተሾሙት የጦር አለቆች ስም ዝርዝርም ላይ በግልጽ ይታያል (በመጽሐፉ መግቢያ "ዐላማውና መሪ ሐሳቡ" የሚለውን ይመ)። የነገዶቹን ቍጥር በተመለከተ ዐሥራ ሁለት የሚለው ተጠብቆአል፤ ይህ ሊሆን የቻለውም ጋድንና አሴርን ሳያወጣ በዝምታ በማለፉ ነው (የ2፥1-2 ማብ ይመ)።

*27፥17 ሳዶቅ፤* የ6፥8 ማብ ይመ። እንዲሁም 12፥28፤ 16፥39 ይመ።

*27፥18 ኤሊሁ፤* የዳዊት ወንድሞች ስም በተጠቀሰባቸው በሌሎች ቦታዎች፣ ስሙ ሳያወጣ የታለፈ ልጅ ሳይሆን አይቀርም (የ2፥10-17 ማብ በዚያው ይመ)። ኤሊሁ የእሴይ የበኵር ልጁ የኤልያብ ሌላ ስሙ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ "ወንድም" የሚለው ቃል ከአባትና ከእናት ለሚወለዱ ልጆች ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ዘመድ መካከል ያለ የቅርብም ሆነ የሩቅ ተወላጅ የሚጠራበት ስም ስለሆነ፣ ሩቅ የሥጋ ዘመድም ሊሆን ይችላል።

*27፥21 የአበኔር፤፣* የንጉሥ ሳኦል ሥጋ ዘመድ ነው (26፥28፤ 1ሳሙ14፥50-51፤17፥55-58፤26፥5-16፤ 2ሳሙ 2፥8-4፥1)።

*27፥23-34 መቍጠር...፤* በም 21 ላይ የተጻፈውን ጠቅላላ የሕዝብ ቈጠራ ያመለክታል (2ሳሙ 24)።

*27፥23 ዕድሜያቸው ሃያና ከዚያ በታች የሆነውን፤* በም 21ና በ2ሳሙ24 ላይ ቍጥሩ የተመለከተው ሰራዊት ዕድሜው ከሃያ ዓመት በላይ ነበር። *እስራኤልን እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደሚያበዛቸው፤* ኢዮአብ የሕዝቡን ቈጠራ የተቃወመው (21፥3፤2ሳሙ24፥3) እግዚአብሔር ለብሉይ ኪዳን አባቶች ዘራቸውን እጅግ እንደሚያበዛ የሰጠውን ተስፋ (ዘፍ12፥2፤13፥16፤ 15፥5፤22፥7) በማሰብ ነው።

*27፥24 አልፈጸመውም፤* ኢዮአብ ዕድሜያቸው ከሃያ ዓመት በታች የሆነውን፣ እንዲሁም የሌዊንና የብንያምን ነገዶች አልቈጠረም።

*27፥25-31፤* የዳዊትን ሀብት ንብረት ለማስተዳደር ኀላፊነቱ የተሰጣቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ነው (ቍ31)። የጥንቶቹ የመካከለኛው ምሥራቅ አገር ከተሞች ሀብት ንብረት በሦስት የተከፈለ ነበር (1) የቤተ መንግሥት (2) የቤተ መቅደስ (3) የግል። በዳዊት ዘመነ መንግሥት ይህንንና ይህንን በመሳሰለው ላይ በቀጥታ የሚጣል ግብር ወይም የሚከፈል ቀረጥ ስለመኖሩ በግልጽ የሚያስረዳ ነገር የለም። ታዲያ ለቤተ መንግሥቱ የሚያስፈልገው ገንዘብ የሚገኘው፣ በስፋት ከተያዘው ርስት፣ ከንግድ ገቢ፣ዳዊት በየጊዜው ካደረገው ጦርነት ከተሰበሰበ ምርኮ፣ ድል ሆነው የበላይነቱን አምነው በመቀበል በየጊዜው ከሚገብሩለት ነገሥታት ነበር።

*27፥32-34፤* በ18፥14-17 ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ የተጠቀሱ የንጉሡ ባለሟሎች ወይም የቅርብ ረዳቶቹ የስም ዝርዝር ነው።

*27፥33 አኪጦፌል፤* አቤሴሎም ባባቱ ላይ ዐምፆ በተነሣበት ጊዜ የደገፈውና ሤራው ሲከሽፍ ራሱን ያጠፋው አኪጦፌል በሌላ ተተክቶአል፡ (2ሳሙ15፥12:31-37፤16፥20-17፥23)።

*27፥34 የበናያስ፤* ቍ5 ይመ።

*28፥1-29፥30፤* የአገዛዝ ሥልጣኑ ከዳዊት ወደ ሰሎሞን እንዴት እንደተላለፈ የሚያወሳውን ታሪክ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ፣ ከዙፋኑ ውርስ ታሪክ ጋር በማነጻጸር፣ የሁለቱን ነገሥታት ዘመን የሚያየው እጅግ ከፍ ያለ ግምት በመስጠት ነው (1ነገ1-2)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ አረጋዊውን ዳዊትን እርጅናው እንዴት እንደ ተጫጫነው (1ነገ1፥1-4)፣ የአዶንያስንና የንጉሡን ልጆች ዐመፅ (1ነገ1፥5-10)፣ የሰሎሞንን ሕጋዊ የዙፋን ወራሽነት ለማደላደልና በእናቱ በቤርሳቤህና በነቢዩ በናታን መካከል የተደረገውን ውስጠ ምክክር (1ነገ1፥11-31)፣ ወይም ደግሞ ዳዊት ከዚህ ዓለም

ጆቹ ንብረትና ከብት ሁሉ ኀላፊ የሆ
ኑትን፣ እንዲሁም የቤተ መንግሥቱን ሹማ
ምት፣ ኀያላንና ጀግና ተዋጊዎቹን፣ በእጠ
ቃላይ የእስራኤልን ሹማምት ሁሉ ጠራ።
2ከዚያም ንጉሥ ዳዊት በእግሩ ቆሞ እን
ዲህ አላቸው፤ “ወንድሞቼና ወገኖቼ ሆይ፤
እስቲ አድምጡኝ፤ ለእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ
ታቦት ማደሪያና ለአምላካችን እግር ማረፊያ
የሚሆን ቤት ለመሥራት ዐስቤ ዕቅድ አው
ጥቼ ነበር። 3እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ፤
‘ጦረኛ ሰው ስለ ሆንህና ደምም ስላፈሰ
ስህ፣ አንተ ለስሜ ቤት አትሠራም’።
4“ነገር ግን የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
በእስራኤል ላይ ለዘላለም እንድነግሥ ከቤተ
ሰቤ ሁሉ እኔን መረጠ፤ መሪ እንዲሆንም
ይሁዳን መረጠ፤ ከይሁዳም ቤት የእኔን
ቤተ ሰብ መረጠ፤ ከአባቴ ልጆች መካከል
ደግሞ በመላው እስራኤል ላይ እንድነግሥ
ፈቃዱ ሆነ። 5እግዚአብሔር ብዙ ልጆች
ሰጥቶኛል፤ ከወንዶቹ ልጆቼ ሁሉ በእግዚአ
ብሔር መንግሥት ዙፋን ላይ ተቀምጦ በእ
ስራኤል ሁሉ ላይ እንዲነግሥ ደግሞ ልጄን
ሰሎሞንን መርጦታል። 6እንዲህም አለኝ፤
‘ቤቴንና አደባባዮቼን የሚሠራልኝ ልጅህ
ሰሎሞን ነው፤ ምክንያቱም ልጄ እንዲሆን
መርጬዋለሁ፤ እኔም አባት እሆነዋለሁ።
7አሁን እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ትእዛዞቼ
ንና ሕጎቼን ምንጊዜም ሳያወላውል የሚፈ
ጽም ከሆነ፣ መንግሥቱን ለዘላለም አጸና
ታለሁ’።
8“እንግዲህ አሁንም ይህቺን መልካሚቱን
ምድር እንድትወርሱና ለልጆቻችሁም የዘላ
ለም ርስት አድርጋችሁ እንድታወርሱአ
ቸው፣ የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ ሁሉ በጥን
ቃቄ እንድታከብሩ በእስራኤል ሁሉ ፊት፣
በእግዚአብሔር ጉባኤና እግዚአብሔርም እየሰማ
አዛችኋለሁ።
9“አንተም ልጄ ሰሎሞን ሆይ፤ እግዚአብሔር
ልብን ሁሉ ስለሚመረምርና ሐሳብን ሁሉ
ስለሚያውቅ፣ የአባትህን አምላክ ዕወቅ፤

28፥2 1ሳሙ 10፥7፤ 1ዜና 17፥2፤2ዜና 6፥41፤መዝ 99፥5፤132፥1-5፡7፤ኢሳ 60፥13
28፥3 2ሳሙ 7፥5፤1ነገ 5፥3፤1ዜና 17፥4፤22፥8
28፥4 ዘፍ 49፥10፤ ዘኍ 24፥17-19፤1ሳሙ 16፥1-13፤ 1ዜና 11፥1፤2ዜና 6፥6
28፥5 2ሳሙ 12፥24፤1ዜና 3፥1፤17፥14፤23፥1
28፥6 2ሳሙ 7፥13፤1ነገ 8፥20፤1ዜና 17፥13
28፥7 1ዜና 22፥13
28፥8 ዘዳ 4፥1፤6፥1፤ 17፥14-20፤1 ዜና 9፥1
28፥9 ዘዳ 4፥31፤ ኢሱ 24፥20፤ 1ሳሙ 2፥3፤1ነገ 9፥7፤1 ዜና 16፥11፤1ዜና 29፥19 2ዜና 6፥30፤7፥19፤15፥2፤መዝ 7፥9፤40፥16፤44፥23፤74፥1፤77፥7
28፥11 ዘፀ 25፥9፤ ሐሥ 7፥44፤ዕብ 8፥5
28፥12 1ዜና 12፥18፤26፥20
28፥13 1ዜና 24፥1
28፥15 ዘፀ 25፥31
28፥16 ዘፀ 25፥23
28፥17 ዘፀ 27፥3
28፥18 ዘፀ 25፥20፡22፤30፥1-10
28፥19 ዘፀ 25፥9፤1ነገ 6፥38

በፍጹም ልብና በበጎ ፈቃድ አገልግለው።
ከፈለግኸው ታገኘዋለህ፤ ከተውከው ግን
እርሱም ለዘላለም ይተውሃል። 10ለመቅደስ
የሚሆን ቤት እንድትሠራ እግዚአብሔር
የመረጠህ መሆኑን አሁንም ዐስብ፤ በርት
ተህም ሥራ።
11ከዚያም ዳዊት የቤተ መቅደሱን መመ
ላለሻ፣ የሕንጻውን፣ የዕቃ ቤቶቹን፣ የፎቁንና
የውስጥ ክፍሎቹን እንዲሁም የማስተስረያውን
ቦታ ንድፍ ለልጁ ለሰሎሞን ሰጠው። 12ደግ
ሞም መንፈስ ቅዱስ በልቡ ያሳደረውን የእ
ግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አደባባይ፣ በዙ
ሪያው ያሉትን ክፍሎች ሁሉ፣ የእግዚአብሔ
ርን ቤተ መቅደስ ዕቃ ቤቶችና የንዋየ ቅድ
ሳቱን ግምጃ ቤቶች ንድፍ ሁሉ ሰጠው፤
13እንዲሁም የካህናቱንና የሌዋውያኑን አመ
ዳደብ፣ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገል
ግሎት ሥራና ለአገልግሎቱ ስለሚጠቀምባ
ቸው ዕቃዎች ሁሉ መመሪያ ሰጠው። 14ለልዩ
ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን የወርቅ ዕቃ
ዎች ሁሉ መጠን፣ ለልዩ ልዩ አገልግሎት
የሚውሉትን የብር ዕቃዎች ሁሉ መጠን
አሳወቀው፤ 15እንደየመቅረዙ አገልግሎት ዐይ
ነት ለወርቁ መቅረዞችና ለቀንዲሎቻቸው
የሚሆነውን የእያንዳንዳቸውን የወርቅ መጠን፣
ለብሩ መቅረዞችና ለቀንዲሎቻቸው የሚያ
ስፈልገውን የእያንዳንዳቸውን የብር መጠን፣
16ለያንዳንዱ፣ ኅብስተ ገጽ ጠረጴዛ የሚያስ
ፈልገውን የወርቅ መጠን፣ ለእያንዳንዱም
የብር ጠረጴዛ የሚያስፈልገውን የብር መጠን፣
17ለሹካዎቹ፣ ለጐድጓዳ ሳሕኖቹ፣ ለማንቆር
ቆሪያዎቹ የሚያስፈልገውን ንጹሕ የወርቅ
መጠን፣ ለእያንዳንዱ የብር ሳሕን የሚያ
ስፈልገውን የብር መጠን፣ 18ለዕጣኑ መሠ
ዊያ የሚሆነውን የጠራ ወርቅ መጠን እንዲ
ሁም ክንፎቻቸውን ዘርግተው የእግዚአብሔ
ርን የቃል ኪዳኑን ታቦት የሚሸፍኑትን
ከወርቅ የተሠሩትን የኪሩቤል ሠረገሎች
ንድፍ ሰጠው።
19ዳዊትም፣ “ይህ ሁሉ፣ በእኔ ላይ ባለው
በእግዚአብሔር እጅ በጽሑፍ ተገለጠልኝ፤

በሞት ከተለየ በኋላ፣ ጠላቶቹን ልጁ ሰሎሞን በሞት ቀጥቶ እንዲበቀልለት ማዘዙን (1ነገ 2፥1-9) ሳይጠቅስ ዐልፎታል። ለቤተ መቅደሱ ሥራ የሚያስፈልገውን ዕቃ መምረጥ፣ ማዘጋጀቱም ሥልጣኑን በተረጋጋና በሰላማዊ መንገድ ለልጁ ለሰሎሞን ማስተላለፉን፣ ይህም “የእስራኤልን ሁሉ” (29፥25)፣ እንዲሁም የሹማምቱንና የሕዝቡን (28፥1-2፤29፥6-9፡21-25) ድጋፍ ማግኘቱን ያሳያል። እንዲህ እንደዛሬው ሽምግሎ ደክሞ ዐልጋ ላይ ከመዋሉና ልጁን ሰሎሞንን ቀብተው ሌሎች እንዲያነግሡት ከማድረጉ በፊት በሥርዐቱ ላይ ተገኝቶ ያነገሠው እርሱ ራሱ አልነበረም (23፥1 ይመ እና ማብ ይመ)።

*28፥11* በዚያ ከተሰበሰቡት የአብዛኛዎቹ ስም በም 27 ላይ ከተጠቀሱት ቡድኖች የስም ዝርዝር ውስጥ ይገኛል። ይህ በአደባባይ ይፋ የሆነው (ቍ 5) የሰሎሞን ሕጋዊ ወራሽነት (ንግሥና) ቀደም ሲል ዳዊት መሪዎችንና ሽማግሌዎችን ሰብስቦ ከወሰነ ም 22 በኋላ ያንኑ ውሳኔ ተከትሎ የተደረገ ነው (የ22፥2-19 ማብ ይመ)።

*28፥3 ጦረኛ ስለሆንህና ደም ስላፈሰስህ፤* የ22፥8-9፡ ማብ ይመ።

*28፥5 ልጄን ሰሎሞንን መርጦታል፤* ቍ 6፡10፤29፥1። ከዳዊት በኋላ በዕብራይስጡ “መርጦታል” በሚል የግሥ ማሠሪያ አንቀጽ ለንጉሥ የተጠቀሰው በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ እዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው፡ (ከመጽሐፉ መግቢያ “ዐላማውና መሪ ሐሳቡ” የሚለውን ይመ)። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ይህን ቃል ከሰሎሞን ጋር ማዛመዱ ለዚህ ንጉሥ ያለውን የማያቋርጥ ድጋፍ በግልጽ የሚያሳይ ነው። *በእግዚአብሔር መንግሥት፤* የ17፥14 ማብ ይመ።

*28፥6 ልጄ እንዲሆን፤* 17፥12-14 እና ማብ ይመ። እንዲሁም 22፥10 ይመ።

*28፥8-9፤* ከመጽሐፉ መግቢ “የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል” የሚለውን ይመ።

*28፥12፤* ዳዊት የቤተ መቅደሱን አሠራር የሚያሳይ ንድፍ ሰጠው። ይህም የሚያመለክተው የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዳዊት የሙሴን ምሳሌነት (አርአያነት) መከተሉን ለማንጸባረቅ ፈልጎ ነው። ሙሴ የምስክሩን ድንኳን አሠራር ንድፍ ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ሁሉ (ዘፀ 25-30) ዳዊትም ይህን የቤተ መቅደስ ቢጋር ከእግዚአብሔር የተቀበለው መሆኑን ለማመልከት ነው።

28፥19 *ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ባለው በእግዚአብሔር እጅ.. በጽሑፍ ተገለጠልኝ፤* የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ዕቅድ፣ ዳዊት የጻፈው ሌሎቹ የእግዚአብሔር ሰዎች በእግዚአብሔር ተመርተው በጻፉበት በተለመደው መንገድ፣ እርሱም በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ የጻፈው እንጂ፣ ከዚያ ውጭ ወይም የተለየ ልምምድ

የንድፉንም ዝርዝር እንድረዳ ማስተዋልን
ሰጠኝ" አለ።
20ደግሞም ዳዊት ልጁን ሰሎሞንን እንዲህ
አለው፤ "እንግዲህ በል በርታ፤ ጠንክር፤ ሥራ
ውንም ጀምር። አትፍራ፤ ተስፋም አትቍ
ረጥ፤ *እግዚአብሔር* አምላኬ ከአንተ ጋር
ነውና፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ
አገልግሎት ሥራ እስኪፈጸም ድረስ አይ
ተውህም፤ አይጥልህም። 21የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ሥራ ሁሉ የሚያስፈልጉት ካህና
ትና ሌዋውያን ምድብም ዝግጁ ነው። በሁ
ሉም የእጅ ሙያ የሠለጠኑ ፈቃደኛ ሰዎች
በሥራው ሁሉ ይረዱሃል። ሹማምቱና ሕዝቡ
ሁሉ ትእዛዝህን ይፈጽማሉ።"

**ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የቀረቡ ስጦታዎች**

**29** ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ለመላው ጉባኤ
እንዲህ አለ፤ "እግዚአብሔር የመረጠው
ልጄ ሰሎሞን ገና ወጣትና ልምድም የሌ
ለው ነው። ይህ ታላቅ ሕንጻ የሚሠራው
ለሰው ሳይሆን ለ*እግዚአብሔር* አምላክ በመ
ሆኑ፣ ሥራው ከባድ ነው። 2እኔም ያለኝን
ሀብት ለአምላኬ ቤተ መቅደስ ለወርቁ ሥራ
ወርቁን፣ ለብሩ ሥራ ብሩን፣ ለናሱ ሥራ
ናሱን፣ ለብረቱ ሥራ ብረቱን፣ ለዕንጨቱ
ሥራ ዕንጨቱን እንዲሁም ለፈርጥ የሚሆ
ነውን መረግድ፣ ኬልቄዶን[ሀ]፣ ልዩ ልዩ ኅብር
ያላቸውን የከበሩ ድንጋዮች፣ ማናቸው
ንም ዐይነት የሚያምር ድንጋይና ዕብነበ
ረድ፣ ይህን ሁሉ በብዛት አዘጋጅቻለሁ።
3ከዚህም በቀር ለአምላኬ ቤት ካለኝ ፍቅር
የተነሣ ለዚህ ለተቀደሰ ቤት ከዚህ በፊት
ከሰጠሁት በተጨማሪ ለዚሁ ለእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ የግል ሀብቴ የሆነውን ወር
ቅና ብር እሰጣለሁ፤ 4ይህም ሦስት ሺህ
መክሊት[ለ] የኦፊር ወርቅና ሰባት ሺህ መክ
ሊት[ሐ] ንጹሕ ብር ለቤተ መቅደሱ የግድግዳ
ግንብ ማስጌጫ 5እንዲሁም ለወርቁ ሥራ፣
ለብሩ ሥራ፣ በባለሙያዎች ለሚሠራው ሥራ
ሁሉ የሚሆን ነው። ታዲያ ዛሬ ራሱን ለእ
*ግዚአብሔር* ለመቀደስ ፈቃደኛ የሚሆን
ማን ነው?"
6ከዚያም የቤተ ሰቡ መሪዎች፣ የነገዱ
የእስራኤል ሹማምት፣ የሻለቆችና የመቶ
አለቆች እንዲሁም በንጉሡ ሥራ ላይ የተ
መደቡ ሹማምት በፈቃዳቸው ሰጡ፤ 7ለእግ
ዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ የሰጡትም አም
ስት ሺህ መክሊት[መ] ወርቅ፣ ዐሥር ሺህ ዳሪክ[ሠ]

28፥20 ዘዳ4፥31፤31፥6፤ኢ
ሱ24፥20፤1ነገ6፥14፤1
ዜና22፥13፤2ዜና7፥11
፤19፥11፤ሐጌ2፥4
28፥21
ዘፀ35፥25-36፤36፥5
29፥1
1ነገ3፥7፤1ዜና22፥5፤2
ዜና13፥7
29፥2
ቍ7፡14፡16፤1ዜና22፥
2-5፤ዕዝ1፥4፤6፥5፤
ኢሳ54፥11፤ሐጌ2፥8
29፥3 2ዜና24፥10፤
31፥3፤35፥8
29፥4 ዘዳ10፥29፤
1ዜና22፥14
29፥6
ቍ9፤ዘፀ25፥1-8፤
35፥20-29፤36፥2፤
2ዜና24፥10፤1ዜና27፥
1፤28፥1፤ዕዝ7፥15
29፥7 ዘፀ25፥2፤
ነህ7፥70-71
29፥8 ዘፀ35፥27፤
1ዜና26፥21
29፥9 1ነገ8፥61
29፥11 መዝ24፥8፤5
9፥17፤62፥11፤89፥11፤
ራእ5፥12-13
29፥12 2ዜና1፥12
፤20፥6፤32፥27፤
ዕዝ7፥27፤ መክ5፥19
29፥14 ቍ2፤
መዝ8፥4፤144፥3
29፥15 ዘዳ17፥8፤
23፥4፤ኢዮ7፥6፤ 8፥9፤
14፥2፤32፥7፤መዝ39፥
12፤102፥11፤
144፥4፤መክ6፥12፤
ዕብ11፥13

ወርቅ፣ ዐሥር ሺህ መክሊት[ረ] ብር፣ ዐሥራ
ስምንት ሺህ መክሊት[ሰ] ናስ አንድ መቶ ሺህ
መክሊት[ሸ] ብረት ነው። 8የከበሩ ድንጋዮች
ያለውም ሁሉ፣ በጌድ ሶናዊው በይሒኤል
አማካይነት ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ መቅ
ደስ ግምጃ ቤት አስገባ። 9ስጦታው በገዛ
ፈቃድና በፍጹም ልብ የቀ ረበ በመሆኑ፣
አለቆቹ ስላደረጉት የበጎ ፈቃድ ስጦታ ሕዝቡ
ደስ አለው፤ ንጉሥ ዳዊትም እንደዚሁ እጅግ
ደስ አለው።

**የዳዊት ጸሎት**

10ዳዊትም በመላው ጉባኤ ፊት እግዚአ
ብሔርን እንዲህ ሲል አመሰገነ፤

"የአባታችን የእስራኤል አምላክ *እግዚአ
ብሔር* ሆይ፤
ከዘላለም እስከ ዘላለም ለአንተ ምስጋና
ይሁን።
11*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በሰማይና
በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና፤
ታላቅነት፣ ኀይል፣ ክብርና ግርማ የአንተ ነው።
*እግዚአብሔር* ሆይ፤መንግሥትም የአንተ
ነው፤
አንተም እንደ ራስ ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ
ያልህ ነህ።
12ባለጠግነትና ክብር የሚገኘው ከአንተ ነው፤
አንተም የሁሉ ገዥ ነህ፤
ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ ለሁሉም ብርታትን
ለመስጠት፣
ብርታትና ኀይል በእጅህ ነው።
13አምላካችን ሆይ፤ አሁንም እናመሰግንሃለን፤
ለከበረው ስምህም ውዳሴ እናቀርባለን።
14"ሁሉ የተገኘው ከአንተ ነው፤ ለአንተም
የሰጠንህ ከእጅህ የተቀበልነውን ብቻ ነው።
ታዲያ እንዲህ ያለ ቸርነት እናድርግ ዘንድ
እኔ ማነኝ? ሕዝቤስ ማነው? 15እኛም እንደ
ቀድሞ አባቶቻችን በፊትህ መጻተኞችና
እንግዶች ነን፤ ዘመናችንም በምድር ላይ
እንደ ጥላ ነው፤ ተስፋ ቢስም ነው። 16*እግ
ዚአብሔር* አምላካችን ሆይ፤ ለተቀደሰው ስምህ
ቤተ መቅደስ እንሠራልህ ዘንድ ይህ በብዛት
ያዘጋጀነው ሁሉ፣ ከእጅህ የተገኘና ሁሉም

[ሀ]2 የዕብራይስጥ የዚህ ቃል ትርጕም በትክክል አይታወቅም
[ለ]4 100 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ሐ]4 240 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[መ]7 170 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ሠ]7 84 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[ረ]7 345 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ሰ]7 610 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[ሸ]7 345 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው

ያለመኖሩን ያሳያል። በሌላም በኩል የምስክሩን ድንኳን አሠራር የሚያመለክተውን መመሪያ ሙሴ ከእግዚአብሔር እጅ እንደተቀበለ ሁሉ፣ ዳዊትም በተመሳሳይ ሁኔታ መቀበሉን ለማሳየት እንደፈለገ መገመት ይቻላል (ዘፀ25፥40፤27፥8፤31፥18 ፤ 32፥16)።

*28፥20፤* ከመጽሐፉ መግቢያ ላይ "የዳዊትና የሰሎሞን ገጸ ባሕርይ አሣሣል'' *ታሪክ ገጽታ* የሚለውን ይመ።

*29፥1 የመረጠው፤* የ28፥5 ማብ ይመ። *ወጣትና፤* የ22፥5 ማብ ይመ።

*29፥2-9፤* ዳዊት የግል ሀብቱ የነበረውን ወርቅ፣ ብር፣ናስ ወዘተ ለቤተ መቅደሱ ማሠሪያ እንዲሆን ከሰጠ በኋላ፣ ሕዝቡም በገዛ ፈቃዱ ለዚሁ ሥራ የሚሆን ስጦታ እንዲያደርግ ይጠይቃል። የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እዚህም ላይ ስለ ዳዊት የሚያቀርበው ዘገባ ዳዊት የሙሴን ድርጊቶች አርአያነት የተከተለ መሆኑን ለማሳየትና ለማመሳሰል ነው (ዘፀ 25፥1-8፤35፥4-9፡20-29)። በሙሴም ሆነ በዳዊት ዘመን የነበረው ሕዝብ በፈቃደኝነት ከሚገባው በላይ ስጦታ በማምጣቱ የማደሪያው ድንኳንና የቤተ መቅደሱ ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲቀላጠፍ (እንዲከናወን) ረድቶአል።

29፥7 *ዳሪክ፤* የፋርሳውያን መገበያያ ገንዘብ ሲሆን የቀዳማዊ ዳርዮስን ክብር ለማሞገስ በስሙ የተሰየመ ነበር። (ዳርዮስ የኖረው 522-486 ዓ.ቅ.ክ. ነበር)።

የአንተ ነው:: [17]ስምሳኪ ሆይ፤ ልብን እንደም
ትመረምርና ቅንነትን እንደምትወድ ዐው
ቃለሁ፤ እኔም ይህን ሁሉ የሰጠሁት በበጎ
ፈቃድና በቀና መንፈስ ነው:: አሁንም በዚህ
ያለው ሕዝብህ በበጎ ፈቃዱ እንዴት እንደ
ሰጠ አይቻለሁ:: [18]የአባቶቻችን የአብርሃም፣
የይስሐቅ፣ የእስራኤል ስምሳክ እግዚአብሔር
ሆይ፤ ይህን ዐሳብ ለዘላለም በሕዝብህ ልብ
ጠብቀው፤ ልባቸውንም ለአንተ ታማኝ አድ
ርገው:: [19]ትእዛዞችህን፣ ደንብህንና ሥርዐ
ትህን እንዲጠብቅ፣ እኔ ባዘጋጀሁለት ነገ
ሮች ታላቅ ሕንጻ ለመሥራት እንዲችል፣
ለልጄ ለሰሎሞን ፍጹም ፈቃደኝነት ስጠው::
[20]ከዚያም ዳዊት ለመላው ጉባኤ፣ "ስምሳ
ካችሁን እግዚአብሔርን ወድሱት" አላቸው::
ስለዚህ የአባቶቻቸውን ስምሳክ እግዚአብሔ
ርን ወደሱ፤ በእግዚአብሔር በንጉሡም ፊት
ተደፍተው ሰገዱ::

## ሰሎሞን ንጉሥ መሆኑ በይፋ ታወቀ

29፥21-25 ተጓ ምብ-1ነገ 1፥28-53

[21]በማግስቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት
ሠው፤ የሚቃጠል መሥዋዕትም አቀረቡ፤
ይህም አንድ ሺህ ወይፈን፣ አንድ ሺህ
አውራ በግ፣ አንድ ሺህ የበግ ጠቦት ሲሆን፣
ከመጠጥ ቍርባኖቻቸውና ከሌሎች መሥ
ዋዕቶች ጋር ስለ እስራኤል ሁሉ በብዛት
አቀረቡ:: [22]በዚያችም ዕለት በእግዚአብሔር
ፊት በታላቅ ደስታ በሉ፤ ጠጡም::
ከዚያም የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ንጉሥ
መሆኑን ለሁለተኛ ጊዜ በይፋ ዐወቁ፤ ገዥ
እንዲሆንም በእግዚአብሔር ፊት ቀቡት፤
ሳዶቅንም ካህናቸው እንዲሆን ቀቡት::
[23]ሰሎሞንም ነግሦ በአባቱ በዳዊት ምትክ
በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ተቀመጠ፤ ተከና
ወነለት፤ እስራኤልም ሁሉ ታዘዙለት:: [24]የጦር
አለቆቹና ኀያላኑ ሁሉ እንዲሁም የንጉሡ
የዳዊት ወንዶች ልጆች በሙሉ ታማኝነታቸ
ውን ለንጉሥ ሰሎሞን አረጋገጡለት::
[25]እግዚአብሔርም ሰሎሞንን በእስራኤል
ሕዝብ ዘንድ ሁሉ እጅግ ከፍ ከፍ አደረ
ገው፤ ከእርሱ በፊት ለነበሩት የእስራኤል
ነገሥታት ያላጐናጸፋቸውን ንጉሣዊ ክብር
ሁሉ ሰጠው::

## የዳዊት መሞት

29፥26-28 ተጓ ምብ - 1 ነገ 2፥10-12

[26]የእሴይ ልጅ ዳዊት በእስራኤል ሁሉ
ላይ ነግሦ ነበር:: [27]እርሱም በኬብሮን ሰባት
ዓመት፣ በኢየሩሳሌም ሠላሳ ሦስት ዓመት፣
በአጠቃላይ አርባ ዓመት ነገሠ:: [28]ብዙ ዘመን
ባለጠግነትና ክብር ሳይጐድልበት ዕድሜ ጠግቦ
ሞተ፤ ልጁ ሰሎሞንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ::
[29]በንጉሥ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከመ
ጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተከናወነው ድር
ጊት በባለ ራእዩ በሳሙኤል የታሪክ መጽሐፍ፣
በነቢዩ በናታን የታሪክ መጽሐፍ፣ በባለ ራእዩ
በጋድ የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎአል:: [30]የተጻ
ፈውም በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ከፈ
ጸማቸው ዝርዝር ጕዳዮችና በዙሪያው ከከበ
ቡት፣ ከእስራኤልና ከሌሎች አገር መንግ
ሥታት ታሪክ ጋር ነው::

29፥17 1ዜና28፥9፤ መዝ15፥1-5፤ 139፥23፤ምሳ11፥20፤ 15፥11፤17፥3፤ ኤር11፥20፤17፥10
29፥19 1ነገ8፥61፤ 11፥4፤1ዜና22፥14፤ 28፥9፤መዝ72፥1፤ ኢሳ38፥3
29፥21 1ነገ8፥62፤1ዜና12፥40
29፥22 1ሳሙ2፥35፤ 1ዜና12፥40
29፥23 ዘዳ17፥18፤1ነገ2፥12፤ 1ዜና17፥14
29፥24 1ነገ1፥9
29፥25 ኢሱ3፥7፤1ነገ10፥7፤ 2ዜና1፥1፡12፤መክ2፥9
29፥26 1ዜና11፥1፤18፥14
29፥27 ዘፍ23፥19፤ 2ሳሙ5፥4-5፤1ዜና 3፥4
29፥28 ዘፍ15፥15፤ 1ዜና23፥1፤ ሐሥ13፥36
29፥29 1ሳሙ9፥9፤ 22፥5፤2ሳሙ7፥2

29፥22 በሉ፤ ጠጡም፤ 12፥38-40ና ማብ ይመ:: ሰሎሞን ለንጉሥነት ሳዶቅ ለክህነት መቀባታቸው፣ በመካከላቸው አንድነት መኖሩን የሚያሳይ ነው (ዘካ 4፥14፤6፥13ንና ማብ ይመ):: ለሁለተኛ ጊዜ፤ የሰሎሞን የመጀመሪያ መቀባት የተዘገበው በ1ነገ1፥32-36 ላይ ሳይሆን አይቀርም፤ የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ ግን ይህን ዘገባ አልጻፈውም (የ28፥1-29፥30 ይመ):: ይሁን እንጂ "ለሁለተኛ ጊዜ የሚለው ሐረግ በሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ላይ አይገኝም:: ለዚህ የተሰጠው አስተያየት የሰብዓ ሊቃናቱ ትርጕም ተሠርቶ ካለቀ በኋላ የጥንት ጸሐፍት የዜና መዋዕሉን ታሪክ ከነገሥቱ ታሪክ ጋር ለማጣጣም ሲሉ የጨመሩት ነው የሚል ነው:: በተደጋጋሚ መቀባት በሳኦልና (1ሳሙ 10፥1፡24፤11፥14-15) በዳዊትም (1ሳሙ 16፥13፤2ሳሙ2፥4፤5፥3) ሕይወት ታይቶአል::

29፥24 በሙሉ ታማኝነታቸውን... አረጋገጡለት፤ ይሁን እንጂ አዶንያስ ዐምፆ የጦር አለቆችና የንጉሡ ዳዊት ወንዶች ልጆች ሥልጣን ለመያዝ ባደረጉት ሙከራ የተባበረ መሆኑን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (1ነገ 1፥9፡19፡25):: የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ እንደገ ናም የዳዊትንና የሰሎሞንን ዝና ያጐድፋሉ የሚላቸውን ማናቸ ውንም ታሪኮች አልጻፋቸውም::

29፥25፤ በእስራኤል... ሁሉ፤ 11፥1፡10፤12፥38-40 ይመ:: እንዲሁም በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ዐላማውና መሪ ሐሳቡ የሚለውን ይመ::

29፥27፤ የ3፥1-9 ማብ ይመ

29፥28 ባለጠግነትና ክብር፤ ዕድሜ ጠግቦ እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘ ያገኘው በረከት መሆኑን የዜና መዋዕሉ ጸሓፊ የመጽሐፉን ፍሬ ሐሳብ እንደ ዋና ቁም ነገር አድርጐ የገለጸበት የአጻፉ ምሳሽ ነው (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ዐላማውና መሪ ሐሳቡ የሚለውን ይመ):: ጻድቃን በእነዚህ በረከቶች ይደሰታሉ (ከመዝ128፤ ከምሳ 3፥2፡4፡9-10፡16፡22፡33-35 ጋር ያነጻጽሩ)::

29፥29፤ በመጽሐፉ መግቢያ ጸሓፊው፣ የተጻፈበት ዘመንና የታሪኩ ምንጭ የሚለውን ይመ::

29፥30 ከሌሎች አገር መንግሥታት፤ በዙሪያው የነበሩትን መንግሥታት የሚያመለክት ነው::